UNIC ETHIOPIA

ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ አ. ማ.

THE UNITED INSURANCE COMPANY S.C.

ለሁሉም የመድን ፍላጎትዎ፣
ለሕይወት፣ ለንብረትና ሕጋዊ ግዴታዎ
ሕብረት አለ ጥሩ አማራጭዎ።

የሕብረት ኢንሹራንስ መሠረቱ
አስተማማኝነት !

Tel. 65 56 56
Fax: 251-1- 65 32 58
E-mail: unitedinsurance@telecome.net.et






# የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ

## አንደኛ መጽሐፍ

(፲፱፻ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም)

ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ

የመተርጎም፣ መልሶ የማሳተምም ኾነ የማባዛት መብቱ የጸሐፊው ነው።

ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ
የመልዕክት ሣጥን ቁጥር 22 27
አዲስ አበባ (ኢትዮጵያ)
E-mail = tamrin@telecom.net.et

የመጀመሪያ ዕትም ፲፱፻፺፮ ዓ.ም



ይህ መጽሐፍ ለአብሮ አደጌ፣ የትምሕርት ቤት ጓደኛዬና፣ የልብ ወዳጄ ለነበረው
ለአቶ ሸዋቀና ዜና ይርዳው መታሰቢያ ይሁንልኝ።

የመጣውን የተፋጠነ ለውጥ በኢትዮጵያ ሁኔታ እንዴት እንዳስተናገደውና መለናከሎቹንም እንዴት እንዳለፋቸው መመርመር ለምሥጋናም ኾነ ለወቀሳ ያበቃል።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያውን ረዥም ወቅት የመሩት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደ መሆናቸው መጠን በመጽሐፉ ውስጥ የእሳቸው ታሪክ ገዝፎ ይገኛል።

❄❄❄





# መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ የኢትዮጵያ አዲሱ ትውልድ ማንነቱን በቅድሚያ እንዲያውቅ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። የራሱን ታሪክ በቅድሚያ ባለማወቁ ለጥራዝ ነጠቆች መጫሪያነት እንደዋለ አይተናል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ቀደም ባለው ዘመን አባት ልጁን ሲያስተምርበት የነበረው ልማድ ልጆችን ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት መላክ ሲጀመር በመቋረጡ ነው። አባት ልጀ ተምሯል፣ ያውቃል ሲል ልጅ ደግሞ አለማወቁን እንኳን ሳያውቅ ቀረና ክፍተት ተፈጠረ። የራሱን ማንነት የሚነግረው በማጣቱ በቅን ልቡና ለአገሩ የከፈለው መስዋዕትነት ከንቱ ኾኖ ቀረ። በዚህ ሥርዓት የተማሩ ሰዎች የአገራቸውን ታሪክና ሁኔታ ጠንቅቀው ለማወቅ ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም። ምክንያቱም የትምሕርት አሰጣጡ የአገርን ታሪክና ሁኔታ ጠለቅ አድርጎ የሚያስገነዝብ ባለመሆኑና በሌሎችም ተጨማሪ ምክንያቶች ነው።

ይህ መጽሐፍ አዲሱ ትውልድ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን የአገሩን ሁኔታ መርምሮና አውቆ የሌላውንም ዓለም አካሄድ አገናዝቦ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ራዕይ ድርሻውን ለመወጣት እንዲዘጋጅ የሚረዳ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በታሪክ መጽሐፎች የተደገፉ ዕውነታዎች ሲዘረዘሩ በተለያዩ ምክንያቶች አቅለሎ በማየት የተዘለሉ አፈታሪኮችም እንዲካተቱ ተደርገዋል። አፈታሪኮቹን በመመርመር ተአማኒነት የሌላቸውን በማለፍ፣ አንዳንዶቹ ላይም ትችት በማቅረብ፣ እንዲሁም ሌሎቹን ለአንባቢ የኅሊና ፍርድ በመተው ከየታሪኩ ጋር ተዛምደው ታክለዋል።

የደረሱኝ በእነሱ ስም እንደመሆኑ መጠን የሌላ ሰው ስም ለመጥቀስ አልቻልኩም። በቅርብ ጊዜ እንኳን ብላታ ሲራክ ኅሩይና ልጅ ይልማ ዲፋሳ ሶተናገሯቸው ናቸው እየተባለ በሕዝብ ዘንድ ብዙ ቀልድ ይነገራል።

በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ ሕዝብ እየደጋገመ የሚናገራቸው ትንቢቶች እንዳሉ ይታወቃል። ትንቢቱን መጀመሪያ ማን እንደተናገረው መጥቀስ ቢያዳግትም ሕዝብ ደጋግሞ መናገሩን ብቻ መሠረት በማድረግ ትንቢት ነበረ በማለት በብዙ ቦታ ላይ ገልጫለሁ። እንዲሁም ሕዝብ የገጠማቸው ግጥሞችና ቅኔዎች የዘመኑን ታሪክና አስተሳሰብ ስለሚያንጸባርቁ አብረው ከየታሪኩ ጋር ተጠቅሰዋል። የተፈጥሮ ቋንቋንም ትርጉም እንመረምራለን።

አንድ ምሰል ከአንድ ሺህ ቃላት ይበልጥ መግለጥ ይችላል እንደተባለው በተቻለ ከየታሪኩ ጋር የተሟላ ምስል ለማቅረብ ሞክሬአለሁ።

ጥላሁን ብርሃን ሥላሴ ቤተ



# ማውጫ


| ምዕራፍ | | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ | ፩ | የንግሥና ሥርዓትና የነገሥታት ዘር ሐረግ | 1 |
| ምዕራፍ | ፪ | የተለያዩ ግዛቶች | 19 |
| ምዕራፍ | ፫ | የአፄ ምኒልክ ፍጻሜ | 59 |
| ምዕራፍ | ፬ | መናኙ ራስ መኮንን | 66 |
| ምዕራፍ | ፭ | መካኗ እቴጌ ጣይቱ ብጡል | 75 |
| ምዕራፍ | ፮ | ደጃች ታየ ጉልላቴ | 80 |
| ምዕራፍ | ፯ | ጎረምሳው አቤቶ ኢያሱ | 84 |
| ምዕራፍ | ፰ | ምስኪንዋ ንግሥት ነገሥት ዘውዲቱ | 114 |
| ምዕራፍ | ፱ | የተፈሪ ውልደትና ዕድገት | 121 |
| ምዕራፍ | ፲ | ድብቋ ወይዘሮ የሺ እመቤት | 128 |
| ምዕራፍ | ፲፩ | ተፈሪ በደጃዝማችነት ዘመን | 134 |
| ምዕራፍ | ፲፪ | ድንገተኛው የተፈሪ ጋብቻ | 138 |
| ምዕራፍ | ፲፫ | ራስ ተፈሪ በአልጋወራሽነት ዘመን | 142 |
| ምዕራፍ | ፲፬ | የራስ ተፈሪ አነጋገሥ | 148 |
| ምዕራፍ | ፲፭ | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | 153 |
| ምዕራፍ | ፲፮ | ጃንሆይ እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ | 156 |
| ምዕራፍ | ፲፯ | የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ | 171 |
| ምዕራፍ | ፲፰ | የማይጨው ጦርነት | 176 |
| ምዕራፍ | ፲፱ | ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ዘመን | 193 |
| ምዕራፍ | ፳ | የጣሊያን ወረራ | 203 |
| ምዕራፍ | ፳፩ | የጣሊያን ጊዜ | 208 |
| ምዕራፍ | ፳፪ | የድል ጉዞ ወደ አገር ቤት | 222 |
| ምዕራፍ | ፳፫ | ንጉሠ ነገሥቱ ከስደት መልስ | 226 |
| ምዕራፍ | ፳፬ | አዲስ ዘመን | 239 |
| ምዕራፍ | ፳፭ | የኤርትራ ታሪክ ዳሰሳ | 247 |
| ምዕራፍ | ፳፮ | የሕዝብ ቅሬታዎች | 261 |
| ምዕራፍ | ፳፯ | ራስ ተፈሪያን | 271 |
| ምዕራፍ | ፳፰ | ሃይማኖትና ንጉሠ ነገሥቱ | 275 |
| ምዕራፍ | ፳፱ | ያለፉትን ማስታወስ | 281 |

ፖርቱጋሎች ወደ አገራቸው ተመልሰው የኢትዮጵያውያንን ክርስቲያንነት በመናገራቸው ይኸንኑ ሰምተው የመጡ ኢየሱሳውያን (ጀስዊትስ) የካቶሊክ ዕምነት ተከታዮች ስብከት ጀምሩ። በዚህም ሳቢያ ንጉሥ ሱስንዮስ ወደ ካቶሊክ ዕምነት ስለተለወጠና ሕዝቡንም እንዲለወጥ ስላስገደደ፣ ሌላ የሃይማኖት ጦርነት ተቀስቅሶ ለስምንት ዓመት ብዙ ሰው ከተጎዳና መንግሥቱም ከተዳከመ በኋላ የአልጋው ወራሽ የኾነው ፋሲል በ1623 ዓ.ም ነገሡና አስተዳደሩን ወደ ጥንቱ ሃይማኖት መልሶ መንግሥቱን እንደገና አጠናክሮ ስመ ጥሩውን የጎንደርን ግንብ አሠራ።

ከጊዜ በኋላ የቀዳማዊ ምኒልክ ሥርወ መንግሥት በጎንደር እየደከመ ሄዶ የንጉሡ እንደራሴ የነበረው ሥሑል ሚካኤል ንጉሥ ኢዮአስን በ1763 ዓ.ም ገድሎ በሥልጣን ከንጉሦቹ በላይ መሆን ስለቻለ ዘመነ መሳፍንት ተጀመረ። ሥሑል ሚካኤል ያልነገሡበት ምክንያት የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጅነት ስላልነበረው ነው። ለሰማኒያ ሦስት ዓመት እንደራሴዎች የመንግሥቱን ሥልጣን ይዘው ለስም ብቻ ንጉሦች እየሾሙ እየሻሩ ሲኖሩ በሸዋ ቀርቶ ከነበረው ከአፄ ልብነ ድንግል ልጆች መካከል የአቤቶ ያዕቆብ ተወላጆች የሆኑት ከባላባትነት ወደ ንጉሥነት አድገው እየጎለበቱ ሄዱ። በተለይ ራስ ወሰን ሰገድ



ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ወሰን ሰገድ

አስከትሎም ልጃቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (አባ ዲና) በዘመኑ የነበረውን እንደራሴ አሸንፈው አገሪቱን በንጉሠ ነገሥትነት ለመጠቅለል ያስቡ ነበር። ለዚህም ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በሚዘጋጁበት ወቅት የጦር አበጋዛቸው ለሆነው ባሻ መተከ ቦርጂያ ልጃቸውን ለልጁ ለጃራ ሲድሩለት ፊቃደኛ መሆናቸውን ገለጹ። በኋላ ላይ ሰዎች ስለ ባሻ መተከ አጉድፈው ስለነገሯቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ መልሰው ልጃቸውን ቢከለክሉት ክፉኛ ተቆጥቶ በስለት ሊገድላቸው በመሞከሩ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ መጠነኛ ሽብር ተነስቶ ይኸንኑ በሚያስተካክሉበት ወቅት ታመው ሞቱና ዕቅዳቸው ተጨናገፈ።



በዚህ መካከል ቋረኛው ካሣ በጎንደር ያለውን የመንግሥት ኃይል በእጃቸው ካስገቡ በኋላ ወደ ሰሜን ተጉዘው አሁንም የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን ድል በመምታት አፄ ቴዎድሮስ (አባ ታጠቅ) - ገብሩ ለክርስቶስ ተብለው በ1845 ዓ.ም ነገሡ። አፄ ቴዎድሮስ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ወሎ ቀጥሎም ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ታመው ይሞቱና ሠራዊታቸው ተሸንፎ ቀጣይ የመንግሥቱን ወራሽ የ12 ዓመት ልጅ ምኒልክን ይዘው ወደ ጎንደር ተመለሱ። በ1860 ዓ.ም ከአፄ ቴዎድሮስ ህልፈተ ሕይወት በኋላ የሰሜኑ ባላባት ዋግ ሹም ጎበዜ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ለሦስት ዓመት ነገሡ። ቀጥሎም የትግራዩ ደጃዝማች ካሣ ምርጫ በ1863 ዓ.ም አፄ ዮሐንስ አራተኛ ተብለው ለ18 ዓመት ዘውድ ጫኑ። በመጨረሻም የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ በ1882 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥት ተብለው እስከ 1906 ዓ.ም ኢትዮጵያን በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር አስተዳደሩ።



ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ

በመሳፍንት ዘመን በጎንደር የነበሩት የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች ኃይላቸው በእንደራሴዎቹ ስለተወሰደና ማንሰራራት ስላቃታቸው አፄ

ሀ) ከሥልጢዋ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ወሪጋ
ራስ ዳርጌ (የበኵር ልጅ)

በ) ከሕግ ሚስታቸው ከወይዘሮ በዛብሽ ደጀን
1ኛ ኃይለ መለኮት
2ኛ ሠይፉ
3ኛ ወሰን የለሽ

ገ) ከሩሲያዊ አባት ከተወለደችው ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ይመኙሻል ቡንኝ
1ኛ ኃይሌ
2ኛ ተናኘ ወርቅ

ደ) ከቡልጋዋ ተወላጅ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ማለፊያ
1ኛ እያሀሉሽም
2ኛ ጠንፍ፡ የለሽ

ጀ) ከወሎየዋ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ እቴነሽ
1ኛ ብርቅነሽን

ሀ) ከአርሲ ባላባት ከአርባ ጉጉ ተወላጅ ከኾነችው ዕቁባታቸው
1ኛ ካሡኝ

ወ) ከዕቁባታቸው ከወይዘሮ ማረፊያ
1ኛ ወርቅ አፈራሁ
2ኛ አቻምየለሽ

ዘ) ከአልዩ አምባ ተወላጅ ዕቁባታቸው ከወይዘሮ ብዝት
1ኛ ባሕርይ
2ኛ ሙላት ወርቅ
3ኛ በለጥሻቸው

ከዚህ በማስከተል የሴት ልጆችን የዘር ሐረግ አስፈላጊ ሲኾን ብቻ በመጥቀስ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።



## የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ትውልድ



## የንጉሥ ኃይለ መለኮት ትውልድ




## የመርዕድ አዝማች ኃይሌ ትውልድ






## የአቤቶ ሠይፉ ትውልድ




## የአቤቶ ባሕርይ ትውልድ

አቤቶ ባሕርይ ልጅ አልነበራቸውም።

## የራስ ዳርጌ ትውልድ




ወይዘሮ ትሰሜ ከንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ (ዋግ ሹም ጎበዜ) ታናሽ ወንድም ከደጃች ኃይሉ ራስ ካሣን ወልደዋል። በተጨማሪም ሌሎች ወንዶች ልጆችም አፍርተዋል።



## የአቤቶ ካሣኹ ትውልድ




## የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ትውልድ




አፄ ምኒልክ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው መንግሥታቸውን ማስተላለፍ የነበረባቸው ለአጎታቸው ልጅ ለመሸሻ ሠይፉ ወይም ከመሸሻ ልጆች ለአንዱ ወንድ ልጅ መሆን ሲገባው ለሴት ልጃቸው ለወይዘሮ ሸዋረጋ ምኒልክ ወንድ ልጅ ለአቤቶ ኢያሱ ማሳለፋቸው በተለምዶው መሠረት ስህተት ነበር። የአፄ ምኒልክ ተወዳጅነት ከፍተኛ ስለነበርና በዘመኑ የነበሩት ሊቃውንቶችም ኾኑ መኳንንቶች ቃላቸውን ለማክበር ሲሉ አሜን ብለው በመቀበላቸው ይኸ ስህተት የነገሮች መዘበራረቅን አስከትሏል።

የዛጔ ነገሥታት ሃይማኖት አጥባቂዎችና በአንድ ሚስት ብቻ የተወሰኑ ነበሩ። ከእነሱ ቀጥሎ በተከታታይ ከነገሡት መካከል አፄ ልብነ ድንግል በአንድ ሚስት ብቻ የተወሰኑ ነበሩ። የተቀሩት ግን እንደ ልምድ አድርገውት ብዙ ዕቁባቶች በየቦታው ያስቀምጡ ነበር። እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ ንጉሦች ከዋና ሚስት ሌላ ዕቁባቶችም የማስቀመጥ ልምድ ነበራቸው። ስለሆነም ከተለያዩ እናቶች የሚወለዱ ልጆች እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው።

ንጉሦችም ኾኑ ሌሎች የበታች ሹሞች በየአገሩ እየሄዱ ብዙ ጊዜ ስለሚቀመጡ ዕቁባቶች በየቦታው ይኖራቸዋል። ልጅም ቢወለድ ከሚስት አልተወለደም ተብሎ ልጅነቱ አይናቅም ነበር። እንዲያውም ብዙ ልጆች በወለዱ ቁጥር የእግዚአሔር ፀጋ እንደሆነ ስለሚቆጥሩት ይደሰቱበታል እንጂ አያፍሩበትም። ስለኾነም ብዙዎቹ የዘመኑ ትላልቅ ሰዎች የልጆቻቸው ቁጥር በርካታ ነበር። ለምሳሌ ያህል የትግራዩ ሹም አጋሜ ወልዱ ሃምሳ ልጆች፣ የጎጃሙ ደጃች ተድላ ጓሉ አሥራ አራት ልጆች፣ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትም ሃያ ልጆችና የሼህ ሆጀሌ ልጆች ሰባ ሁለት እንደነበሩ ይነገራል።

## ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ምኒልክ ከአሥር ዓመት ግዞት በኋላ በ22 ዓመት ዕድሜያቸው ከአፄ ቴዎድሮስ አምልጠው ሸዋ ከገቡ በኋላ ነሐሴ 24 ቀን 1857 ዓ.ም አንኮበር ላይ የሸዋ ንጉሥ ኾነው ዘውድ ጫኑ። ከአፄ ዮሐንስ ህልፈተ ሕይወት በኋላም በ1882 ዓ.ም “ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ” ብለው አወጁ። ከአፄ ምኒልክ ቀጥሎ በዚሁ ተቀጽላ የነገሡት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በኋላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ። ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ልጅ ከቀዳማዊ ምኒልክ አንስቶ ሲቆጠር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ **225**ኛ ንጉሥ ናቸው። ይህንን ተቀጽላ ንጉሦቹ ያወጁበት ምክንያት የይሁዳ ዘር የንጉሥ ዳዊት ትውልድ ነን በማለት በሕዝብና በቀሳውስቶች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ስለሚፈልጉ ነው። በቀደሙት ጊዜያት በዚህ ተቀጽላ ራሱን የገለጸው አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ብቻ ነበር።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለ ንጉሥ ሲነግሥ የሌላ ተወዳዳሪን ቅስም ከመስበሩም በላይ በሰፊው የክርስትና ተከታይ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኛል። የዛሬ ዘመን ሰው ይህንን ይቀበለዋል ብሎ



ለማለት ያስቸግራል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ የይሁዳ አንበሳ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ለሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ ይህ ስያሜ ትርጉም አይሰጣቸውም።

ዛሬ ዴሞክራሲ የሚባለውን ቃል ዘመናዊ ፖለቲከኞች እንደሚጠቀሙበት ሁሉ ቀደም ብሎ የነበሩት ነገሥታት ሃይማኖትንና የዘር ግንድን ለሥልጣን መወጣጫነት ይጠቀሙበት ነበር። የቋንቋና የዘዴ ልዩነት እንጂ ዓላማውና ግቡ አንድ ነው። ሕዝብ ቀደሞም ኾነ አሁን የሚፈልገው ከወገኑ አንድ ሰው መርጦ እንዲያስተዳድረውና ሥራውንም መሥራት ባቃተው ጊዜ ወይም በሞት ሲለይ በሌላ ለመለወጥ ነው። ሥልጣኑን የጨበጠው ሰው ግን ከያዘው ስፍራ ላለመነቃነቅ እንዲያውም ሲሞት ልጁን ለመተካትና በሥልጣን እርካብ ላይ የዘር ዘሩ እንደተፈናጠጠ እንዲቆይ በሚሸርበውና በሚሠራው ተንኮል ሕዝቡ ለመሪዎቹ መገልገያ መሣሪያ እየሆነ እንዲኖር ይገደዳል። አልፎ ተርፎም ጥቅም ፈላጊዎች ሥልጣን ላይ ላሉት ሰዎች በምን ዓይነት ዘዴ በሥልጣን ለመቆየት እንደሚችሉ ብዙ መላ ይተልሙላቸዋል። የጥቅም ፈላጊዎች ተሳትፎ በመንግሥት ሥልጣን አያያዝና ቆይታ ላይ ቀላል አይደለም።

## የሴቶች እኩልነት

አንድ ነገር ብዙ ጊዜ ሲደጋገም ትክክል መስሎ ይታያል። አንድ ሰው በልምድ እየተበደለ ከበደሉ ነፃ የሚያወጣውን ሰው ራሱ ተበዳዩ እንደሚታገለው ይታወቃል። አንድ ሴት ልጅ ስትወልድ “ምን ወለደች” ሲባል “ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ” ከተባለ “እሰይ!” ይባላል። የወለደችው “ሴት” ነው ሲባል “ትሁን” ይባላል። እንደዚህ የሚሉት ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችም ናቸው።

ንግሥተ ሳባ የመንግሥቱ ወራሾች በወንድ በኩል ያሉት ናቸው ስትል የሴቶችን መብት መርገጧ መሆኑ በተለይ በአሁኑ ዘመን ቁልጭ ብሎ ይታያል። ንግሥተ ሳባ ብቻ ሳትሆን እስከ ዘመናችን ድረስ ያለው የአነጋገሥ ሁኔታ በየትም ዓለም በወንድ ተወላጅ በኩል ነው የሚወሰነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያው ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ሲሆኑ አልጋ ወራሽ የተባሉት የመጀመሪያ ወንድ ልጃቸው ልዑል አስፋ ወሰን ናቸው። በሌሎችም አገሮች የሚደረገው እንዲሁ ነው። ለነገሩማ አሜሪካን አገር ላለፉት ሁለት

ሃይማኖት አጥባቂዎችን ከአገር አባሮ ወደ ጎረቤት አገር እንዲሰደዱ አደረጋቸው። በንጉሠ ነገሥቱ ሥር ሌሎች ንጉሦችና ባላባቶች ሲኖሩ እያንዳንዳቸው የአፄ ዮሐንስን የበላይነት በመቀበል አገሪቱን በደቡብ በኩል ከቅኝ ገዥዎች ለማዳን እየተዋጉና እሳቸውም በሰሜን በኩል ያለውን ወሰን እያስከበሩ አገር እያስተዳደሩ ኖረዋል።


ዳግማዊ አፄ ምኒልክ

አፄ ዮሐንስ በዘመናቸው ብዙ የመከላከል ፍልሚያ ቢያደርጉም ራስ አሉላን ከኤርትራ አገረ ገዥነት ማንሳታቸው ግን አካባቢውን ያለጠባቂ ስላስቀረው መጨረሻ ላይ በቅኝ ገዥዎች ከመቦርቦር ለመከላከል አልተቻለም። ዘመኑ የቅኝ ገዥዎች የመስፋፋት ፍልሚያቸውን ያፋፋሙበት ወቅት ስለነበረ አገሪቱን ከወራሪ ለማዳን ብዙ ጦርነቶች ላይ ተሳትፈው መጨረሻ ላይ ከደርቡሾች (ሱዳን) ጋር ባደረጉት ጦርነት ሕይወታቸውን ሰውተዋል።

ዳግማዊ ምኒልክ በተለይ የደቡቡንና የምሥራቅን ግዛቶች በመጠቅለልና ወሰን በመከለል ረገድ ከቅኝ ገዥዎች የአሁኒቱን ኢትዮጵያ ማትረፍ ችለዋል። በዚህም ወቅት አንዳንድ ባላባቶች ሲገብሩላቸው አንዳንዶች አልገብርም ይሉ ስለነበረ ብዙ ጦርነቶች አካሂደዋል። በጦርነት ከተሸነፉ ባላባቶች መካከል እንደገና ግዛታቸው እየተመለሰላቸው፣ ያልታመኑት ደግሞ ሌላ ባላባት እንዲተካቸው እየተደረገ ግዛቶቹ በሙሉ በአንድነት በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥር የሚተዳደሩ መሆን ሲችሉ ለመጠቅለል ያቃቱዋቸው የሶማሌና የባሕር ነጋሽ ግዛቶች ግን በቅኝ ገዥዎች ሥር ኾነው ቀርተዋል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ በይበልጥ አንድ የኾነችበት ጊዜ ቢሆንም ችግሩ በሥልጣን አወጣጣቸው ምክንያት በየቦታው ጥቃቅን ግጭቶች መካሄዳቸው ነው። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፊት የነበረው ሁኔታ ንጉሥ የነበረው በንጉሥ፣ ባላባት የነበረው በባላባት፣ እያንዳንዱ ክፍለ አገር ከጥንት ጀምሮ በነበረው



ሥርዓት ከሞላ ጎደል ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ራስ ገዝ ነበር። የአገሪቱ የበፊት ነገሥታት በጠቅላላው በአገር ጉዳይ ከየራስ ገዝ አስተዳዳሪዎቹ ጋር ይመካከራሉ እንጂ በውስጥ አስተዳደር ገብተው አይሾሙም አይሽሩም ነበር። በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ግን እያንዳንዱ ንጉሥ ወይም ባላባት ከግዛቱ በየምክንያቱ ተሽሮ አገሩ በሙሉ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ፍጹማዊ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ በተሾሙ አገረ ገዥዎችና ባላባቶች ብቻ ይተዳደር ጀመር። ግብር ሁሉ በቀጥታ ለማዕከላዊው መንግሥት እየገባ በፊት የፌዴራል ቅርጽ የነበረው አስተዳደር የአንድ ኃይለኛ ማዕከላዊ መንግሥት ግዛት ኾነ። ጥንት የነበረው አስተዳደር ምን መልክ እንደነበረውና በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ምን ሁኔታ ላይ እንደደረሰ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## አገው

አገው አግዐዚያን ከደቡብ አረቢያ ወደ ደጋው ኢትዮጵያ ከመፍለሳቸው በፊት አገሩ ላይ ነዋሪ የነበረ የኩሽ ጎሣ ነው። አግዐዚያን መንግሥት አቋቋሙና የአገውንም ሕዝብ በግዛታቸው ጨምረው ያስተዳድሩ ጀመር። በመራ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት አገዎች የመንግሥት ሥልጣን የያዙት ከ920 ዓ.ም እስከ 1255 ዓ.ም ነው። መንግሥታቸው ሲያበቃ በተደረገው ውል መሠረት የዛጔ ሥርወ መንግሥት ወራሾች በባላባትነት ዋግ ሹም እየሆኑ በዋግና ላስታ እንዲቀመጡ ተደረገ። በተገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት የመጀመሪያው ዋግሹም ተብሎ የተሾመው ዮናታን ነው።

ከዮናታን ጀምሮ በተከታታይ በዋግ ሹምነት ማዕረግ ሲኖሩ በ1860 ዓ.ም አፄ ቴዎድሮስ ሲሞቱ ዋግ ሹም ጎበዜ ኃይል ተሰምቷቸው ነበርና ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ በመባል ነግሠው ከሦስት ዓመት በኋላ በባለቤታቸው ወንድም በአፄ ዮሐንስ ተሸንፈው መንግሥታቸው ተወሰደባቸው። ቢሆንም በዋግ ሹምነት ባላባትነታቸው ዋግና ላስታን ማስተዳደር ቀጥለው በ1966 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ሲወርዱ የመጨረሻው ዋግ ሹም ጌታነህ አድማሱ ወሰን ሲታሰሩ ሌላ ዋግ ሹም ስላልተተካ ሹመቱ በእሳቸው አበቃ።

አገው በኢትዮጵያ ምድር ቀደም ብሎ በመኖር የታወቀ ጎሣ ሲሆን የእሥራኤልን ሃይማኖት አስቀድሞ በመቀበሉና ከዮዲት ጋር

እስከ መሙርስ ደርሰዋል። በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በእንደራሴነት የሚታወቁት የትግራይ ባላባት ሥሑል ሚካኤል በንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴነት ጎንደር ላይ ሲያገለግሉ ኖረው በተከፋ ጊዜ የእቴጌ ምንትዋብን የልጅ ልጅ ንጉሥ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቀው አስገደሉ። ሥሑል ሚካኤል ዝነኛ ስለነበሩ ከእሳቸው ሕ ኋወት በኋላ ተወላጆቻቸው በትግራይ ሹም በመሆን አገር ሲያስተዳድሩ ኖረዋል። ዳሩ ግን ከትግራይ ባላባቶች ውስጥ ከዚህ በተረፈ መንገሥ አለብኝ፣ የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጅነቴን እቆጥራለሁ የሚል አልተገኘም።

የዘመነ መሳፍንትን ሥርዓት የደመሰሱት አፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ ከነገሡት የላስታው ዋግሹም ጎበዜ (አፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ሥልጣኑን በመቀማት ደጃዝማች ካሣ ምርጫ (አፄ ዮሐንስ) የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኾነው አስተዳድረዋል። አፄ ዮሐንስ የአፋሯን ተወላጅ ወይዘሮት ዳቶን ክርስትና አስነስተውና ጥበበ ሥላሴ አሰኝተው አገቡና ራስ አርአያ ሥላሴን ወለዱ። ራስ አርአያ ሥላሴ ገና የ18 ዓመት ልጅ እንዳለ ሞተ። አጼ ዮሐንስ በእናታቸው በኩል የአጎታቸውን የትልቁ ራስ ጉግሣን ልጅ ራስ መንገሻን ወስደው እንደልጃቸው ያሳድጉት ስለነበረ የሚጠራውም በወላጅ አባቱ ስም ሳይሆን በአሳዳጊው በአፄ ዮሐንስ ነበር። አፄ ዮሐንስ ራስ መንገሻ ዮሐንስ መንግሥታቸውን እንዲወርሱ ቢናዘዙላቸውም አልነገሡም። ራስ መንገሻም በተራቸው ራስ ሥዩምን፣ ልዕልት ወለተ እሥራኤልን፣ ወይዘሮ አስቴርንና ወይዘሮ አልማዝን ወለዱ። የአጼ ዮሐንስ ልጅ ራስ አርአያ ሥላሴ ከወይዘሮ ዘውዲቱ ልጅ አልወለደም። ሆኖም በልጅነት ዕድሜው ከመሞቱ አስቀድሞ በምስጢር ከአንድ ወሎዬ ሴትና ከአንድ ሌላ ሴት የወለዳቸው ልጆች ነበሩት። ራስ ጉግሣ በምስጢር ከራስ አርአያ ሥላሴና ከወሎዬዋ ሴት የተወለዱ ልጅ ናቸው። ራስ ጉግሣ የደጃች ኃይለ ሥላሴ አባት መሆናቸው ነው። ራስ አርአያ ሥላሴ በምስጢር ሌላም ልጅ ነበራቸው። እሱም ተሰዶ ወደሸዋ የመጣው ደስታ ሲሆን የእሱ ልጅም በሕይወት ያለው ታዋቂው ጋዜጠኛ አቶ ጌታቸው ደስታ ነው።





አፄ ዮሐንስ ፬ኛ ከራስ አርአያ ሥላሴ ጋር

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ከባለቤታቸው ከልዕልት ዘነበ ወርቅ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ልዕልቲቱ በወሊድ ምክንያት ሞቱ። ሆኖም ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ባለቤታቸው ነፍሰጡር ሆነው ይደበድቡዋቸው ስለነበር የሞቱትም በዚሁ ጠንቅ ነው መባሉ በወላጆቻቸው ስለተሰማ የውስጥ ቅራኔ ተፈጠረ። በዚህም ምክንያት የሚችትን የወግ ዕቃ መልስ ተብለው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ መልሰዋል። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ቅምጥል የነበሩና ወደ አዲስ አበባ እንኳን የሚመጡት በኤርትራ በኩል በመርከብ ወደ ጅቡቲ ተሻግረው በባቡር እንጂ እንደ ሌሎቹ መኳንንቶች በበቅሎ ወይም በፈረስ አልነበረም።

የትግራይ ክፍለ አገር ምዕራቡ በራስ ሥዩም ምሥራቁ በደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ይተዳደር ነበር። ይሁንና ደጃች ኃይለ ሥላሴ ያስተዳድሩት የነበረው በፊት አባታቸው ራስ ጉግሣ ከሚያስተዳድሩት ተቀንሶ ስለነበረ ቅሬታ ነበራቸው። በመሃሉ ጣሊያን ኢትዮጵያን ሊወር ሲመጣ ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ መላው ትግራይ ላይ ጣሊያኖች ይሾሙኛል ብለው ከጠላት ጎን ተሰለፉ። በዚህም የተነሳ በማይጨው ጦርነት ብዙ ጉዳት ኢትዮጵያ ላይ እንዲደርስ ምክንያት ሆኑ። ወረራው ሲያበቃ በእንግሊዞች አግባቢነት ከታሰሩበት ከሲሼልስ ደሴት ምሕረት ጠይቀው ከተመለሱና ከብዙ ዓመት ግዞት በኋላ በደርግ ዘመነ መንግሥት ተለቀው ነበር።

አሁን ወሎ የሚባለው ግዛት አማራ ይባል ነበር። ሕዝቡም ሃይማኖቱ ክርስቲያን ስለ ነበረ ሃይማኖቱን ሳይለውጥ የቀረውን ሁሉ አማራ ማለት ተጀመረ። ይህ አማራ ተብሎ የሚታወቀው ጎሣ ራሱን አማራ እያለ ሲጠራ ሌሎች አምሓራ ለምን እንደሚሉት አይታወቅም። በተጨማሪም አማራን የጎሣ ስም አይደለም የሚሉት ከሌሎች ጎሣዎች መሥፈርት የአማራ በምን ተለይቶ እንደሆነ አልገለጹም። ይሁንና አማራ በሚል ስያሜ የሚታወቅ አንድ ግዙፍ ጎሣ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እንደሚገኝ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ብቻ ተወስኖ የሚገኝ መሆኑ ለፍጹም ኢትዮጵያዊነት ሥነ ልቡናው አስተዋጽኦ አድርጎለታል።

ይሁንና አማርኛ ቋንቋ ከዮዲት ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የሕዝብ መገናኛ ቋንቋ እንደነበረ ይታወቃል። ምንም እንኳን ግዕዝ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑ አማርኛ ተጨቁኖ ቢቆይም ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ በይፋ የጽሑፍ ቋንቋ ለመሆን በቅቷል። በሸዋ፣ በወሎ፣ በጎንደር፣ በጐጃም፣ ያለው ሕዝብ በብዛት አማራ ይባላል። ከኦሮሞ መስፋፋት በፊት ወሊጋ፣ ኢሉባቦር፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ሊሙ፣ ሸዋ ውስጥና ወደ ሐረርጌ በሚወስደው ደጋ አገር ላይ ያለው ሕዝብ በብዛት አማራ እንደነበረ ይነገራል። በተለይ በሸዋ ሜዳ ሜዳው ላይ ነዋሪ የነበረው አማራ ሸሽቶ በየሸንተረሩ በመደበቅ ዘሩን ማትረፉን መልክአ ምድሩን በመመልከት ለመረዳት ይቻላል። ገደላ ገደሉ አማራ ሜዳ ሜዳው የኦሮሞ አገር የሆነው ኦሮሞው በፈረስ ሆኖ በጦር እየወጋ አማራውን አባሮት ነው ተብሎም ይነገራል። ከጊዜ ብዛት አማራውም ኃይል ሲያገኝ ተመልሶ ከገደላ ገደሉ ወጥቶ በጦር ድል አድርጎ በመውጣቱ፣ በአሁኑ ወቅት በጋብቻ ጭምር ተሳሥሮ ከኦሮሞ ጋር የኦሮሞ አገር በተባለው ሁሉ በብዛት አብሮ በመኖር ላይ ይገኛል። የአማራ ጎሣ ለጋብቻ ጎሣ የመለየት ጠባይ ስለሌለው በተለይ ከኦሮሞ ጎሣ ጋር በብዛት በጋብቻ ተሳሥሯል።

የሸዋ፣ የወሎ፣ የጎንደርና የጐጃም አስተዳደር ብዙውን ጊዜ በማዕከላዊው መንግሥት ሥር ሆኖ በየክፍለ ግዛቱ የተለያዩ ባላባቶች ኢኗቸው። ከፊታውራሪና ደጃዝማች እስከ ራስና ንጉሥ ድረስ እንደ ጀብዱቸውና ውልደታቸው የማዕከላዊው ንጉሠ ነገሥት የተለያየ ማዕረግ ይሰጣቸዋል። በተረፈ የማዕከላዊው መንግሥት ባለሥልጣኖች እየሆኑ በሹመት በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ይዘዋወራሉ።



በጎንደር ቤተ መንግሥት በቋረኞችና በየጁ መኳንንቶች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በደከመበትና እንደራሴው ሥልጣኑን ከዘዘበት ጊዜ ጀምሮ እንደራሴነቱን ይዘው የቆዩት ውልደታቸው ከአማራም ከኦሮሞም የነበረው የየጁ ባላባቶች ነበሩ። ከሌሎቹ ፊንጠር ብሎ ጐጃምና ዳሞት የተለዩ ጠንካራ ባላባቶች ነበሯቸው። የጎንደሩ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በእንደራሴዎች ሥር በወደቀበት ወቅት በሸዋ ያለው የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች ኃይለኛ ባላባቶች ኾነው ስለነበረ የጎንደሩን መንግሥት ለመተካት ዕቅድ ነበራቸው። በተለይ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዝግጅት ጀምረው በድንገት ስለሞቱ ልጃቸው ኃይለ መለኮት በሸዋ ንጉሥነት ቆዩ።

## ጐጃም

ጐጃም ምንም የአማራ አንዱ ትልቅ ክፍል ቢሆንም የራሱ የሆኑ ተከታታይ ባላባቶች ነበሩት። ሆኖም ባላባቶቹ በጋብቻም በመተባበርም አንድ ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜ እርስ በርስ ጐጃምና ዳሞት ብለው እየተለያዩ በመዋጋት ግዛቱን ሲያስተዳድሩ ኖረዋል።

ቋረኛዋና ጥሩይቱ እቴጌ ምንትዋብ የአፄ በካፋ ባለቤት በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያን ለሠላሳ ዓመት አስተዳድረዋል። አፄ በካፋ በወጣትነታቸው ስለሞቱ ከሁለቱ የተወለደው ቀዳዩ ዳግማዊ ኢያሱ ዓለም ሰገድ ነግሦ እቴጌ ምንትዋብ በሞግዚትነት መንግሥቱን ያስተዳድሩ ነበር። እቴጌ ምንትዋብ ወጣት ስለነበሩ ከምልምል ኢያሱ ሦስት የሚያማምሩ ሴቶች ልጆች ወለዱ። ኢያሱ ምልምል የተባሉበት ምክንያት የአፄ ኢያሱ ዓለም ሰገድ አባት የአፄ በካፋ እህት ልጅ ስለነበሩና ግንኙነቱም ድብቅ ስለነበረ ነው።

የእቴጌ ምንትዋብ ሦስቱ ውብ ሴት ልጆች አልጣሽ፣ አስቴርና ወለተ እሥራኤል (ዳግሚት) ናቸው። የተዳሩትም:-

| | |
|---|---|
| አልጣሽ | ለስሜኑ ባላባት |
| አስቴር | ለአዝማች ነሪሙ ቀጥሎ ለትግሬ |
| | ባላባት ለራስ ማርያም ባሪያው |
| | በመጨረሻም ለራስ ሥሑል ሚካኤል |
| ወለተ እሥራኤል | ለጎጃሙ ባላባት ለደጃች ዮሴዴቅ ነው። |

# የጐጃሙ ባላባት የደጃች ዮሴዴቅ ትውልድ




አፄ ኢያሱ ዓለም ሰገድ በሦስቱ እህቶቹ መወለድ ያፍር ስለነበረ ምልምል ኢያሱን አድብቶ ወደ ገደል አስገፍቶ አስገደለ። የሟች



እህትም አዘናግታ አፄ ኢያሱን በመርዝ በመግደል የወንድሟን ሞት ተበቀለች። ስለኸነም መንግሥቱን የአፄ ኢያሱ ዓለም ሰገድ ልጅ አፄ ኢዮአስ ወርሶ እቴጌ ምንትዋብ አሁንም በሞግዚትነት ማስተዳደር ቀጠሉ። የአፄ ኢዮአስ እናት የየጁ ባላባት ልጅ ስትሆን በትውልዷ ኦሮሞ ነበረች። ንጉሥ ኢዮአስ ወደ እናቱ ዘመዶች በማድላቱ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በቋረኞችና በየጁ ኦሮሞዎች አለመግባባት ስለተነሳ መንግሥቱ እየደከመ ሄዶ መጨረሻ ላይ እንደራሴው የትግራዩ ተወላጅ ራስ ሥሑል ሚካኤል አስገድሎት ሥልጣኑን ወሰደበት። የተለያዩ ጎሣዎች በጋብቻ የበለጠ ይቀራረባሉ ተብሎ ሲጠበቅ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ጋብቻ የጎሣ አለመግባባትን ሲፈጥር ይታያል።

ራስ መርዕድ የእህታቸውን ባል ደጃች ዘውዴን አስረው ጐጃምና ዳሞትን ሲያስተዳድሩ ኖረው ሲሞቱ ልጃቸው ደጃች ጓሉ ጐጃምን፣ የእህታቸው ልጅ ደጃች ጎሹ ዳሞትን ያስተዳድሩ ነበር። ደጃች ጓሉ ከሞቱ በኋላ ግን ደጃች ጎሹ ጐጃምን ከይመር ጓሉ ቀምተው ወደ ራሳቸው ግዛት ደረቡት:: አፄ ቴዎድሮስ የጐጃምን ገዥ ደጃች ጎሹን በ1845 ዓ.ም. ገድለው ልጃቸውን ብሩን ከማረኩና ከነገሡ ወዲህ ደጃች ተድላ ጓሉን በጐጃም ሾሙዋቸው::

በኋላ ግን ደጃች ተድላ ስለከዱዋቸው አፄ ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ ቢያሳድዱዋቸውም ለማግኘት አቃታቸው:: የሆኖ ሆኖ በጥር ወር በ1860 ዓ. ም. ደጃች ተድላ ሞተው በተክሌት የውሽ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስከሬናቸው አረፈ:: አሳቸውም ከሞቱ ከአራት ወር በኋላ በሚያዝያ ወር አፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ ራሳቸውን አጠፉ:: ደጃች ተድላ በጐጃም በጣም ተወዳጅ ስለነበሩ ብዙ ግጥም ተገጥሞላቸዋል ካህናት እንኳን የሚከተለውን አስካሁን ይዘምሩላቸዋል

ዘመኔ ዘመኔ ተድላ ዘመኔ
እሱ ተወልዶ ወልዶ ለኔ
እሱ ተወልዶ ወልዶ ለኔ ተድላ ዘመኔ

ራስ ዓዳል ተሰማ በልጅነታቸው ደጃች ተድላ ጓሉ ቤት ያድጉ በነበረበት ጊዜ ደጃች ተድላ አምነዋቸው ባለሟል አድርገዋቸው እያለ ከዕቁባታቸው ከወይዘሮ ጉዳዬ ልጅ ስለወለዱ ሸሽተው በርሃ ይኖሩ ነበር። ከአፄ ቴዎድሮስ ቀጥሎ ነግሠው የነበሩት የሰሜኑ ዋግሹም ጎበዜ (አፄ ተክለ ጊዮርጊስ) ጐጃምን ለማስገበር ዘምተው ለባላንባራስ ዓዳል እህታቸውን ወይዘሮ ላቀች ገብረ መድኅንን ድረውላቸውና የራስነት ማዕረግ ሰጥተው ጐጃም ላይ ሾመዋቸው ተመለሱ።



ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት

አፄ ዮሐንስ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስን አሸንፈው መንግሥታቸውን ስለ ወሰዱባቸው ራስ ዓዳል አልተደሰቱም ነበርና አልገብርም ስላሉ አፄ ዮሐንስ ለማስገበር ጎጃም ሲመጡ ራስ ዓዳል ሸሽተው በርሃ ገቡ። አፄ ዮሐንስ ለራስ ደስታ ተድላ ዘመዳቸውን ድረውላቸው ጐጃም ላይ አገረ ገዥ አድርገው ሾሙዋቸው። በተጨማሪም ሐጎስ የሚባል አስተዳዳሪ በሥራቸው ሾመው ተመለሱ። ራስ ደስታ ምንም ለአፄ ዮሐንስ ቢጋብቻ ቢዛመዱም የጐጃም ሰው ግብር በዝቶበታልና እኔ አልገብርም እያሉ ሲሉ ራስ አዳል ከበርሃ ተመልሰው ይወጓቸውና በጦርነቱ ራስ ደስታም ሐጎስም ይገደላሉጮጮ የራስ ደስታንና የሐጎስን አስከሬን ወደ መቃብር ሲወስዱ የራስ ደስታን በእንጨት አልጋ የሐጎስን በአጎበር በተከለለ አልጋ ሲወስዱ የጐጃም ሕዝብ ተመልክቶ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ገጠመ።

እኔስ ምንቸገረኝ ካንተም አልዋጋ
እሥራኤሉን ዘንጨት ወታደሩን ባልጋ



## የተድላ ጓሉ ትውልድ





ካዎ ጦና

- ካዎ ፖቶሎሚ
- ካዎ ታላሚ
- ካዎ ሞስካ
- ካዎ ሞታ
- ካዎ ኦቼ
- ካዎ ላቼ



የካዎ ላቼ መንግሥት ስለደከመ ከተንቤን ለመጣ ጦረኛ ለሹም አጋሜ በጋብቻ ከተሳሰሩ በኋላ መንግሥቱን በ1553 ዓ.ም. ለቀቀለት።

- ካዎ ሹም አጋሜ (ሹማግብ)
- ካዎ ሚካኤል
- ካዎ ግርማ
- ካዎ አዳዮ
- ካዎ ኮቴ

ካዎ ኮቴ የትንቢት ንጉሥ ይባል ስለነበረ ከእኔ 10ኛው ትውልድ መንግሥት ከዘሬ ይወጣል ብሎ ተነበየ።

- ካዎ ኮቴ
- ካዎ ሊበን
- ካዎ ቱቢ
- ካዎ ሳና

ካዎ ሳና ጦረኛ ንጉሥ ስለነበረ የወላይታን ሰባት ወረዳዎች ያስገበረና የሃዲያን መንግሥት ወግቶ ያዳከመ ነበር። በዚያን ጊዜ የሃድያ መንግሥት አሁን አርሲ የሚባለው አገር ነበረ። ሕዝቡ በአሁኑ ዘመን አብዛኛው አርሲ ኦሮሞ ሆኖ የሚታየው ወላይታ ያዳከመውን የሃድያን ሕዝብ ኦሮሞ ወግቶና አባሮ ስለተካው ነው።

ካዎ ሳና

ካዎ ኢጋቶ

ጦሳ ካዎ አማዶ

ካዎ ዳሞቴ

ካዎ ዳሞቴ በጦረኝነት የሚታወቅ ንጉሥ ሲሆን ተከታዩ ካዎ ኀቤ ግን ብልህና አስተዋይ ንጉሥ ከመሆኑም በላይ የአባ ጅፋር አማችም ነበር።

ካዎ ዳሞቴ

ወጋ ካዎ ኀቤ

ቡሻሻ ጋጋ

ካዎ ጦና



ቡሻሻ ጋጋ አባታቸው ላይ መፈንቅለ መንግሥት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረና አባትየውም በነገሩ ስለተናደዱ ረገሟቸውና በሳምንቱ በልብ ህመም ሳቢያ ሞቱ።



ፊታውራሪ ደስታ ፍስሐ

ከዚያም ካዎ ጦና ነግሠው ገና አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው በ1887 ዓ.ም በምኒልክ ስለተሸነፉ የመጨረሻው የወላይታ ንጉሥ ሆኑ። አፄ ምኒልክ ጦና ጀግና በመሆናቸው ስላከበሯቸው የክርስትና አባት ኾነው መልሰው የወላይታ አገረ ገዥ አድርገው ሾሟቸው። እሳቸውም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አዲስ አበባ በዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን አስከሬናቸው አርፎ በአሁኑ ወቅት መቃብራቸው በቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ በስተቀኝ በኩል ይገኛል።

ሕዝቡ የካዎ ጦናን ልጅ ቡሻሻ ሮቤ ወይም ፍስሐን ጦና ብሎ ይጥራቸው እንጂ አልነገሡም። የሳቸውም ልጅ ፊታውራሪ ደስታ ፍስሐ ናቸው። ፊታውራሪ ደስታ የሸዋ መኳንንት የአዛዥ ሽብሩን ልጅ ወይዘሮ አልታሽ ሽብሩን አግብተው አምስት ልጆች ወልደዋል።

ፊታውራሪ ደስታ ወይዘሪት እመቤት ደስታን ለሪር አድሚራል እስክንድር ደስታ በጋብቻ እንዲሰጡ ሽማግሌ ቢላኩባቸው አልሰጥም ስላሉ ወጣቶቹ ሳይጋቡ ቀሩ። በኋላ ላይ ነገሮች ተለዋወጡና እመቤት ደስታ ነጭ አገባች። ፊታውራሪ ደስታ ፍሰሐን ሰዉ ደስታ ጦና በሚል ስም ይጠራቸው ነበር። አሜሪካን አገር ሄደው ስለሞቱ አስከሬናቸው እዚያው ቨርጂንያና ዋሽንግተን ዲሲ መካከል በሚገኘው ግሬት ፓቶማክ ወንዝ አጠገብ ከቀድሞ ፕሬዜዴንት ዊድሮው ዊልሰን መቃብር ቁጥር 2176 አጠገብ አርፏል። ቁጥር 2146 መቃብራቸውም ላይ SON OF WOLAITA’S KING የሚል ጽሑፍ ተደርጎበታል።




## ከፋ

ከፋ ከወላይታ ቀጥሎ በአፄ ምኒልክ ጦር ላይ ኃይለኛ መከላከል ያደረገ ትልቅ የንጉሥ አገር ነበር። ንጉሡ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ከከባድ መከላከል በኋላ ተይዘውና ታስረው በምትኩ የማዕከላዊው መንግሥት ሹም በአገራቸው ተሾመበት።

መለኮታዊ ንጉሥ እንደነበረ የሚነገርለት ታቶ ጋኪ ሼሮቾ የከፋ ሥርወ መንግሥት 19ኛው ትውልድና የመጨረሻው ንጉሥ ሲሆኑ ሄኮ የሚባለው አምላክ በእሳቸው አድሮ የሚናገር መኾኑ ይታመን ነበር። የንጉሥ ሰሎሞንና የንግሥት ሳባም ዘር ናቸው ይባላል።

ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ለመዋጋት በሚሰናዱበት ጊዜ እንግሊዞች ዩጋንዳ ኾነው መሣሪያ እንላክልህ ቢሏቸው "አሁን የማካሂደው ጦርነት የወንድማማች ጦርነት ስለኾነ ዕርዳታ አያስፈልገኝም። እኔ ምኒልክን ካሸነፍኩት አገሩን በሙሉ አስተዳድራለሁ። እሱ ካሸነፈኝ



አገሩን በሙሉ ይግዛ። እርዳታ የምጠይቃችሁ የውጭ ጠላት ሲመጣብኝ ብቻ ነው" ብለው መልሰዋል።


ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ

ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ በጣም ኩሩ ከመሆናቸው የተነሳ በጦርነት ተሸንፈው እጃቸው ሲያዝ በእግር ብረት ሊያስሯቸው ሲሉ "እኔን ያህል ንጉሥ በብረት እግረሙቅ ሳይሆን ከብር በተሠራ ነው የምታሰረው" ብለው ራሳቸው ባቀረቡት የብር እግረሙቅ ታሰሩ።

ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾ ተይዘው ሲመጡ ጎጀብ ወንዝን ሲያቋርጡ ቀለበታቸውን አውልቀው ወንዙ ውስጥ ጥለው "የከፋ መንግሥት ከእንግዲህ አበቃ። ከእንግዲህ ወዲህ ሌላ ንጉሥ አይኖርም። የንጉሡ ቀለበትም በወንዙ ውስጥ ታርፋለች" ብለው ተናገሩ።

አፄ ምኒልክ ንጉሥ ታቶ ጋኪ ሼሮቾን እንደ አረመኔ አድርገው ስላዩዋቸው ምሕረት አድርገው መልሰው አገራቸው ላይ ሊሾሙዋቸው አልፈለጉም። ስለሆነም ወሎ ራስ ሚካኤል ዘንድ በእስር ተቀምጠው አቤቶ ኢያሱ በዘመኑ ስለፈታቸው አዲስ አበባ መጥተው ሲኖሩ በ1911 ዓ.ም ሞቱ።

## ጉራጌ

ከጊቤ እስከ አዋሽ መካከል ባለው አገር ይኖሩ ከነበሩ ሰዎች ጋር በአፄ ዓምደ ጽዮን ዘመን ከባሕር ነጋሽ አዲ ኳላ አውራጃ ደቀ መሃሪ ወረዳ ጉራዓ ከሚባል ቦታ የመጡ ወታደሮች ተደባልቀዋቸው ጉራጌ በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ጎሣ ኾኑ ይባላል። በእርግጥ የወታደሮቹ ብዛት ይኼን ያህል በነበረው ኅብረተ ሰብ ላይ ለውጥ

አምጥቷል ለማለት ያስቸግራል። ከቀድሞ ጀምሮ ጉራጌ በማዕከላዊ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ጎሣ ሲሆን በተለይ በግራኝ ወረራና በኦሮሞ መስፋፋት የተደቆሰና በሚመርጣቸው የጦር አበጋዞች አማካይነት ራሱን ተከላክሎ እንደ ደሴት ሊቆይ የቻለና ያልተደመሰሰ ብርቱ ጎሣ ነው። በዘመነ መሳፍንት ወቅት ተረስቶ ያለምንም ደጋፊ ራሱን እየጠበቀ የኖረ ጎሣ ሲሆን ከሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የጦር ዕርዳታ ቢጠይቅም ከጉብኝት በስተቀር በወቅቱ ምንም ያገኘው ዕርዳታ አልነበረም።

በመሠረቱ ጉራጌ በሦስት ይከፈላል። በምዕራብ ሰባት ቤት ጉራጌ፣ በምሥራቅ ስልጤና ወለኔ ወይም አደሬ ሲባሉ በሰሜን ያሉት በአጠቃላይ ክስታኔ በሚል ስም ይታወቃሉ። ለምሳሌ ሰባት ቤት ጉራጌ፣ የሚባሉት ኤነር፣ ቸሃ፣ እነሞር፣ እንደጋኝ፣ ጉመር፣ እዣ፣ ጌቶ ናቸው። በክስታኔነት የሚታወቁት በሁለት ተከፍለው ሶዶ ጅዳና ሶዶ ጎርደና ተብለው ይታወቃሉ። ሶዶ፣ ጉራጌና ኦሮሞ በብዛት የተደባለቁበት አካባቢ ነው። የምስራቁ የሰልጤው ክፍል በብዛት ሙስሊም ሲሆን ራሱን "ቶቦ" ብሎ ሲጠራ ክርስቲያኑን "ጠመኛ" ይለዋል። አንዳንዶች ደግሞ ክርስቲያኖቹን በጠቅላላው ጉራጌ ብለው ሙስሊሞችን በተለያዩ ስሞች ይጠሯቸዋል። ይኸውም በወሎ እስላም ነህ አማራ ተብሎ ባልተማሩ ሰዎች ይጠየቅ እንደነበረው መሆኑ ነው።

በአፄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጉራጌ ትኩረት እየተሰጠው ቢሄድም በ1870ዎቹ ላይ በከፊል ጉራጌ ለብቻ መንግሥት እንመሠርታለን በሚሉ ባላባቶች መሪነት ችግር በመፍጠሩ የአፄ ምኒልክ ደጃዝማቾች በተከታታይ ብዙ ዘመቻዎች አድርገው የተሸነፉበትና የሞቱበትም ሁኔታ ነበር። ሆኖም መጨረሻ ላይ ከብዙ ድካም በኋላ ስለተሸነፉ ሁኔታው በርዶ እንደቀድሞው በመካከለኛው መንግሥት ሥር መተዳደር ጀመሩ። ጉራጌዎች በአሁኑ ስሙ እንደ ሜጫ ያሉት ቦታዎቻችን በኦሮሞዎች ተወስዶብናል ይዳኙን ብለው ለአፄ ምኒልክ አቤቱታ ሲያቀርቡ ከወሰንተኞቻቸው ጋር የነበረውን ችግር ለማጥፋት አዲስ አበባ ውስጥ ጌጃ ሰፈርን ለመስፈሪያነት ሰጧቸው። በዙሪያው ባሉት አገሮች ላይ ገሚሱንም አሸንፈው ነጥቀውት እንደ ሶዶ ባሉት ቦታዎች ላይ ደግሞ ተደባልቀውት ከሚኖሩ ኦሮሞ ጎረቤቶቹ ጋር በአሁኑ ሰዓት በጉርብትናና በጋብቻ እየተደባለቀ ይኖራል። ቀደም ብሎ አዲስ አበባ ውስጥ በየካ ሚካኤል አካባቢ የሶዶ ጂዳ



ሰዎች ከእንግሊዝ ሌጋሲዮን አንስቶ ያለው ቦታ ላይ ሰፍረው ስለነበረ ዳግማዊ ምኒልክ ወደ ዓድዋ ሲዘምቱና በድል ሲመለሱ በሞቀ አሸኛኘትና አቀባበል ስላስደሰቷቸው እስከ ሰንዳፋ ድረስ ያለውን ቦታ በርስትነት መርቀውላቸው አሁን አካባቢው ሶዶ ጂዳ ይባላል።

የጉራጌ ጎሣ በብዛት በመላው ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ እየሠራ የሚኖር ታታሪ ሕዝብ ስለኾነ በሄደበት ሁሉ ተመሳስሎ ይኖራል። በአዲስ አበባም ውስጥ በሕዝብ ብዛት ከአማራ ቀጥሎ ይመደባል። ለኢትዮጵያችን ሙያና ባህል መዳበር የጉራጌ ኅበረተ ሰብ ያበረከተው አስተዋጽዖ በምግብ በኩል ብርንዶ እያሉ የሚበሉትን በአማርኛ ክትፎ በመባል የታወቀውን ተወዳጅ ምግብና ቆጮ የሚባል የዳቦ ዓይነት ሲሆን በማኅበራዊ ሥነ ምግባር ደግሞ ዕድርን ለመላው ኢትዮጵያ አውርሰዋል። በገንዘብ ቁጠባ በኩል አበዛኞዎቹ በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ስለሆነ የዕቁብን አሠራር ከሌላው ሕብረተ ሰብ በበለጠ ይጠቀሙበታል።

## ኦሮሞ

አለቃ ታየ ኦሮሞ የፈለሰው ከማዳጋስካር ነው ብለው ያሉት መሠረቱ ምን እንደኾነ የማይታወቅ ከመሆኑም በላይ የማዳጋስካር ሰዎች በአብዛኛው የእስያ የማላይ ዘር ሲሆኑ በአገሪቱ የቅርብ ሰፋሪዎች መሆናቸው ይታወቃል። ደሴት እንደመሆኑ መጠን በዙሪያው በተለይ በደቡብ ጥቂት አረቦች፣ በምሥራቅ የፖሊንኤዥያ ጥቁሮችና በምዕራብ የአፍሪካ ጥቁሮች በየወደቦቻቸው በቅርቡ እየተደባለቁዋቸው ነው። በተረፈ አብዛኞዎቹ በተለይ በመሃል አገር የሚኖሩት ጠጉራቸውም ቀጥ ያለና እንደ ኢንዶኔዥያንና ማሌዥያኖች ዓይነት ነው። በቋንቋቸውም የኢንዶኔዥያኖችና የማሌዥያኖች ቋንቋ ዓይነት ሲሆን ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት በብዛት ያሉበት ነው። የሚያመርቱትም በዓይነቱ አንደኛ የኾነ ሩዝ ሲሆን በዓለም ውስጥ በአማካይ በሰው ከፍተኛ ሩዝ የሚበሉ ሕዝብ ናቸው።

ደሴቱ የጥንት ሰዎች ትተውት ያለፉት ምልክት ሊገኝበት ስላልቻለ በቅርብ ሰዎች የሰፈሩበት አንድ ትልቅ ደሴት እንደኾነ ነው የሚገመተው። ደሴቷ ስም እንኳን የወጣላት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በቫስኮ ዳ ጋማ ሲሆን በዚያን ጊዜ የኦሮሞ ጎሣ በባሌ አካባቢ ሰፍሮና

ተበራክቶ እየኖረ ወደ ሰሜንና ምዕራብ መፍለስ የጀመረበት ወቅት ነበር። ከዚህም ሌላ የኦሮሞ ጎሣ እንደሌሎች የኢትዮጵያ ጎሣዎች ሁሉ የካም ዘር ሲኾን በባህል ከህንድ አምልኮት ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት የሚታይበት ነው። እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ጎሣ ሁሉ በተለይ እንደ ሶማሌ የደቡብ ሕንድ ደም ጥንት በመጠኑ ተደባልቆበት ሊሆን ይችላል። እንደ ኢጋጣሚ እኔ ጸሐፊው ማዳጋስካር ውስጥ ለሁለት ዓመት የኖርኩ ስለኾንና ይህንኑ አባባል አውቅ ስለነበር በትኩረት ተመሳሳይነት ብፈልግም ላገኝ ስላልቻልኩ አባባሉ ትክክል ለመሆኑ ፍንጭ አላገኘሁበትም።

የኦሮሞ ሕዝብ ከ10ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ጀምሮ አሁን የበርበራ ሱማሌ በምትባለው አካባቢ የሚኖር ሕዝብ የነበረና በ12ኛው ክፍለ ዘመን በሶማሌዎች ግፊት ወደ ደቡብ ሄዶ በባሌ አካባቢ ሲኖር ቆየ። ከዚያም ኑሮው ከቆለኛነት ወደ ደገኛነት ሲለወጥ ጤናማና ከበርቴ ስለኾነ የሕዝቡም ቁጥር እየበዛ ሄደ። በመሠረቱ የኦሮሞ ሕዝብ መብዛትን የሚወድ ስለነበረ ጦርነት ላይ ሴትና ልጅ ማርኮ በባህሉ ማግባትና ማሳደግ፣ በሠላሙም ጊዜ ከአራት ሚስት በላይ በማግባቱና በጉዲፈቻና በማደጎ የሌላ ሰው ልጅ እየወሰደ እንደራሱ ልጅ በሞጋሳ የሚያሳድግ ስለኾነ ቁጥሩ እየበዛ ሄደ። በአሁኑ ወቅት በሕዝብ ብዛት የሚወዳደረው አማራ እንጂ ሌላ የሚደርስበት ጎሣ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም። በቅርቡ በጉዲፈቻ ልጅነት ካደጉት ውስጥ ከሚታወቁ የአማራ ልጆች መካከል ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንጠቅሳለን።

1ኛ ደጃች ወልደ ሚካኤል ጉዲሳ - አማራ (መንዜ)
2ኛ አቶ ተስፋዬ ቀጀላ - አማራ (መንዜ)
3ኛ ደጃች. ክፍሌና ካፒቴን አክሊሉ ዳዲ - አማሮች (ጎንደሬዎች)
4ኛ ደጃች. ገለታ ቀርቾ - አማራ (መርሐ ቤቴ)
5ኛ አፈ ንጉሥ መስፍን ገመቹ - አማራ (መንዜ)
6ኛ አበበ ቢቂላ (ተጉለትና ቡልጋ)

የተቸገረ አማራ፣ ትግሬ ወይም ጉራጌ ልጁን በጉዲፈቻ የመስጠቱ ልምድ አሁን ድረስ ይሠራበታል። በተጨማሪም ልጅ ከከተማ እየወሰዱ በባላገር ለሚኖሩ የሚያቀርቡላቸው ሰዎች እስክ ዘመናችን ድረስ አሉ። ከከተማ ከሚወሰዱ ልጆች መካከል ለምሳሌ ነጭ አሜሪካኖች የሆኑ ሁለት እህትማማቾችና አንድ ወንድማቸው ሰበታ አካባቢ ከመኪና ውስጥ በልጅነታቸው ተወስደው በኦሮሞነት



አድገዋል። ወንዱ አሁን አዲስ አበባ አንበሳ አወቶቡስ ኩባንያ ውስጥ ይሠራል። ከሴቶቹ አንደኛዋ ሰበታ ከተማ እንጨት በማቅረብ ንግድ ስትተዳደር ሌላዋ ትዳር ይዛ ባላገር ውስጥ ትኖር ነበር። በአሁኑ ጊዜ ሁለቱም ሴቶች አዲስ አበባ ነዋሪ ቢሆኑም ነጋዴዋ ግን ሰበታ በገበያ ቀን ብቅ ማለቷን አልተወችም። በልጅነት ስለተወሰዱ የእናት አባት ቋንቋቸውን ረስተው በምትኩ ኦሮምኛ ተናጋሪ ሆነዋል። ከአደጉ በኋላ ትምሕርት ቤት ገብተው አማርኛ ተምረው መናገር ችለዋል። የሦስቱ ኦሮሞ ነጭ አሜሪካኖች ስም

አቶ ኃይለ ማርያም (ቀልቤሳ) ጋዲሳ
ወይዘሮ ትዕግስት ጋዲሳ
ወይዘሮ ሌንሳ ጋዲሳ ነው።

አንድ ሌላም ተመሳሳይ ሁኔታ ያላት ነጭ አሜሪካዊት ነኝ የምትል በችግረኛነት በአምቦ መንገድ ላይ እንደምትኖር ይታወቃል። በትዳር ስትኖር ባልዋ ልጆች ከወለዱ በኋላ በመሞቱ ተቸግራ እርዳታ እስከመጠየቅ መድረሷንና ዜናውም በቴሌቪዥን መተላለፉን ሰዎች ይናገራሉ። ይሁንና በልማድ አንድ የጉዲፈቻ ልጅ መብቱ ከተፈጥሮ ልጅ ጋር እኩል ነው።

የግራኝ ጦርነት የደጋውን የክርስቲያን ንጉሥ አገር ስላዳከመው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በይበልጥ ለኦሮሞ መስፋፋት ቀላል ኾነለት። በየደረሱበት ቦታም በባላባታቸው ስምና በአገኙት ምክንያት ሁሉ ለሶፈሩበት ቦታ የኦሮምኛ መጠሪያ ስም በመስጠት የበፊት ስሙን ደመሰሱ። አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጎጃም ውስጥ ያሰፈራቸው ኦሮሞዎች አገሩን ሜጫ ብለውት በዚሁ ስም ይታወቃል። በሸዋም ሌላ ሜጫ የሚባል አገር አለ። የባላባቶቻቸውን ስሞች እንደ ሜጫና ወሎ ያሉትን በአገር መጠሪያነት ተኩ።

| | | |
|---|---|---|
| ለምሳሌ | ደዋሮ | ጨርጨር |
| | ጋፋት | ሆሮ ጉድሩ |
| | ግራርያ | ሰላሌ |
| | ዳሞት | ወሊጋ |
| | እናሪያ | ሊሙ |
| | አበቤ | በቾ |

አፋሮች ብልጫ እያላቸው ሥልጣኑን አንድ ሦስተኛ ለሆኑት ሶማሊዎች አስረክባ በመሄዷ ለጭቆና ዳርጋቸዋለች። የሞቃድሾ ሶማሊ መንግሥት ሲፈራርስ በስደተኝነት ከሶማሊ እየመጡ ጂቡቲ ውስጥ መኖር ሲጀምሩ በአገሪቱ ውስጥ የሶማሊው ቁጥር እየጨመረ ሄደ።

በአፋር ሁሉ ነገር የባላባቱ ስለኾነ በባህሉ መሠረት የፈለገውን ማድረግ ይችላል። ሆኖም ባላባቱ ለንጉሠ ነገሥቱ በተራው ይገብራል። የደጃዝማች ያሆ ሞሐመድ አባት ሃንፍሬ ዳግማዊ ምኒልክ ወደ አድዋ ሲዘምቱ አብረው እንዲዘምቱ ቢነገራቸው አሻፈረኝ ብለው ሸፈቱ። በዚህም ምክንያት አሣኸር ወልደ ጻድቅ ታዘው ወግተዋቸዋል። ይሄንን ዘመቻ የሰሙት ደጃዝማች ኀንጉል በአፄ ምኒልክ ላይ ሸፍተው ከነበረበት ከአዳል በርሃ መልዕክተኛ ልከው አብሬ የአገሬን ጠላት እንድዋጋ ምሕረት ይደረግልኝ ብለው በመጠየቅ አፄ ምኒልክ ወዲያው ተስማምተው አብረው ዘመቱ። ተተኪው ዋናው የአፋር ባላባት ፊታውራሪ ያሆ በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ከማዕከላዊው መንግሥት በማፈንገጣቸው በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ከሞቱ በኋላ ቢትወደድ ዓሊ ሚራህ ሃንፍሬ በምትካቸው የበላይ ባላባት ኾነዋል።

ቢትወደድ ዓሊ ሚራህ ሃንፍሬ ዕድሜያቸው ረኸርምና ዕድል ያልከዳቸው ሰው ናቸው። ደርግ ባንድ በኩል እየረገመ በአንድ በኩል እየመረቀ እጃቸውን ሊይዝ ባደረገው ሙከራ ብዙ ወታደር ከሁለቱም ወገን ካለቀ በኋላ አምልጠውት ወደ ጅቡቲ ገብተው ከዚያም በኋላ በስደት ኖረው ኢሕአዴግ ሲገባ እንደገና ወደ አገራቸው ተመለሱ። ኢሕአዴግ ባመቻቸው አንድ ትልቅ ስብሰባ ላይ ተካፍለው የባንዲራ ጉዳይ ተነስቶ “እንኳን እኛ አፋሮቹ ግመሎቻችን ሳይቀሩ የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቃሉ” ብለው ተናግረዋል። ምንም እንኳን አሁን አፋርን የተመረጡ አስተዳዳሪዎች ያስተዳድሩታል ቢባልም አሁንም በሕይወት ያሉ የተከበሩና የታመነባቸው የአፋር የባህል መሪ ቢትወደድ ዓሊሚራህ ሃንፍሬ ናቸው።

## ሶማሊ

በሶማሊ ጎሣ ውስጥ ብዙ ጎጦች (ክላኖች) ስላሉ እያንዳንዳቸው በየባላባታቸው ይተዳደራሉ። አገራቸውን ከኢትዮጵያ ነጥለው



የምዕራባውያን አገሮች ሲወስዱ ተደራጅተው መዋጋት የማይችሉ ግና በጦርና በፍላፃ የሚጠቀሙ ስለነበሩ አብዛኞዎቹ በቅኝ ግዛት ቀንበር ውስጥ ገብተዋል። ይሁንና የማዕከላዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ራሱ ደካማ ስለነበረ ከመሬት ዘረፋው ተከላክሎ ሊያድን የቻለው የኦጋዴንን ሶማሊ ብቻ ነበር። ስለኾነም ምሥራቁ በኢጣሊያን ሰሜኑ በእንግሊዝ ሲያዝ በከፊል ደግሞ እንግሊዝ ከኬንያ ጋር ደባልቆ ደቡቡን ያስተዳድር ነበር። በኋላ ግን እንግሊዝ በጎነጎነችው ተንኮል ታላቅዋ ሶማሊያ የሚል አስተሳሰብ በመፍጠሯ በሞቃድሾ የተመሠረተው የሶማሊ መንግሥት ከጎረቤቱ ጋር ሁሉ ሲዋጋ ራሱ ደክሞ ማዕከላዊው የሶማሊ መንግሥት ስለፈረሰ እንደገና ሶማሊዎች በየጎሣቸው እየተዋጉ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ሶማሊዎችም እንዱ የኢትዮጵያ ጎሣ ስለሆኑ መብታቸው ተከብሮ ቢኖሩም የሞቃዲሾውን መንፈስ ይዘው የመጡ ስደተኞች አድራጊ ፈጣሪ እየሆኑ ችግር በመጠኑም ፈጥረዋል። ይሁንና በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ኦጋዴን ውስጥ ያሉት በየባላባታቸው ሥር ቢኖሩም የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት አንድ አውራጃ ስለነበረ የበላይ አስተዳዳሪ ነበረው። መጨረሻ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በደርግ ዘመነ መንግሥት ሲተካ 29 የአስተዳደር አካባቢዎች ራስ ገዝ ሲሆኑ ኦጋዴንም አንዱ የአስተዳደር አካባቢ በመሆን በሚሾም ባለሥልጣን ይተዳደር ጀመር።

የሞቃድሾው መንግሥት ፈራርሶ በስደት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሶማሊዎች በፊት ሲነገራቸው የነበረው ጥላቻ አለመኖሩንና የኢትዮጵያ ሕዝብ በሠላም ስለተቀበላቸው ጥላቻው የመንግሥት ፖለቲካ እንጂ የሕዝቡ እንዳልነበረ ተረዱ።

## አደሬ

አደሬ በሐረር ከተማ ውስጥ ብቻ የሚኖር የአንድ የጎሣ ስም ነው። አደሬዎች ቀደም ባለው ዘመን ከሸዋ አይመለል ወደ ሐረርጌ የሄዱ ሲሆኑ በቅርበት የሚዛመዷቸው ስልጤዎች ናቸው። በግራኝ አሕመድ ንቅናቄ ጊዜ ከአረብና ከቱርክ አገሮች በቅጥርና በዕርዳታ የመጡ ወታደሮች ጦርነቱ ሲያበቃ ያልተመለሱት በሃይማኖት አንድነት ምክንያት ከአደሬዎች ጋር ተጋብተው ቀርተዋል። በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመነ መንግሥት ግብጾች አስግረው ገብተው ለአሥራ አንድ

ዓመት ስለቆዩ በዘመኑ የወለዷቸው ልጆች በጎሣው ውስጥ ተውጠዋል። ስለሆነም ከሌላው ኢትዮጵያዊ በአማካይ ቀላ ይላሉ።

በኦሮሞ መስፋፋትና በሌሎችም ምክንያቶች አደሬዎች በመጨረሻ የተገኙት በሐረር ከተማ ግንብ ውስጥ ብቻ ነበር። በ1940 ዎቹ ዓ.ም ውስጥ መንግሥት ለመመሥረት ሲያደሙና በመስጊዳቸው ውስጥ በድብቅ የጦር መሣሪያ ሲያከብቱ ተይዘው አድመኞቹ ከተፈረደባቸው በኋላ በመላ ኢትዮጵያ ስለተሰራጩ፣ ፖለቲካውን ትተው የንግድ ሥራቸውን በማስፋፋት ኑሯቸውን ቀጠሉ። አዲስ አበባ ውስጥ በመርካቶ አካባቢ በብዛት ይኖራሉ። በዚሁ ምክንያት አዲስ አበባ ውስጥ የአደሬ ሠፈር የሚባል መንደር አለ። በተጨማሪም በመካኒሳ መንገድ ከቫቲካን ኤምባሲ በታች የሚኖሩበት ሰፈር ከእነ መስጊዱ ጭምር አላቸው። በተጨማሪም በሰበታ መንገድ ዳለቲ በሚባል መንደር በከብት እርባታ፣ በአነስተኛ ኢንዱስትሪና እርሻ ተሠማርተው ይኖራሉ።

አደሬዎች ቋንቋቸው እንደ ግዕዝ፣ አማርኛ፣ ትግርኛና ጉራጊኛ የሴም ቋንቋ ሲሆን በብዛት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። የተለየ የባህል ልብሳቸውም ቀለምና ጌጥ የበዛው ነው። ሴቶቻቸው የእጅ ሥራ አዋቂ ከመሆናቸውም በላይ በመኖሪያ ቤታቸው ግድግዳዎች ላይ የተጌጡ የምግብ ቤት ቁሳቁሶችን በመስቀል ቤታቸውን ያስውባሉ።

የአደሬዎች የሕዝብ ብዛት በአሁኑ ወቅት ወደ አርባ ሺህ ስለሆነና ከሌላው ጎሣ ጋር ሲወዳደር በጣም በማነሱ ምክንያት ዘራቸው እንዳይዋጥና እንዳይጠፋ በማለት ወታደርነት እጅግም አይገቡም፤ እንዲሁም ከሌላም ጎሣ ጋር በተቻለ መጠን አይጋቡም። ጋብቻቸው ብዙውን ጊዜ ከቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር (Inbreeding) ነው።

## ማጂ

በከፋ ግዛት ውስጥ የማጂ ጎልዲያ ጎሣ የሚገኘው በኢትዮጵያ የምዕራብ ጠረፍ ሲሆን የማጂ ከተማ የተቆረቆረው በ1879 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ጋር አንድ ዘመን መሆኑ ነው። ከተማው የተመሠረተው



በራስ ወልደ ጊዮርጊስ ነው። ማጂ ሱዳን ወሰን አጠገብ ያለ አውራጃ ሲሆን የራሱ ቋንቋና ባህል ያለው ጎሣ የሚኖርበት አገር ነው።

ማጂ አውራጃ ለሱዳን አገር የቀረበ ስለሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የእንግሊዝ መንግሥት በማጂ ከተማ ቆንስላ ጽሕፈት ቤቱን አቋቁሞ ነበር። በኢትዮጵያና ጣሊያን ጦርነት ሳቢያ የእንግሊዝ መንግሥት በማጂ ተቋቁሞ የነበረውን የእንጨት መሰንጠቂያና የጡብ ፋብሪካ ነቅሎ ወደ ሱዳን አሻግሮታል። የማጂ ወረዳዎች ትርማና ጥዱ፣ ቲሻ ወይም ሜኢኒት በመባል ይታወቃሉ። የሕዝቡ ብዛት አናሳ ነው። እንደማንኛውም ጎሣ ማጂ ባላባቶች አሉት። ከነዚህም የሚታወቁት ፊታውራሪ ኩሪ፣ ፊታውራሪ ጋሲ፣ ፊታውራሪ አዲካስ፣ ፊታውራሪ አርቡርጂ ናቸው።

ጣሊያን ጀምሮት የሄደው የመኪና መንገድ ስላላለቀና ስላልተጠገነ ማጂ ከአዲስ አበባ ጋር ያለው ግንኙነት በአየር ብቻ ተወስኖ ቀረ። አገሩ ቀደም ሲል ጀምሮ ስልክ፣ የአይሮፕላን ማረፊያ፣ ትምሕርት ቤትና ጤና ጣቢያ አለው። በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ስልክ ሲገባ ከሐረር አዲስ አበባ ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ ጊዳሚና ማጂ ነበር።

## ማጠቃለያ

በዓለማችን በሚገኙት አብዛኞዎቹ አገሮች ውስጥ የተለያዩ ጎሣዎች እንዳሉ ይታወቃል። ከእነዚሁም መካከለ ጥቂቶቹ የጎሣቸው ሰው ብዛት ከፍ ያለ ሲሆን በርካታዎቹ ደግሞ አነስተኛ ቁጥር አሉዋቸው። ለምሳሌ ህንድ ከ 400 በላይ ጎሣዎች አሏት። ኢትዮጵያም ውስጥ ወደ 80 ጎሣዎች እንዳሉ የነገራል። በመግባባትና በዘዴ ከተጠቀሙበት ይህ ራሱ ትልቅ ሃብት ነው። መላው ኅብረተ ሰብ "ልዩነት በአንድነት" ብሎ ካመነና የእያንዳንዱን ኅብረተ ሰብ ባህል ካዳበረው ጥቅሙ ወደፊት ይታወቃል። አለበለዚያ ግን ጠላቶች እንደሚመኙት ለመፍረክረክ፣ አቅመቢስና ደካማ ለመሆን የጠላት መሣሪያ ሊሆን ይችላል። ይሁንና እላይ ከተጠቀሱት ጎሣዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ አነስተኛ የሰው ብዛት ያላቸው ጎሣዎች በየቦታው ይኖራሉ። አንዳንዶቹ ቁጥራቸው ከፍ ያሉ ሲሆኑ እንዲሁም ሌሎቹ አነስተኛ ናቸው። በመሠረቱ ሁሉም በየባላባታቸው የሚተዳደሩ የነበሩ ሲሆን በአፄ ምኒልክና በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን

ወራሹ ለአቤቶ ኢያሱ እንዲተላለፍ ስለተስማሙ ይኸው በመጋቢት ወር 1902 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን ተደረገ።



አፄ ምኒልክ ኃይለ መለኮት

የእቴጌ ጣይቱ ከሥልጣን መወገድ የብዙ ነገሮች ውጤት ነበረ። በአንድ በኩል የአድዋ ጦርነትና የድሉም መሳካት የእሳቸው ቆራጥነት ያስከተለው ስለነበረ ፈረንጆቹ እቴጌን ጥምድ አድርገው ስለ ያዙዋቸውና መኳንንቶቹን እንደቀሰቀሱባቸው ግልጽ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከግብጽ ጳጳስ ማስመጣቱን እንደማይደግፉ ይታወቅ ስለነበረና አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆነው የዴር ሡልጣን ባለቤትነት የኢትዮጵያ መሆኑን እያወቁ ለግብጽ አድልተው ስለመሰከሩ እቴጌ ጣይቱ ለአንድ ዓመት አዲስ ዓለም አግዘዋቸው ስለነበረ ሊቀ ጳጳሱ እቴጌን በማሻር ተበቀሉ። በመጨረሻው ደግሞ ዘውዱን ወደ ጎንደር ይመልሱታል የሚል የሸዋ መኳንንቶች ፍርሃትም ነበረ። በመሆኑም ራስ ቢትወደድ ተሰማ የልጅ ኢያሱ ሞግዚት የአልጋ ወራሹ አደራ በላቸው ጫንቃ ላይ ስለነበረ የእቴጌ ሥልጣን መያዝ ያስፈራቸው ነበር። ይህ ሁሉ ተደማምሮ እቴጌ ጣይቱ ባለቤታቸውን እንዲያስታምሙ ስለተባለ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከእንጀራ ልጃቸው ከወይዘሮ ዘውዲቱ ጋር አርፈው ተቀመጡ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ማቴዎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በነበረ ጊዜ የኢትዮጵያ ገዳማት ርስት ሆኖ በቆየውና የሚካኤልና አርባዕቱ እንስሳት ታቦቶች በሚገኙበት ዴር ሡልጣን ገዳም ይዞታ ላይ ጥያቄ ተነስቶ ገዳሙ የግብጻውያን ስለመሆኑ እንደመሰከሩ በኢትዮጵያ ወሬው ደርሶ ነበር። ነገሩም ለኢትዮጵያ መንግሥት የደረሰው ከደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ጋር የአቡነ ማቴዎስ ተከታይ ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ተልከው የነበሩት አቶ ኃይለ ማርያም ሰራቢዮን ጋሻ ለእቴጌ ጣይቱ



ባቀረቡት ሪፖርት ነው። ይህን በተመለከተ በኢየሩሳሌም ሃያ አምስት ዓመት የተቀመጡት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ስለዴር ሡልጣን የተናገሩትን ገበታ ሐዋርያ የንባብ መማሪያ በ1928 ዓ.ም ከደስታ ተክለ ወልድ ከተጻፈው መጽሐፍ ገጽ 49 ላይ ይመልከቱ። ጉዳዩን ለማብራራት ያህል አቡነ ማቴዎስ የዴር ሡልጣን ገዳም ንብረትነቱ የግብጽ እንጂ የኢትዮጵያ እንዳልሆነ በማስመልከት የበሩ ቁልፍ ወደ ግብጻውያን መነኮሳት መዛወር እንዳለበት በሰጡት የጽሑፍ ማስታወሻ የተረጋገጠ ነው። በ1945 ዓ.ም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሆነው አዲስ የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ ጉዳዩን ተከታትለው ከቆዩ በኋላ አቡነ ማቴዎስ ትውልዳቸውም ሆነ ዜግነታቸው ግብጻዊ እንደመሆናቸውና ለእኛም ጳጳስነት የበቁት በግላችን በምንከፍላቸው ገንዘብ እንደመሆኑ ለግብጽ አድልተው በእኛ መመስከራቸው ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ መሆኑን አስረዱ። ውሳኔውንም በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ በወቅቱ የግብጽ ኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ አቡነ ቁርሎስ ይህንኑ ከመቃወም አልፈው አቡነ ፊልጶስን ከኢየሩሳሌም የጽጽስና ወንበር እስከነአካቴው እንዲነሱ በሰጡት ትዕዛዝ ጉዳዩ እንደተዘጋ ቆይቶ ነበር።

ቀደም ብሎ እቴጌ ጣይቱ ይህንኑ ጉዳይ ከሥረ መሠረቱ በማጤን ከተረዱት በኋላ ለአቡነ ማቴዎስ የነበራቸው ክበሬታና ስለታማኝነታቸው የነበራቸው አስተያየት እጅጉን ዝቅ ያለ ነበር። ይህም በመሆኑ አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያን ጥቅም የማይወክሉ መሆናቸውን በመገንዘብና እቴጌይቱ አቡኑን እንደ አደገኛ ሰው በማየት ተጻራሪ አቋም ይወስዱባቸው ነበር። በተለይም አፄ ምኒልክ በ1900 ዓም የተለያዩ ሚኒስትሮችን ሲሾሙ አቡነ ማቴዎስ የመጀመሪያውን የዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት በማቋቋም በኩል የነበራቸውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ የትምሕርት ሚኒስትርነትን ስፍራ ለእሳቸው እንደሚገባ ተጠቁሞ አፄ ምኒልክ ዘንድ ሲቀርብ እቴጌ ጣይቱ "ጌታችን ለጥቂት ያልታመነ ለብዙ እንዴት ይታመናል ብሎ የለምን" ብለው በመከራከር ስለተቃወሟቸው ሥልጣኑ እንደማይገባቸው ታምኖበት ሳይሾሙ ቀሩ። እንዲያውም በየምክንያቱ ሳይሳካላቸው ቀርቶ ነው እንጂ እቴጌ ጣይቱ ከዚህ አልፈው በመሄድ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ በግብጽ ፋንታ ከሶርያ ኦርቶዶክስ

ሲያገለግል የታወቀ ሰው ስለሆነ የንጉሥ ማህለ ሥላሴን ልጅ አግብቶ ራስ መኮንንን ይወልዳል። በዚህም ሳቢያ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተንቤን ትግራይ ውስጥ የሚገኘውን የዘር ርስታቸውን ፊታውራሪ አበበ ገብረ መድህንን ወክለው ተከራክረው ከረቱ በኋላ ተረክበዋል ይላሉ። ሆኖም ፊታውራሪ አበበ ገብረ መድህን "ይወክሉኝና የዘር ርስትዎን ላስመልስ" ብለው ስላመለከቱና ጃንሆይም "በል እስቲ ሞክር" ብለው ስለፈቀዱላቸው እንጂ በእርግጥ ውልደታቸው የተረጋገጠ ሆኖ አይደለም የሚሉም ብዙ ናቸው። ፊታውራሪ አበበ ገብረ መድህንንም ብዙ ሰው በዚህ ጉዳይ አምቷቸዋል። ከዚህም ጋር ለማያያዝ ጃንሆይ ትግራይ ሄደው ንግግር ሲያደርጉ "ትግሬ የተወለድኩበትም የወለድኩበትም ነው" ሲሉ ተናገሩ።

በሌላ በኩል ጃንሆይ የሞጃ ተወላጅ ናቸው በማለት መኳንንቶችና የጊዜው ሰዎች ቢወለዱም ባይወለዱም ሞጃ ነን በማለት እንደ ልዩ ፍጡር ራሳቸውን በመቁጠር አንድ ቡድን ፈጥረው ነበር። ድሃውን የሞጃ ተወላጅ እንኳን ሳያስጠጉ ራሳቸውን ብቻ በመካብ ያገኙትን ሁሉ "የድሃ ልጅ! ማን እንደሆንኩ ታውቃለህ?" እያሉ ሲመጻደቁና ሲንፈላሰሱ ምንም ሳይሠሩ ተበታተኑ። ቡድኑ ያተረፈው ነገር ቢኖር የአማራን ጎሣ በሌሎች ጎሣዎች እንዲጠላ ማድረግ ብቻ እንጂ የሠራው ፋይዳ ያለው ነገር አልነበረም። እንዲያውም ሞጃዎች ራሳቸውን ብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ አድርገው ስለተመለከቱ በጃንሆይ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 22 ሚሊዮን ደረሰ ሲባል አንዱ ከመካከላቸው "እኛ 500 እንኳን አንሞላም" እስከማለት ደርሳ ነበር። በተለይ የአማራ ጎሣ ነን የሚሉት ሞጃዎች አማራው ወዳጅና ጠላቱን እንዳይለይ፣ ራሱን እንዳይጠብቅና እንዳይዘጋጅ ክልለው ሜዳ ላይ ጥለውት ራሳቸውም ተበታትነዋል።

ራስ መኮንን በሕይወት ዘመናቸው ልዑል አልተባሉም። ሆኖም ጃንሆይ ስለ አባታቸው በሚናገሩበት ጊዜ ሁሉ "ልዑል አባቴ" እያሉ ስለሚናገሩ እሳቸውን በመፍራትና ደስ ለማሰኘት ሲሉ ብዙ ሰዎች ልዑል ራስ መኮንን እያሉ ይገልጹ ጀመር። ቢሆንም ራስ መኮንን በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከፍተኛው ባለሟል እንደነበሩ የታወቀ ነው።

ዳግማዊ ምኒልክ አራት ዓመት ከሚበልጡዋቸውና ሲጋቡም ፊት የነበሩና የ43 ዓመት ዕድሜ ከነበራቸው ባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ብጡል ኃይለ



ማርያም ልጅ አልወለዱም። ቀደም ብለው የወለዱዋቸው ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው ሞተውባቸው አልጋቸውን የሚወርስ ወንድ ልጅ አልነበራቸውም። ሆኖም ከሴት ልጃቸው ከወ/ሮ ሸዋ አረጋና ከወሎው ራስ ሚካኤል የተወለደ የልጅ ልጅ አቤቶ ኢያሱ ነበረ። ሌላ በሕይወት ያለች ሴት ልጅ ወ/ሮ ዘውዲቱ ብቻ ስለነበረች ሕዝቡ 'ዳግማዊ ምኒልክ አልጋውን የሚያወርሱት ለራስ መኮንን ነው' እያለ ያወራ ነበር።

እቴጌ ጣይቱ ደግሞ ከሳቸውም ባይሆን ከዘመዶቻቸው ንግሥና እንዳይወጣ ብዙ ጥረት አድርገዋል። የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛዋ ሴት ልጅ የዘውዲቱ ባል የጣይቱ ወንድም የደጃች ወሌ ብጡል ልጅ ራስ ጉግሳ ወሌ እንዲሆኑም አድርገዋል። እንዲሁም የተፈሪ ታላቅ ወንድም የደጃች ይልማ መኮንን ባለቤትም የእቴጌ ጣይቱ እህት ልጅ የነበረችው አሰለፈች ወንዴ ናት። ከልጅ ኢያሱ ቀጥሎ ለዘውዱ ቅርበት ያለውን ታየ ጉልላቴን ጣይቱ ከወንድማቸው የልጅ ልጅ ከአልማዝ መንገሻ ጋር አጋብተዋል። ሌሎቹንም እህቶቻቸውን ለተለያዩ መኳንንቶች፣ ወንዶች ዘመዶቻቸውንም ለወይዛዝርት ድረዋል።

እቴጌ ጣይቱ 'ከመኮንን የሚወለድ አልጋውን ይወርሳል' የሚባል ትንቢት ስለሰሙና ወ/ሮ የሺ እመቤትም ሞተው ራስ መኮንን ብቸኛ መሆናቸውን ስለተገነዘቡ፣ የወንድማቸውን የራስ ወሌን ሴት ልጅ ምንትዋብ ወሌን ሰጥተው እንዲያገቡ አዘዙ። ልጅቷ ዕድሜዋ በጣም ትንሽ ስለነበረ ራስ መኮንን ትደግ እያሉ ከተፈሪ፣ ከእምሩና ማሚት ጋር እየተጫወተች ተላምዳ ስድስት ወር ያህል ከቆየች በኋላ ልጆቹን ሰብስበው ከዘመዶቻቸው እንዲላመዱ በየጊዜው ወደ አዲስ አበባ ያመጡ ነበርና እሷንም ከሌሎቹ ጋር ይዘዋት መጡ። ታዲያ እቴጌ ጣይቱ 'ጸነሰች ወይ?' ብለው ቢጠይቋት 'ምንም ግንኙነት አልነበረም!' ብላ በመመለሷ እቴጌ ይናደዱና ሌሎቹ ልጆች ወደ ሐረር ሲመለሱ ምንትዋብን አስቀሯት።

ይህንን ሁኔታና የራስ መኮንንን ጸዋሚና ጸሎተኛነት በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ ራስ መኮንንን 'መነኩሴው!' ማለት ጀመሩ። በመሃሉ ራስ መኮንን ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ እንደተነሱ ታመሙና ወደ ቁልቢ ተመልሰው መታከም ጀመሩ። ለሁለት ወር ያህል ከታከሙ በኋላ በሽታው ይጠናባቸውና መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም ሲሞቱ ባለሚሎቻቸውና ዘመዶቻቸው አስከሬናቸውን ይዘው ወደ ሐረር ይሄዱና ሐረር ጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ባለቤታቸው ወይዘሮ የሺ እመቤት መቃብር አጠገብ ወዳጅ ዘመድ በተሰበሰበበት ተቀበሩ።

ከላይ የተጠቀሰውን የራስ መኮንንን መመነን ሕዝቡ በክፊል ሲቀበለው አንዳንድ ሰዎች ግን አያቶቻችን "ቆመን አስቀብረናል" ብለውናል ይላሉ። እንዲያውም ራስ መኮንን ሊሞቱ ሲሉ ለራስ እምሩ አባት ለፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ "ልጄን ተፈሪን አደራ ሰጥቼሃለሁ" ብለዋቸው እንደነበረ ጭምር ይነገራል። በሌላ በኩል ደግሞ የቀበረ ሁሉ አስከሬኑን አየ ለማለት ያስቸግራል። ጥቂቶች ደግሞ "አይ የቅዱስ ልጅ መስሎ ለመታየት በተፈሪ የተነዛ ወሬ ነው" ብለው ያጣጥሉታል። እንዲያውም ራሳቸው ጃንሆይ ሰዎች ይኽን ነገር ብዙ ጊዜ ሲያነሱባቸው ፈገግ ብለው ነገሩን ችላ ብለው ያልፉታል ይባላል።





# ምዕራፍ ፰

## መካኗ እቴጌ ጣይቱ ብጡል

እቴጌ ጣይቱ ብጡል ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም ደቡብ ጎንደር በደብረ ታቦር ከተማ ተወለዱ። እናታቸው ወ/ሮ የውብዳር አባታቸው የሰሜኑ ባላባት ደጃች ብጡል ኃይለ ማርያም ናቸው። ጣይቱ ውልደታቸው ከሸዋም፣ ከየጁም፣ ከጎንደርም መሳፍንቶች ሲሆን እንዲያውም ከአፄ ሱስንዮስ ሴት ልጅም ከሐመልማላዊት ዝርያ አላቸው።

ጣይቱ በልጅነታቸው እቤት አስተማሪ ተቀጠሮላቸውና በየአድባራቱም የሃይማኖት ትምሕርት በደንብ ተምረዋል። የግዕዝ ቋንቋ አጥርተው ያውቃሉ፣ በገናም ይደረድራሉ።

አፄ ምኒልክ የሚያፈቅሯቸው የመርሃቤቴዋ ተወላጅ ሚስታቸው ወይዘሮ ባፈና ከጠላቶቻቸው ጋር በባላቸው ላይ እየዶለቱባቸው ስላስቸገሯቸው ተፋቱ። ወዲያው ሚስት ፈልጉልኝ ብለው አዘው ከወላይታ ቆንጆ ተመርጣላቸው ስትመጣ፣ በድንገት ጣይቱ ብጡል መምጣታቸውን እንደሰሙ፣ አዲሷን ሚስት ይዘው ለመጡት የኮፉ ዳሞቴ የልጅ ልጅ ለሆኑት ለፊታውራሪ ዲቢሶ ጋሻ፣ አንተው አግባት ብለው መረቁላቸው።

አፄ ምኒልክ በልጅነታቸው ጎንደር ስለነበሩ እንዲሁም ሸዋም ከተመለሱና ከነገሡ በኋላ የጣይቱ ብጡል ሁለት ወንድሞች ልጅ አሉላ ብጡልና ባላንባራስ ወሌ ብጡል አድረውላቸው ነበረና ስለጣይቱ አስቀድመው ብዙ ያውቁ ነበር። ስለኾነም በወቅቱ የጣይቱ

ይሁንና የበጌምድርና ስሜን አገረ ገዥ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ በትግራይ ወስጥ የተፈጠረውን አለመግባባትና ንጉሡ ሳያዙ በተደረገው ጦርነት አጥፊውን ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ ታዘው ሲሄዱ፣ ደጃች ገብረ ሥላሴ ሸሽተው ከነሠራዊታቸው ኤርትራ ውስጥ ገቡ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስ የኤርትራ ወሰን ላይ ከነሠራዊታቸው ሰፍረው ሲጠባበቁ በወቅቱ የጣሊያን ጦር ወደ ሊቢያ ተልኮ ነበረና የኤርትራ አስተዳዳሪ ጉዳዩ ስላስፈራው የራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጦር የሠፈረበትን ወንዝ በራስጌው መርዝ ስላደረገበት ወታደሩ ውሃውን እየጠጣ ስለታመመ ጦሩ ሊፈታ ቻለ።



ልዕልት ወለተ እሥራኤል ሥዩም

ደጃች ስብሐት የአጋሜ ገዥ ስለነበሩ በሳቸው መገደል የአድዋና የአጋሜ ሰዎች ቂም ተያይዘው እስከ አሁን አይጣጣሙም። ከአራት ዓመት በኋላ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ይቅርታ ተደርጎላቸው ወደ ሸዋ ከተመለሱ በኋላ ይህንን መቃቃር ለማጥፋት የራስ ሥዩም ልጅ የሆኑትን ልዕልት ወለተ እሥራኤልን እንዲያገቡ ተደርጎ ሸዋ ውስጥ ሜጫ ሲኖሩ ደጃዝማች ዶክተር ዘውዴ ገብረ ሥላሴን ወለዱ።

ከባለቤታቸው ዕረፍት በኋላ ልዕልት ወለተ እሥራኤል ወጣት ስለነበሩ የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን የመጀመሪያ ሚስት ኾነው ልዕልት እጅጋየሁ አስፋ ወሰንን ወለዱ። በጠላት ወረራ ጊዜ በስደት እሥራኤል አገር ሄደው በነበረበት ወቅት ባለቤታቸው ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን እሳቸውን ትተው ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅን ሲያገቡ በድርጊቱ ተናደው ልጃቸው ዘውዴን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ለጠላት እጅ ሰጡ። ልዕልት ወለተ እሥራኤል ሰዓሊ ስለ ነበሩ ለየቤተ ክርስቲያኑ የጻድቃንን ምስል እየሠሩ ያበረክቱ እንደ ነበረ ይታወቃል። በእርጅና ምክንያት በ1982 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።



ራስ ወሌ ብጡል እህታቸውን እቴጌ ጣይቱን በሥልጣን ለማቆናጠጥ እርምጃ መውሰድ ሲችሉ "ከምኒልክ ጋር የገነባሁትን አገር መልሼ አላፈራርስም" ብለው ሳይዋጉ ቀሩ።

እቴጌ በሥልጣን ለመቆየት ያደረጉት ጥረት በባለሥልጣኖች ተንኮል ተሰናከለ። ይሁንና እቴጌ ጣይቱን መኳንንቶቹ ከሥልጣን ካስወገዱዋቸው በኋላ አፄ ምኒልክን ሲያስታምሙ ቆይተው አፄ ምኒልክ ሲሞቱ ልጅ ኢያሱ ከቤተ መንግሥት አስወጥቶ እንጦጦ ላይ በግዞት አስቀምጧቸው ሲኖሩ፣ በመሃሉ በኩላሊት በሽታ እግራቸው አብጦ የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም ሞተው እንጦጦ ማርያም ተቀበሩ። በኋላ ግን አስከሬናቸው ወደ ባዕታ ማርያም ተዛውሮ ከባለቤታቸው ከአፄ ምኒልክ አስከሬን አጠገብ አርፏል።

እቴጌ ጣይቱ አድዋ ላይ ዘምተው በመልስ ላይ የጣሊያን ምርኮኞችን እንዳይርባቸው ጧት ጧት 30 ከረጢት ዳቦ እየተቆረሰ ለምርኮኞቹ ጣሊያኖች ሁሉ ያድሉ ስለነበረ እቴጌ ብቅ ሲሉ ጣሊያኖቹ "ኤኮ! ኤኮ! ሲኞሪና አል ዳቦ" እያሉ ወደ እሳቸው ይሮጡ ነበር። እንዲያውም ከአጀባቸው ከግማሽ በላይ የጣሊያን ምርኮኛ ወታደሮች ኾነው ነበር።

እቴጌ ጣይቱ ከአድዋ ጦርነት ታሪካቸው ሌላ ከሚታወሱባቸው ነገሮች ዘመናዊ ሆቴል መክፈት፣ የነጭ ጤፍ ዘር ከጎንደር አስመጥተው ሸዋ እንዲያበቅል አድርገው በቤተ መንግሥት ነጭ ጤፍ እንጀራ እንዲበላ ማድረጋቸው አንዳንዶቹ ሲሆኑ በተጨማሪም አዲስ አበባ ከተማንና ጽጌ ረዳ አበባን ስም ያወጡላቸው እሳቸው መሆናቸው ይታወቃል።



# ምዕራፍ ፮

## ደጃች ታየ ጉልላቴ

ከዳግማዊ ምኒልክ ቀጥሎ መንግሥ የነበረበት ትክክለኛው ሰው እያለ ሌሎች የነገሡት ያለአግባብ እንደነበረ የሚተቹ በወቅቱ ቢኖሩም የኃይል ሚዛኑን እያዩ ነገሩን ከማራገብ ተቆጥበዋል።

ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ስድስቱ ወንዶች ልጆች መካከል አንዱ መርዕድ አዝማች ኃይሌ ሲሆኑ የሳቸውም ልጅ ከወይዘሮ እንጆሪ የተወለዱት ፊታውራሪ ጉልላቴ ኃይሌ ናቸው። ፊታውራሪ ጉልላቴ ኃይሌ አፄ ምኒልክን ከቤት ሠራተኛ በመወለዳቸው ይንቋቸው ነበርና አፄ ምኒልክ ገና ከሩቅ ብቅ ሲሉ ተነስተው ይቆሙ ነበር። አፄ ምኒልክም "እዩት ጉልላቴን ቀድሞ የሚነሳው እኮ እኔ ስደርስ ኖሮ ብሎ እንዳይነሳልኝ ማሳሳቱ ነው" እያሉ ለሰዎች ይናገሩ ነበር። ፊታውራሪ ጉልላቴ ኃይሌ መንግሥ ይመኙ ስለነበረና ምኒልክም ስለተጠራጠሩ አስረዋቸው እንደነበረም ይተረካል።

ከዳግማዊ ምኒልክ በኋላ ከሌሎቹ ዘውዱን ለመረከብ ከተሰለፉት መኳንንቶች ይልቅ ልጅ ታየ ጉልላቴ የሚለዩት ውልደታቸው ቀጥታ የሣህለ ሥላሴ የወንድ የልጅ ልጅ ስለሆኑና ሌሎቹ ራስ ተፈሪንም ጨምሮ ተወላጅነታቸውን የሚቆጥሩት በእናታቸው ወይም በሴት አያታቸው በኩል ስለኾነ ነው። ይህንኑ በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ የወንድማቸውን የራስ ወሌን የልጅ ልጅ አልማዝ መንገሻን ለልጅ ታየ ጉልላቴ ድረውላቸው የሠርጉ ሥነ ሥርዓት በቤተ መንግሥት ተከበረ። የዚህን ጊዜ አዝማሪ በዘፈንና በቀረርቶ ስማቸውን እያገነነ የሚከተለውን ገጥሞላቸዋል።





ደጃች ታዬ ጉልላቴ

ቀና ብዬ ባየው አፈሰሰ ቡቴ
መጥቶህ ከደንልኝ ታዬ ጉልላቴ

የእቴጌ ጣይቱ መሻርና የዘውዱ አወራረስ መሽጋሸግ በአድማ የተቀነባበረ ስለነበረ እንቅፋት ይሆናል ተብሎ የተጠረጠረውን ግለሰብ መከታተል ወይም ማጥፋት አስፈላጊ ስለነበረ ልጅ ታየ ጉልላቴን የልጅ ኢያሱ እንደራሴ ራስ ቢትወደድ ተሰማ ሥልጣን በያዙ በአራተኛው ቀን አስረው ወደ ወሎ ላኩና ልጎት በተባለ አምባ በእስረኛነት እንዲቀመጡ አደረጉ። በዚህም አምባ እስከ ሰገሌ ዘመቻ ዘመን ድረስ ታስረውበታል። በኋላም ደጃዝማች ተብለው የጊሚራ ገዥ በመሆን ለሃያ አንድ ዓመት ርቀው እንዲቀመጡ ሆኗል። ለሹመታቸው የተሰጠው ምክንያት ደጃች ታየ ጉልላቴ በምኒልክ ጊዜ የጠመንጃ ጥገና በደንብ ተምረው ስለነበረና እሳቸውም ከሺ ጠመንጃ ጋር የሰለጠነ ሠራዊት ስለነበራቸው ጠረፍ ይጠብቅ የሚል ነው። ደጃች ታየ በፋንታቸው ቀኛዝማች መላኩንና ወይዘሮ አመዘነችን ይወልዳሉ።



# ምዕራፍ ፯

## ጎረምሳው አቤቶ ኢያሱ

የአቤቶ ኢያሱ እናት ሸዋረጋ ከእናትዋ ከወይዘሮ ደስታና ከዳግማዊ ምኒልክ ኃይለ መለኮት በድብቅ ተወለደች። ወይዘሮ ደስታ ቤተ መንግሥት ውስጥ ጠጅ ክፍል ስትሠራ የኖረች ቀይ ወፍራምና ቆንጆ ሴት ነበረች። እርግዝ በነበረበት ጊዜ ሸሽታ ወደ ወሎ ሄዳ ስትኖር ልጇን ሸዋረጋን ወልዳ፣ አሳድጋ ዳረች። ሸዋረጋም ወታደር ባሏን አግብታ ወደ ሐረርጌ ሄደች።

የሸዋረጋ ባል ከአንገቷ ላይ የማይለየውን ክታብ ስለተጠራጠረ ሚስቱን አግባብቶ ክታቡን ከፍቶ ሲያነበው የዳግማዊ ምኒልክ ልጅ መሆንዋን ይገነዘባል። እሱም ይደነግጥና ትንሽ ካሰበበት በኋላ ድሃ ወታደር ስለነበረ ሊሾም ሊሸለም ፈለገና ሚስቱን ወስዶ ለእቴጌ ጣይቱ ምስጢሩን አስረድቶ ይሰጣቸዋል። እቴጌ ጣይቱ ልጅቷን ይቀበሉና በድብቅ ወደ ቤተ መንግሥት አስገቧት። ከዚያም ልብስ አለባብሰው ከሌሎች ሴቶች ጋር አሰባጥረው አፄ ምኒልክን እጅ እንዲነሱ አስልፈው አቀረቧቸው። አፄ ምኒልክ ግን ከሌሎች ልጆች መካከል ትክ ብለው ሸዋረጋን ይመለከቱና "ይቺ የማነች ልጅ?" ብለው ቢጠይቁ የወይዘሮ ደስታ ልጅ መሆንዋ ይነገራቸዋል። ከዚያ ቀን በኋላ ልጅቷ ቤተ መንግሥት መኖር ጀመረች። ከጊዜ በኋላ ጉዳዩ ግልጽ እየኾነና ልጅቷም እያማረባት በመሄዱ የመኳንንቱን ቀልብ መሳብ ጀመረች። ከዚያም የአፄ ምኒልክ አብሮ አደግ ለሆኑት ለራስ ጎበና ዳጬ ልጅ ለወዳጆ ጎበና ተዳረች። መጨረሻ ላይ ግን የወሎውን ባላባት ራስ ሚካኤልን አገባች።

ልጅ ኢያሱ ከእናቱ ከአፄ ምኒልክ ሴት ልጅ ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከወሎው ራስ ሚካኤል ዓሊ ጥር 25 ቀን 1888 ዓ.ም በወሎ ጠቅላይ ግዛት



ወረሂመኑ ተንታ ውስጥ ተወለደ። ስመ ክርስትናውም ክፍለ ያዕቆብ ተባለ።

የኢያሱ አባት ራስ ሚካኤል ወይም ክርስትና ከመነሳታቸው በፊት መሐመድ ዓሊ የተወለዱት ከኢማም ዓሊ አባቡላና ከግንደበረት ከተወሰደችው አገልጋይ ከወይዘሮ ጌቴ ነው። ግንደ በረት በምዕራብ ሸዋ ውስጥ የሚገኝ በባርያ ፍንገላ የታወቀ ወረዳ ነበር።

ልጅ ኢያሱ በአባቱ በኩል ከሌሎች እናቶች የተወለዱ እህቶችና ወንድሞች ነበሩት። እነሱም:-

| | |
|---|---|
| ደጃዝማች ደስታ | ደጃዝማች ዓሊ |
| ደጃዝማች ኃይለ ማርያም | ወይዘሮ ስሂን |
| ራስ ገብረ ሕይወት | ወይዘሮ ተዋበች ናቸው። |

ልጅ ኢያሱ ሰውነቱ ደልዳላ፣ ቁመቱ ዘለግ ያለና መልኩ የሚያምር ወጣት ነበር። እንደ አብዛኛው ወሎዬ ቤተ ዘመዶቹ መልከ መልካም ናቸው። ኢያሱ ገና በ12 ዓመቱ እቴጌ ጣይቱ የወንድማቸውን የራስ ወሌን የልጅ ልጅ የኾነችውን ጽጌ ሮማን መንገሻ ዮሐንስን በ8 ዓመቷ ድረውለት ነበር።

ዳግማዊ ምኒልክ ታመው በነበረበት ጊዜ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው የልጅ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን አልጋ ወራሻቸው መሆኑን አስታወቁ። ዕድሜው ገና 13 ዓመት ስለነበረ በልጅ ኢያሱ ስም ራስ ቢትወደድ ተሰማ አገር ሲያስተዳድሩ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ዕድሜያቸውም ገፍቶ ነበርና በሚያዝያ ወር 1903 ዓ.ም ስለሞቱ ልጅ ኢያሱ ምትክ ይሾምልህ ቢባል "አሁን ትልቅ ነኝ ማስተዳደር እችላለሁ" ብሎ አሻፈረኝ አለ። ሆኖም ራስ አባተ ቧያለው እንደራሴ ለመሆን ሲሞክሩ ሌሎች ስላልተስማሙ አቤቶ ኢያሱ አገሩን ማስተዳደር ጀመረ። ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስና ሌሎችም የመስፍኑን ልጅነት እያዩ ያለሞግዚት አገር እንዲያስተዳድር የተስማሙት በእልህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከልብ እንደማይደግፉትና ውድቀቱን እንደተመኙ ግልጽ ነው።

ልጅ ኢያሱ ጉርምስና የሚያጠቃው ባህሪ ስለነበረው ያያትን ቆንጆ ሁሉ ሥልጣኑን በመጠቀም ማግኘት ቻለ። ቆንጆ ትሁን እንጂ ባል ቢኖራትም ባይኖራትም ግድ አልነበረውም። ያንገራገሩትንም ሰዎች ራሱም ኾነ

"የአባትህን ሃይማኖትስ የለወጥክ አንተ ነህ!" ብሎ አፀፋውን በቁጣ መልሶ ሄደ ብለው ተናገሩ ተብሏል።



አቤቶ ኢያሱ ሚካኤል

የአቤቶ ኢያሱ ሁኔታ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም በይፋ ግን ሃይማኖቱ ክርስቲያን መሆኑ ግልጽ ነው። መጨረሻ ላይ እንኳን እጁ የተያዘው ቅብጽያ ገዳም ውስጥ ተሸሽጎ ነበር። በጠቅላላው በአቤቶ ኢያሱ ላይ እበላ ባዩ ሁሉ የስም ማጥፋት ዘመቻ ስላካሄዱበት የሚወዱት እንኳ በዘመኑ ደፍረው ሊከራከሩለት አልቻሉም።





ልጅ ኢያሱ በሰባት ዓመቱ ዳዊት ሲደግም

አባቱ ንጉሥ ሚካኤል መሻሩንና የተሻረበትን ምክንያት እንደሰሙ "እኔ እቆባውና አርመው የነበረውን ሳያማክሩኝ እንዴት ከአባቱ ዙፋን ያወርዱታል" ብለው ተቆጡ። የንጉሥ ሚካኤል ክርስቲያንነት በጣም የጠለቀ ስለነበረ ቄሶች 'ያላመነና ያልተጠመቀ መንግሥት ሰማያት አይገባም' እያሉ ሲነግሯቸው ለወላጆቻቸው ከመጨነቃቸው የተነሳ "ወላጆቼ ከመቃብር እንደገና ቢነሱ የክርስትና ሃይማኖት እንዲከተሉ አስጠምቃቸው ነበር በማለት አዘውትረው ይናገሩ ነበር ይባላል። በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ታላቁ ራስ ዓሊ ሴሩ ጓንጉል ተመሳሳይ አመለካከት እንደነበራቸው ተዘግቧል። በዚህ የተነሳ ንጉሥ ሚካኤል በክርስትና ሃይማኖት ፍቅር ልባቸው የነደደ መሆኑ እየታወቀ ልጃቸው ጭልጥ ብሎ የእስልምና ተከታይ ነበረ ለማለት ያስቸግራል።

ልጅ ኢያሱ አንዳንድ ተራማጅ የሆኑ አዋጆችን አውጥቷል። ለምሳሌ የሌባ ሻይንና የቁራኛ ፍርድን ከማስቀረቱም በላይ የባለርስትና የጭሰኛን ግንኙነት በተመለከተም የተሻሻለ ሕግ አውጥቋል። በተጨማሪም የልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ምንም አጭር ቢሆንም ሠላም የሰፈነበትና የጥጋብ ጊዜ ስለነበረ ሕዝቡ የሚከተለውን ገጠመ።

ፊቱምሮ ወደ ደሴ መወሰዱና ዋና ከተማውንም ወደ እዚያው ለማዛወር ማሰቡ ስለተወራ ነው።

መኳንንቶቹም በልጅ ኢያሱ ተግባር ደስተኛ ስላልነበሩ አድመው መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም እንዲሻር አደረጉ። በምትኩም የአፄ ምኒልክ ሴት ልጅ ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥት ተብለው ሲነግሡ ደጃች ተፈሪ መኮንን ራስ ተብለው አልጋ ወራሽ እንዲሆኑ ተወሰነ። የዚህ አድማ ጠንሳሾች ቤተ መንግሥት አካባቢ ያሉ መኳንንቶች ናቸው። በኋላ ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ተወሰነ ተብሎ ተገለጸ።



በሐረር ልጅ ኢያሱ ባለበት ስብሰባ ቲ. ኢ. ሎሬንስ እንደተገኘ

"በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም" እንደሚባለው ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ለማጥላላት የተለያዩ ፎቶግራፎች በመገጣጠም እየበተነ ሰው ሲራብ እሳቸው ውሻ ሲመግቡ፣ ሌላም ፎቶግራፍ እየቀጣጠለ በትኗል።

ልጅ ኢያሱን የሚወዱ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም የመኳንንቱን ውሳኔ ለመቃወም አመች አልነበረም። አንድ ወታደር አቤቶ ኢያሱን ለማገዝ ወደ ሐረር ከመሄዱ በፊት እንደሚከተለው ሸለለ ይባላል።

"አባ ጤና ኢያሱ ጥይት ግዛ! ጥይት ግዛ! ወገብክን ይጭንቀው!
እኛ ሰማን ወሬ አንተ የማታውቀው!"





ንጉሥ ሚካኤል (በሞንታጅ የተዘጋጀ ምስል)

የአቤቶ ኢያሱ መሻር ሐረር ላይ እንደተሰማ ከተማው ተረብሾ ወደ 500 ያህል ሰው ሞተ። አቤቶ ኢያሱም መሻሩን እንደሰማና የተሰጠውንም ምክንያት እንደተረዳ መኳንንቶቹንና ካህናቱን ቤተ መንግሥት ሰብስቦ መጽሐፈ ቄደር ተጠምቆ ስለመ የተባለውን አሰተባበለ። ሐረር የነበሩትንም የካቶሊክ ጳጳስ ጠርቶ ሁኔታውን እንዲገነዘቡና ምስክር እንዲሆኑት አደረገ። አቤቶ ኢያሱ ወደ አባቱም ወደ ንጉሥ ሚካኤል መልዕክት ላከ። ጦርም አዘጋጅቶ ወደ ሸዋ ሊዘምት ሲል ከሸዋ የተላከ ጦር ሚኤሶ (ሐረርጌ) ላይ ገጥሞት ተሸነፈ። የአባቱም ጦር ወደ ሸዋ ገብቶ ሰገሌ ሜዳ ላይ ተሸንፎ ንጉሥ ሚካኤልም ተማረኩ። የዚህን ጊዜ ልጅ ኢያሱ በአዳል በረሃ አቋርጦ ወደ መቅደላ ሄደና ጦር ሰብስቦ ውጊያ ቢጀምር አልቀናውም። ከዚህ በኋላ በአውሳ በርሃ አድርጎ ቢጋብቻ የሚዛመዱት ራስ ሥዩም ዘንድ ምዕራብ ትግራይ ግዛት ሄደ። ዕርዳታ የማያገኝ መሆኑን ሲረዳ ወደ ምሥራቅ ትግራይ ዘልቆ ራስ ጉግሣ አርአያ ዘንድ ሄደ። የእስላም ባላባቶች ወደ ቆላ ግባና እኛ ዘንድ እንደብቅሃለን፣ ሚስትም እንድርሃለን በሠላምም ትኖራለህ ወይም ወደ ኤርትራ ይዘንህ እንጥፋ፣ ቢሉት ከአገሬ አልወጣም ሚስትም አለችኝ፣ መስለምም አልፈልግም ብሎ ቅብጽያ ገዳም ገብቶ ተደበቀ። እዚያም እንዳለ ራስ ጉግሣ ስለፈሩ ያዙትና ደሴ ወስደው ለራስ ተፈሪ አስረከቡት። መጨረሻ ላይ ወደ ሸዋ ተይዞ መጣና ሰላሌ በራስ ካሣ ኃይሉ ሥር ግዞት ወረደ። ይህ ሁሉ ግብግብ በጠቅላላው አራት ዓመት ፈጀ።

በራስ ካሣ ጠባቂነት በግዞት ሰላሌ እያለ ልጃቸውን ባገባው በራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት አቀነባባሪነት ከአሥመራ አይሮፕላን መጥቶ አራት ቀን ጠብቆት ተሰፋ ቆርጦ ከተመለሰ በኋላ ልጅ ኢያሱ ከእስር ቤት አምልጦ የሚቀበለው ሲያጣ ወደ ጐጃም ሲሄድ ተያዘ። ከዚህ በኋላ በግዞት ወደ ሐረር ተወስዶ ቢጋራ ሙለታ አውራጃ በግራዋ ከተማ እስር አምባ ሲኖር በ1928 ዓ.ም ተገደለ ተብሎ በሰፊው ተወራ።

ሦስተኛው ገለጻ ደግሞ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሚለው መጽሐፍ የገለጹት ሲሆን እሳቸውም መጋቢት 7 ቀን 1927 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ መሞታቸው በቤተ መንግሥት ተነግሮ ሃዘን ተቀምጠው ነበር ብለው አትተዋል። ይህንኑ ሁኔታ የሚያጠናክር ከአንድ ታሪኩን በደንብ አውቃለሁ ከሚሉ አዛውንት ሴት እንደሰማሁት "ልጅ ኢያሱ ከወልወል ግጭት በኋላ በ1927 ዓ.ም መሞቱ ተነግሮ ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ ቤት ሃዘን ተቀምጠው እቴጌ ልቅሶ መድረሳቸውን አውቃለሁ" ማለታቸውን ነው። ቀጥለውም "የአሟሟቱን ሁኔታ ግን አላውቅም" ብለዋል። ስለሆነም ይህ አባባል አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከጠቀሱት ወቅት ጋር ይገጥማል። ስለ ልጅ ኢያሱ አሟሟት ሕዝቡ በይፋ ሊገለጽለት ስላልቻለ እንዲህ ዓይነት ብዙ ሃሜት ቢነገር አይደንቅም።

ሥልጣን ከልጅ ኢያሱ ወደ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ቀጥሎም ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዞር፣ የነበረው ሁኔታ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። በመሠረቱ የመንግሥት ግልበጣ ነው ለማለት ይቻላል። አንድ የመንግሥት አመራር ላይ ያለን ሰው በኃይል አውርዶ በምትኩ ሌላ ካስቀመጡ የመንግሥት ግልበጣ መባሉ ተገቢ ነው። ግልበጣው የተደረገበትም ምክንያት የብዙ ጉዳዮች ውጤት ነው። የሃይማኖቱ ጉዳይ ዕውነትነቱ ቢያጠራጥርም ዕውቀት ባልተስፋፋበት አገር ውስጥ የሃይማኖት ነገር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ልጅ ኢያሱም በዘዴ ችግሮችን መወጣት ሲችል በልጅነት ምክንያትና የሚሰማቸው የበሰሉ አማካሪዎች በጎኑ ስላላሰለፈ ውድቀቱ ተፋጠነበት። በተጨማሪም የአያቱን መኳንንቶች ማክበር ሲገባው ጭራሽ ከማወረዱም በላይ አባቱ የቆረቆሩትን ከተማም ትቶ የአገሪቱን መናገሻ ከተማ ወደ ደሴም ለማዛወር መከጀሉ የሸዋን መኳንንቶች በማሳዘኑ ብዙ የሚወዱትም ቢኖሩ ከግልበጣው እንዳያድኑት ራሱ በሩን ዘጋ።

አፄ ምኒልክ ገና እንደታመሙ አልጋቸውን ስለሚወርሰው የልጅ ልጃቸው በማሰብ ከመኳንንቶቻቸው መካከል በውልደት የማይመኩትን ራስ ተሰማንሞግዚት አድርገው ሾመውለት እያለ ታመው የአልጋ ቁራኛ ሲሆኑ የመንግሥት ሥራው በእቴጌ ጣይቱ መካሄድ ጀመረ። የአልጋቸው ወራሽ ልጅ ኢያሱ መሆኑን አውጀው ነበርና ራስ ተሰማ ከሌሎች መኳንንቶች ጋር በመደማደም የእቴጌን ሥልጣን በልጅ ኢያሱ ስም ይዘው ማስተዳደር ሲጀምሩ ብዙ



ነገሮችን ማበላሸት ጀመሩ። ልጅ ኢያሱ የሚኖረውም እሳቸው ቤት ስለነበረ ቤታቸው ውስጥ ሥነ ሥርዓት የተጓደለ ከመሆኑም በላይ ይህ ትንሽ ልጅ በወጣት ሴቶች የተከበበ አኗኗር ውስጥ ተዘፈቀ። ራስ ተሰማ ራሳቸው የሥልጣን ጥመኛ ስለነበሩ ለመንግሥም ሃሳብ ስለነበራቸው ገና ሥልጣን እንደጨበጡ ለንግሥናው ቅርበት የነበረባቸውን ልጅ ታየ ጉልላቴን አጋዙዋቸው። ዓመት ያህል እንዳስተዳደሩ ሽማግሌም ስለነበሩ በደም ብዛት ድንገት ወድቀው ወዲያው ሞቱ። ይህ ወጣት ልጅ ምናልባት ሌሎች መኳንንቶችን ያላስጠጋበት ምክንያት አንድም ራስ ተሰማ ጥላቻ አሳድረውበት ይሆናል። በተጨማሪም በአካባቢው የነበሩ ወጣት ምሁሮች ምናልባትም መኳንንቶቹን አናንቀውበትም ሊሆን ይችላል።



አቤቶ ኢያሱ በእስር ቤት

ይሁንና ልጅ ኢያሱ ከአንደኛ የዓለም ጦርነት በፊት የወገነው ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ስለነበረ እነሱ በተሸነፉ ጊዜ የኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ ምን ይሆን ነበር ብሎ ለገመተ ሰው 'እንኳን በጊዜው ልጅ

ኢያሱ ወረደ' ብሎ መደምደም ይችላል። ባይወርድስኖሮ ከማይጨው ጦርነት የባሰ ነገር ኢትዮጵያ ላይ ይደርስባት ኖሯል? ምዕራባውያኖች የራሳቸውን ጥቅም እንጂ ወዳጅ የማያውቁ ስለሆኑ ምናልባት ልጅ ኢያሱ የወሰደው እርምጃ የተለየ ሁኔታ ሊፈጥር ይችል ነበር ማለትም ሌላ አማራጭ ነው። ልጅ ኢያሱ ተሸሮ ሌላ ሰው ሥልጣን ስለያዘ ኢትዮጵያ ወደቦችዋን እንደ አጣች ቀረች እንጂ ያገኘችው የተለየ ጥቅም አልነበረም።

## የልጅ ኢያሱ ትውልድ

ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን ላይ የወጣን ሰው ክርስቲያን ከሆነ ከንጉሥ ሰሎሞን ለማዛመድ እንደሚሞከረው ሁሉ ሙስሊምም ከሆነ ከነቢዩ ሙሐመድ እንዲዛመድ ጥረት ይደረጋል። ልጅ ኢያሱ የነቢዩ ሙሐመድ ተወላጅነት አለው ተብሎ ተወስቷል።

## የነቢዩ ሞሐመድ ትውልድ በልጅ ኢያሱ መስመር

1 ነቢዩ ሞሐመድ 519 ዓ.ም
2 ፋጡማ (የአሳብ አሊይ ሚስት)
3 ሁሴን (አንገቱን የተቀላው)
4 ዛና ላባዲን
5 ሞሐመድ አልባጂር
6 አብደላህ
7 ሙሳ አልካዲን
8 ዑመር
9 ታጅ አላህ
10 ያህያ
11 ኢስማኤል
12 ኑር አህመድ
13 ከሊል
14 ኢብራሂም
15 ሞሐመድ
16 ታማም
17 ታጅ አዲን
18 ሞሐመድ
19 ያጉት
20 ያኩብ
21 ኢማም ኑር
22 ሳኒ አላህ
23 ኢሳ
24 አይሻ
25 ዛኒ ኤል ኬር
26 ኑር ሁሴን
27 ሻምስ አዲን
28 ኑር አዲን
29 ዲዋ አዲን
30 ጋፑ
31 ኢማም ዓሊ(ወደ ኢትዮጵያ መጡ)
32 ኢማም ሙሐመድ
33 ኢማም አህመድ
34 ኢማም ሙሐመድ
35 ኢማም ሊሻን
36 ኢማም ዓሊ (የንጉሥ ሚካኤል አባት)
37 ሞሐመድ ዓሊ (ንጉሥ ሚካኤል)
38 አቤቶ ኢያሱ[9]

[9] ከአምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ጽሑፍ የተወሰደ



የልጅ ኢያሱ አባት ንጉሥ ሚካኤል ወይም ሞሐመድ ዓሊ በእናታቸው በወይዘሮ ስሂን 1ኛ በኩል የአፄ ፋሲል 6ኛ ትውልድ ናቸው ተብሎ ተጽፏል። ነገር ግን እናታቸው ወይዘሮ ጌቴ ነበሩ እንጂ ወይዘሮ ስሂን 1ኛ አልነበሩም። የንጉሥ ሚካኤል አባት ኢማም ዓሊ የነቢዩ ሞሐመድ 36ኛ ትውልድ በመሆናቸው ልጅ ኢያሱ የነቢዩ ሞሐመድ 38ኛ ትውልድ ኾኖ ይቆጠራል።

ንግሥና እንደ ንግሥተ ሳባ ሕገ ደንብ መሠረት በአባት እንጂ በእናት ስለማይቆጠር ከዳግማዊ ምኒልክ በኋላ የነበረው ውስብስብ ችግር አቤቶ ኢያሱንም ጠልፎታል።

## የአቤቶ ኢያሱ ልጆች

አቤቶ ኢያሱ ብዙ ዕቁባቶች በማስቀመጥና ከየጎሣው በመውለድ አንድነትን አመጣለሁ ብሎ የሚያስብ በመሆኑ ብዙ ልጆች በየቦታው ወልዷል እየተባለ ይነገራል። እርግጥ መጀመሪያ ላይ ያሳይ የነበረው ባሕርይ ሥርዓት ያጣ መሆኑን ብዙ ሰው ታዝቧል። በሌላ መልኩ ይህንን ወጣት በርካታ ሰዎች እንዳካለቡት ይታወቃል። አንድ ቦታ ለጉዳይ በሄደ ቁጥር ሁሉም ወጣት ሴቶች ልጆች እያቀረቡ ይህችን አግባ ያችን አግባ እያሉ አስቸግረውታል። ከዚህም ሌላ ያረገዘች ወጣት ሴት ሁሉ የጸነሰኩት ከልጅ ኢያሱ ነው ስለምትል እውነተኛ ልጆቹ የትኞቹ እንደሆኑ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ተፈጥሯል። ይሁንና በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የአቤቶ ኢያሱ ልጆች ከየቦታው ብቅ እያሉ እነሱን በየምክንያቱ ማሰርና መቆጣጠር ራሱን የቻለ ችግር ፈጥሯል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው በመሳሳት የአቤቶ ኢያሱ ልጅነታቸው ተደብቆ የቀሩም ልጆች እንደሚኖሩ ይገመታል። ይሁንና ከዚህ በታች ልጅነታቸው የተደረሰበትን ሰዎች ስምና ታሪካቸውን ለመዘርዘር ተሞክሯል።

## ልጅ ግርማ ኢያሱ

ልጅ ግርማ ኢያሱ በጣሊያን ወረራ ጊዜ በስደት ኬኒያ ይኖር ነበር። በዚያ ቆይታው ወቅት የኬንያ የበላይ አስተዳዳሪ የነበሩት እንግሊዞች ለቁጥጥር ሲሉ በቀን ሁለት ጊዜ በአቅራቢያው ፖሊስ ጣቢያ እንዲፈርም አደረጉት። በዚህም ቁጥጥር ማብዛት የተነሳ በመሰላቸትና

በሰዎች ማበረታታት ምክንያት ባለ.ያኖች ኢትዮጵያ ውስጥ መፍረክረክ ሲጀምሩ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ሲሸሽ እዚያው ኬኒያ ውስጥ ተይዞ እስር ቤት ገባ። መጨረሻ ላይ ታቤት በሚባል እስር ቤት እያለ ታሞ ሆስፒታል ከገባ በኋላ በህክምና ላይ እያለ ሞቷል። ሆኖም ከሞተ በኋላ ሰው መርዝ ተደርጎበት እንደተገደለ ያወራል።

## ሚናስ ኢያሱ (ወልዱ)

ልጅ ሚናስ ኢያሱን ጎጃሜዋ እናቱ ለአንድ ባሕታዊ አደራ ብላ ሰጥታ ወደ ወሎ አብረው ሲጓዙ ዓባይ ሞልቶ ነበርና ሲያቋርጡ እርሷን ውኃ ወስዷት ስትሞት ልጁና መነኩሴው ዳኑ። ሚናስም ወሎ ግሼን ማርያም አጠገብ በምትገኘው ሙፋ ኪዳነ ምሕረት እየተማረ ባህታዊ መስሎ አደገ። ጣሊያን በገባ ጊዜ ዝናውን ሰምቶ ያስረውና ቢመረምረው በጣም ሠላማዊና ዝንባሌው መንፈሳዊ መሆኑን ተረድቶ ፈታውና ቤትም ሰጥቶት አስቀመጠው። ከጠላት ወረራ በኋላ ከወሎዬ እናት የተወለደው ወንድሙ ልጅ ጌዲዮን ኢያሱ ፈረሱን አስጭኖ መሸፈቱ ሲሰማ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ሚናስን ይዘው ለጃንሆይ ላኩትና አልጋ ወራሽ ቤት ተቀማጭ ሆነ። በዚህን ጊዜ ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበና ልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን ይንከባከቡት ነበር።

ጃንሆይ ግን ወደ ወህኒ ቤት እንዲገባና ራስ አንዳርጋቸው መሳይ እንዲከታተሉት አድርገው ነበር። ራስ አንዳርጋቸውም ቢመለከቱት ሠላማዊና ጸሎተኛ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ በኃላፊነታቸው እንዲለቀቅ አደረጉ። ራስ አንዳርጋቸው መሳይ የፍርድ ሚኒስትር ስለነበሩ አሁን ገብረ ማርያም ትምሕርት ቤት የሆነው የፍርድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ውስጥ ሥራ እንዲጀምርና እዚያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ቤት ተሰጥቶት ተቀመጠ። የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤቱ አሁን የመከላከያ ሚኒስቴር ፎቅ ውስጥ ሲዛወር ግሚሱ የጦር ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ሆቴል ፊት ለፊት ያለው ደግሞ የፍርድ ሚኒስቴር ስለሆነ አብሮ ከነቤተሰቡ እዚሁ ግቢ ውስጥ መኖር ጀመረ። ከዚያም ደጃች ሰሎሞን አብርሃ የአባቱን ስም እንዲለውጥ መከሩትና ወልዱ ይሁን በማለቱ ልጅ ሚናስ ወልዱ ተባለ። በመጨረሻ የፍርድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በዋናው ፖስታ ቤት ፊት ለፊት ካሉት ሁለት ሕንጻዎች በአንዱ ውስጥ ሲዛወር፣ እሱም ጎላ ሠፈር ቤት ተከራይቶ እዚሁ መሥሪያ ቤት ሥራውን እየሠራ በመኖር ላይ እያለ



በ1957 ዓ.ም ምሽት ላይ ከሚሠራበት ፎቅ ላይ ወድቆ ሞተ። በዚህን ጊዜ የሶማሌ ሬዲዮ "የአቤቶ ኢያሱን ልጅ ሚናስን የኢትዮጵያ መንግሥት ከፎቅ ወርውሮ ገደለው" ሲል ተናገረ። ሚች ሰባት ልጆች ወልዶ እነሱም ወልደው ከብደው ተበራክተዋል። ሰባት ልጆቹም

1ኛ ጌታቸው ሚናስ — 2ኛ የሺ ሚናስ
3ኛ ልዑል ሰገድ ሚናስ — 4ኛ ብርሃኑ ሚናስ
5ኛ ሸዋዬ ሚናስ — 6ኛ ገነት ሚናስ
7ኛ ኤፍሬም ሚናስ

እንዲሁም የሰባት ልጆቹ እናት ወይዘሮ ፈለቀች ታደሰ ዛሬ በሕይወት ይገኛሉ።

## ጌዲዮን ኢያሱ

ጌዲዮን ኢያሱ የተባለ ከልጅ ኢያሱ የተወለደ ኃይለኛ ልጅ ነበረ። ከጠላት ወረራ በኋላ ብዙ ፈረስ አስጭኖ ለመሸፈት ወሎ ጠቅላይ ግዛት ወስጥ በርሃ ገባ። ከዚያ በኋላ ተይዞ ጋሞ ጎፋ ታስሮ ነበር። ከጌዲዮን ኢያሱ የተወለዱ ልጆች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ እስጢፋኖስ ጌዲዮን
2ኛ በቃሉ ጌዲዮን (የአየር ኃይል ባልደረባ የነበሩ)

## ጎሹ ኢያሱ

ጎሹ ኢያሱ በግዞት ሲዳሞ ይኖር በነበረ ጊዜ የሚከተሉትን ልጆች አፍርቷል። 1ኛ ተናኘ ጎሹ የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው
2ኛ ሉሊት ጎሹ ሲዳሞ ውስጥ ነዋሪ ናቸው።

## መልዓከ ፀሐይ ኢያሱ

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ከአቤቶ ኢያሱ ልጆች መካከል ሁለቱ በአርበኝነት ይታወቃሉ። ከመንዜዋ ባላባት የተወለደው እንግዳሸትን እቴጌ መነን ወደ ስደት ሲሄዱ ለባዕታ ገዳም አለቃ ለነበሩት አባ ይርዳው በአደራ ሰጡት። አባ ይርዳውም ጣሊያን ሲገባ ልጁን ይዘውት ቡልጋ ወስጥ ወደሚገኘው ገደራ አብዬ ገዳም ገቡ። ሻቃ በልሁ በኢጣሊያን ሲገደሉ አጋፋሪያቸው የነበሩት አለቃ ወልደ ጻድቅ ዘውዴ ጦራቸውን ይዘው ቡልጋ ሲገቡ እንግዳእሸትን አዩና የንጉሥ ልጅ እመሃከላችን እያለ እንዴት ዝም እንላለን? እንሹመውና ያስተባብረናል በማለታቸው እምቡር ገበያ ላይ ነጋሪት

እየሙ፣ እንግዳእሽት ኢያሱን መልዓክ ፀሐይ ንጉሠ ነገሥት አሰኝተው አወጁ። ከዚህ በኋላ ከያለበት አርበኛው ሁሉ ተሰበሰበና ሹመት ተካሄደ። በርከት ያለ ጦር አስከትለው የመጡት ባላንባራስ አበበ አረጋይ ስለነበሩ ራስ ተብለው የጦር አበጋዝ ኾነው ተሾሙ። አለቃ ወልደ ጻድቅም ፊታውራሪ ተባሉ። ራስ አበበ የራስ ጎበና ዳጬ የልጅ ልጅ ከመሆናቸው ሌላ ከባሊያን ወረራ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ በሻለቃነት ማዕረግ የአራዳ ዘበኞች አለቃ ነበሩ።

'ቀሪን ገረመው የአርበኞች ታሪክ' የሚለው መጽሐፍ ገጽ 146 ላይ "መልዓክ ፀሐይ ኢያሱ መስከረም 16 ቀንና 17 ቀን 1931 ዓ.ም የደመራንና የመስቀልን በዓል ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት የጥንቱን የኢትዮጵያ ባህል አክብረው ወታደራዊ ሠልፍም ተመለከቱ። ከሠራዊቱም ብዛት የተነሳ ሠልፉ ከስምንት ሰዓት የጀመረ እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ቆይቶ ነበር። የጥንቱንም የወታደር ልምድ ላለማስቀረት ሲባል በተገኘው ግብር ተደርጎ ነበር። በዚሁ ዕለት ልጅ መልዓክ ፀሐይ በድንገት ታመው ለሕመማቸው መፍትሔ ስላልተገኘ በቃሬዛ ወደ ገና መምቻ ወሰዷቸው። መስከረም 27 ቀን ሌሊቱን አረፉና አርበኞቹና መኳንንት በቃሬዛ ወስደው ቆቦ ማርያም በታላቅ ኀዘን በስውር ቀበሯቸው" ሲል ተዘግቧል። ልጅ መልዓክ ፀሐይ በነገሡ በስምንተኛው ወር ተመርዘው ሞቱ። ጥርጣሬው ከጅቡቲ የመጡ መነኩሴ መርዝ አቅምሰዋቸዋል ይባላል። በምን ምክንያት መነኩሴው እንደመረዟቸው ግን አልታወቀም።

## ደጃች ዮሐንስ ኢያሱ

ደጃች ዮሐንስ ኢያሱ በጎንደርና በጐጃም በአርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው ጃንሆይ ሲመለሱ በሥራቸው ያሉትን አርበኞች አሠልፈው እንደሌሎቹ አርበኞች ንጉሡን ተቀበሉ። ጎንደሬዎች ከራስ ጉግሣ ወሌ መገደል በኋላና በአጎታቸው በደጃዝማች አያሌው አለመሾም ምክንያት ቅሬታ ስለነበራቸው ጃንሆይ ከስደት ሲመለሱ የጎንደር አርበኞች "የሸሸ ንጉሥ አይነግሥም፤ ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም" በማለት ንጉሡን እናስገባም ከማለታቸው በተጨማሪ ደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱን የማንገሥ ፍላጎትም አሳይተው ነበር። ጃንሆይ ደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱን ከአምስት ዓመት አርበኝነት በኋላ በእስር ወደ ከፋ ልከዋቸዋል። ደጃዝማች ዮሐንስ በርካታ ልጆች ወልደው በ1966 ዓ.ም ከመንግሥት ለውጥ በኋላ ተፈተው ከወንድማቸው ከልጅ ምኒልክ ኢያሱ ጋር ተገናኝተው



ተወያይተዋል። መጨረሻ ላይ ጅማ ሄደው ታመሙና ሞቱ። ደጃች ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ላይ በነበሩበት ወቅት ደብዳቤ በሚጽፉላቸው ጊዜ አክባሪዎ እያሉ እንጂ እንደሌሎቹ ባሪያዎ ባለማለታቸው ጃንሆይ ቅሬታ ነበረባቸው። ከልጆቻቸው መካከል ጀርመን አገር ነዋሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ግርማ ዮሐንስ በየጊዜው እስተያየታቸውን በተደጋጋሚ ይገልጻሉ።

## ቴዎድሮስ ኢያሱ

ስለ ቴዎድሮስ ኢያሱ ለማወቅ የቻልኩት ጋምቤላ ውስጥ ሸፍቶ ሲዋጋ ኖሮ በኋላ ናዝሬት ውስጥ ታስሮ እንደነበረ ነው።

## ልጅ ምኒልክ ኢያሱ

ምኒልክ ኢያሱ አዳል ውስጥ ተወልደው ፖለቲካ ውስጥ ሳይገቡ ከኢያሱ በመወለዳቸው ብቻ አፍንጮ በር እስር ቤት ከ25 ዓመት በላይ ታስረው በነጻ የተለቀቁ ናቸው። እሳቸውም የኢሳ ተወላጅ የኾኑትን ወይዘሮ መሪማ አብዱርሃማንን አግብተው ድሬዳዋ በሶማሊ መንደር ሲኖሩ ቆይተው ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ። ልጅ ምኒልክ ኢያሱ በጣም ብዙ ሰው የሚቀረቀርላቸው ነበሩ። አንደኛ ልጅ ለመውለድ ያልቻሉበትን ምክንያት ብዙ ሰዎች በተለያየ መልክ ይናገራሉ። ሁለተኛ ደግሞ ያለምንም ጥፋት በመወለድ ብቻ መጉላላታቸውን ማንንም ያሳዝን ነው።



ልጅ ምኒልክ ኢያሱ

ምንም እንኳን ልጅ ምኒልክ ኢያሱ ፖለቲካ ውስጥ መግባት ባይፈልጉም አገራቸውን ለመርዳት በተጠየቁ ቁጥር የተቻላቸውን ለመፈጸም ወደኋላ አላሉም። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ የጅቡቲ ነፃነት ጉዳይ የተፋፋመበት ወቅት ነበረና የጅቡቲም የበላይ ባላባት አልአሪፍ ከልጅ ምኒልክ ጋር የአንድ አያት ልጆች ስለነበሩ ለማግባባት የተቻላቸውን ጥረዋል። አልአሪፍ ጃንሆይን የአክስቴን ባል የገደለ ነው እያለ ይጠላቸው ስለነበረ ለማየትና ለማነጋገር አይፈልግም ነበር። በደርግ ላይ ግን የግል ቂም ስላልነበረው ልጅ ምኒልክ ኢያሱ

ሁኔታቸው የጅቡቲን መሪዎች ለማግባባት ጠቅመዋል።

## ልጅ መስፍን ኢያሱ

የልጅ ኢያሱ ልጅ ነኝ ዋልድባ ገዳም ውስጥ ተደብቄ ነው የኖርኩት የሚሉት ልጅ መስፍን ኢያሱ በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ታዋቂ ሆነው ነበር። ልጅ መስፍን ቀደም ብሎ ስማቸው መኮንን እንዳልካቸው የነበረ ሲሆን በ1983 ዓ.ም በጋዜጣ ስማቸው መስፍን ኢያሱ መባሉን ማስታወቂያ ካወጡ በኋላ በሕዝብ መካከል በይፋ ይጠሩበት ጀመር። ልጅ መስፍን የቤተክህነት ሰው በመሆናቸው ከፓትርያርኩ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እርዳታ ተደርጎላቸው ከብቶች በማርባት ይኖሩ ነበር። በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አዲስ አበባ ውስጥ ክብረ በዓል ሲኖር አባ ምርጥዋ ከሚባሉ ቀልደኛ አዝማሪ ጋር በመሆን ጎራዴያቸውን ይዘው አብረው ይንጎራደዱ ነበር።

ኢሕአዴግ ሲገባ ደርግ ዘግቶት የነበረውንና ወደ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሚወስደውን መንገድ ያስከፈቱና ከማዘጋጃ ቤቱ ፈቃድ ውጭ የአፄ ምኒልክን ሐውልት ብርማ ቀለም ያስቀቡ ናቸው። ይኸ ሐውልት የተሠራው በነሃስ ነው። ስለሆነም መወልወል እንጂ የብር ቀለም መቀባት አልነበረበትም። ቀደም ብሎ ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ ከንቲባ በነበሩበት ወቅት የወርቅ ቀለም መቀባቱ ይታወሳል። በተጨማሪም በእሳት አደጋ በኩል ያለውና በብረት ሠንሰለት የተዘጋውን የአራዳ ጊዮርጊስ ቅጥር ግቢ በር ከባሕታዊ ገብረ መስቀል ጋር በመጋዝ ቆርጠው አስከፍተዋል። በዚህም ተከሰው ነበር።

የልጅ መስፍንን ልጅነት በከፊል ሰዉ አልተቀበለውም። እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱም ተጠይቀው "እኛ አናውቀውም" በማለት መልስ ሰጥተዋል።

## አባ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ

የአቤቶ ኢያሱ ልጅ እንደኾኑ የሚነገርላቸው አባ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ የሚባሉ የካቶሊክ መነኩሴ ሐረርጌ ውስጥ ይኖሩ ነበር። መልከ ቀና ስለሆኑና የልጅ ኢያሱ ልጅ ናቸው ተብሎ ስለሚነገር የአባታቸውን ስም ወልደ ነጎድጓድ አስኝተው ቆዩ። በይበልጥ ሰው ስላስቸገራቸው



መልካቸውን ለማሳሳት ቅንድባቸውን እየላጩ ለመለወጥ ሞክረዋል። በወቅቱ እሳቸው ያስተምሯቸው ከነበሩት ዲያቆኖች መካከል አንዱ የአባታቸውን የልጅ ኢያሱን ፎቶግራፍ አውጥተው እንደ አሳዩዋቸው አጫውተውኛል። አባ ዮሐንስ መነኩሴ ስለነበሩ ልጅ ሳይተኩ ሞቱ።

## ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ

ስለ ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ ታሪክ በጥልቀት የሚያውቅ ሰው ስለታጣ ለማተት አልተቻለም። ይሁንና ትልቋ ሴት ልጅ እሳቸው እንደነበሩና ልጅ ኢያሱም ሞቱ በተባለ ጊዜ ልቅሶ ይደረስ የነበረው እሳቸው ዘንድ ነበረ። እንዲያውም እቴጌ መነን ልቅሶ የደረሱት ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ ዘንድ ነው ይባላል።

## እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱ

የወንዶቹ ልጆቻቸው ሁኔታ እንደተጠቀሰው ሲሆን ከሴት ልጆቻቸውም መካከል በይፋ የሚታወቁት ከራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ከወይዘሮ ስብለ ወንጌል የተወለዱት እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱ የሚባሉ እስከ ቅርብ ጊዜ በሕይወት ነበሩ። ልጃቸውም አቶ ዓለም ሰገድ አበበ ወይም ማሞ በመባል ይታወቃል።



እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱ (በግራ)
እናታቸው እመቤት ሰብለ ወንጌል ኃይሉ (በቀኝ)

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ራስ ተፈሪ ተከራርፈው የሚነጋገሩት በሽማግሌ አማካኝነት ብቻ ኾነ።

በመሠረቱ ደጃዝማች አባውቃው ለንግሥት ተቆርቁረውና የሚደረገውን ደባ ስለደረሱበት ኃላፊነታቸውን በሥርዓት ቢወጡም ጉዳዩ ሁሉ የሥልጣን ሽሚያ ስለነበረ ደጃች አባውቃው በመቃወማቸው የተነሳ ተቀጡ። ግን በወር ውስጥ የተባለው ነገር በገሃድ ወጥቶ ቀኛዝማች ባንትይዋሉና ግራዝማች ይገዙ የሚመሩት ቡድን ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱን "ራስ ተፈሪን ያንግሡልን" ብለው ሲጠይቁ "እስቲ ልዋል ልደርና መክሬ መልሱን እሰጣችኋለሁ" ሲሉ ቢመልሱላቸውም "አይሆንም አሁኑኑ መልሱን ካልሰጡን ብለው ሰቅዘው ያዙዋቸው"። ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ነገሩ ስለገባቸው የነበራቸው ምርጫ መስማማት ብቻ ኾነና እሺ አሉ። ስለሆነም ራስ ተፈሪ ንጉሥ ተፈሪ ተብለው መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም ዘውድ ደፉ።

ከዚህ ሹመት በኋላ ግብር ሁለት ቦታ እየተበላ ሰው እየተከፈለ ንግሥቲቱና አዲሱ ንጉሥ ውስጥ ውስጡን አለመግባባት እየፈጠሩ ከመሄዳቸውም በላይ ቅሬታ ያላቸውን የንግሥቲቱን የበፊት ባልና የጎንደሩን ገዥ ራስ ጉግሣ ወሌን ማስወገድ አስፈላጊ ኾነ። ራስ ጉግሣ ወሌ ወደ አዲስ አበባ ሲጠሩ አኩርፈው ለመምጣት ስላልፈለጉ በነደጃች ሙሉጌታ የሚመራ ጦር ዘምቶባቸው ቋና አንቺም ላይ በውጊያ ላይ እንዳሉ ራሳቸውን በጎራዴ ተመተው ተገደሉ። በዚሁ ጦርነት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር በአይሮፕላን ቦንብ ተጣለ። ደጃች ሙሉጌታ የራስ ጉግሣ ወሌን ጭንቅላት አስቆርጠው በጆኒያ ይዘው መጥተው ለአዲሱ ንጉሡ ነገሥት ግዳይ አቀረቡ። ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱም ከባላቸው ሞት በኋላ በሁለተኛው ቀን መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞቱ ተለዩ። ልጅ ስላልነበራቸው መሬታቸውንና ንብረታቸውን ልዕልት ተናኘ ወርቅ እንዲወርሱ ተደረገ።





# ምዕራፍ ፱

# የተፈሪ ውልደትና ዕድገት

ከሐረር ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ኤጀርሳ ጎሮ፣ ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም ከወይዘሮ የሺ እመቤት የሰባት ወር ልጅ ተወለደ። ወ/ሮ የሺ እመቤት ስድስት ልጅ ወልደው የሞቱባቸው ስለኾነ ቤተዘመድ ሁሉ እሳቸው ልጅ ሊወልዱ ሲሉ ይጨነቃሉ። ሰባተኛው አዲሱ ሕፃን እንደ ተወለደ ቤተዘመድ እናቱ ካዩት ይሞታል ብለው ስላመኑ ግድግዳ ቀደው ከቤት አወጡት። እንዲህ ዓይነት ክስተት በሚፈጠርበት ጊዜ ወላጅ ሾተላይ [11] አለባቸው ተብሎ ይታመናል። ሾተላይ በባህል የሚታመነው ሰው ላይ ሊኖር የሚችል ኃይለኛ የዓይን ጨረር ሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ተደርጎ ነው።

ሕጻኑ በተወለደበት ቀን ከእናቱ መለየት ስለነበረበት፣ ከእናትና አባቱ ቤት ወጥቶ ዘመድ ቤት ማደግ ጀመረ። ወላጅ እናቱም የልጃቸውን ቁመት በገመድ ላይ ምልክት እያስደረጉ በማስመጣት ዕድገቱን በርቀት ይከታተሉና ልብስም እያሰፉ ይልኩለት ነበር። ያለመታደል ሆኖ የሕጻኑ ወላጅ እናት ወይዘሮ የሺ እመቤት ዓሊ እንደገና አርግዘው ስለነበረ ከ20 ወር በኋላ መጋቢት 6 ቀን 1886 ዓ.ም በወሊድ ምክንያት ሞቱ። ስለኾነም ሕጻኑ የእናት ጣዕም ምን እንደኾነ ሳያውቅ የአጎቱ የደጃች ብሩ ኃይለ ማርያም ባለቤት ወይዘሮ ትስሜ አባይርጋ ከእምሩና ከልጃቸው ከደስታ ብሩ ጋር አሳደጉት።

[11] የእናት ወይም የአባት የደም ዓይነት RH Negative ሲሆን የሌላኛው RH Positive ይሆንና የሁለቱ ወላጆች ደም ባለመጣጣሙ የሚከሰት ችግር ነው።

እንዳለውና የልጆቹን መከረር ስላዩ ፊታወራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ "እናንተ ልጆች ተው ይቅርባችሁ" ብለው ውድድሩን አስቁመዋል።

ተፈሪ ዕድሜው ለትምሕርት በደረሰ ጊዜ፣ በሰባት ዓመቱ፣ አባ ወልደ ኪዳን የሚባሉ አስተማሪ እቤት ውስጥ ተቀጥረው ከአብሮ አደጉ እምሩና ማሚት ጋር እስከ አሥር ዓመቱ በጥሩ ሁኔታ አማርኛና ግዕዝ የማንበብና የመጻፍ ትምሕርት አጠናቋል። ልዑል ራስ መኮንን የውጭውን ዓለምና የአገርንም ሁኔታ በደንብ የተመለከቱ ስለነበሩ፣ ልጃቸው ከአማርኛና ከግዕዝ በተጨማሪ የውጭ አገር ትምሕርት እንዲማርላቸው ፈለጉ። በዚህ የተነሳ በሐረር ከተማ ያሠሩት ሆስፒታል ውስጥ ዶክተር ቪታልያ የተባለ ሃኪም በትርፍ ጊዜው በቀን አንድ ሰዓት ፈረንሳይኛ ልጃቸውን እንዲያስተምርላቸው አደረጉ። በተጨማሪም፣ አባ ሳሙኤል ወልደ ካህን የሚባሉ ኢትዮጵያዊ በካቶሊክ ሚስዮን ያደጉና ራሳቸውም የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የነበሩ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ተፈሪን አስተምረዋል።



ተፈሪና አባታቸው ራስ መኮንን

ተፈሪን ገና በ 13 ዓመቱ ራስ መኮንን መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ደጃዝማች ብለው በሐረርጌ ግዛት ውስጥ የጋራ ሙለታ አውራጃ ገዥ አድርገው ጥቅምት 21 ቀን 1898 ዓ.ም ከሾሙት በኋላ፣ "ልጄን ተፈሪን አደራ፣ ለዓይናችሁ እንዳትጠሉት ነው እንጂ ዕድሉ በፈጣሪ እጅ ነው" ብለው በመናገራቸው ሁሉም ሰው አዘነ። ራስ መኮንን በዚያው ዓመት



ለሥራ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ መንገድ ላይ እያሉ በጠና ታመሙና ጉዟቸውን አቋርጠው በመመለስ ቁልቢ ኾነው በህክምና ሲረዱ ቆይተው መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም አረፉ።

አስከሬናቸው ሐረር ጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከባለቤታቸው ከወይዘሮ የሺ እመቤት ዓሊ አስከሬን ጎን አረፈ። ሆኖም



ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ብዙ ሰዎች ራስ መኮንን መሞታቸውንና መቀበራቸውን ቢያምኑም ከፊሉ ሕዝብ ደግሞ መነኑ እንጂ ሞቱ መባሉን አልተቀበለም።

# ምዕራፍ ፲

## ድብቋ ወ/ሮ የሺ. እመቤት

ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ የሚለው መጽሐፍ ላይም ይሁን በማንኛውም አጋጣሚ ልጃቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእናታቸውን ፎተግራፍ አሳይተውም ኾነ የአባት ስም ተናግረው አያውቁም። ታሪክ ጸሐፊዎችም፣ በመፍራት ሊሆን ይችላል፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የአባት ወላጆች ሲዘረዝሩ የእናታቸውን አባት ስም ግን አይጠቅሱም። የሚገርመው ደግሞ፣ ከልጅየው ህልፈተ ሕይወትም በኋላ የእናታቸውን አባት ስም በጽሑፍ ወይም በይፋ ለመጥቀስ ብዙዎቹ እስከ አሁን አልደፈሩም። ስለኾነም በምንም ይፋ ነገር ላይ የወይዘሮ የሺ. እመቤት ምስል ለሕዝብ አልተናኘም።

ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ወይም ወይዘሮ ቂቶ የወይዘሮ የሺ. እመቤት እናት ቁመታቸው አጭር ሲሆን ብስል ቀይና በጣም ውብ የሆኑ ሴት ነበሩ። ትውልዳቸውም የስልጤ ጉራጌ ናቸው ይባላል። ‘ከአንዲት ጉራጌ ሴት የሚወለድ ልጅ ትልቅ ንጉሥ ይሆናል’ የሚል ትንቢት ስለነበረ የሸዋ መኳንንት ሁሉ የጉራጌ ሚስት እየፈለገ ያገባ ነበር። በተለይ የወለኔ ሴቶች ቆንጆዎች ስለነበሩ ብዙ መኳንንቶች ተረባርበውባቸዋል። ወለኔ ወሊሶ ከተማ አጠገብ ያለ አገር ሲሆን ነዋሪዎቹ ጉራጌዎች መልካቸው ቀያይና ቆንጆዎች ስለሆኑ ይመረጡ ነበር። የመኳንንቶቹ አማራ ሚስቶች በቅናት ጉራጌዎቹን ሴቶች “ምርኮኞች” ይሏቸው ነበር። ራስ ዳርጌ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን በይፋ ሚስትነት ሳይሆን በዕቁባትነት አስቀመጠው ሦስት ልጆች ወልደዋል። ይሁንና ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ሌሎች ልጆችም ከተለያዩ ሰዎች ወልደዋል።



ራስ ዳርጌ በምርኮ ጎንደር ሄደው በእስር ብዙ ዓመት ከቆዩ በኋላ ተለቀው ሸዋ ላይ ለመሾም በደጅ ጥናት ላይ እንዳሉ አንዱ ወንድማቸው አቤቶ ሠይፉ ሣህለ ሥላሴ ከእስር ቤት አመለጡ። እርሳቸውም ከዚሁ ሁኔታ ጋር በተያያዘ መልኩ ስለተጠረጠሩ መቅደላ ላይ ታስረው ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ላይ ራስ ዳርጌን ለመሾም አስበው አንድ ቀን አስጠርተዋቸው “ልፈታህ ነበረ፣ ግን ፈራሁህ!” አሏቸው ይባላል። አፄ ቴዎድሮስ የሸዋ እስረኞችን ብቸኝነት ተመልክተው አዘኑና ሚስቶቻቸው እንዲጠይቋቸው ስለፈቀዱ ራስ ዳርጌ ወለተ ጊዮርጊስ ትምጣልኝ አሉ።



ድብቋ ወ/ሮ የሺ.እመቤት

ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ራስ ዳርጌን ለመጠየቅ ወደ መቅደላ ለመሄድ በወረኢሉ በኩል ሲጓዙ በእንግድነት ዘመድ ቤት ያርፋሉ። በዚህ መሃል ደጃዝማች ዓሊ ጋምሬ የሚባል የወረኢሉ ተወላጅ የነድድና የካቤ ወረዳ ባላባት የሙስሊም ሃይማኖት ተከታይ የኾነና በጠገራ ብሩ ብዛት እጅግ የታወቀ ሃብታም የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን ቁንጅና በመመልከት እንደሚስት ያስቀምጣቸዋል። እሳቸውም የሺ.እመቤትንና ልክምየለሽን ከዓሊ ጋምሬ ወለዱ። ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ካስቀመጣቸው ዓሊ ጋምሬ ኮብልለው ወደ ሸዋ ተመለሱና ሸዋን



ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ (ቂቶ)

የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ የሕይወት መጨረሻ ደግሞ ራሱን የቻለ ታሪክ አለው። ታሪኩ "የአፄ ምኒልክ የቀድሞ ባለቤታቸው ወይዘሮ ባፌና እሳቸውን ትተው ሌላ ስላገቡ አፄ ምኒልክን በመርዝ ለማስገደል ፈልገው በቤተ መንግሥት ወጣ ገባ የሚልና የሚታመን ሰው ሲፈልጉ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን ያገኛሉ። ወይዘሮ ባፌና ኃይለኛና የሚፈሩ ሴት ስለነበሩ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን "ይኸንን መርዝ ምግብ ውስጥ ጨምረሽ ለአጼ ምኒልክ እንድታቀርቢ በማለት አግባቡዋቸው። በዚሁ መሠረት ምግብ ሠርተው ሊያበሉ ሲሉ ለአፄ ምኒልክ ሰው አስቀድሞ ሹክ ብሏቸው ነበርና የቀረበውን ምግብ ለውሻ ቢሰጡት ውሻው ወዲያው ሞተ። ስለኾነም ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ተይዘው ፍርድ ላይ ቀርበው በችሎት ስለተበየነባቸው ባሶ ገቢያ ላይ በስቅላት ተቀጡ። የልጅ ልጃቸው ተፈሪም አፄ ምኒልክን የሚጠሉበት ምክንያት ከዚህ ሁኔታ ተነስተው ይመስላል ብለው የሚናገሩ አሉ። ከተወላጅ ያገኘሁት ማረጋገጫ ግን በመርዝ መገደላቸውን ሲሆን ምክንያቱ ግን አልተብራራልኝም።



የተፈሪ እናት ወይዘሮ የሺ. እመቤት በአንድ ወገን ከጉራጌና አማራ የተወለዱ ሲሆኑ በሌላ ወገን ከወረይሉ ተወላጅ ከደጃዝማች ዓሊ ጋምቤ እንደኾነ ቢነገርም ጃንሆይ ግን ስለ እናታቸው አባት ዝምታን መርጠው የወላጅ እናታቸውን ታሪክ እንዲታወቅ አላደረጉም። ዓሊ የምትለውን ስም ጃንሆይ ለመጥቀስ ያልደፈሩበት ምክንያት ልጅ ኢያሱን የወነጀሉበት ጉዳይ ራሳቸውንም እንዳይመለከታቸው በመፍራት ይኾናል። እንዲያውም ጃንሆይን ይኸ ሁኔታ ከልጅ ኢያሱ በላይ የከበባቸው ይመስላል። ይኸውም የሴት አያታቸው አባት ስም ሁሴን፣ የእናታቸው አባት ስም ዓሊ፣ የባለቤታቸው አያት ስም ዓሊ ሲሆን እንዲሁም በአባታቸው እናትም በኩል ወይዘሮ ይመኙሻል ቡንኝ የአፋር ተወላጅ በመኾናቸው ነው።

ተፈሪ መኰንን ገጽታቸው እናታቸውን ይመስላል የሚሉ ሰዎች ነበሩ። ከማሊያን ወረራ በኋላ ጃንሆይ የእናታቸውን ፎቶግራፍ ከየዘመዶቻቸው ያፈላልጉ እንደነበረና ለሚያቀርብላቸውም ሰው የገንዘብ ወሮታ ለማድረግ ሞክረው ነበር ይባላል። የወይዘሮ የሺ. እመቤት ፎቶግራፍ ይኑር አይኑር በእርግጠኛነት ባይታቅም የተወሰኑ ሰዎች እጅ እንደሚገኝ አንዳንድ ፍንጭ ተሰመቶ ቢጠየቁም ሰዎቹ ግን ፎቶግራፉን ለማሳየትም ኾነ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ፈቃደኛ አልሆኑም።



# ምዕራፍ ፲፩

# ተፈሪ በደጃዝማችነት

ተፈሪን በ13 ዓመት ዕድሜያቸው አባታቸው ራስ መኮንን ደጃዝማች ብለው ሐረርጌ ውስጥ የጋራ ሙለታ አውራጃ ገዥ አድርገው ሾሙዋቸው። አገሩን ፊታውራሪ ቆለጭ ተመድበው ሲያስተዳድሩት ተፈሪ ግን የደጃዝማችነት ማዕረግን ይዘው ሹመቱን እየተለማመዱ እንዲቆዩ ኾነ። ወዲያውም ራስ መኮንን ስላረፉ አፄ ምኒልክ የራስ መኮንን አርባ የሚወጣው አዲስ አበባ እኔ ዘንድ ስለኾነ ልጁን ተፈሪን ይዛችሁ በቶሎ እንድትመጡ ብለው አዘዙ። ተፈሪም ራስ መኮንን ለአፄ ምኒልክ ያስቀመጡትን ስጦታ ይዘው ከነሠራዊታቸው አዲስ አበባ ደርሰው የአርባ ቀን መታሰቢያው ሚያዝያ 22 ቀን 1898 ዓ.ም በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተዘከረ።



ደጃዝማች ይልማ መኮንን

ተፈሪ የአባታቸውን ግዛት ሐረርጌን ለመሾም ሲጠባበቁ፣ አፄ ምኒልክ በእቴጌ ጣይቱ ግፊት የራስ መኮንን ትልቁ ልጅ ደጃዝማች ይልማን ሐረርጌ ላይ ሾሙና ሰላሌን ደግሞ ለትንሹ ልጅ ለደጃዝማች ተፈሪ ሰጥቻለሁ ብለው አወጁ። ተፈሪ በልጅነት ዕድሜያቸው የሰላሌ አገረ ገዥ ኾነው በነበሩበት ጊዜ፣ አገሩን በእንደራሴ እያስተዳደሩ አዲስ አበባ ደጅ እየጠኑ፣ በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት መማር እንደሚፈልጉ አፄ ምኒልክን አስፈቅደው፣ ትምሕርት ጀመሩ። ነገር ግን፣ ተማሪዎቹ ገና ጀማሪ ስለነበሩና ቀደም ብለው ተፈሪ የተማሩትን ሌሎቹ ያልደረሱበት



ስለኾነ ለብቻቸው እየተማሩ ቆዩ። የደጃች ተፈሪ ትልቅ ወንድም ደጃዝማች ይልማ ሐረር ላይ በተሾሙ በዓመት ከአምስት ወራቸው ሞቱ። ከወንድማቸው ከደጃዝማች ይልማ ሞት በኋላ ሐረርን ደጃች ተፈሪ ይሾማሉ ተብሎ ሲጠበቅ ሹመቱ ለደጃዝማች ባልቻ ተሰጠ። ደጃች ተፈሪም እንደገና ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛትን ተሾመው ሄዱ።

በዘመኑ አንድ አገረ ገዥ ከግዛቱ የሚያገኘው ጥቅም ሁሉ በፊናው ለንጉሠ ነገሥቱ ከሚገብረው ሌላ የራሱ ጥቅም ስለኾነ ከአንዱ ግዛት ሌላው ስለሚሻል እንደ ሐረርጌ ያሉ ግዛቶች በጣም ይመረጣሉ። በተለይ ሐረርጌ የውጭ ዕቃዎች በጅቡቲ በኩል የሚገቡበት በር ስለነበረ ጥቅሙ ቀላል ስላልኾነ ሐረርጌን መሾም ማለት መታደል ነበር።



ደጃች ተፈሪ መኮንን በለጋ ዕድሜ

ተፈሪ ሲዳሞ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ እዚያው እንዳሉ አፄ ምኒልክ መታመማቸውን ሲሰሙ ወደ አዲስ አበባ አስፈቅደው መጡ። አዲስ አበባ ሲመጡም ቤተ መንግሥት ውስጥ የሥልጣን ውዝግብ ስለነበረ ደጃች ተፈሪ ድምጻቸውን አጥፍተው ተቀመጡ። እቴጌ ጣይቱ በሚኒስትሮቹና በመኳንንቶቹ ውዝግብ ውስጥ ደጃች ተፈሪ አልገቡም ብለው በማመን ሐረርጌን ሾመዋቸው ወደ አዲሱ ግዛታቸው በደስታ ሄደው ያስተዳድሩ ጀመር።

አንድ ወቅት የሐረርጌ ገዥ ኾነው ሲኖሩ የሚስታቸው የወይዘሮ መነን አጎት ደጅአዝማች ኃይለ ማርያም ሚካኤል ሞተው ስለነበር ወይዘሮ መነን ለልቅሶ ወደ አዲስ አበባ ተሸኙ። ደጃች ተፈሪ እቴጌ መነንን ሸኝተው ሲመለሱ ዓለማያ ሃይቁ ዳር እረፍት ተድርጎ በጀልባ ከሌሎች መኳንንቶች ጋር ለሽርሽር

ሃይቁን አቋርጠው ሲመለሱ ሃይቁ መካከል ጀልባው መስመጥ ጀመረ። ተሳፋሪዎቹ በባርኔጣቸውና በተገኘው ነገር ሁሉ ውኃውን እየጨለፉ ወደ ውጭ ቢረጩም የሚገባው ውኃ እየበዛ ሲሄድ ጀልባዋ እየሰመጠች ሄደች። በዚሁ አደጋ ሰባት ሰው ሲሞት ተፈሪና ሌሎች ሁለት ሰዎች በዋናተኞች ዕርዳታ ሕይወታቸው ሊተርፍ ችሏል። ደጃዝማች ተፈሪን በተለይ ዋኝተው ያዳኗቸው የፈረንሳይኛ አስተማሪያቸው የነበሩት አባ ሳሙኤል ሲሆኑ እሳቸውን ካወጡ በኋላ ሌላ ሰው ለማውጣት ሲታገሉ ስለደከሙ ሰምጠው ሞተዋል።



ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን

አንዳንድ ሰዎች ይኸንን አደጋ ደጃች ተፈሪን ለማጥፋት የተደረገ የልጅ ኢያሱ ተንኮል አድርገው ቆጥረውታል። እነሱም ሊመለሱ ሲሉ ተሳፋሪዎቹ ሳያውቁት ሆን ተብሎ ጀልባው ከሥሩ ተቆርቁሮ ውኃ እንዲያስገባ ተደርጎ ስለነበረ ሃይቁ መካከል ሲደርሱ እየሰመጠ ስለሄደ ዋና የማይችሉት ሰመጡና ሞቱ። ሆኖም አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች "ጀልባው አሮጌ ስለነበረ ነው" ብለው ያትታሉ። ሌሎች ደግሞ ጀልባው ላይ የተሳፋሪ መብዛት ያመጣው አደጋ ነውም ይላሉ።

ልጅ ኢያሱ የመንግሥቱን ሥልጣን ከተረከቡ ከአምስት ዓመት በኋላ ደጃች ተፈሪ ሐረርን በማስተዳደር ላይ እያሉ ወደ አዲስ አበባ ጠርተው ራሳቸው ልጅ ኢያሱ ድንገት ተነስተው በባቡር ወደ ሐረር ሄዱ። ሐረር ላይም ኾነው ተፈሪን ከሐረር ገዥነታቸው አንስተው ከፋ ላይ ሾሙዋቸው። በዚህን ጊዜ ደጃች ተፈሪና ልጅ ኢያሱ በቃለ መሃላ ሲተሳሰሩ ልጅ ኢያሱ ተፈሪን ከአባታቸው ግዛት ሐረርጌ እንዳይሽሯቸው ደጃች ተፈሪም የልጅ ኢያሱን ሥልጣን እንዳይቀናቀኑ የተስማሙትን ልጅ



ኢያሱ ሻረ። ደጃች ተፈሪም ስምምነቱ መሻሩን ተገንዝበው በራሳቸው በኩል ማድረግ ያለባቸውን ለመፈጸም ውስጥ ውስጡን መዘጋጀት ጀመሩ። ደጃች ተፈሪን ወደ አዲሱ ሹመት አገራቸው እንዲሄዱ ልጅ ኢያሱ ቢወተውትም ተፈሪ ከአዲስ አበባ ሳይነቃነቁ ልጅ ኢያሱ ተሻሩና ደጃች ተፈሪ ራስ ተብለው አልጋ ወራሽ ሆኑ።

መሳፍንቶችና መኳንንቶች ልጅ ኢያሱን ከመንግሥት ሥልጣን አውርደው ተፈሪን ለመሾም ሲዘጋጁ ደጃች ተፈሪ ደግሞ ጧት ጧት በየመኳንንቱ ቤት ደጅ እየጠኑ ውስጥ ውስጡን ይገፋፉ ነበር። ከፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ጋር እንዲያማልዷቸው ነጋድራስ ተሰማ እሸቴን ደጅ በሚጠኑበት ጊዜ ተኝቷል እያሰኙ አጉላልተዋቸዋል። ምክንያቱም ነጋድራስ ተሰማ የልጅ ኢያሱ ወግት ምሁር አማካሪ ከመኾናቸውም በላይ ልጅ ኢያሱን በጣም የሚወዱ ሰው ስለነበሩ ነው።

የውጭ አገር ለጋሲዮኖች በቀጥታ በአንድ አገር ውስጥ ጉዳይ ላይ አይገቡ እንጂ ልጅ ኢያሱ ተሽሮ ተፈሪ እንዲሾሙ የበኩላቸውን ማግባባት በምስጢር አድርገዋል። ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት ልጅ ኢያሱ በሶማሌና በአፋር ያሉትን ባላባቶች የአገር ፍቅር ከፍ እንዲልና በዚያውም ጦር እንዲያዘጋጁ ሲያሰናዷቸው ሌሎቹንም ደጃዝማቾች ቅኝ ገዥዎችን ለማባረር ጦር እንዲያዘጋጁ በማዘዙ በጉዳዩ ሌጋሲዮኖቹ ተጨንቀውበት ስለነበረ ነው። ስለኾነም ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን አውርደው ተፈሪን ያሾሙዋቸው በተባባሪነት የውጭ አገር በተለይ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ለጋሲዮን ሚኒስትሮች ጭምር ነበሩ።

ባሽከሮቹ ክፉት ደግሞ ባጋፋሪ
ዘውዱ ቷዞር ዓየን ወደ ልጅ ተፈሪ

ሼህ ሁሴን ጅብሪል

በአንድ ትዳር ውስጥ ብዙውን ጊዜ ሁለት ኃይለኛ ሊኖር ስለማይችል ወንዱ በጣም ኃይለኛ ሲሆን ሴቲቱ ዝምተኛ፣ በተቃራኒው ደግሞ ሴቲቱ በጣም ኃይለኛ ስትሆን ወንዱ ለስላሳ፣ ካልሆኑ አብሮ መኖር ያስቸግራል። አንዳንዴ ሁለቱ ጾታዎች በአንድ ትዳር ውስጥ እኩል ተሳትፎ ያላቸው እንደነበሩ ይታወቃል። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ናቸው። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያወሳቸው ኃይለኛና ዘዴኞች እቴጌዎች ነበሩ። እነዚህም እቴጌ እሌኒ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ባለቤት፣ እቴጌ ምንትዋብና እቴጌ ጣይቱ ነበሩ።



እቴጌ መነን አስፋው

እቴጌ መነን በማይጨው ጦርነት ጣሊያን ኢትዮጵያን ወርሮ ሲሰደዱ ለእንጦጦ ራጉኤል ስዕለት ገብተው ነበር። ስዕለታቸውም ለቅዱስ ራጉኤል "ከአገራችን ጣሊያን ተባርሮ ባንዲራችን እንደገና ከተመለሰች ቤተ ክርስቲያንህን አሠራለሁ" የሚል ነበር። በዚህም የተነሳ ከስደት መልስ የእንጦጦ ራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደስ ሲነሱ ጃንሆይ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ብታሠሪለት ይሻላል ብለው አዲስ አበባ ውስጥ አዲስ ከተማ አንዋር መስጊድ አጠገብ የፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ መኖሪያ ቤት ጎን የሚገኘውን ቦታ ሰጧቸው። በዚህ የተነሳ የራጉኤል ቤተ ክርስቲያንን አሠርተው ታቦቱን ከእንጦጦ አስመጥተው አስገቡት። በፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ዳግማዊ ምኒልክ ከአሠሩት ቤተ ክርስቲያን መወሰዱን የሚጠሉ ሰዎች አቡኑን ሌላ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ተክቶ የምኒልክን ታቦት ወደ ነበረበት እንጦጦ እንዲመለስ አስፈቀዱ። በዘመኑ ደርግ የሃይማኖትን ነገር ይጫን ስለነበረ በአካባቢ ያሉ ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች በሃይማኖት በኩል አንድ ዓይነት አቋም ስለነበራቸው ታቦቱን እንደማያስነኩ ይታወቅ ነበር። ስለሆነም ጥቂት ቀሳውስት ሌሊት ታቦቱን በሌላ ተክተው ሊወስዱ ሲሉ ደወል ተደወለና ሕዝብ ተሰብስቦ አለመግባባት ተፈጠረ። በዚህም ጊዜ አንድ ቄስ ሲገደሉ ሌሎችም ቆስለው ታቦቱ እዚያው እንዳለ ቀረ። የእንጦጦ ራጉኤል



እምዬ ምኒልክ ያሠሩት ስለነበረ የቤተ ክርስቲያኑ መታደስ ቅርሰነት ሊኖረው ሲገባ በአሁኑ ወቅት የራጉኤል ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ቀርቶ የእንጦጦ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን በመባል ይታወቃል።

ለኢትዮጵያ ሴቶች ምሳሌ ለመሆን እቴጌ መነን የተለያዩ የአገር ልብሶችን በየጊዜው ይለብሱ ነበር። ዙሪያ ጥበብ ለመጀመሪያ ጊዜ የለበሱ እቴጌ መነን ነበሩ። ለዚህ አድራጎታቸው የአገር ፍቅር አርቲስቶች ዘፈን ዘፍነውላቸዋል።

ፈትላለች መነን ፈትላለች መነን
የጥበብ ኩታ ልታላብሰን" የሚል ነበር።

እቴጌ መነን ብዙ መሬት ያላቸው ባለጸጋ ሲሆኑ ጠባያቸው ጨዋና እርጋታ ያላቸው ምንም ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ያልገቡ ቁጥብ ልዕልት ነበሩ። ባለቤታቸውን ምንም እንኳን በአንድ ዓመት ቢበልጧቸውም እርስዎ ብለው ነበር የሚጠሯቸው። ከሰውም ጋር ሲያወሩ ጌቶቹ! ብለው ነበር የሚያነሱዋቸው። ትንሽም ገንዘብ ውጭ አገር ስለነበራቸው የልጅ ልጆቻቸው በስደት ላይ በነበሩበት ወቅት ለችግራቸው ደረሶላቸዋል ይባላል።

እቴጌ መነን ትምሕርታቸው ከአማርኛ ማንበብና መጻፍ የዘለለ መሆኑ አይታወቅም። ንጉሠ ነገሥቱ ከ1916 ዓ.ም አንስቶ እስከ 1954 ዓ.ም ድረስ የውጭ ጉብኝት ሲያደርጉ እቴጌይቱ ግን እሥራኤልንና ግብጽን ከመጎብኘት በስተቀር ወደ ሌላ አገር አብረው አልሄዱም። ጋብቻው ለ51 ዓመት ጸንቶ ስድስት ልጆች ወልደው በ1954 ዓ.ም እቴጌ መነን በ71 ዓመት ዕድሜ በሞት ሲለዩ ከስድስቱ ልጆቻቸው መካከል በሕይወት የነበሩት ልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰንና ልዑል ሣህለ ሥላሴ ብቻ ነበሩ። ሆኖም ልዑል ሣህለ ሥላሴ ከሁለት ወር በኋላ በህመም ምክንያት አርፈዋል። ከእቴጌ ሞት በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀረውን ዕድሜያቸውን በብቸኝነት ጨርሰውታል።



# ምዕራፍ ፲፫

# ራስ ተፈሪ በአልጋ ወራሽነት

የራስ ተፈሪ አልጋ ወራሽነት ከንግሥተ ነገሥት ዘወዲቱ ንግሥና ጋር አብሮ የተፈጸመ ስለነበረ ምንም በልጅ ኢያሱ መሻር ምክንያት ቅሬታና ጦርነት ቢኖርም በደጋፊና በኃይል ሚዛን ተሳክቷል። ሆኖም ሹመቱን የመንግሥት ግልበጣ አድርገው የሚያዩትና የልጅ ኢያሱ መሻር የሚቆጠቁጣቸውና ጉዳትም የደረሰባቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ። አልጋ ወራሽነትም ቢሆን ከመኳንንቶቹ መካከል ለአልጋው የሚቀርቡትና ልዑል እንኳን ሳይባሉ የቀሩት የንጉሥ ሚካኤል ሥላሴ በወንድ ልጅነት ቀጥታ መስመር ላይ የነበሩት እነ ልጅ ታዬ ጉልላቴና ደጃዝማች ማሞ ሥዩም በሕይወት ነበሩ። በተጨማሪም ሌሎች የልጅ ልጆችም በብዛት እንዳሉ ይታወቅ ነበር።

በራስ ተፈሪና በንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ሹመት ላይ ከመኳንንቶቹ መካከል ግምባር ቀደሙና የመንግሥት ግልበጣውን የመሩት ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ነበሩ። ከዚህም ሌላ ደጃች ተፈሪ የፈረንሳይኛ ቋንቋ በማወቃቸው ከውጭ አገር ዲፕሎማቶች ጋር መግባባት ፈጥረው ስለነበረ ውስጥ ውስጡን ብዙ ድጋፍ አግኝተውበታል።

መጨረሻ ላይ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ደጃች ተፈሪን ካደላደሉ በኋላ እያደር አንዳንድ ሰዎች ላይ የሚፈጸመውን ድርጊት ስላልወደዱት ደስተኛ አልነበሩም። ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ አንድ ቀን ሊጋባ በየነ እንዲገረፍ መበየኑን ሰምተው ፈረሳቸውን አስጭነው ቢሄዱ ሊጋባ በየነ ተገርፈው ደረሱ። የዚህን ጊዜ "ወይ ጉድ ቁጭ ብለን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ አቃተን" ብለው ተረቱ።





ራስ ተፈሪ መኮንን

ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ብልህና ዘዴኛ በመሆናቸው አባ መላ በሚል ቅጽል ስም ይታወቃሉ። ዕድሜያቸው ገፍቶ በ1919 ዓ.ም ሲሞቱ የሳቸውን 15,000 ጦር ራስ ተፈሪ ተረክበው ኃይላቸውን አጠናከሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ አከራካሪ ሆኖ የቆየው "ራስ ተፈሪ ዕውነት በአዋጅ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተብለው ተሹመዋል ወይስ በጉልበት ነው ሥልጣኑን የወረሱት?" የሚለው ጉዳይ ነው። የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ "ሰነድ መርምረን ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መባላቸውን ልናገኝ አልቻልንም" ብለዋል። ነገሩን እንዲህ ሲመለከቱት በአገር አስተዳደር ልምድ የሌላትን ንግሥተ ነገሥት ብለው ሲሾሙ ልምድና ትምህርት ያለውን አልጋ ወራሽ ብሎ መሾም በውስጠ ታዋቂነት ባለሙሉ ሥልጣን እንደማለት ይቆጠራል ቢባል ያወዛግባል። ሆኖም የነበረው ችግር ሹመቱ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ሰዎች ቀደም ሲልም የልጅ ኢያሱን መሻር እንዲሁም አዲሱን ሹመት አለመቀበልና ንግሥቲቷ እያሉ ከአልጋወራሹ ትዕዛዝ መቀበል ያልተለመደ አሠራር መሆኑም ጭምር

ነበር። በዚህም የተነሳ ጥቂት መኳንንቶች ሹመቱን ባለመቀበል የተገረፉና የታሰሩ ነበሩ።

ራስ ተፈሪ አስተዋይ ስለነበሩ ችግር እንዳይፈጠር አንዳንድ ትልቅ ጉዳይ ሲኖር ንግሥቲቱን አስፈቅደውና አስረድተው ሥራቸውን ይሠሩ ነበር። ይሁንና አንዳንድ መኳንንቶች ንግሥቲቱን እየመከሩና ልባቸውን እያሸፈቱ በአንዳንድ ሃሳብ ላይ ችግር እየተፈጠረ ራስ ተፈሪ የማስረዳትና የማሳመን ተጨማሪ ሥራ ነበረባቸው።

በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ የልጅ ኢያሱን መሻር አልቀበልም ብለው የተቃወሟቸው የንጉሥ ሚካኤል ጦር መስበቅ በሸዋ ሲሰማ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ በፍጥነት እቴጌ ጣይቱን ለማማከር ወደ እንጦጦ ሄዱ። እቴጌ ጣይቱም ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስን ሲመክሩ "ሚካኤል ችኩል ነው፣ እዚህ ይመጣል፣ ጠብቁት፣ ወታደሩን መንገድ አታስመቱት" ብለው መከሯቸውና እንደተባሉት አደረጉ። በራስ ልዑል ሰገድ የሚመራ ቀዳሚ ጦር ንጉሥ ሚካኤልን ለመከላከል ተልኮ በወሎ ጦር ተደመሰሰ። በመሃሉ ሙሉ ዝግጅት ተደርጎ ሲጠበቁ ንጉሥ ሚካኤል እንደተባለው ወደ ሸዋ ስለገፉ ሰገሌ ላይ በፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ዘዴኛነት ተሸንፈው አንኮበር እስር ላይ እንዳሉ በዓመቱ አረፉ።

ይሁንና ብዙ ወጣት ምሁሮች የልጅ ኢያሱን መሻር ባለመቀበላቸው የተገረፉም፣ ወደ ዳር የተገፉም ነበሩ ከመኳንንቶችም መካከል ያኮረፉ ቢኖሩም ምንም ለማድረግ አልተቻለም። ቀጥሎም ልጅ ኢያሱን ፈልጎ ማሰር፣ የልጅ ኢያሱን ባለሟሎች ቅስም መስበርና ከሥልጣን ማባረር ሲሆን በእነሱም ምትክ አዳዲስ ሰዎች መተካት ቀዳሚ ሥራቸው ነበር።

አቤቶ ኢያሱን ከሹመት አውርዶ ወይዘሮ ዘውዲቱንና ደጃዝማች ተፈሪን ለማሾም በተደረገው ሽኩቻ ለመኳንንቶቹ መሣሪያ ኾነው የነበሩት መሃል ሰፋሪ ወይም የመንግሥት ጦር በ1910 ዓ.ም ሌላ አድማ መቱ። ይኸውም በ1889 ዓ.ም በአፄ ምኒልክ የተሰየሙትንና በአቤቶ ኢያሱ ጊዜ በተጨማሪ የተሾሙትን ወይም የተዛወሩትን ሚኒስትሮች ከጦር ሚኒስትሩ ከፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ በስተቀር ወንጅለው ይሻሩልን አሉ። ራስ ተፈሪ ይህንን ጌራ ቢጠሉትም በፊት የተሠራውን ሥራ ስለሚያውቁ ሚኒስትሮቹን ሻሩና ለጥቂት ጊዜ ሹሞች መድበው ራሳቸውም በሥራ ተጠመዱ።



በመጨረሻ ሕግና ደንብ አውጥተው ለእያንዳንዱም ሚኒስትር ቢሮና አማካሪ አድርገው አዳዲስ ሚኒስትሮች ሾሙ። ዳኞች እንደፈለጉ መፍረዳቸው ቀርቶ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በማውጣትና ፍርድ ቤት በማቋቋም በደንቡ መሠረት ሥራው ሁሉ እንዲሠራ አደረጉ። አስከትሎም የባሪያን ንግድ የሚከለክል ሕግ ከማወጃቸው በተጨማሪ ነፃ የወጡ የባሮች ልጆች በወታደርነት ትምሕርት ቤት እንዲገቡ ተደረገ። አገሪቱ ሕገ መንግሥት ስላልነበራት ይኸው እንዲረቀቅ ተደርጎ በ1922 ዓ.ም እንዲጸድቅ ኾነ።



ማተሚያ መኪና ( በሰው ጉልበት የሚሠራ )

በምባኔ ሃብት በኩል ምንም እንኳን የሕትመት ሥራ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ቢጀመርም ራስ ተፈሪ አዲስ የማተሚያ መኪናዎች ከጀርመን አገር አስመጥተው በግዕዝና በአማርኛ መጽሐፍት ማሳተም ጀመሩ። በተከታታይም ጋዜጦች ታተሙ። በዘመኑ የማተሚያው መሣሪያ በኤሌክትሪክ ሳይሆን በሰው ጉልበት ይንቀሳቀስ ነበር። ይህ ማተሚያ ቤት ጣሊያንን ለማስወጣት እናግዛለን ብለው የመጡት እንግሊዞች አወላልቀው ሊወስዱት ሲሉ አርበኞች ራስ መኮንን ድልድይ ሥር አድፍጠው በኃይል ከመወሰድ አድነውታል። ማተሚያ ቤቱም የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት በመባል እስከ አሁን ያገለግላል። በ1916 ዓ.ም

ራስ ተፈሪ በአልጋ ወራሽነታቸው አውሮፓን በጎበኙበት ወቅት የሕትመት ሥራ በማስፋፋታቸው የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ዕውቅና ሰጥቶ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አበርክቶላቸዋል።



ራስ ተፈሪና ቤኒቶ ሙሶሊኒ

በዲፕሎማሲው በኩል በ1916 ዓ.ም አውሮፓን ለመጎብኘት ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ራስ ሥዩምና ሌሎች ችግር ይፈጥራሉ ብለው የሚጠራጥሩዋቸውን መሳፍንቶችና መኳንንቶች በማስከተል በጅቡቲ በኩል ወደ አውሮፓ ተጉዘዋል። የጎበኙዋቸውም አገሮች ግብጽ፣ ኢየሩሣሌም፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ስዊዘርላንድ፣ እንግሊዝ፣ ግሪክ፣ ቤልጅየምና ስዊድን ሲሆን ጀርመንን ግን ለመጎብኘት ቢፈልጉም የመመለሻቸው ጊዜ በመድረሱ ሳይጎበኙ ቀርተዋል። አንዱ የሄዱበት



ምክንያት ለኢትዮጵያ የባሕር በር ለመጠየቅ ነበር። ጥያቄያቸው ግን ጥሩ ምላሽ አላገኘም። ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በተደረገው ጦርነት በምርኮ የተወሰዱትን ቅርሳ ቅርሶች እንዲመልሱላቸው ጠይቀው ነበር። ሊመልሱ ሲሉ በስንብት ጊዜ የእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ 6ኛ የአፄ ቴዎድሮስን ትልቁን ዘውድ ለመመለስ የእንግሊዝ መንግሥት ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸላቸው። በተረፈ አንዳንድ የጽሕፈት ማተሚያ መኪና፣ ኦቶሞቢሎች፣ የውኃ ቧንቧዎች፣ አይሮፕላንና መጽሐፎች እንዲላክላቸው ግዥውን ፈጽመው ተመልሰዋል።

የባላባት አገሮች ደግሞ ጎጃም፣ አፋር፣ ሱማሌ፣ ወሎ፣ ሊሙ ወዘተ.. ናቸው።



ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ



ልጅ ኢያሱ አባቱን ንጉሥ ብሎ በወሎ ቢሾምም በባላባት የሚተዳደር አገር ነበር። ጎጃም ላይም አፄ ዮሐንስ ራስ አዳልን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ብለው ሾሙዋቸው። ከዚያ በፊት ግን በባላባት የሚተዳደር አገር ነበር። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ልጅ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ንጉሥ ባይባሉም ጎጃምን ሲገዙ ኖሩ። ራስ ኃይሉም ንጉሥ ባለመባላቸው ተቀይመው ይመስላል ዕድል ባገኙ ቁጥር ንጉሠ ነገሥቱን እየከዱ ለኢያሊ ዘመን ጎጃምን አስተዳድረዋል። ሆኖም ጥፋት ተገኝቶባቸው ተሽረው መጨረሻ ላይ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ በግዞት ቆዩ።

በኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ላይ ከባላባቶችም ኾነ ከጎሣ መሪዎች ከነሥልጣናቸው የቀሩት የአፋሩ የበላይ ባላባት ቢትወደድ አሊሚራህ ሃንፍሬ ብቻ ነበሩ። ሌሎቹ ግን በሙሉ በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ ሥር የሚተዳደሩ ኾኑ። ስለኾነም ብዙ አኩራፊ በየአገሩ ቢኖርም ያንኑ ያህል ደግሞ ሹመት ፈላጊና አረባጅ ተፈጠረ። ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውጋት ሲያስብ "ጊዜው አሁን ነው ምክንያቱም ብዙ አኩራፊ ስላለ ለንጉሠ ነገሥቱ ሕዝቡ ፀአንድ ልብ አይተባበርለትም" ብሎ ገምቶ ነበር።



# ምዕራፍ ፲፯

# ጃንሆይ እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ

ተፈሪ ከ1909 ዓ.ም እስከ 1921 ዓ.ም ለአሥራ ሁለት ዓመት በአልጋ ወራሽነት፣ ለአንድ ዓመት በንጉሥነት፣ ቀጥሎም ከ1922 ዓ.ም እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ በንጉሠ ነገሥትነት ለስድስት ዓመት በድምሩ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት፣ አያሌ መልካም ሥራዎችን ለመሥራት ሞክረዋል። ከነዚህም መካከል ቀዋሚ ሠራዊት ለማቋቋም የገነት ጦር ትምሕርት ቤትን ከፍተው ኦሠልጣኞችን ከቤልጅግ በማስመጣት ዘመናዊ የወታደር ሥልጠና በማስጀመርና በመንግሥት ሥራ አካሄድም ዘመናዊነትን የተላበሰ አሠራር እንዲመሠረት አድርገዋል።

አርግጥ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት የመጀመሪያውን ጥረት ያደረጉት አፄ ምኒልክ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም። ምናልባት እንደ ተፈሪ በልጅነታቸው የውጭ አገር ትምሕርት ቀስመውና የተደላደለ ሥልጣን ይዘው ለብዙ ዘመን የማስተዳደር ዕድል አግኝተው ቢሆን ኖሮ በሳቸው ቀናነትና ብልህነት አገሪቱን ምን ያህል እንደሚያራመዷት ለመገመት አያስቸግርም። ተፈሪም የሥልጣን አያያዛቸው ሁኔታ ባይወደድም ከአራት ዓመት ውጣ ውረድ በኋላ ለሥልጣን መብቃታቸውን የሚያውከውን ሁሉ በዘዴ ተወጥተውታል። ኋላ ቀር በሆኑ ሰዎች የተከበቡ ስለነበሩም አሠራሩ ላይ አንዳንድ ችግሮች ገጥሟቸው ነበር። ይሁንና በአሥራ ዘጠኝ ዓመት ውስጥ በአጠቃላይ ሲታይ መልካም ሥራ ሠርተዋል።

በ1890 ዓ.ም አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት አባል መሆኗን በማጎተማቸው ቢያረጋግጡም ቀዳማዊ ኃይለ ሳሴ ኢትዮጵያ የዓለም ማኅበርተኛ እንድትሆን ደጃዝማች ናደው ተሰማን በመሪነት፣ አቶ



ሓኑይንና አቶ ፋሲካን በረዳት መልዕክተኛነት ተልከው ነሐሴ 1 ቀን 1914 ዓ.ም ጄኔቫ በሚገኘው የዓለም ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሺን) ዋና ጽሕፈት ቤት ተገኝተዋል።

## የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባልነት



የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ማኅበርን ራስ ተፈሪ ሲጎበኙ (1916 ዓ.ም.)

መልዕክተኞቹ ሲመለሱ አባል ለመሆን አገር ውስጥ መሻሻል ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ ተነገራቸው። እነዚህም የሕገ መንግሥት አለመኖርና እንደ ባርያ ንግድ የመሳሰሉ የሰብዓዊ መብት አለመጠበቅ ጉዳዮች ነበሩ። ይሄንኑ ለማስተካከል ተቀዳሚ ሥራ አድርገው የተነሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ማውጣትና የዳኞች አመዳደብ አስከትሎም የሕገ መንግሥት መረቀቅንና የመንግሥት ሥራ አካሄድን መልክ ማስያዝ

ነበር። ሌላው ደግሞ ምክር ቤት ማቋቋምና የሚኒስትሮችን ሥራ መመሪያ ማውጣትና ጽሕፈት ቤት መስጠት ነበር። ስለኾነም ምንም እንኳን ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ አዋጆች ቢወጡም በመጨረሻ የባሪያን ሽያጭ የሚያግድ ሕግ ወጣ። ሆኖም የባርያ ንግድ እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ እንደነበረ ሰዎች ይናገራሉ። እነዚህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ካስተካከሉ በኋላ በሚያዝያ ወር 1915 ዓ.ም በይፋ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል ኾነች።

አንበሳው ታረርጌ ጊደሪቱ ተኛ (ከወሎ)
ታለም መንግሥታት ጋር ኾነ ማበርተኛ
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

## ትምህርት

ኢትዮጵያ ውስጥ የቀለም ትምህርት አሰጣጥ ጥንታዊ ሲሆን ክርስቲያኑ በገዳማት፣ በቤተ ክርስቲያን ጥግና በአንዳንድ ባለጸጋ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሃይማኖት መምህሮች ዙሪያቸው ተማሪዎችን አስቀምጠው እያንዳንዱ ተማሪ ከደረሰበት እየተማረ አስተማሪው እያዳመጠ ያርመዋል። ለአንድ ተመልካች በዚያ መሰሉ ጫጫታ መካከል አስተማሪው ተማሪዎቹን ለይቶ መምራቱ ያስገርማል። ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ተማሪዎችም ትምህርት ቤቱን ሳይሆን የታወቁ አስተማሪዎችን ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ። ኑሯቸውንም የሚገፉት ከአካባቢ ነዋሪ እየቀፈፉ ወይም እየለመኑ ነው። ስለዚህም የቆሎ ተማሪ ተብለው ይታወቃሉ። ሙስሊሙም በመሠረቱ በዚሁ ዓይነት ጫጫታ በተሞላ ትምህርት ቤት ወይም መድረሳ ወይም የቁርዐን ትምህርት ቤት ልጆቹን ያስተምራሉ።

ይሁንና አንዳንድ ሚስዮናውያን ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመክፈታቸው በክፍል ውስጥ እያንዳንዱ ተማሪ መቀመጫና የሚጽፍበት ጠረጴዛ ተደርጎለት በዘመናዊ መልኩ ይማር ጀመር። አጼ ምኒልክ አዲስ አበባ ላይ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤትን በ1897 ዓ.ም ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተው ቀጥሎ ጃንሜዳ አጠገብ ንጉሥ ሚካኤል መኖሪያ ቤት አስከትሎም ሙሴ ኤልግ መኖሪያ ቤት የነበረውና እሪ በከንቱ አሁን የቀይ ባሕር ሆቴል የሆነው ቦታ ላይ ተዛውሮ እንደቆየ በ1905 ዓ.ም አሁን በሚገኝበት አባታችን ሠፈር አራት ኪሎ ተመሠረተ። ሕዝቡ ልጆቻችን የሚሲዮናውያኑን ሃይማኖት ይከተላሉ (ይኮተልካሉ)



ብሎ እንዳይፈራ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ አሥራ አምስት ግብጻዊ መምህሮች አስመጥተው ችግሩን አቃለሉ።



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪዎችን ሲጎበኙ

ከሚታወሱት ነገሮች አንዱ ይማሩ ለነበሩ ተማሪዎችም ምግብ ተሠርቶ ከቤተ መንግሥት ይመጣላቸው ነበር። ከምግቡም ጋር ለማወራረጃ ብርዝ አብሮ ይቀርብላቸዋል። ንግሥት ዘውዲቱ የአባታቸውን አርአያ በመከተል የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት የሚባለውን አሁን የአራዳው ቴሌ መሥሪያ ቤት የኾነውን ከፈቱ። ልጅ ኢያሱ ንጉሥ ሚካኤል ሠፈር ወይም ጊሚራ ሠፈር ውስጥ አሠርተውት ሳይጨርሱት የቀረውን ትምህርት ቤት በ1917 ዓ.ም ራስ ተፈሪ አስጨርሰው በስማቸው የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ብለው ከፈቱት። አከታትለውም የእቴጌ መነን፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ሌሎችም ትምህርት ቤቶችን አሠሩ። ቤተሰብ ልጁን ወደ ፈረንጅ ትምህርት ቤት አልልክም እያለ ባስቸገረበትም ወቅት ራስ ተፈሪ



የክብር ዘበኛ የመንግሥት ወታደር

ራስ ተፈሪ ከቤልጅግ ጥቂት መኮንኖች አስመጥተው በሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት አቋቁመው ዘመናዊ ሠልፍና የወታደር ሥነ ሥርዓት ማስተማር ጀመሩ። የቤልጅግ መኮንኖቹም በትምህርት አሰጣጣቸው ደህና ቢሆኑም በሙሉ ሰላይ እንደነበሩ ተደርሶበት ነበር። ምክንያቱም የቤልጅግ መንግሥት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ምኞት የነበራት ስለሆነ ነው። በጠላት ዘመን የፈረሰውን የወታደር ተቋም እንደገና ገንብተው እስከ ጦር አካዳሚ ድረስ በመክፈት ኢትዮጵያን በጠራ የጦር ኃይሏ በመላው አፍሪካ እንድትታወቅ ያበቋት ጃንሆይ ናቸው።

ሕዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሡ ነገሥቱ የዘውድ በዓል ጊዜ በደንብ ልብስ የተሽቆጠቆጠ የወታደር ሠልፍ በማየቱ ተደሰተ። ወታደሮቹ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ በማይጨው ጦርነት ባሳዩት ተሳትፎ ተመስግነዋል። የሚለብሱት የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) ከራስ ቆብ አንስቶ የእግር ገምባሌ ላይ ያልቃል። ስለኾነም አንዳንድ ጫማ ያላቸው ይጫሙ እንጂ አብዛኛው ባዶ እግር ነበር። ጣሊያን የማይጨው ምሽጉን ካጠረበት ዘዴ አንዱ የወይን ጠጅ ጠርሙስ ሰባብሮ የኢትዮጵያኖችን እግር



ለመቆራረጥና ለማስቀረት ብሎም ምሽጉን ለመከላከል ነበር። ታዲያ መደበኛውም ኾነ ወዶዘማቹ ወታደር ጫማ ባይኖረውም ያሳየውን ጥንካሬ የተመለከተ ጣሊያን "የአበሻ እግር ከትሬንታ ኳትሮ ጎማ ይጠነክራል" አለ ይባላል። ከ25 ዓመት በኋላ በወሬ የሰሙትን የአበሻን እግር ጥንካሬ የጣሊያን ሰዎች ሮም ከተማ ላይ አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮጦ ማራቶን ሲያሸንፍ ተመልክተዋል።

ተፈሪ ታትሞት ታለች በሕይወት
አገሯን ወስደው የጦር ሠራዊት
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

## ሕግና ደንብ

ራስ ተፈሪ ከአልጋ ወራሽነት አንስቶ እስከ ጣሊያን ወረራ ጊዜ ድረስ መሻሻልን ለማምጣት ብዙ ጥረዋል። ዳኞች የሚፈርዱት እንደፈለጋቸውና መጥቀስም ከፈለጉ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከፍትሐ ነገሥት ከመሆኑ የተነሳ አሠራሩ ጥንታዊ የሆነ እጅ መቁረጥን የመሳሰሉ የግፍ ብይኖች በሰው ልጅ ላይ ይፈጸም ነበር። ይህንን ለማስቀረት ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አጽፈው ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል። በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያትና ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ ያረቀቁት ሕገ መንግሥት ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም ታወጀ። በተጨማሪም የሕግ መምሪያንና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶችን ጥቅምት 23 ቀን 1924 ዓ.ም ከፈቱ።

በጊዜው ሚኒስትሮች ሥራቸውን የሚሠሩት በገዛ ቤታቸው ስለሆነ የአሠራሩ ሁኔታ መልክ አልነበረውም። በዚህ የተነሳ ጽሕፈት ቤት ከፍተውላቸውና አማካሪዎች ቀጥረውላቸው በቀለጠፈ መልኩ የመንግሥት ሥራ ሁሉ መሥራት ተጀመረ።

## ሌሎች ሥራዎች

ራስ ተፈሪ በምኒልክ ዘመን የተጀመረውን የአውሮፓን ዕውቀት በስፋት ወደ አገር ለማስገባት ጥረት አድርገዋል። ራስ መኮንን ሐረር ላይ፣ እቴ ምኒልክ አዲስ አበባ ላይ ካሠሯቸው ሁለት ሆስፒታሎች በተጨማሪ ራስ ተፈሪ ቤተ ሳይዳ ሆስፒታልን አዲስ አበባ ውስጥ

አሠሩ። የዚህ ሆስፒታል ስም ከተፈሪ መንግሥ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል እየተባለ ይጠራ ጀመር። ከዚያም ደርግ ሥልጣን እንደያዘ የካቲት 12 ሆስፒታል ብሎ ቀይሮታል።



ጃንሆይ በ1924 ዓ.ም ፓርላማ ሲከፈት

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ፍልውሃ የሚገኘውን የንግሥት ዘውዲቱ የማዋለጃ ሆስፒታልን አስቀድመው አሠርተው ነበር። ምንም እንኳን ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ዙፋኑ ላይ ለአሥራ ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ቢቀመጡም አብዛኛው ሥራ ይሠራ የነበረው በአልጋ



ወራሹ ራስ ተፈሪ መኮንን ነበረ ማለት ይቻላል። ቢሆንም አንዳንዱ ሥራ የሚሠራው ንግሥተ ነገሥት ራስ ተፈሪን ትዕዛዝ እየሰጡ ነበረ የሚሉም አልታጡም። በተለይ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ አሠሩት ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው በ1917 ዓ.ም የተሠራውና ዘመናዊ የሆነው ሴትና ወንድ በአንድነት ይማሩበት የነበረው ትምህርት ቤት ሲሆን ይኸውም በስሜ ሳይሆን በቅዱስ ጊዮርጊስ ይሰየም ያሉት አሁን የአራዳ የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት ያለበት ቤት ውስጥ ነው። ከጠላት ወረራ በኋላ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ተመልሰው ሲከፈቱ ይህ ትምህርት ቤት ባለመከፈቱ አንዳንድ ሰዎች ቅሬታቸውን ሲገልጹ መጀመሪያውኑ ጃንሆይ ያልከፈቱት ስለነበረ ነው ይላሉ።




በ1937 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ብር

በተጨማሪም ንግሥቲቱ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችንና የአፄ ምኒልክን ሐውልት አሠርተዋል። እንዲሁም ንግሥት ዘውዲቱ በምስላቸው ገንዘብ እንዲታተም እንዲያዙ ሲጠየቁ "የአባቴ ምስል ያለበትን በእኔ ምስል አልተካም" በማለታቸው የአፄ ምኒልክ ብር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምስል በ1937 ዓ.ም እስከተተካ ድረስ ቆይቷል።

ጃንሆይ ንፋስ ስልክ እየተባለ የሚታወቀውን የስልክ ማዞሪያ ከማሠራታቸውም ሌላ የአርመን ሙዚቀኞችን አስመጥተው የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር፣ ተፈሪ ማርሽና ሚሊተሪ ማርሽ እንዲዘመር አደረጉ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርን

ሚስተር ዱዙዛ የሚባል ህንዳዊ ተተኳ። እንግዲህ ይህን መሰሉ እርምጃ ጃንሆይ ምን ያህል ንቁ እንደነበሩ ከማሳየቱም በላይ በዘመኑ ሥነ ሥርዓት እንዴት ይከበር እንደነበረ ያሳያል። በተጨማሪም ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣም ኾነ ሲወርድ ሰው ሁሉ ተሽከርካሪም ጭምር ባለበት ቀጥ ብሎ መቆም ግዴታው ነበር። ባርኔጣም ያደረገ ሁሉ አውልቆ በደረቱ ላይ ይይዛል።

## አስተዳደር

የመንግሥት ቀረጥ በየአካባቢው ላሉ ገዥዎች ገቢ መሆኑ ቀርቶ ለማዕከላዊ መንግሥት መግባት እንዲጀምር በማድረጋቸው ብዙ መኳንንቶች እየከረፉ ቢያስቸግሩም ራስ ተፈሪ ችግሩን ማደሪያ መሬትና የማዕረግ ስም በመስጠት መቋቋም ችለዋል።

ዘመኑ የሚያመጣው የአውሮፓ ሥልጣኔ ያለ ችግር መግባት ጀመረ። ግሩንዲንግ ሬዲዮና መኪና በብዛት ጨመረ። አይሮፕላንም መጣ፣ መብራትም በአውራ ጎዳናዎች ተተከሉ፣ በየመንግሥት መሥሪያ ቤትና በየመኳንንቱ ቤት በስፋት የኤሌክትሪክ መብራት ገባ። የሥልጣኔ ጭላንጭል እየታየ ሄደ። በየመንገድ ዳር ያለውን መብራት በመመልከት የአዲስ አበባ ነዋሪ

"አበሩ ፋኖስ አበሩ ፋኖስ
ከፊት በር አንስቶ ለገሃር ድረስ" ብሎ ገጠመ።

በነዚህ በ19 ዓመት ውስጥ የተሠራው ኢትዮጵያን ከአንድ ጥንታዊ ከኾነ የመንግሥት አስተዳደር ወደ ዘመናዊ ቅርጽ ያለው አስተዳደር ለመሸጋገሯ ግልጽ የኾነ ማስረጃ ነው። እርግጥ ከተሠራው መካከል ምኒልክ ያልጀመሩት ነገር ቢኖር ዘመናዊ ወታደር ማደራጀትና አይሮፕላን ማስመጣት እንጅ ሁሉንም ነገር ጀማምረውታል።

መኪና ለመንዳት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አፄ ምኒልክ ሲሆኑ በብስክሌት ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ ይንሸራሸሩ የነበሩት ሴት ደግሞ በዚያ ግዙፍ ሰውነት እቴጌ ጣይቱ ነበሩ። እንዲሁም ራስ ተፈሪ ሐረር በነበሩ ጊዜ ጫማ በማድረግና ቢስኪሌት በማሽከርከር ይታወቁ ነበር። አፄ ምኒልክ በተፈጥሮ ብልህና የሜካኒክ ችሎታ



ዝንባሌ ስለነበራቸው በዘመናቸው አይሮፕላን መጥቶ ቢሆን ኖሮ ለመንዳት እንደሚሞክሩ አያጠራጥርም።



ፋርማሲ ከጠላት ወረራ በፊት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዞች ተጋብዘው የመን ውስጥ የእንግሊዝ ወታደር ልምምድ ሲመለከቱ እሳቸውና ራስ እምሩ በጦር አይሮፕላን እንዲበሩ ስለተደረገ በአይሮፕላን የበረሩ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ሁለቱ መሆናቸው ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጃንሆይ አይሮፕላን አገር ውስጥ እንዲገባ ፈ ይፈልጉ ነበርና ከየአገሩ አይሮፕላን እየገዙ መጀመሪያ የቤተ መንግሥት ሾፌሮችን በኋላ ደግሞ የተማሩ ልጆችን ለአይሮፕላን አብራሪነት አሠማርተው ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ኢትዮጵያ አሥራ አምስት አይሮፕላኖች ነበሩት። እነዚህም አይሮፕላኖች ዋናው ሥራቸው መልዕክት ማድረስና አንዳንዴም የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ማጓጓዝ ነበር። የጃንሆይ አጎት ደጃች ወልደ ሥላሴ ለመንግሥት ሥራ ደሴ ደርሰው ሲመለሱ አደጋ ተፈጥሮ ቀበቶ ሳያስሩ ቆመው ሲሮኩ አይሮፕላኑ ሲያርፍ ራሳቸውን በኃይል ስለመታቸው ከተሳፋሪዎቹ መካከል እሳቸው ብቻ በአደጋው ሞቱ። ስለኾነም በአይሮፕላን አደጋ

አረማሞዎች (አልጌ) ቀይ ስለሆኑና ባሕሩን ሲመለከቱት ቀይ መስሎ ስለሚታይ ነው።



ፋሽስት ቤኒቶ ሙሶሊኒ

ኢትዮጵያ ከአምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የይፋ መጠሪያ ስሟ "ኢትዮጵያ" ሲሆን በጣሊያን ጋዜጦች ግን የሚጠቀሰው "አቢሲኒያ" የሚለው ስም ነበር። አቢሲኒያ አረቦች ለኢትዮጵያ ካወጡላት ሃበሻ ከሚለው ስም የተወሰደ የአውሮፓውያኖች አጠራር ነው። ሃበሳት ቀደም ብሎ በምዕራብ ሳዑዲ አረብያ ቀይ ባሕር ዳር የሚኖሩ ከጥቁር ጋር የተደባለቁ የአረብ ነገዶች ስም ነበር። የቃሉም ትርጉም ድብልቅ እንደማለት ነው። ከጊዜ ብዛት ይህ ስም ባሕሩን ተሻግሮ በአረቦች ዘንድ የኢትዮጵያውያን መለያ ስም ኾነ።



እንደሚታወቀው አንድ ልጅ ሲወለድ ስም ለራሱ አያወጣም። የተወለደው ልጅ እናቱ ወይም ቤተ ዘመድ ባወጣለት ስም ይጠራል። ስሙን ከወደደው ስሜ ነው ብሎ እስከ ዕድሜ ልኩ ይጠራበታል። ካልወደደው ግን እንዳይጠራበት ይከላከላል። አንድን ሰው ባልወደደው ስም ያለፍላጎቱ የሚጠራው ግን እንደ ስድብ ያህል ስለሚቆጠር ያቃቅራል። አገርም በአንድ ታሪክ አጋጣሚ ስም ይወጣላትና ስሜ ነው ብላ ከተቀበለችው ይፋ ታደርገዋለች። እንዲሁም ሕብረተ ሰብም ባልወደደው ስም መጠራት አይኖርበትም። አለበለዚያ አጨቃጫቂና የግጭት መንስዔ ሆኖ ይገኛል። ለምሳሌ ነፍጥ በትግርኛ ትርጉሙ ጠብመንጃ ማለት ነው። የመንግሥት ወታደሮችም በአፄ ምኒልክ ዘመን ነፍጠኛ ይባሉ ነበር። መደበኛ ወታደር ሲቋቋም ይህ ስም ጡረታ የወጡ ተዋጊዎች ስም ኾኖ ቀረ። በዛሬ ጊዜ አማራን ነፍጠኛ እያሉ የሚጠሩ አማሮችን ለማስከፋት አስበው ቢኾንም አማሮች ግን የሚያፍሩበት ባይኾንም መንፈሱን የሚወዱት አይመስልም። ነፍጠኛ የሚለውን ቃል ጉልተኛ ሥርዓትን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ከኾነም ሁሉም ጎሣ ውስጥ ጉልተኛ ስለአለ የተለየ ጎሣን ብቻ አይመለከትም። ስለኾነም አማራዎች ነፍጠኛ፣ ኦሮሞዎች ጋላ፣ ወላይታዎች ወላሞ፣ አፋሮች አዳል፣ ወዘተ.. ብላችሁ አትጥሩን ስለሚሉ ይህ ጥያቄ መከበር አለበት። ከፍ ሲልም ኢትዮጵያውያን ሃበሻ ሲሏቸው እጅግም እንደማይደሰቱ፥ ሁሉ አሜሪካኖችም ያንኪ ሲሏቸው ይጠሉታል።

ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ የነበሩት ነገሥታት የኢትዮጵያ ንጉሥ ወይም ንጉሠ ነገሥት እያሉ በይፋ ያውጁ ነበር እንጂ የሃበሻ ንጉሥ ነን ብለው አላወጁም። ኢትዮጵያም በ1915 ዓ.ም የዓለም ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል ሆና "ኢትዮጵያ" ተብላ መመዝገቧ እየታወቀ ጣሊያኖች በ1933 ዓ.ም ተሸንፈው ኢትዮጵያን እስከለቀቁ ድረስ አገሪቱን የይፋ ስሟ እያለ አቢሲኒያ እያሉ ይጠሩ ነበር። ሃበሻ የሚለውን ስም በይፋ ኢትዮጵያውያኖች ባይቀበሉትም የሚጠሉት ስም ስላልኾነ በጊዜ ብዛት በልማድ በንግግራቸው ውስጥ እያስገቡ የሃበሻ ልብስ፣ የሃበሻ ምግብ እያሉ እንደሚጠቀሙበት አይካድም። ቅሬታ የፈጠረው ጣሊያኖች ስሙን የአጠቃቀማቸው መንፈስ እንጂ የሚያሳፍር ኾኖ አልነበረም።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በግሪክኛ ቋንቋ ፀሐይ የለበለበው ፊት ማለት ሲሆን ብሉይ ኪዳን ሲተረጎም ግብጾችና አይሁዶች ኩሽ

የሚሉትን ቃል ተክቶ የገባ የግሪክ ቃል ነው። እንዲሁም ደግሞ ቀደም ብሎ የግሪክ ታሪክ ጸሐፊዎች ብዙ የጻፉበት ስም ስለኾነ የሕዝቦቹን ገናናነትና ትልቅነት ገልጸውበታል። በቅርብም ታሪክ ቢሆን ነጭን ያሸነፈ የጥቁር ሕዝብ መለያ ስለኾነ ይህ ስም በተነሳ ቁጥር ማንኛውም ጥቁር ስሜቱ ከፍ ይላል። ስለዚህም ጣሊያኖች ይህንን ስም ለመጠቀም አልፈለጉም።

ከቀን ብዛት ኢትዮጵያውያንም ተለማምደውት አቢሲኒያ ወይም ሃበሻ የሚለውን ቃል መጠቀም ሲጀምሩ በ1944 ዓ.ም ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በውጭ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ቆንስላዎች፣ ለጋሲዮኖችና ኤምባሲዎች አቢሲኒያ ወይም ሃበሻ የሚለውን አጠራር እንዳይጠቀሙበት፤ ማሕተማቸውንና የደብዳቤ ርዕሳቸውን በሙሉ እንዲያርሙና ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ብቻ እንዲጠቀሙ የፅሑፍ ትዕዛዝ አስተላልፏል። በአሁኑ ጊዜ ታሪካዊ ስም እየመሰላቸው ጠላት ለፕሮፓጋንዳ ይጠቀምበት የነበረውን አቢሲኒያ የሚለውን ስም እንደ ታሪካዊ ስም በመቁጠር ሲጠቀሙበት ይታያል።

ሁለቱ የታሪክ ጠላቶች ግብጾችና እንግሊዞች በአፄ ምኒልክ ጊዜ በአዲስ አበባ ውስጥ አንድ ባንክ ሲያቋቁሙ ካላጡት ስም አቢሲኒያ ባንክ ያሉት ባልታሰበና ባልተጠበቀ መንገድ ማንኳሰሳቸው ነበር። በተለይ ሕዝቡን ዕዳ ውስጥ እያስገባ የከተማውን ቦታ ሁሉ በመውረስና ለአውሮፓውያኖች በመሸጥ ቀስ በቀስ በሠላማዊ መንገድ አገሪቱን በተዘዋዋሪ የቅኝ ግዛት ለማድረግ ጥረት ማድረጋቸው ስለታወቀና ባንኩ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለከፋ እንዲዘጋ ተደረገ[12]።

ስም በማንኛውም ቋንቋ አጠራሩ አንድ ዓይነት መሆን አለበት። ሃበሻ የሚለውን አቢሲኒያ ብለው መለወጣቸው ለምን እንደሆነ አይታወቅም። እንግሊዞች የፈደላቸው አነባበብ ላይ ችግር እያለባቸው ከእኛ ወዲያ ለአሳር በሚል አስተሳሰብ ስህተታቸውን ለማረም አይሞክሩም። ስለሆነም ሃበሻ የሚለውን አቢሲኒያ፣ የሱስ የሚለውን ጂሰስ፣ ኒል የሚለውን ናየል፣ ሚካኤል የሚለውን ማይክል፣ አሁን ደግሞ ኢራቅ የሚለውን አይራክ፣ እያሉ መጠሪያ ስምን እንደፈለጋቸው ያበላሻሉ። ጣሊያኖችም የእንግሊዞቹን አጠራር

[12] ጣይቱ፡ ብጡል በቀኛ ታደሰ ዘወልዴ ገጽ 44



ከመከተል እኛ በምንጠቀምበት ዓይነት ሃበሻ ማለት በተገባቸው ይሻል ነበር። ለምሳሌ ኮት ደ ቯዋር የምትባለው አፍሪካዊ አገር አይቮሪ ኮስት በሚል ስም እንዳትጠራ በቅርቡ አስታውቃ ይኸው ማስተካከያ ጸንቶ በሥራ ላይ ውሏል።

በሥነ ልቡና ረገድ ደግሞ የሚጠሩበት ስም ቀላል አይሆንም። ለዚህም ነው እያንዳንዱ ወላጅ ልጅ በተወለደ ገዜ ስም ለማውጣት ሲቸገር የሚታየው። በዚህም ምክንያት ሃይማኖተኛው ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከቁርዐን፣ ውበትን አድናቂው ከተፈጥሮ፣ ጀግናው ገድልን የሚገልጽ ስም ሲያወጣ ይታያል። እዚህ ላይ በሃይማኖት ሰበብ ለልጆች የግሪክ፣ የእብራይስጥና የአረብ ስም ሲያወጣ የኢትዮጵያውያን ስም እየተረሳ መሄዱ በብዙ ሰው ዘንድ የተዘነጋ ይመስላል።

ጣሊያን በጦርነት አሸንፎ አገሩን ከመያዙ በፊት አንስቶ በፕሮፓጋንዳ ልክ እንደራሱ ግዛት አድርጎ ስለሚወተውት አውቀውም ሆነ አጥርተው የማያውቁ አውሮፓውያን ኢትዮጵያን የጣሊያን ቅኝ ግዛት አድርገው መጻፍም ጀምረው ነበር። ይኸ ሁሉ አገሪቱን ለመውረር የተደረገ ዝግጅት ነበር። እንኳን በዚያን ወቅት አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ በሕዝብ ግንኙነት ሥራ ኋላ ቀር ነች። በውስጥ የሥልጣን ውዝግብ ምክንያት የጣሊያንን ጠላትነት እንደ ትልቅ ቁም ነገር የቆጠረው ስላልነበረ በወቅቱ በፕሮፓጋንዳም ይሁን በጦር ኃይል ለመከላከል ጥሩ ዝግጅት ባለመደረጉ፣ በተለያዩ ተንኮሎችና በዘመን አመጣሽ መሣሪያ ብልጫ ኢትዮጵያ በ1928 ዓ.ም በተካሄደው ጦርነት ተሸነፈች። የተዋጋችው በፊት ለፊት ከጣሊያን ጋር ሲሆን በተዘዋዋሪ ግን ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ጭምር ነበር። በስዊዝ ካናል ጣሊያን እንደልብ ወታደርና መሣሪያ እንድታሳልፍ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ሲፈቀድላት ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የጦር መሣሪያ እንዳይገባ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን እ.አ.አ. በ1930 ዓ.ም ላይ ስምምነት አድርገው ነበር። በሊግ ኦፍ ኔሽን የዓለም ማኅበርም አቤቱታው ምላሽ እንዳያገኝ ያደርጉ የነበሩት እንግሊዝና ፈረንሳይ ነበሩ።



# ምዕራፍ ፲፰

## የማይጨው ጦርነት

እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ምንም እንኳን ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን ወርዶ በምትኩ ደጃች ተፈሪ ሥልጣን እንዲይዙ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ቢያደርጉም አንድ የነጭ መንግሥት በአንድ የጥቁር መንግሥት በጦርነት መሸነፉ ያስደነገጣቸውና አፍሪካን ለመቀራመት ያዘጋጁትን ውጥን ያበላሸባቸው ስለመሰላቸው ቂማቸውን አልረሱም። በተለይ ጣሊያን ከአድዋ ድል በኋላ በደረሰባት ሃፍረት ቂም ይዛ ብድሯን ለመመለስ መዘጋጀት የጀመረችው ወዲያው የአድዋ ጦርነት እንደተፈጸመ ነበር። እንግሊዝና ፈረንሳይ በቅኝ ግዛታቸው የኢትዮጵያ አዋሳኝ ስለነበሩ ነገሩ በጣም እየቆረቆራቸው ሄዶ በኢትዮጵያ ባለሥልጣን ሹም ሽረት ሂደት ውስጥ በዙሪያ መንገድ እጃቸው ቢኖርበትም አገሪቱ ነፃ የጥቁር አገር ሆና መታየቷ ሌሎች ጥቁሮችን "ይህም አለ ለካ!" ብለው እንዳይነሱባቸው ያሳስባቸው ነበር። ስለዚህም ኢትዮጵያ ባልተሳተፈችበት ድርድር ላይ ስለ ዓባይ ወንዝና ስለምድር ባቡር መዘርጋት ጉዳይ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን ስምምነት አደረጉ።

የተፈሪ ሹመት ያስከተለው የውስጥ ጭቅጭቅና አለመግባባት የአገሪቱን የተባበረ ኃያል የቀነሰው መሆኑ ግልጽ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያንዳንዱን ግዛት በራሳቸው ሹሞች ማስተዳደር ሲጀምሩ የሕዝቡን አለመደሰት በመገንዘብ አገሪቱን በጦርነት ለመምታት ወቅቱ አመች መሆኑን ገመቱ። ቅኝ ገዥዎች በወንጌል መልዕክተኞችና በነጋዴዎች አማካይነት ሠላዮች በብዛት መላክ ጀመሩ። ጣሊያን በብዛት የጦር ኃይል መኮንኖቹዋን ለሥለላ ሥራ በወንጌል መልዕክተኞች ስም ላከች። በተጨማሪም በጎንደር፣ በደሴ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በነቀምት፣ በሐረርና አድዋ ላይ ቆንስላዎች አስቀምጣ መኳንንቶቹን ወዳጅ ለማድረግ ብዙ ሰዎች አሰማርታ ነበር።





ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (1928ዓ.ም.)

ቫቲካን ካሰማራቻቸው የወንጌል መልዕክተኞች በተጨማሪ ለተለያዩ ሥራዎችም ከሚመጡት ሰዎች መካከል ብዙ ሠላዮችም ነበሩ። ለምሳሌ በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ የቪክቶር ኤማኑኤል አጎት ዱክ ዳብሩዚ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ሲመጣ ለመታያ ለተፈሪ ለሰጠው ታንክ ነጅ የኾነው ሲኞር ዲ ማርቲን አማርኛ አቀላጥፎ የሚያውቅ ሲምል 'ተፈሪ ይሙት!' ሲፎክር 'የጠቅል አሽከር!' እያለ በቤተ መንግሥት ውስጥ እንደልቡ እየገባና እየወጣ [13] ደህና አድርጎ ይሠልል ነበር።

ቅኝ ገዥዎቹ በኢትዮጵያ ወሰን አካባቢ ያሉ አስተዳዳሪዎችን በማግባባት ከገንዘብ ሌላ ጊሻን ሁሉ እየሸለሙ አገሪቱን ከዘመቻው በፊት ቦርቡረው ጨርሰው ነበር። መጨረሻ ላይ በአካባቢ ባሉ ቅኝ ግዛቶችዋ ላይ ጣሊያን ወታደር በብዛት አስቀምጣ ነገር መቆስቆስ ጀመረች።

ንጉሠ ነገሥቱ የዓለም ማኅበር አባል የኾነችው ኢትዮጵያ ተበደለች በማለት መልዕክተኛ እየላኩ አቤቱታቸውን ማቅረብ ጀመሩ። የማኅበሩ አባሎች እንግሊዝም ፈረንሳይም ጣሊያንን እንዳያስቀይሙና አኩርፋ ከጀርመን ጋር እንዳታብር ይጠነቀቁና የራሳቸውንም ጥቅም ያስጠብቁ ስለነበር ኢትዮጵያ ከማኅበሩ ፍትሕ አጣች። በዘመኑ ኃይለኛው የእንግሊዝ መንግሥት ሲሆን አሜሪካን ጭራሽ ማኅበርተኛም አልነበረችም። በዚህ ምክንያት የማኅበሩን ውሳኔ ሌላ የሚያስፈጽም አካል በወቅቱ ባለመኖሩ ለጣሊያን አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮ በማን አለብኝነት ጦርነት እንኳን ሳታውጅ ጣሊያን የኢትዮጵያን ድንበር በወልወል በኩል ገፍታ ገባች። አልፋ ተርፋም በሰሜን በኩል ድንበር ጥሳ አገር መያዝ ጀመረች።

[13] የሕይወቴ ማስታወሻ ከቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ

ከሁሉም የሚያስገርመው ደግሞ በዘመኑ የነበሩት በቫቲካን የካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ የኢጣሊያን ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ ለወረራ ሲዘምቱ እንደመቃወም ዘማቹንም መድፉንም ባርከዋል። ምዕመናኑንም ለዚህ ለተቀደሰ ጦርነት ገንዘብ እንዲያዋጡ፣ ገንዘብ የሌላቸው ደግሞ የአንገታቸውን ሃብል፣ የጣት ቀለበታቸውን፣ የጆሮ ጉትቻቸውን እንዲሰጡ አድርገዋል። እውነተኛ የሃይማኖት አባት ቢሆኑ ኑሮ የሌላን ሰው አገር በግፍ ለመውረር የከጀለውን መንግሥት ማውገዝ በተገባቸው ነበር።



የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ቂም ይዞ እያለ በዘመናችን ያሉት ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ ጳውሎስ ሁለተኛ ዓለምን በሙሉ ሲጎበኙ ኢትዮጵያ ውስጥ ጉብኝት ለማድረግ ጠይቀው ሕዝብ ስላጉረመረመ ሳይሳካላቸው ቀርቷል። የአንድ ሰው ወንጀል ወደሌላ ባይተላለፍም ወንበሩ ላይ የተቀመጡት የዘመኑ ሊቀ ጳጳስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅና ቂሙን እንዲተው ማድረግ ይገባቸው ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የካቶሊክ ዕምነት ተከታዮች ቁጥር አነስተኛ ሆኖ የቀረው የቫቲካን ቢሮክራሲ ከግራኝ ጦርነትእስከትሎ የተደጋገሙ ስህተቶች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ በማድረጉ ነው።

የማይቀረው ጦርነት መምጣቱ ግልጽ ሲሆን የኢትዮጵያ የጦር ኃይል ሊቋቋመው የማይችለው መሆኑ ታወቀ። አንድ ትልቅ ስብሰባ በቤተ መንግሥት ተደርጎ የጣሊያን ጦር ከፍተኛና ዘመናዊ ትጥቅ ያለው ስለሆነ ምን እናድርግ እየተባለ ሲወሳ የተሰብሳቢውን ሰው ዓይን ውሃ የተመለከተ አንድ ተሳታፊ ተነስቶ "አቅምስ ባይኖረን ነፃነታችንን



ሳንዋጋ ልንሰጥ ነው ወይ!" ብሎ ስብሰባው መካከል ሽለላና ቀረርቶ አሰማ። የዚህን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ካባቸውን አጣፉና እንዘምታለን ብለው ስለቆረጡ ስብሰባው አበቃ። ወዲያው መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም የክተት አዋጅ ተነገረ።



የማይጨው ጦርነት አዋጅ ነጋሪት ሲጎሰም



ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል

በየአቅጣጫው የጦር አበጋዞች ተመድበው የጦርነትና የጉዞ ዝግጅት ተጀመረ። የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ስለዚህ ስብሰባ በጽሑፋቸው መካከል አያነሱም። ስለሆነም ስብሰባው ላይ የፎከረውን ሰው ስም ለማግኘት አዳጋች ሆኗል። ይሁንና የተከበሩ አቶ ከበደ እንግዳ ሰው "የምክር ቤታችን ዕድል ኃይለ ሥላሴ የጄኔቭ ቁልፍ" በሚል ርዕስ በ1953 ዓ.ም በታተመው መጽሐፋቸው ስለዚህ ስብሰባ ሲያትቱ "‥ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጀግኖች

የራሱን ስንቅ እየበላ ተዋግቶ ሲመለስ ጣሊያን በመንግሥት በኩል የተከማቸውን በአይሮፕላን አቃጠለው። በተረፈ ግን ወታደሩ በጦርነቱ ያሳየውን ቆራጥነትና ውግያ በማድነቅ ጣሊያን በአይሮፕላን ባይታገዝ ኖሮ ጳግመኛ ድል ለኢትዮጵያ እንደሚሆን ጣሊያኖቹ ራሳቸው በኋላ ገልጸውታል።

በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ በኩል የጦር መሪ አሿሿም ላይ ስህተት ነበር። አፄ ምኒልክ ለጦር አበጋዝነት ሹመት የሚመርጡት የጨዋ ልጅ የሚባሉትን ነበር። ጨዋ ማለት በኀብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቅ፣ በትምሕርት ያልዘለቀ፣ ማንበብና መጻፍ ከዚያ ሌላ የጸሎት መጽሐፍ መመልከት የሚችል እንጂ በትምሕርት የተራቀቀውንማ ተማሪ ነበር የሚሉት። ተማሪንም ፈሪ፣ ወላዋይ፣ ከዳተኛ፣ አድርገው ነበር የሚቆጥሩት። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ጦረኛውን ራስ ሙሉጌታን ከጦር ሚኒስትርነት ሽረው ወግ አጥባቂውንና ቄሱን ራስ ካሣን የማይገባቸውን ሥልጣን ሰለሰጡ ዘማቹ ራስ ሙሉጌታን ትቶ ወደ ራስ ካሣ ስለዞረ ራስ ሙሉጌታ አቅም አንሷቸው በጠላት ሳይሆን በወገኖቻቸው በራያና አዘቦ ተከበው ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተገደሉ። ራያና አዘቦ ከአድዋ መልስ በገዛ ወገኑ ላይ የተኮሰ ከመሆኑም በላይ ከማይጨውም መልስ ከጣሊያን ጋረ ተመሳጥሮ ገንዘብ በመቀበል ተመሳሳይ ጉዳት አድርሷል።

የዘመናዊ አስተሳሰብና የጦር ትምሕርት የቀሰሙትን መሾም ሲገባቸው ንጉሠ ነገሥቱ ለራሳቸው ሥልጣን የሚታመን ብቻ ሲሾሙ ነገር አበላሹ። መጀመሪያውኑ ራስ ሙሉጌታ ምንም እንኳን ጦረኛ ቢሆኑም የተሾሙ ዕለት ቤተ መንግሥት ውስጥ ያገኟቸው ደጃች ባልቻ "ለመሆኑ አንተስ ሹመቱን ተቀበልክ?" ብለው በመገረም ጠይቀዋቸው ነበር ይባላል። ይኸ የሚያሳየው ለግዳጁ ይበልጥ የሚጠቅሙ እያሉ ራስ ሙሉጌታ ለንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን በመታመናቸው ብቻ እንደተሾሙ ነው።

ራስ ደስታና ደጃች በየነ መርዕድ የጃንሆይ የሴት ልጆች ባሎች ናቸው። ራስ ደስታ የጀግኖች አስኳል ዘር ሆነው የረባ ጦርነት ሳያደርጉ ወዲያውኑ ድል ተመቱ። መጨረሻም ላይ አጥብቆ እንደ መዋጋት ሲወላውሉ ቆይተው ወደ እናታቸው ትውልድ አገር ገብተው ከተደበቁበት ተይዘው ከራስ ካሣ ሁለት ልጆች ጋር ተገደሉ።



እንደዚሁም ደጃዝማች በየነ መርዕድ ከገቡላቸው የኤርትራ ወታደሮች ጋር ኾነው ውጊያ ላይ ተማርከው ተገደሉ። ባለቤታቸው ልዕልት ሮማነ ወርቅም ተማርከው ጣሊያን አገር ተወሰዱና እዚያው በእስር እንዳሉ ሞቱ።



የክብር ዘበኛ የሙዚቃ ባንድ ከጣሊያን ወረራ በፊት ሁለት ሜትር ከሰማኒያ ርዝመት ባለው ዱላ አሸከርካሪ እየተመራ (የቢኒሻንጉል ተወላጅ በኋላ ጣሊያን የገደለው)

ራስ ካሣ ለንጉሠ ነገሥቱ በእናታቸው በኩል የአክስታቸው የወይዘሮ ትሰማ ዳርጌ ልጅ ናቸው። በአባታቸውም በኩል የአባታቸው አጎት የራስ ዳርጌ የልጅ ልጅ ናቸው። ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤልም በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን ተፈሪን ንጉሥ እንዲሆኑ ውስጥ ውስጡን አድማ የመቱ ለንጉሡ ታማኝ ይሁኑ እንጂ ጦሩ የማይታዘዝላቸው በአዝማችነት የማይታወቁ ሰው ነበሩ። ጃንሆይ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ ደጃዝማች ነሲቡ በሥራቸው ያለው ጦር ሳይሰማ ከጥቂት አዝማቾች ጋር ሾልከ ብለው ጅቡቲ ድረስ ሄዱና አብረው ተሰደዱ። እንደእውነቱ ድሉ የኢትዮጵያ ቢሆንና በስደት ላይ ባይሞቱ ኖሮ ለጦር ፍርድ ቤት

የሚያስቀርብ ስህተቶችም ሠርተው ነበር[14]። ባጭሩ የንጉሡ ነገሥቱ ካድሬ እንጂ ለዘመቻ ኃላፊነት የማይበቁ ሰው ነበሩ። ሆኖም ወጣትና ምሁር ስለነበሩ በኤርትራ የኢትዮጵያ ቆንሲል ጄኔራል፣ የማዕከል መካሪ ማኅበር መሪ፣ በአዲስ አበባ ከንቲባነትና የሐረር ገዥ በመሆን በወጣትነት ዕድሜያቸው ብዙ አገልግለዋል።

ወሎ በልጅ ኢያሱ መሻርና በንጉሥ ሚካኤል ተሸንፎ መማረክ፣ ጎንደር በራስ ጉግሣ መገደልና በደጃች አያሌው ብሩ አለመሾም፣ ጎጃም በራስ ኃይሉ መጋዝ፣ በሸዋም ጥቂት መኳንንቶች በአቤቶ ኢያሱ መሻር ስላኮረፉ፣ በአፋርና በሶማሌ ባላባቶች ዘንድ በአቤቶ ኢያሱ ከሥልጣን መወገድ ቅሬታ ስለነበረባቸው ለጦርነቱ ቢሠለፉም በሙሉ ልብ አልነበረም። የጐጃም ጦር በከፊል ሳይዋጋ ተመለሰ። አፋር ጭራሽኑ ሳይዘምት ቀረ። በወሎ በኩል ያለው ቆለኛ ከማይጨው የሚመለሰውን ዘማች ፈጀው። ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱም የተመለሱት በላሊበላና በመርሐቤቴ በኩል ነው።

በጣሊያኖቹ በኩል በቂ ዝግጅት አድርገው ስለነበረ የማሸነፍ ዕድሉ የእነሱ እንደሚሆን አስቀድመው አውቀውታል። በአድዋ ጦርነት የተሸነፉት በወታደር ማነስ ምክንያት መሆኑን በመገንዘብ ማይጨው ጦርነት ላይ በተሰላፊ ብዛት እነሱ ይበልጡ ነበር። ሙሶሎኒ "ወታደር አንሶ ከምሸነፍ ከድል በኋላ ወታደር አብዝተህ ነበር ተብዬ ብወቀስ ይሻለኛል" ብሎ ተናግሯል። ኢትዮጵያ የትራንስፖርት ሥራ ብቻ የሚሠሩ 12 ትንንሽ አይሮፕላኖች ስታሠልፍ ጣሊያን ግን በሰሜን ግንባር ብቻ 300 ያህል በምሥራቅ ደግሞ 150 የጦር አይሮፕላን አሠማርቷል። እ.ኤ.አ በ1935 ዓ.ም ጣሊያንና ኢትዮጵያ የመርዝ ጭስ እንደማይጠቀሙ የተዋዋሉትን ስምምነት ጥሶ ይህንኑ የመርዝ ጭስ በሕዝብ ላይ በመርጨት የሰውን ልጅ እንደ ትንኝ በመፍጀቱ ይቅርታ የማይደረግለት የጠላትነት ተግባር ፈጽሟል። ይኸም አሜሪካ ጃፓንን ማሸነፍ ሲያቅታት ሂሮሺማና ናጋሳኪ የጃፓን ከተሞች ላይ የለፈረውን ጦር ለመፍጀት ከጣለቻቸው ሁለት የአቶሚክ ቦንቦች ባይወዳደርም ጭካኔው ግን አይተናነስም። ይኸንንም የምንልበት ምክንያት ኢትዮጵያውያን የታጠቁትንና ጠላት የታጠቀውን የመሣሪያ ዓይነት በማወዳደር ነው።

[14] የታሪክ ማስታወሻ ከደጃ ከበደ ተሰማ



ንጉሠ ነገሥቱ ደሴ ደርሰው ስምንት ቀን ከቆዩ በኋላ የጣሊያን አይሮፕላኖች እየመጡ ቦንብ እየጣሉ መሄድ ጀመሩ። ንጉሠ ነገሥቱም የአይሮፕላን መጣያ ቢተኩሱም ከአይሮፕላኖቹ ርቀት የተነሳ እጅግም ጉዳት ሊያደርሱባቸው አልቻሉም።



ጃንሆይ ደሴ ላይ ሆነው የአይሮፕላን መጣያ (ኦርሊኮን) ሲተኩሱ

ራስ ሙሉጌታ የቀዳሚ ጦር አበጋዝ እንጂ እንደ ጦር ሚኒስትርነት ኃላፊነታቸውን አልተወጡም። ካርታ እንኳን ሲያቀርቡላቸው "ይህንን መመልከት የሚወድ ራስ ካሣ ነው፤ እኔን ተውኝ" በማለት ለጦሩ ተገቢውን አመራር መስጠት አልቻሉም። እርግጥ በዘመቱበት መስመር ጀግንነታቸው የታወቀ ጦረኛ ነበሩ።

ራስ ሙሉጌታ ወታደሩን "ሌሊት እንዲጓዝ ያድርጉ፤ በቀን የሚደረገው እንቅስቃሴ ለጣሊያን ምቹ በመሆኑ ዘማቹን በአይሮፕላን ይደበድበዋል" ቢሏቸው "እኔ ሙሉጌታ! ፈርቼ ነው ሌሊት እንደ ጅብ የምሄደው?" ብለው በቀን መጓዙን ስለመረጡ ብዙ ዘማች አስፈጁ። ንጉሡም በሬድዮን መልዕክት ሲያስተላልፉ ጣሊያን መልዕክቱን እየጠለፈና እያስተረጎመ

አስቀድሞ ዝግጅት እያደረገ ዘማቹን ፈጀው። ይህ ሁሉ ሲሆን በኢትዮጵያ የጦር መሪዎቹ በኩል መልዕክቱ መጠለፉ እንኳን አይታወቅም ነበር።



የማይጨው ዘማቾች ጃገማና ጢንቂሳ ኬሎ



የራስ እምሩ ጦር ብቻ በዘዴ ለመርዝ መርጨት የማይመች ቦታ ላይ ሰፍሮ የመርዝ ጭሱንም ነጠላውን እየቀደደና ውኃ እየነከረ አፍንጫው ላይ በማድረግ ራሱን ተከላከለ። ሆኖም ግሚሱ የጎጃም ጦር ትቷቸው በመመለሱና ደጃች አያሌውም ስለለገሙባቸው በጦራቸው መሳሳት ቢቸገሩም በሥርዓት የተዋጉና ተመልሰው ጎጃም እስኪገቡ ጦራቸው ያልተፍረከረከ የራስ እምሩ ጦር ብቻ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱም ከደሴ ተነስተው ወደ ማይጨው ሄደው የጦር አለቆቻቸውን ገና አልተዘጋጀንም እያሉ ጦርነት የሚደረግበት ጊዜ በጣም ተራዘመ። በዚህን ወቅት ጣሊያን በያዛቸው ቦታዎች ላይ ምሽጉን ይሠራ ስለነበረ ራስ ደምሰው ነሲቡ "እንዴት ምሽጉን ሲሠራ ቁጭ ብለን እናያለን? በኋላ ምሽጉ ውስጥ ሆኖ ጉዳት ያደርስብናል" እያሉ ቢሮሙሁ ስሚ በማጣታቸው ወታደሮቻቸውን ይዘው በራሳቸው ውሳኔ አደጋ ሲያደርሱ በዚያው ሞቱ። በወቅቱ አዝማቾች እርስ በርሳቸውም መልዕክት ለመላላክ አይፈቀድላቸውም ነበር። ማንኛውም መልዕክት በራስ ካሣ በኩል ለጃንሆይ ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ መገናኘት እንዲችሉ ስለተደረገ ብዙ አዝማቾች ትዕግስታቸው እያለቀ ጠላት ላይ አደጋ መጣል ሲጀምሩ ራስ ካሣ በበኩላቸው ዝግጅቱ ሳይጠናቀቅ ለምን ጦርነት ትጀምራላችሁ በማለት ዳግመኛ ጥቃት እንዳይከፍቱ ዋስ ያስጠሩ ጀመር። ይኸ ሁሉ ሁኔታ ለጣሊያኖቹ ዝግጅት ጊዜ ሰጣቸው።

ጦርነቱ ማይጨው ላይ መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ለአንድ ቀን ከተደረገ በኋላ በማግስቱ ጃንሆይ የማፈግፈግ ትዕዛዝ ሰጡ። ወታደሩም የንጉሠ ነገሥቱን መመለስ ሲሰማ ጥቃት በዝቶበት ስለነበረ ወዲያውኑ አፈገፈገ። ዘማቹን እንደገና አስቁሞ ለጦርነት ማብቃት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ሲመለሱ አዘቦና ራያ ወታደሩን መፍጀት ጀምሮ ጦርነቱ ከጠላት ጋር መሆኑ ቀርቶ እርስ በርስ ሆነ። ይኸ ሁሉ ሲሆን የአልጋ ወራሽ ጦር የተባለው ከደሴ እንኳን ሳይነሳና ሳይዋጋ ተመለሰ። ንጉሠ ነገሥቱም ከደሴ በላሊበላ በኩል ስለተጓዙ ወታደሩ ንጉሠ ነገሥቱ ጠፍተውበት ጠብቆ ተበታተነ። ጃንሆይ ቤተ ክርስቲያን እየሳሙ ወታደሩ ተበታትኖ ብዙ ጊዜ ከባከነ በኋላ ጃማ ሲደርሱ ያሉበት ስለታወቀ ልጅ ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ አዲስ አበባ ስልክ ደውለው ለእቴጌ ይኸንኑ ሁኔታ ስለተናገሩ ያሉበት ታወቀ። በወራቸው በመርሐ ቤቴና በዜጋመል በኩል ፍቼ ራስ ካሣ ቤት አርፈው ሌሊቱን

መሰናታቸው ታወቀ። ጃንሆይ ድሬ ዳዋን አልፈው ባቡሩን ያስቆሙና ከታሰሩበት ይዘዋቸው ለሄዱት ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ለራስ ገብረ ሕይወት ሚካኤልና ለሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች ምሕረት አድርገው ጉዞ ሲጀመሩ ደጃዝማች አባ ውቃውን ግን በእስር ላይ እንዳሉ ትተዋቸው ሄዱ።

በባቡሩ የተለየ ፉርጎ ውስጥ አንድ ቢዩከና ክራይዝለር በጠቅላላው አራት መኪናዎች በሌላ ፉርጎ ደግሞ የተለያዩ ሻንጣዎች ነበሩ። በሌሎች ፍርጎዎችም በርካታ ሰዎች ተሳፍረው ስለነበረ እንደገና ባቡሩን አስቁመው ምንም ከተማ በሌለበት በርሃ ብዙ ሰዎች እንዲወርዱ ተደረገ። የፈረንሳይ ሶማሊ ወሰን ከመድረሳቸውም በፊት የፈረንሳይ መንግሥት የጦር መሣሪያ የያዘ ሰው ግዛቴ አይገባም ስላለች አሥራ አምስት የንጉሠ ነገሥቱ ጠባቂ የክብር ዘበኞች አለመሣሪያችን "እንጠቅምዎትምና ይፍቀዱልን እንውረድና ለነፃነታችን እንታገል" ብለው ስለጠየቁ ተፈቅዶላቸው ወረዱ[15]።

ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ በሄዱ በሦስተኛው ቀን የጣሊያን ወታደር በጦር አዛዡ ጄኔራል ባዶሊዮ እየተመራ በየካ በኩል አዲስ አበባ ገባ። በዚህ ዕለት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በመሠለፍ ልክ ጄኔራል ዲ ቦኖ አድዋ ሲገባ እንዳደረጉት ለጄኔራል ባዶሊዮም የክብር አቀባበል አደረጉለት።

ሙሶሊኒ ኢትዮጵያ በኢጣልያ የጦር ኃይል በመያዝዋ ሁለተኛው የሮም የንጉሠ ነገሥት መንግሥት (የሮማን ኤምፓየር) መመሥረቱን እ.አ.አ. ግንቦት 5 ቀን 1935 ዓ.ም ለዓለም አስታውቆ አዲሱን መንግሥት የሚያናውጥ ኃይል በምድር ላይ ሊኖር አይችልም ብሎ በታላቅ ትዕቢት ተናገረ።

የኾነው ኾኖ ብዙ አደጋ እየተጣለ ጠላትን ማስቸገርና ለውድቀትም ማድረስ ሲቻል በንጉሠ ነገሥቱ የጥድፊያ ስደት ምክንያት ብዙ ሰዎች እጃቸውን እየሰጡ ወደ ግል ኑሮ መሠማራት ጀመሩ። የምሥራቁ ጦር ወደ በርበራ ሶማሌና ወደ ኬኒያ ተሰደደ። የሰሜኑም ተበታትኖ የሞተው ሞቶ የተረፈው ወደየትውልድ አገሩ ገባ። ንጉሠ ነገሥቱ ዋና የጦሩ አዛዥ ኾነው ውጊያውን እንደመምራት ራሳቸው ለመሄድ የተሸቀዳደሙበት

[15] ጥርስ የገባች አገር ኢትዮጵያ በጆን ሐዛወይ ስፔንሰር ገጽ 95-97



ሁኔታ ብዙ ጠላቶችን እንዲያፈሩበት አደረገ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንጉሡ እንዲህ ያለ ነገር አልጠበቀም ነበር። በጦሩ ውስጥ ዋና አቀንቃኝ ሆነው የነበሩት ራስ ካሣም አብረው መሄዳቸው የሚያስገርም ነበር። እነራስ ካሣና ራስ እደፍርሰው የውጭ አገር ትምሕርት ስላልነበራቸው ሽሽት እንጂ ለዲፕሎማሲው የሚያበረክቱት ጠቀሜታ አልነበራቸውም።

የማይችሉት ጠላት ሲመጣ ቢዋጉ ትርፉ ሞት ብቻ ውጤቱም ጎጂ ይሆን ነበር የሚሉም ቢኖሩ ያለው አከራካሪ ነጥብ ንጉሡ በቂ ውጊያ አላደረጉም የሚል ነው። በእሳቸው የተፋጠነ አካሄድ ምክንያት ሲዋጉ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ ቶሎ እጅ ሰጡ። ያልሰጡትም ቢሆኑ ተስፋ ስለቆረጡ አጥብቀው አልተዋጉም የሚል ቅሬታ በሕዝቡ ዘንድ ሰፍኗል። ሌላው በኢትዮጵያ የተለመደው ሁኔታ ንጉሡ አጥብቆ ተዋግቶ ይሞታል እንጂ ሸሽቶ አይሰወርም የሚል ነው። ስለኾነም መጀመሪያ የተቻላቸውን ያህል ተዋግተው ከዚያ በኋላ ሾልከው በስደት ቢሄዱ ያስመሰግናቸዋል እንጂ አያስወቅሳቸውም ነበር የሚል አስተያየትም አለ። አፄ ቴዎድሮስ ለክብራችን ራሳቸውን ማጥፋታቸው፣ አፄ ዮሐንስ በጦርነት መሠዋታቸው፣ አፄ ምኒልክ ጠላታቸውን ብትንትኑን ማውጣታቸው፣ የሚያኮራውን ያህል በአንጻሩ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መሰደድና የኮሎኔል መንግሥቱ መፈርጠጥ ለኢትዮጵያ ታሪክ እጅግ አሳፋሪ ነጥብ ነው። ይሁንና ለአገሪቱ አንድነት አስተባባሪ ሊሆን የቻለ አንድ ንጉሥ በሕይወት መኖሩ መጨረሻ ላይ ጠቅሟል። በሌላ በኩል ንጉሠ ነገሥቱ በጦርነቱ ላይ ሞተው ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በቅኝ ተገዥነትም ልትመደብ ትክል ነበር።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን የንጉሡ ወታደሮች ግራኝ አህመድ ኢብን ኢብራሒምን በጦርነት ማሸነፍ ባቃታቸው ጊዜ እያደቡ አደጋ በመጣል አዳክመው በመጨረሻ በተደረገው ጦርነት አሸነፉ። እንደሚባለው የጥሬ ሥጋ መብላት የተጀመረው ያዚያን ጊዜ ነው። ይኸም ጠላት ከርቀት ጭስ አይቶ መጥቶ እንዳያጠቃ የታረደውን ከብት ሥጋውን ሳይጠብሱ መብላት ስለጀመሩ ነው ይባላል። ስለዚህ የሽምቅ ጦርነት ኢትዮጵያ ውስጥ ድል ያስገኘ መሆኑን ከታሪክ የተገነዘበው የቻይናው አብዮት መሪ ማኦ ሴ ቱንግ እንኳን "እንደ ሃበሾች ተባበሩና ተዋጉ" ብሎ ወታደሮቹን ይመክር ነበር።



አራዳ ጊዮርጊስ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ በአንድነት ሲጸልይ

ሌላው ቀርቶ ጣሊያን አገር ታስረው የነበሩ ኢትዮጵያውያንን የኢጣሊያን ነፃ አውጭዎች እየፈለጉ ከእነሱ አንዳንድ ሁኔታን ይማሩ እንደነበረ እስረኞቹ አገራቸው ሲመለሱ ተናግረዋል። አብዲሳ አጋ የጣሊያን አርበኞችን እየመሩ ሮማ የገቡት አገራቸው ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ብዙ ታዋቂነት አላገኙም። ይኸም ብቻ ሳይሆን ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ እስረኞች ብዙ ነገር ተምረዋል። አዚናራ በምትባል ደሴት የታሰሩት ኢትዮጵያውያን ሥጋ ለመግዛት አቅም ስላልነበራቸው የሚገዙት ጣሊያኖቹ የማይበሉትንና ርካሽ የነበረውን ጨጓራ ነበር። ጣሊያኖች ጨጓራ የሚበላ መሆኑን ተመልክተው ስለነበረ አሁን ተለማምደውት ትሪፓ እያሉ ይበሉታል።





# ምዕራፍ ፲፱

# ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ዘመን

ሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ከጅቡቲ ወደ እሥራኤል አገር በመሄድ ኢየሩሣሌም አራት ሳምንት ከሰነበቱ በኋላ እቴጌንና በከፊል አጃቢዎቻቸውን ትተው እስከ ጅብራልታር ድረስ በብሪታንያ የጦር መርከብ፣ ከዚያም በንግድ መርከብ ኾነው ግንቦት 26 ቀን እንግሊዝ አገር ሳውዝ ሃምፕተን ወደብ ገቡ። እንግሊዝ አገር ሲደርሱ የብሪታኒያ መንግሥት አስቀድሞም ኢትዮጵያን ለጣሊያን መንግሥት አሳልፎ የሰጠ ስለነበረ አንድም የመንግሥት ባለሥልጣን እንዲቀበላቸው አላደረገም። የእንግሊዝ ሕዝብ ግን ከመርከብ ኾነ ከባቡር ሲወርዱ በእግርም ወዲያ ወዲህ ሲዘዋወሩ ሁሉ በጋለ ስሜት አቀባበል ያደርግላቸው ነበር።
ባዝ በሚባል ከተማ ፌርፊልድ መንገድ ዳር ንጉሠ ነገሥቱ አንድ ቤት ገዝተው የስደት ኑሮ ጀመሩ። ከዓመት በኋላ በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም በፈረንሳይ አገር አቋርጠው በባቡር ወደ ጄኔቭ ተጉዘው በሊግ ኦፍ ኔሽን ስብሰባ ላይ ተገኝተው ታሪካዊ ንግግር አደረጉ። ንግግራቸውን ሲጀምሩ ጣልያኖች በፉጨት አላሰማ ብለው በማወካቸው ከስብሰባው አዳራሽ ተባርረው ጃንሆይ ግን ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ተደረገ።

ፈረንጆች መጥቀስ አይፈልጉም እንጂ ጃንሆይ በንግግራቸው መካከል ታላቅ መልዕክት ሰንዝረው ነበር። እሱም "እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ኾነው ይመለከታሉ" ማለታቸው ነበር። ብዙ ሰዎች ይኸንን መልዕክት "አፍሪካ ላይ የተጫረው እሳት አውሮፓን ያነዳታል" ማለታቸው ነው ብለው ተረጉመውታል።



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በስደት እንግሊዝ አገር ሲገቡ

በተጨማሪ የአውሮፓ ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያን በመናቅ እንጂ እንደ እውነቱ ከኾነ ግን የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረው በጣልያንና በኢትዮጵያ መካከል በ1928 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት ሳቢያ ነበር። ይኽንንም አፍሪካዊው ደራሲ አሊ ኤ ማዝሩዊ ዘ አፍሪካንስ ኤ ትሪፕል ሄሪቴጅ በሚለው መጽሐፉ ገጽ 276 ላይ እንደሚከተለው ገልጾታል።



"Indeed, I and other African political scientists and African historians believe that the Second World War did not begin in 1939 following the violation of the territory of Czechoslovakia and Poland. It began in 1935 following the violation of Ethiopia's sovereignty by Mussolini's Italy."

"በእውነቱ፡ እኔና ሌሎች አፍሪካዊ የፖለቲካ ሳይንቲስቶችና የአፍሪካ ታሪክ ተመራማሪዎች የምናምነው የሁለተኛ የዓለም ጦርነት የተነሳው እ.ኤ.አ. በ1939 በቼኮዝሎቫኪያና ፖላንድ መወረር አለመሆኑን ነው። የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1935 ዓ.ም የኢትዮጵያ ልዕልና በሙሶሎኒ ጣልያን ሲጣስ ነው"



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጄኔቭ ንግግር ሲያደርጉ

እንግሊዞም ኾነ ፈረንሳይ ጣሊያንን ብዙ መነካከት ወደ ጀርመን ጓደኝነት ይገፋፉታል ብለው ስለፈሩና ራሳቸውም አስቀድመው ጣሊያን ኢትዮጵያን እንድትወር በስዌዝ ካናል በኩል መሣሪያዋንና ወታደሮችዋን እንድታሳልፍ ፈቅደው ስለነበረ ለኢትዮጵያ የጠቀመ ውሳኔ ሊገኝ አልተቻለም።

ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዝ አገር በሚኖሩበት ወቅት አመርቂ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ ብዙም ዕድል አልነበራቸውም። እሳቸውም መላ ጊዜያቸውን እንግሊዝ አገር ከመቀመጥ ይልቅ ወደ ካናዳ፣ ስዊድንና ወደ ሌላም አገር እየሄዱ እርዳታ መሰብሰብና የፖለቲካ ሰዎችን ማነጋገር መቻል ነበረባቸው። አንዱም ችግር በገንዘብ የሚገዙ ሰዎች አደጋ ሊያደርሱባቸው ይችላሉ ተብሎ ስለተገመተም ነበር። ለወጉ እንኳን በእንግሊዝ የንጉሣውያን ቤተሰብ አንድም ቀን ግብዣ ተደርጎላቸው አያውቅም ነበር። ለዚህም ምክንያቱ የብሪታኒያ መንግሥት በፊት በስውር ቀጥሎ ደግሞ በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም ኢትዮጵያ የጣልያን ግዛት መሆንዋን አምኖ መቀበሉን በይፋ ገልጾ ስለነበረ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ብሪታንያ የራሷ ጥቅም ባይነካ ኖሮ ጃንሆይ ምንም ነገር ሊያደርጉ አይችሉም ነበር። ይህም ሆኖ ጨዋነታቸውን ጠብቀው እንደማንኛውም ስደተኛ ኖሩ። በየጊዜውም ለአርበኞች መልዕክትና አዋጅ ያስተላልፉ ነበር። የጣሊያናዊ ባል የነበራቸው እንግሊዛዊቷ ሲልቪያ ፓንክረስት ከልጃቸው ጋር አገራቸው ተመልሰው ያዘጋጁት በነበረው "ኒው ታይምስ ኤንድ ኢትዮጵያን ኒውስ" በሚል ጋዜጣ ላይ በተለያየ ወቅት ጃንሆይ መግለጫ ሰጥተውበታል። የሲልቪያ ፓንክረስት ታላቅ እህት ናንሲ ፓንክረስት በንጉሥ ጆርጅ 5ኛ ጊዜ የታወቁ የሴቶች መብት ተከራካሪ ነበሩ። ሲልቪያ ፓንክረስት ከጣሊያናዊው ባለቤታቸው የወለዷቸው ሚስተር ሪቻርድ ፓንክረስት የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

በቢ.ቢ.ሲ. ራዲዮ ጣቢያ ጋባዥነት ጃንሆይ አንድ ቀን ኢትዮጵያን ለሚረዱ እንግሊዞች "እንኳን ለልደት በዓልና አዲስ ዓመት አደረሳችሁ" ለማለት በታክሲ ወደ ራዲዮ ጣቢያው ሲሄዱ የነበሩበት ታክሲ ተጋጭቶ ብራኳቸው ላይ መጠነኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ሃኪም ቤት እንውሰድዎት ብለው ሰዎች ቢጠይቋቸው በፊት ወደ ቢቢሲ ስቱዲዮ



ሄደው መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ስለመረጡ ይኸው ተፈጽሟል። ከዚያ በኋላ ሃኪም ቤት ተወስደው ታክመዋል።

በብሪታኒያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበሩት የቀድ ሕክምናው ዶክተር ሃኪም ወርቅነህ እሸቴ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሊጋሲዮኑ ገንዘብ ምክንያት ሳይግባቡ ቀርተው ነበር። መጨረሻ ላይም ሃኪም ውርቅነህ (ዶክተር ማርቲን) ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ በርማ ሥራ ፈልገው ሄዱ። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በጡረታ ኖረው በ1945 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። የልጅና የልጅ ልጆቻቸው ብዛት በአሁኑ ወቅት ከ52 በላይ ይሆናሉ።


ሃኪም ወርቅነህ እሸቴ (ዶክተር ማርቲን)

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ጥቂት ጊዜ እንደሠሩ እዚያው ሞተው ተቀበሩ። ኤምባሲው ውስጥ ገንዘብ እጥረት ስለተፈጠረ በጸሐፊነት ይሠሩ የነበሩት ወጣቱ አማኑኤል አብርሃም በኪስ ገንዘብ ብቻ ለመተዳደር በመቻላቸው እስከ መጨረሻው ቆዩ።

በዚህ መካከል አንድ ብርቱ የዲፕሎማቲክ ሰው በፈረንሳይ አገር ብቅ አለ። ይኸውም ወጣቱ አቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ሲሆን ፈረንሳይ አገር የነበረው የኢትዮጵያ አምባሳደር ስለከዳ የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪል ሆኖ በግል መኖሪያ ቤቱ ባንዲራውን ተክሎ የዲፕሎማቲክ ሥራውን ይሠራና ይታገል ጀመር። እንዲሁም ምሁሩ አቶ ሎሬንሶ ታእዛዝም ከጃንሆይ ጋር አብረው ከተሰደዱት መካከል የንጉሡን መልዕክት ወደ ኢትዮጵያ አርበኞች በማድረስ እየተላላኩ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ሠርተዋል።



የኢትዮጵያ ጦር በሱዳን ልምምድ ሲያደርግ

የብሪታኒያ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት ያሰለፈው ጦር መጠነኛ የእንግሊዝ መኰንኖችና ከተለያዩ ቅኝ ግዛቶቹ ወታደሮች በማምጣት ነበር። ስለሆነም የደቡብ አፍሪካ፣ የህንድ፣ የሱዳን፣ የናይጀሪያ፣ የጋና፣ የቤልጂግና የነፃይቱ ፈረንሳይ ወታደሮች ዘምተዋል። ጥርነቱ ከተገባደደ በኋላ የብሪታኒያ አንጻ ችግር እነዚህ ወታደሮች አንድ የጥቁር መንግሥት በነፃነት ሊኖር መቻሉን እንዳያጤኑትና አገራቸው በተመለሱ ጊዜ ለሕዝባቸው የጥቁር መንግሥት መኖር መቻሉን ዓይተው ወደየአገራቸው ሲመለሱ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉትን ሕዝቦች እንዳይቀሰቅሱባቸው ነበር። በተለይ ከካልካታ የመጡት የህንድ ወታደሮች የነፃነት ስሜት በፊቱንም አሳይተው ስለነበረ ያመጧቸው ከህንድ ለማራቅና እንቅስቃሴያቸውን ለማጨናገፍ መሆኑ የታወቀ ነበር። ሆኖም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በጐጃም በኩል የኢትዮጵያን ምድር ረግጠው አሜድላ ላይ ሰንደቅ ዓላማ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም ሰቀሉ። የዚህን ጊዜ ሰማዩ ላይ ቀስተ ዳመና በመታየቱ መልካም ዘመን መምጣቱን አበሠረ ተብሎ ተገመተ።





# ምዕራፍ ፳

## የጣሊያን ወረራ

ጣሊያኖች ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት አደረግን ብለው቞ ቢመጻደቁም ባኢትዮጵያውያን አመለካከት አገሪቱ ተወረረች እንጂ ቅኝ ተገዢ አልኾነችም። ይኸ ከኾነማ ፈረንሳይ በዚያኑ ወቅት የጀርመን ቅኝ ግዛት በሆነች ነበር፣ ዩጎዝላቪያና ግሪክም በዚያኑ ወቅት በጣሊያን ተወርረው ነበር። የኢትዮጵያን ንጉሥ አልማረኩ፣ አልገደሉ ወይም ሕዝቡ አሜን ብሎ ባልተገዛበት ሁኔታ ቅኝ ግዛት ሊባል ይችላል? ነገሩ ያልኾነ ሲሸነፍ ቅኝ፣ ነገሩ የኾነ ግን ሲሸነፍ ወረራ ከኾነ ይህ አስተሳሰብ ለነገሩ የሚያደላ ስለኾነ ፍትሐዊ አይሆንም።



ዘመናዊ ያልሆነው የኢትዮጵያ ጦር ወደ ማይጨው ሲዘምት

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላቶች እንግሊዝና ግብጽ እንጂ ጣሊያን አይደለችም። እንደማንኛውም ሌላ የአውሮፓ አገር ጣሊያንም ከአፍሪካ ቅርጫ ለመካፈል ስለጓጓች ሞኘነቷን የተገነዘበው እንግሊዝ ኢትዮጵያን ተወላት። እንግሊዝ ቀደም ብሎ ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በገጠመው አለመግባባት ወደ ኢትዮጵያ ዘምቶ ብዙ ሁኔታ ተመልክቶ በመጣ እግሩ ሳይዋረድ ተመልሷል። ምክንያቱም በየአካባቢው የነበሩት ባላባቶች እያንዳንዳቸው ከንጉሡ እጅግ የሚበልጥ ጦር ስለነበራቸው አገሪቱን ይዞ መቀመጥ እንደማይቻል ወዲያዉኑ ተረድቶት ነበር። ጣሊያን ግን ቀላል መስሏት ኢትዮጵያን ለመግዛት ብዙ ትግል አድርጋለች። ታዲያ "የሞኝ ብትር ሆድ ይቀትር" እንዲሉ በጦርነቱ ወቅት ያዘነበችው መርዝ ይቅርታ የማይደረግለት ጥቃት ስለነበረ ሌላው የዓለም ሕዝብም ኾነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቀላሉ ሊረሳው አይችልም።



የኢትዮጵያ ዘመናዊ ጦር ወደ ማይጨው ሲዘምት

ከጦርነቱ በኋላ ኢትዮጵያ በእኩል ደረጃ ባልነበረችበት ወቅት በድርድር የተደረሰበት የ25 ሚሊዮን ዶላር የካሣ ክፍያ በምንም መልኩ በቂ አልነበረም። ጣሊያን ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ለዩጎዝላቪያ



እንድትከፍል ሲበየንባት ለኢትዮጵያ 25 ሚሊዮን ዶላር (ብር 62.5 ሚሊዮን) ብቻ እንድትከፍል መወሰኑ ያስተዛዝባል። በድርድሩ ወቅት አራቱ ኃያላን መንግሥቶች የተሸናፊዋን የጣሊያንን መብት ሲያከብሩና የግሪክና የዩጎዝላቪያን ካሣ ከፍ ሲያደርጉ በጦርነቱ በግፍ የተደበደበችውንና በመርዝ ጢስ ሕዝቧ ያለቀውን የኢትዮጵያን ጉዳት ሳያገናዝቡት በአነስተኛ ካሣ ጉዳዩን ዘግተውታል።

በተለይ ጣሊያን ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቴ ነች ብላ ማስታወቋን ስህተት እንደነበረ አምና ይቅርታ መጠየቅና ለዓለምም ማስታወቅ ነበረባት። ፈረንሳይም ብትሆን ከጅቡቲ አዲስ አበባ በተዘረጋው ባቡር በጦርነት ጊዜም ቢሆን ኢትዮጵያ የመጠቀም መብቷ በውሉ ላይ ተጠቅሶ እያለ ጣሊያን ባቡሬን ይመታብኛል በማለት ከልክላለች። በጣሊያን ወረራ ወቅት ግን የጠላት ጦር እንደፈለገው ሲመላለስበት ዝም ብላ ትመለከት ነበር። ስምምነቱ ላይ በግልጽ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያን መብት ፈረንሳይ ከጣሰች ባቡሩ በኢትዮጵያ መንግሥት ይወረሳል ይላል። ስለኾነም ፈረንሳይ ስምምነቱን ያፈረሰች ስለኾነ ኢትዮጵያ ደግሞ ጉዳዩን ዝም ማለት አልነበረባትም።

ኢትዮጵያ በማይጨው ጦርነትና በወረራው ምክንያት የደረሰባት ጉዳት እንደሚከተለው ነው።

| | |
|---|---|
| የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት | 2,000 |
| የተቃጠሉ አይሮፕላኖች | 15 |
| የፈረሱ ቤቶች | 525,000 |
| የተገደሉ የሠራዊት ብዛት | 275,000 |
| የተገደሉ አርበኞች ብዛት | 75,000 |
| በየካቲት 12 ቀን1929 ዓ.ም የተገደሉ | 30,000 |
| በፍርድ ቤት በሞት የተቀጡ | 2,400 |
| በማጎሪያ ቤት የሞቱ | 25,000 |
| በችጋር እንዲያልቁ የተደረጉ ሰዎች | 30,000 |
| የሞቱ የቀንድ ከብቶች | 500,000 |
| የጋማ ከብቶች (ፈረስ አህያ በቅሎ) | 1,000,000 |
| ግመሎች | 789,060 |

በጠቅላላው በ746,800 ሰው ላይ የሞት አደጋ የደረሰ ሲሆን በአካለ ስንኩልነት በየቤቱ ምንያህል ሰው እንደተጎዳ አይታወቅም። ለጦርነቱ ማካሄጃ የባከነው ወጭ በቁሳቁስና በለው ጉልበት ሲተመን አያሌ ነው። በዝርፊያ የተወሰዱት የታሪክ ቅርሶችም አያሌ ናቸው። ለዚህ ሁሉ በደል በካሳ መልክ ኢትዮጵያ ያቀረበችው ኪሣራ 175 ሚሊዮን ስተርሊንግ ሲሆን የተሰጣት 25 ሚሊዮን ዶላር ሊሠራ የቻለው የቆቃን ግድብ ነው። ስለኾነም የወረራው ቀጥተኛ ተጎጂዎች በግል ያገኙት ዕርዳታ አልነበረም። በአንጻሩም ወራሪው መንግሥት አገሩን እኖርበታለሁ ብሎ በማሰብ መንገዶችንና ሌሎች የአገልግሎት ተቋሞች መሥራቱ ባይዘነጋም የጣሊያን ጦር ግን በሚሸሽበት ወቅት እንደገና አፈራርሶታል። ሊረዱ የመጡትም እንግሊዞች ቢሆኑ የተቻላቸውን ያህል ዘርፈዋል።



ጀኔራል ባዶሊዮ



በማንኛውም ችግር ላይ ኢትዮጵያ ስትወድቅ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ውሳኔ ኢትዮጵያን የሚያግዝ ሆኖ አያውቅም። ከእንግዲህም ወዲያ ከዓለም መንግሥታት በችግሯ ጊዜ ኢትዮጵያ ፍትሕ ታገኛለች ብሎ መጠበቅ ተላላነት ነው። ኢትዮጵያ ግን የዓለም መንግሥታትን ሕግና ደንብ ከማክበሯም በላይ ወታደሮቿን ኮርያ፣ ኮንጎ፣ ሩዋንዳና ቡሩንዲ ልካ በጀግንነት ተዋግታለች። ለዓለም መንግሥታት ማኅበራትም የሚጣልበትን መዋጮ በወቅቱ በመክፈል የሚወዳደራት የለም።



የኢትዮጵያ ወታደር በኮሪያ የተባበሩት መንግሥታት ዘመቻ ላይ

ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች አገር ጦርነት ገጥሞ ድል ስላገኘ ብቻ የእኔ ቅኝ ነች ብሎ ለዓለም ሕዝብ ቢያስታውቅም አንድም የተቀበለው የታሪክ ጸሐፊ አልተገኘም። በእርግጥም አንድን ነፃ አገር በጦርነት አሸንፎ ገብቶ መያዝ ወረራ እንጂ ሌላ አልነበረም።

ድንጋይ ዱቄት አርገው መንገድ የሚሠሩ
ጠብቅ ይመጣሉ ታዘበኝ ቢቀሩ

ሼህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፳፩

## የጣልያን ጊዜ

ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ባዶሊዮ በነጭ ፈረስ ተቀምጦ ጦሩን እየመራ አዲስ አበባ በገባ ዕለት በኢጣሊያን በኩል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን በኢትዮጵያ ላይ አከተመ። ንጉሠ ነገሥቱ በተቻኮለ መልኩ ሚያዝያ 23 ቀን ሌሊቱን በባቡር ሲጓዙ አድረው ሚያዝያ 25 ቀን ጅቡቲ ገብተው በመርከብ ከመኳንንቶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ እሥራኤል አገር አመሩ። ደጋፊዎቻቸው ለዓለም መንግሥታት አቤቱታ እንደሄዱ አድርገው ያቅርቡት እንጂ በተቃዋሚዎቻቸው ዘንድ እንደሸሹ ተቆጥሯል። ይህንን ሁኔታ በመገንዘብ ባላባቶችና የጦር አበጋዞች ሁሉ ለጠላት እጅ እየሰጡ ወደ እርሻቸውና ንግዳቸው ተመለሱ።



ኃይለ ማርያም ማሞ

ሆኖም የሕዝቡ መንፈስ ቢዳከምም አርበኝነቱ ግን ገና ጣሊያን ወደ አዲስ አበበ ለመግባት በሚጓዙበት ጊዜ ደብረ ሲና ላይ ባሻ ወልዴና ፊታውራሪ ተሰማ እርገጤ ከባለሟሎቻቸው ጋር በጠላት ጦር ላይ በጣሉት አደጋና ባደረሱት ጉዳት የደፈጣ ውጊያ ተጀመረ። አስከትሎም ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም ኃይለ ማርያም ማሞ ደብረ ብርሃን መንገድ ላይ ሰባት መኪና በማቃጠልና ወደ 140 የሚሆኑ



የጣሊያን ነጭ ወታደሮች በመፍጀት ትግሉ ተቀጣጠለ። ጣሊያን አዲስ አበባ ከገባም በኋላ የአርበኝነት እንቅስቃሴ ባይጠናከርም በየቦታው እያቆጠቆጠና እያደገ ሄደ።

የጣሊያንን ጦር እንዲያዘምት ተዘጋጅቶ የነበረው በወቅቱ ኤርትራን ያስተዳድር የነበረው ማርሻል ጄኔራል ደቦኖ በዕድሜ ገፋ ያለ፣ ጦረኛ ያልኾነ፣ ፖለቲከኛና የሰለላ ሹም የነበረ ስለኾነ ሙሶሎኒ ጦርነቱን እንዲመራ አላመነበትም። ስለኾነም የተዘጋጀውን የሰናፍጭ መርዝ በሕዝብ ላይ ለመርጨት ዝግጁ የነበሩት አረመኔዎቹ ጄኔራሎች ባዶልዮ በሰሜን፣ ግራዚያኒ በምሥራቅ ተመድበው የሙሶሎኒን ቅዠት ዕውን ለማድረግ ችለዋል።



አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒ የኢጣሊያን ንጉሥ ወንድ ልጅ መወለድን ምክንያት በማድረግ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ

የአዲስ አበባ ከተማን ነዋሪ ሰብስቦ ንግግር ሲያደርግ ቦንብ ተወርውሮበት ባይሞትም 365 ቦታ ላይ ቆሰለ። የዚህን ጊዜ ጣሊያኖች ለበቀል ባገኙት መሣሪያ በአካፋና በዶማም ጭምር ያገኙትን ኢትዮጵያዊ ጨፈጨፉት፣ ቤቱንም አቃጠሉት። በተለይ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮች የአዲስ አበባን ሕዝብ ሦስት ቀን ሙሉ ሲጨፈጭፉ ከርመው በግምት ወደ 30,000 ሰው ገደሉ።

ይህንን አደጋ የጠነሰሱት ሦስት ወጣቶች ሲሆኑ ሁለቱ ቦንብ እንዲወረውሩ አንዱ ግን መኪና አሰናድቶ ቦንብ ወርዋሪዎችን ይዞ ለመጥፋት ተዘጋጁ። በዚሁ መሠረት ግራዚያኒ ላይ ጉዳት ከአደረሱ በኋላ ተያይዘው የሸሹት ወደ ደብረ ሊባኖስ መሆኑ ተደርሶበት ፋሽስቶቹ እዚያው ድረስ ተከታትለው ሄደው ብዙ ቀሳውስት ሲፈጁ ሁለቱ ቦንብ ወርዋሪዎች ከአርበኞች ጋር ተደባለቁ። በኋላም ወደ ሱዳን ለማምለጥ ሲሞክሩ መንገድ ላይ ዘራፊዎች ገደሏቸው። ሦስተኛው ግን መኪናውን እየነዳ ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ በፊርማቶሪ (ሰላይ) ጠቋሚነት ተይዞ ስሲቃይ ቆይቶ ተገደለ።


ባለታክሲው ስምዖን አደፍርስ

ይህ ድርጊት በዓለም የዜና መገናኛ ሁሉ ስለተወሳ ለአቤቱታው ተሰሚነት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዲያውም ሃሳቡን የሰጡትና ያቀናጁት አቶ ሎሬንሶ ታዕዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አለመገዛቱንና ጣሊያንም ሠላም እንደሌለው የዓለም ሕዝብ እንዲገነዘበው ያደረጉት ጉዳይ መሆኑ ይነገራል። ፈንጂውንም የሰጧቸውና ግቢም እንዲገቡ የረዷቸው ደጃዝማች ለጥይበሉ ገብሬ ነበሩ። እነዚህ ሦስቱ ወጣቶች ቦንብ ወርዋሪዎቹ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ሲሆኑ ሦስተኛው በታሪክ ስሙ ሳይጠራ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኖረው ስምዖን አደፍርስ ነው። ምክንያቱም ይህ ወጣት ብዙ ታክሲ የነበረው ስለሆነ የእሱን ታክሲዎች



የነጠቁት ባንዳዎች ከነፃነት መልስ ባለሥልጣን ሆነው ስለነበረ የእሱ ስም መነሳት ምስጢራቸውን እንዳያጋልጥባቸው በመሥጋታቸው ነው[16]።

በሆለታ የጦር ትምሕርት ቤት ይማሩ የነበሩና ወጣትና ምሁር አገር ወዳዶች አምቦ (ሃገረ ሕይወት) ላይ ስብሰባ አድርገው አንድ የህቡዕ ማኅበር መሠረቱ። ለማኅበሩም ፕሬዚዳንት አድርገው ምሁሩን ልጅ ይልማ ደሬሳን ቢሾሙት ስለኦሮሞ ነፃነት ጉዳይ ሲያነሳ ስለዚህ ለመነጋገር ወቅቱ አይደለም በማለት ጭራሽ ከሥልጣኑ አንስተው ዶክተር ዓለመ ወርቅን ሾሙ። በኋላም ለማኅበሩ ስም ሲያወጡለት የይሁዳ አንበሳ የሚለውን ስም ቀይረው ጥቁር አንበሳ ብለውታል። በነበረው ውይይት ላይ ደጃች ታከለ ወልደ ሃዋርያት ተገኝተው የንጉሣዊ አገዛዝን በማጣጣል ስለ ሪፓብሊክ መንግሥት ምሥረታ እንነጋገር ቢሉ ይህ ጉዳይ በቆይታ እንዲያዝ ተወሰነ። በዚህን ጊዜ ታከለ ተለይተው ሲቀሩ ሌሎቹ ወደ ጎሬ ሄደው ማጥቃት ጀመሩና የጣሊያንን አይሮፕላኖች አቃጥለው ወታደሮችንም ገደሉ። በዚህ በጣሉት አደጋ ምክንያት ጎሬ ላይ ችግር ስላጋጠማቸው ራስ እምሩን አጅበው ወደ ጅማ ሲያመሩ ሲደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው በጣሊያኖች ተማረኩ። ሌሎቹ ደግሞ በየበኩላቸው ሲታገሉ ጥቃት ሲበዛባቸው ወደ ሱዳንና ወደ ኬንያ ተሰደዱ።


የጣሊያን ወታደሮች

የተማረኩት የጥቁር አንበሳ አባሎች መጨረሻ ላይ ምሕረት ተደርጎላቸው ሲኖሩ የእንአብርሐ ደቦጭ ቦንብ መጣል ባስከተለው ቂም አብዛኞዎቹ እንደገና ተሰብስበው ተገደሉ። አንዳንድ እጅ አንሰጥም ብለው የወላወሉ መኳንንቶችም ጥብቅ ክትትል ተደርጎባቸው እየታደኑ ተገደሉ። ሌሎች ደግሞ እየተደራደሩ እጅ የሰጡ በእስር ስለነበሩ የዚሁ

[16] ጦቢያ መጽሔት 8ኛ ዓመት ቁ 9

የአነ አብርሃ ደቦጭ የቦንብ ውርወራ ባስከተለው ቁጭት ተሰብስበው በእስር ወደ ጣሊያን አገር ተወሰዱ።

ጣሊያን በተቻለው ዘዴ ሁሉ ሕዝቡ በፍርሃት እንዲገዛለትና በአድዋ ጦርነት የተዋረደውን ለማካካስ ሲል ቂሙን መወጣት ጀመረ። የአድዋው ተወላጅ አውዓሎም የሚባል በስለላ ጣሊያኖችን በአድዋ ጦርነት ወቅት ከድቶ እንዲሸነፉ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ የታወቀ ስለነበረ፣ እሱን ምንም በሕይወት ባያገኙትም ተወላጆቹን እየፈለጉ በመፍጀት ቂማቸውን ተወጡ።



ጄኔራል ግራዚያኒ

የጣሊያን አስተዳደር ጭካኔ ስላበዛ በየአካባቢው አርበኞች እንደገና መንቀሳቀስ ጀመሩ። ኃይለ ማርያም ማሞ ሸዋ ውስጥ ተደራጅቶ እስከ አዲስ አበባ ድረስ እየገባ አደጋ ጥሎ ጣሊያኖችን አደናገጠ። እንዲሁም እነሻለቃ መስፍን፣ እነደጃች ባልቻ፣ ከተሰወሩበት መንቀሳቀስ ጀምረው በተለያየ ወቅት አደጋ ማድረስ ጀመሩ። እስከትሎም አዲስ አበባን ለመያዝ በእነአቡነ ጴጥሮስ ጎትጓችነት አርበኞች በአራት አቅጣጫ ገብተው አደጋ ለማድረግ ተስማምተው በሁለት አቅጣጫ ያሉት መግባት ሲጀምሩ በሌላው በኩል ያሉት በተባለው ወቅት በመገናኛ እጦትና በመወላወል ምክንያት በአንድነት ባለመግባታቸው ውጤቱ እልሰመረም። ይኸውም ደጃች ፍቅረ ማሪያም አባ ተጫን በየካ በኩል ገብተው ታላቁን ቤተ መንግሥት ለመያዝ ባዕታ ለ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ደርሰው ሌሎቹ በዕቅዱ መሠረት ስላልደረሱላቸውና ኃይል ስላነሳቸው ተመለሱ። ደጃች ባልቻም በአሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ በኩል አልፈው ነፋስ ስልክ ደርሰው የማይሆን ሲሆን ተመለሱ። በሰሜን በኩል የተሰለፉት ሁለቱ የራስ ካሣ ልጆች ደጃዝማች አበራ ካሣና ወንድ ወሰን ካሣ ደግሞ በራስ ሥዩም አግባቢነት እጃቸውን ለጣሊያን ሰጡ። የሞተው ሞቶ የሸሸው ሸሽቶ ውጥኑ ሳይሳካ በመቅረቱ የጣሊያንን አስተዳደር ይበልጥ አበረታው። አቡነ ጴጥሮስ ግን አልሸሽም ብለው አዲስ አበባ ቁጭ ካሉበት ቤታቸው ተይዘው "ለጣሊያን ተገዙ" ብለው ሕዝቡን እንዲሰብኩ ቢጠየቁ ጭራሽ "ለጣሊያን የተገዛህ ውጉዝ ሁን!" ብለው ስላሉ ፍርድ ቤት ቀርበው ተፈረደባቸውና በሞት ተቀጡ። ችሎቱን የመራው ጣሊያናዊ የመሃል ዳኛ ኮንቴ ዴ. ላ. ፖርቶ፣ የቀኝ ዳኛ፣ ብላታ አየለ ገብሬ፣ የግራ ዳኛ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ፣ አስተርጓሚዎች (ትርጁማኖች) ደጃዝማች አርአያ ዋሴና ፊታውራሪ ሮዛርዮ ነበሩ። የተሰየሙት ዳኞች አቡነ ጴጥሮስ ላይ በአንድ ድምጽ የሞት ፍርድ ፈርደውባቸው ሕዝብ ፊት በመትረየስ ተረሸኑ። አቡነ ጴጥሮስ በተረሸኑበት ዕለት መሣሪያ ለሽፍታ አቀብላችኋል ተብለው የተያዙ አራት ወንድና አንድ ሴት ከአፍንጮ በር እስር ቤት ተወስደው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበቴ ቤቱ አጠገብ ተሰቀሉ።





አስተርጓሚው ዘርዓይ ድረስ

ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጣሊያን ዋና ከተማ በሆነችው በሮማ ውስጥ በአስተርጓሚነት የሚሠራው ዘርዓይ ድረስ አንድ ቀን ከአንድ ታላቅ መኮንን ቤት ጎራዴ አምጣ ተብሎ ተላከ። በአጋጣሚ ጎራዴው እላዩ ላይ በተጻፈው ስም የራስ አሉላ የነበረ መሆኑን ተረዳ። ይህችን ጎራዴ ይዞ ሲመለስ ጣሊያኖች ከለገሃር ነቅለው ወስደውት የነበረውን የይሁዳ አንበሳ የተባለውን ሃውልት አስቀምጠው ሲሳለቁበት ዓይቶ ንዴቱ ግንፍል ይልበትና በአካባቢው ያለውን ሰው ሁሉ በያዘው ጎራዴ አስፈራራ። ከዚያም ሐውልቱ ላይ ወጥቶ ይቆምና "እናንተ ጣሊያኖች ነፃነታችሁን ካገኛችሁ ገና ጥቂት ጊዜ በመሆኑ ስለነፃነት የምታውቁት ነገር አንድም ስለሌለ ነውራችሁ እዚህ በምታደርጉት ተገልጿል" እያለ ሲናገር አንድ ወታደር ተኩሶ እግሩን

አቁስሎ ያዘው። ከዚያም ዕብድ ነው ብለው የአእምሮ ህመምተኞች ሆስፒታል አስገቡት። ዘርዓይ ድረስ የፈጠረው ሁኔታ ጣሊያኖችን ስላስቆጣቸው በንዴት ጣሊያን አገር ከነበሩት እስረኞች 147 ያህሉን ወደ አዚናራ የእስር ደሴት ሲወስዱ ሌሎቹን ደግሞ ሰብስበው ወደ ሞቃድሾ አመጧቸው። ከነፃነት በኋላ ዘርዓይ ድረስ ወደ አገሩ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ተወስኖ ሊመጣ ሲል ከትባት ነው ብለው በመርፌ መርዝ አድርገውበት ገደሉት። በኋላም ለስሙ ማስታወሻ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ ዘርዓይ ድረስ ተብላ ተሰየመች።



የኢትዮጵያ ካርታ በጣልያን ጊዜ

የጣሊያን መንግሥት በመጀመሪያ ድል አድርጎ የገባውን ባዶሊዮን፣ ከእሱም ቀጥሎ በጥቂት ቀን ውስጥ ግራዚያኒን ጠቅላይ ገዥ በማድረግ ኢትዮጵያን፣ ኤርትራንና የጣሊያን ሱማሌን በአንድነት የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት በማለት ስድስት ክፍለ አገሮች ፈጥሮ ማስተዳደር ጀመረ። ከነዚህ ስድስት ክፍለ አገሮች ውስጥ አዲስ አበባና አካባቢዋ



አንዷ ነበረች። የቅኝ ግዛት ቢሮውም አዲስ አበባ ዋናው ፖስታ ቤት ፊት ለፊት የሚገኙት ሁለት ፎቅ ቤቶች ሲሆኑ የሙሶሎኒ ጽሕፈት ቤት ይባሉ ነበሩ። በኋላም እነዚሁ ፎቅ ቤቶች የፍትህና የአገር ግዛት ሚኒስቴር በመባል ይታወቁ ነበር።

አርበኞች በተቻላቸው መጠን ተጋድሎ ቢያደርጉም እጅ ሰጥተው የገቡ መኳንንቶች ግን ደሞዝ ተቆርጦላቸው ለጣሊያን ገብረው ይቀመጡ ነበር። በተለይ ራስ ኃይሉ በውስጣቸው የባንዳ ወታደር ስለ ነበራቸውና እሳቸውም አልገብርም ያለውን መኳንንት በማግባባት ብዙ አገልግሎት ለጣሊያን ሰጥተዋል።

የቄሣር መንግሥት የወር ደሞዝ ይከፍላቸው የነበሩት የሚከተሉት ናቸው

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ | ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት | 40,874 ሊሬ በወር |
| 2ኛ | ደጃ. ኃይለሥላሴ ጉግሣ | 25,000 ሊሬ በወር |
| 3ኛ | ሼክ ኤል ሆጀሌ | 25,000 ሊሬ በወር |
| 4ኛ | ራስ ሥዩም መንገሻ | 22,900 ሊሬ በወር |
| 5ኛ | ደጃ አያሌው ብሩ | 16,000 ሊሬ በወር |
| 6ኛ | ሡልጣን ሙሐመድ ሃንፋሬ | 15,000 ሊሬ በወር |
| 7ኛ | ደጃ. ሆማና ጆቴ | 15,000 ሊሬ በወር |
| 8ኛ | ደጃ. ዮሐንስ ጆቴ | 15,000 ሊሬ በወር |
| 9ኛ | ሡልጣን አብዱላሂ አባ ጂፋር | 8,000 ሊሬ በወር |
| 10ኛ | ሡልጣን አባ ጆቢር አብዱላሂ | 8,000 ሊሬ በወር |
| 11ኛ | ራስ ጌታቸው አባተ | 7,000 ሊሬ በወር |
| 12ኛ | ደጃ. ታየ ጉልላቴ | 1,000 ሊሬ በወር |

ከወር ደሞዝ በተጨማሪ የሜዳሊያ ሽልማትና ጉብኝት ተችረዋል።

1ኛ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት የኢጣሊያ ኮከብ ሜዳሊያ
2ኛ ለሡልጣን አባ ጆቢር የአረብ አገሮች ጉብኝት
3ኛ ለደጃ. አያሌው ብሩ የኢጣሊያ ኮከብ ሜዳሊያ

በዘመኑ እጅ ሰጥተው የገቡና የቄሣር መንግሥት ሠራተኛ የነበሩ በርካታ ሰዎች እንደነበሩ ዕሙን ነው። በጋዜጠኛነት በአስተርጓሚነት በአስተዳደር ጽሕፈት ቤት ሥራ ተሰማርተው የነበሩና ደሞዝ ያገኙ ከነበሩት ታዋቂ ሰዎች መካከል ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው።

በአንጻሩም የቪክቶር አማኑኤል ወኪል ዱካ ዳውስታ ሙሶሎኒን "አርበኞችን በፍቅር ብናስጠጋቸው ይሻላል" ብሎ አሳምኖ አዲስ አስተዳደር ጀምሮ ነበር። በዚሁ መሠረት ጣሊያን ከአርበኞች ጋር መደራደር፣ ገንዘብ መስጠትና ከበሬታ መስጠት ስለጀመረች፣ በባንዳነት ከጣሊያን ጋር ከሚሠሩት ይልቅ አሁን አርበኞቹ ገበርዲን እየለበሱ ከነሱ በበለጠ ክብር ይታዩ ጀመር። በዚህን ጊዜ አንዳንድ ባንዳዎች አርበኝነት የሚያስከብር መሆኑን ሲመለከቱ ወደ አርበኝነቱም የተቀላቀሉ ነበሩ።

በዚህ ሁኔታ ላይ ጣሊያን ከጀርመን ጋር ስላበረች እንግሊዝና ፈረንሳይ መልሰው ለጣሊያን ጠላት መሆናቸውን አርበኞች ሲሰሙ ተስፋ ማግኘት ጀመሩና ፍልሚያው ተባባሰ። አስከትሎም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሱዳን መምጣታቸው ሲሰማ አርበኛው እየበዛ ሄደ። የእንግሊዝ ዕርዳታ፣ የጃንሆይ በሱዳን በኩል መግባት መስማት ሲጀምር ጣሊያኖች መበታተኑን ትተው በየትልልቅ ካምፖች ኃይላቸውን እያደራጁ መቀመጥ ጀመሩ። በአንጻሩም አርበኞቹ እንደልባቸው መገናኘትና በኅብረትም የጣሊያንን ካምፖች እያጠቁ ማሸነፍም ማባረርም ቻሉ። በጠቅላላው ድሉ ወደ ኢትዮጵያ ሰለዞረ የጣሊያን ወታደር ወዲያው ተሸነፈ። የጣሊያኖችን ተግባቢነት በመመልከት መጨረሻ ላይ የጣሊያን ወታደር ተሸንፎ እጁን ኒሰጥ ኢትዮጵያውያን ጭካኔ አላሳዩዋቸውም።

በነበረው ግብግብ ብዙ አርበኞች ቢሞቱም በየአካባቢው ተርፈው ዝና ካተረፉና ከነጻነት በኋላም በጣም ታዋቂ ከነበሩት መካከል በጣም ስማቸው የገነነ ቢኖርም በአርበኝነት ብዙ ጀግንነት የሠሩና ያልታወቁ ስላሉ በጠቅላላው የተዋጋው ሁኔታ ያመቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለኾነ ታሪኩ የጥቂት ሰዎች ብቻ አለመሆኑ ዕሙን ነው።

አንድ ሕብረተ ሰብ ከሌላ ሕብረተ ሰብ ጋር አብሮ መኖር ሲጀምር ብዙ የሚለዋወጠው የኑሮ ሁኔታ ይኖራል። ለምሳሌ ቱርኮች መካከለኛ ምሥራቅን ሲያስተዳድሩ ብዙ ዓይነት የአመጋገብ ስልት አስተምረው ሄደዋል። ከነዚሁም ተርኪሽ ኮፊ፣ ሸዋርማ፣ የሚባሉት ሁሉ የቱርኮች የባህል አመጋገብ ውጤቶች ናቸው። በኦስትርያ በሚኖሩበትም ወቅት ጥለውት የሄዱት ባህል አልፎ ተርፎ አውሮፓንም አጥለቅልቋል። ዛሬ ፈረንሳዮች የሚወዱት ክሯሳ የሚባለው ብስኩት ቱርኮች በጨረቃ ተምሳሌት ለቁርስ የሚጋግሩት ብስኩት ነው።



በኢትዮጵያም ውስጥ ሕዝቡ ከጣሊያኖች የአመጋገብ ልምድ እንደ ፓስታና ማኮሮኒ ያሉትን መጀመሪያ ቢጠየፈውም እየለመደው ሄደ። ሻይ መጠጣትና ፉርኖ ወይም ፓኔ የሚባልም የዳቦ ዓይነት መብላት ተለመደ። ጣሊያኖችም አይናገሩት እንጂ ፒዛ የሚባለውን ምግብ ለመሥራትና ለዓለም ለማስተዋወቅ የቻሉት እንደቂጣ፣ አነባበሮና አምባሻ ከመሳሰሉት የኢትዮጵያውያንን የዳቦ አሠራር ተመልክተው ይመስላል። ይኸንንም የምልበት ምክንያት ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በፊት ፒዛ የሚባል ምግብ በጣሊያኖች የማይታወቅ ስለነበረና ጣሊያኖች የምግብ አሠራርን በብዛት ከውጭ ስለሚወስዱ ነው። እነሱ ለዓለም ያስለመዱት ምግብ ጀላቲ ወይም አይስ ክሪም የሚባለውን ብቻ ሲሆን፣ ጣሊያኖች ፓስታ የሚሉትን መደበኛ ምግባቸውን ማርኮ ፖሎ ወደ ቻይና በተጓዘ ጊዜ ቻይናዎች የሚሠሩትን ኑደልስ ዓይቶ አገሩ ሲመለስ ስላስለመዳቸው ነው።



# ምዕራፍ ፳፪

# የድል ጉዞ ወደ አገር ቤት

አዛዥ ከበደ ተሰማ የጃንሆይን መምጣት ለአርበኞች እያበሠሩና መንገድ እየጠረጉ በጎንደር አድርገው ወደ ጐጃም ገቡ። በየመንገዱ የገጠማቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ሪፖርት እያደረጉና ሊደረግ የሚገባውን እየጠቆሙ ወደ መሃል ዘለቁ። አስፈላጊ ሲሆንም ትናንሹን ጉዳይ ራሳቸው ውሳኔ እየሰጡበት የተቃረኑትን አርበኞች እያስማሙና እያስታረቁ ጥሩ ሥራ ሠሩ። አብሯቸው ይጓዝ የነበረው የእንግሊዝ ኮሎኔል ሳንድፎርድ ሁሉም ነገር ከሱ ቁጥጥር ውጭ መሆኑ ስላላስደሰተው ጣልቃ ሊገባ ፈልጎ ቢሞክርም የተወሳሰበ ስለኾነ ሊገባው ባለመቻሉ እንዲሁም ለአዛዥ ከበደ የሚሰጠውን ክብር ሊያገኝ ስላልቻለ መጨረሻ ላይ ዝምታን መርጧል።

ንጉሠ ነገሥቱ በአሜድላ አድርገው ወደ ጐጃም ተጉዘው ደብረ ማርቆስ ሚያዝያ 22 ቀን 1933 ዓ.ም ገቡ። ጎንደርን ትተው በጐጃም መምጣትን የመረጡት የጎንደር አርበኞች እነ ደጃች ታከለ ወልደ ሃዋርያትና ሌሎችም "የሸሸ ንጉሥ አይነግሥም ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም" ብለው ተቃውሞ አሳይተው ስለነበረ ነው። ነገር ግን እንደነ ነጋሽ በዛብህ፣ ኃይሉ በለው፣ መንገሻ ጀምበሬና አሞራው ውብነህ ያሉት ንጉሡን ይደግፉ ስለነበረ ጐጃም ድረስ ሄደው ተቀብለዋቸዋል።

እንግሊዞች በጎንደር አድርገው ወደ ኤርትራ ተሸቀዳድመው ገቡ። ከደቡብ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር በሐረር በኩል ተንደርድሮ አዲስ አበባ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ገብቶ በላይኛው ግቢ የብሪታኒያን ባንዲራ (ዩኒየን ጃክ) በታችኛው ግቢ ደግሞ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውለበለበ። በዚሁ ዕለት ማታ በፊት ለፈረንጆች ብቻ በተወሰነው ጊያሳ ባለው ትሪያኖን ሆቴል ቤት ኢትዮጵያውያን የጣሊያንን ድል



መሆን በመመልከት በደስታ ተንጋግተው መግባት ሲጀምሩ የነበሩት አሳላፊዎች አንታዘዝም በማለታቸው አለመግባባት ተፈጠረ።



ጃንሆይ አሜድላ ላይ ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ

በዚህ ምክንያት እንግሊዞች ትጥቃቸውን ካልፈቱ ጣሊያኖች ጋር በመወገን በአካባቢው ባገኙት ኢትዮጵያዊ ላይ ሁሉ መተኮስ ጀምረው የቆሰለው ቀስሎ 150 ሰው ተገደለ። ይህም ስለሆነ ብዙ ሰው ቅር ብሎት የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት በጉጉት መጠበቅ ጀመረ። ተንጉሠ ነገሥቱ ግን ጣሊያን አዲስ አበባ የገባበትን ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ጠብቀው በክብር አዲስ አበባ ገቡ። የደርግ መንግሥት ግን የጃንሆይን ታሪክ ለማሳነስ ሲል እንግሊዞች አዲስ አበባ የገቡበትን ቀን እንደ ነፃነት በዓል ለ17 ዓመት ሲያከብር ቆየ። ኢትዮጵያዊ መሪ በቦታው ሳይኖር የውጭ ኃይል ሥልጣኑን እያዘዘበት ባለ ሁኔታ ላይ የነፃነት ቀን መባሉ ትክክል አይመስልም ነበር።

በርካታዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ ካዛንቺስ አካባቢ የሚገኙ ሲሆን በኋላ በችሮታ ከተሰጡት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

<u>የንጉሣውያን ቤተ ሰብና መሳፍንት</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | ራስ እሥራት ካሣ | ስደተኛ ተማሪ |
| 2ኛ) | ራስ ገ/ሕይወት ሚካኤል | የእ/መነን አጎት |
| 3ኛ) | ልጅ ደስታ ብርሃነ መስቀል | የራስ ካሣ የልጅ ልጅ |
| 4ኛ) | ልጅ አርአያ አበበ | የጃንሆይ ዘመድ |
| 5ኛ) | ኮሎኔል አበበ ወልደ ሥላሴ | የጃንሆይ የክርስትና ልጅ |

<u>በንጉሡ የተቸሩ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | አቶ በለጠ ገብረ ጻድቅ | ስደተኛ |
| 2ኛ) | አባ ማርቆስ ኢጋጅየለው | ስደተኛ ካህን |
| 3ኛ) | አቶ መንበረ ያየህ ይራድ | ስደተኛ |
| 4ኛ) | አቶ ገብረ አብ ቢያድግልኝ | |
| 5ኛ) | ወ/ሮ ፈለቀች | ስደተኛ |
| 6ኛ) | አቡነ ዮሐንስ | ባንዳ |
| 7ኛ) | አቶ አበበ ረታ | ስደተኛ |
| 8ኛ) | አቡነ አብርሃም | ባንዳ |
| 9ኛ) | ጀኔራል ኃኘው ከበደ | |
| 10ኛ) | አቶ አባተ | |
| 11ኛ) | ብላታ ዘውዴ በላይነህ | ስደተኛ |
| 12ኛ) | ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ | ዲፕሎማት |
| 13ኛ) | ቢትወደድ አስፍሃ ወልደ ሚካኤል | የጣሊያን አስተርጓሚ |
| 14ኛ) | አቶ አካለ ወርቅ ሃብተወልድ | ስደተኛ |

<u>ለኤርትራውያኖች የተሰጠ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | አቶ ዓውአሎም ፈካክ | |
| 2ኛ) | አቶ ዘካርያስ | |
| 3ኛ) | ደጃች ተድላ ባይሩ | |
| 4ኛ) | ራስ ኃይለ መለኮት | |
| 5ኛ) | ብ/ጌታ ኤፍሬም ተ/መድህን | ስደተኛ |
| 6ኛ) | ጀኔራል ያዕቆብ ገ/ልዑል | ስደተኛ |
| 7ኛ) | ጀኔራል ኢያሱ መንገሻ | ስደተኛ |
| 8ኛ) | አፈ ንጉሥ ሐጎስ | |
| 9ኛ) | አቶ ጳውሎስ ብርሃኔ | |
| 10ኛ) | አቶ ጴጥሮስ ጎይቶም | |

<u>በአርበኛነትና በመሳሰሉት ለአገር ውለታ የሠሩ</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | ወ/ሮ ቆንጂት | የራስ አበበ ባለቤት እስረኛ |
| 2ኛ) | ብ/ ጀኔራል ኃ/ማርያም ግዛው | ስደተኛ |
| 3ኛ) | ራስ እምሩ ኃ/ሥላሴ | አርበኛ/እስረኛ |



| | | |
|---|---|---|
| 4ኛ) | ደጃዝማች አሉላ በቀለ | አርበኛ |
| 5ኛ) | ደጃዘማች አልማው | አርበኛ |
| 6ኛ) | ልጅ ዳንኤል አበበ | እስረኛ |
| 7ኛ) | ደጃዝማች ገብረ ኪሮስ | አርበኛ |

<u>እንዲሁም በላይ ዘለቀ መንገድ (ሦስተኛ ፖሊስ ጣቢያ) አካባቢ የጣሊያን ፖለቲካ ቢሮ ጽሕፈት ቤቶችን</u>

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ) | ደጃች መኮንን ደስታ | ስደተኛ |
| 2ኛ) | ወ/ሮ ሙሉወርቅ ባንት ይርጉ | |

የተቀሩት ለኤርትራውያኖች ቢሰጡም መጨረሻ ላይ ግን ምትክ ቦታ እየተሰጣቸው ቤቶቹ ተመልሰው ለመንግሥት መሥሪያ ቤትነት ውለዋል።

በተጨማሪም ባንኮ ዲ ናፖሊ የነበረበት ፎቅ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በአጠገቡ ያለው ፎቅ ለደጃዝማች ከበደ ተሰማ ተሰጥቶ ነበር። ይህ ፎቅ አሁን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሃይጅንና የፋርማሲ መምሪያዎች ሆኗል። ኢትዮጵያ ሆቴል አጠገብ የአንበሳ ቡና ቤት ያለበት ፎቅ የልዑል ማህለ ሥላሴ ነበር።

ሊሎችም የታወቁትን ቤቶች ለመግለጽ ያህል የመከላከያ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጣሊያን ሠርቶት በሆቴልነት ሲያገለግል ከኖረ በኋላ ለልዕልት ተናኘ ወርቅ ተሰጥቶ መንግሥት ኪራይ እየከፈላቸው ይገለገልበት ነበር። ልዕልት ተናኘ ወርቅ ብዙ ንብረት የተሰጣቸው ስለነበሩ በጣም ባለጸጋ ሆነው እንደነበር ይታወቃል። አልፈው ተርፈው ወንዶ ገነት የተባለውን የሽርሽር ቦታ ልዕልት ተናኘ ስለወደዱት ጃንሆይን ጠይቀው ሚስተር ማታኖቪች ከሚባሉ በስደት ከምስራቅ አውሮፓ መጥተው በኢትዮጵያዊነት ከሚኖሩ ግለሰብ ተወሰዶ ተሰጣቸው። ለሚስተር ማታኖቪች በምትክ የተሰጣቸውንም ቦታ ደርግ ስለወረሰባቸው እኚኸ ሰው አንድ ዓይና ስለነበሩ በአንድ ዓይናቸው አለቀሱ ይባላል። ሚስተር ማታኖቪች ኢንጂኔር ስለነበሩ የቀይ ባሕርን ከሩዶልፍ ባሕር ጋር በማገናኘት መርከብ እንዲሄድበት ለማድረግና 300 ግድብ በመሥራት አገሪቱን ከችግር ለማውጣት ዕቅድ አውጥተው በጃንሆይና በደርግ ዘመን የሚሰማቸው አጥተው ነገሩ ትኩረት ሳያገኝ ቀረ።

አርበኞች ግን ያገኙት ነገር ኢምንት ሲሆን እንዲያውም ከራስ አበበ አረጋይ ወታደሮች በከፊል ወደ ሸዋ ሮቢትና ወደ አርሲ ተልከው የእርሻ መሬት አከፋፍለዋቸው እያሰ በወባ በሽታ (በንዳድ) አለቁ። ጥቂት አርበኞች በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ በየባለገሩ በምስለኔነት፣ በወረዳና በአውራጃ ገዥነት እየተሾሙ ተበታተኑ። ብዙዎቹም በማዕረግ ስምና በሜዳሊያ ብቻ ተሸንግለዋል። የሚያሳዝነው የሴት አርበኞች ጥቂቶች ብቻ ሜዳሊያ ሲያገኙ የማዕረግ ስም እንኳን አለማግኘታቸው ነው። ወ/ሮ ከበደች ሥዩምና ወ/ሮ ቀለመ ወርቅ ጥሩነህ በአርበኞቹ የደጃዝማችነት ማዕረግ ቢለገሱም በመንግሥት ስለአልጸደቀላቸው በማዕረጉ አልተጠሩበትም። ስለሆነም አንድም ደጃዝማች ወይም ፊታውራሪ ወይም ቀኝ አዝማች የምትባል ሴት አርበኛ አልነበረችም። ይሁንና አርበኞች ለከፈሉት መስዋዕትነት የሚገባቸውን ወሮታ እንዳላገኙና እንደተጎዱ ስለቀሩ ክፉኛ አማረሩ። የአርበኞቹን ቅሬታ ለመግለጽ ዮፍታሄ ንጉሤ የሚከተለውን ተቀኙ።

“አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ
የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ”

አንድ ሰው አገሩ ስትወረር መዋጋት ግዴታው ነው። የሚዋጋውም በገንዘብ ወይም በንብረት ለመካስ ስላልኾነ ከነፃነት በኋላ አስተከፈለኝም ብሎ መናደድ ተገቢ አይደለም። ሆኖም የጠላት ንብረት ለግለሰቦች ከታደለ ቅድሚያ ለአርበኞች መስጠት ፍትሃዊ ይሆን ነበር።

## የብሪታንያ ጣልቃ ገብነት

ብሪታንያ ኤርትራንና ኦጋዴንን ከመያዝ በተጨማሪም በቅኝ ግዛቶቻቸው ጠረፍ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ አገር እየቆረሱ ወሰን ማስፋት ጀመሩ። በገለብ በኩል የተወሰደው መሬት ኢትዮጵያን ከሩዶልፍ ሃይቅ ተጠቃሚነት አግልሏታል። እስከ አሁንም ድረስ ቦታው በኬንያ ውስጥ እንደተከለለ ነው። በዚህም ምክንያት የገለብ ሕዝብ አኩርፎ ንጉሠ ነገሥቱ ስጉብኝት በሄዱ ጊዜ በባላባታቸው በፊታውራሪ ነመርሙስ



ከስክስ አማካይነት “ምነው አገራችንን ቆርሰህ ሰጠህ? አሁንስ የቱን ልትሰጥ ነው የመጣኸው?” ብሎ ጃንሆይን አሳፍሮ መልሷቸዋል።



የብሪታንያ (እንግሊዝ) ወታደሮች

አፄ ምኒልክ በገለብ በኩል ናስማስር (ውጅግራ) ጠብመንጃ ከጋሻ ጋር አድርገው በሲሚንቶ የቀበሩት የድንበር ምልክት ኬንያ ውስጥ 40 ኪሎ ሜትር ያህል ገብቶ ይገኛል። ስለኾነም የገለብ ሰዎች አሁን ዘመን ድረስ እንደመሪያቸው የሚቆጥሩት ምኒልክን እንጂ ሌላ መሪ አያውቁም። በዚህም የተነሳ አሁን ድረስ ሲምሉ ‘ምኒልክ ይሙት!’ ይላሉ። አንድ ወቅት የገለብ ባላባት ፊታውራሪ ነመርሙስ ከስክስ የእንግሊዝ አይሮፕላን ወሰን አልፋ ስትበር ተመልክተው በአንድ አልቤን ጥይት መተው ጥለዋት ኃይሉን ከማረኩት በኋላ በምሕረት ለቀውት ወደ ኬንያ እንደተመለሰ ይታወቃል።

በሞያሌ በኩል አሁን በከፊል ኬንያ ውስጥ የኾነው የአየር ማረፊያ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ እንደነበረ ይነገራል። ከዚህም ሌላ በወሰኑ አካባቢ የነበሩ ጠቃሚ የሆኑ ቦታዎች በብሪታንያ ተወስደው አሁን በኬንያ ግዛት ውስጥ ተጠቃልለዋል። በፊት የአካባቢው ሰዎች ፊታቸውን የሚቀቡት የተለየ አፈር ያለበት አንድ ተራራ አሁን ኬንያ ውስጥ ስለተከለለ የአካባቢው ሰዎች ያንን አፈር ከኬንያ እየገዙ መጠቀም ተገደዋል። በፊት ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የቱርጋና ጎሣ በወሰን መገፋት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ለሦስት ተከፍሎ የኢትዮጵያ

ቱርጋና፣ የኬንያ ቱርጋናና የሱዳን ቱርጋና ተብለው ይጠራሉ። እንደዚሁ ሁሉ በሱዳን በኩል መሬት ከኢትዮጵያ በየምክንያቱ እየተወሰደ በአሁኑ ወቅት በምሥራቅ ሱዳን ወሰን አካባቢ የአማርኛ፣ የኦሮምኛና የትግርኛ ተናጋሪ ሕዝብና የቦታ ስም ይገኛል።

በተደጋጋሚ ሱዳኖች (ደርቡሽ) ከአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ በውስጥ ችግር ስትጠመድ የወሰን ጭቅጭቅ እየፈጠሩ እንደምንም ብለው መሬት ለማግኘት ይሞክራሉ። በ1952 ዓ.ም ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰው የጋምቤላ አውራጃ ምትክ በስሜን የሚገኘውን የሰቲት ሁመራ አካባቢ ለሱዳን እንዲሰጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲመክሩበት ሲደረግ ሃሳቡ ገና እንደተነሳ የጎንደር ተወካይ ሽጉጡን አወጥቶ ማን ነው መሬታችንን ቆርሶ ለባዕድ የሚሰጠው ብሎ ተቆጣ። በዚሁ ምክንያት ጉዳዩን ንጉሡ ነገሥቱ እንዲቆይ አደረጉት። እንደ እውነቱ ከኾነ ከሰላ የምትባለው ከተማና የሁመራ መሬት በጠቅላላው ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ እንደነበረና እንግሊዝ ወስዶት አፄ ዮሐንስ ለማስመለስ ቢሞክሩም አልቻሉም።

የንጉሡ ነገሥቱን መምጣት ሰምተው ከጣሊያን እየከዱ ወደ ሱዳን የመጡትን ኢትዮጵያውያን እንግሊዞች በማሰር ሰብአዊ ርህራሄ በሌለው መልኩ ያጉላሏቸው ነበር። ከጣሊያኖች ጋር ሆነው የተማረኩትንና ንጉሡን ፍለጋ ከድተው በመጡት ወታደሮች መካከል ምንም ልዩነት አይደረግም ነበር። የኢጣሊያን ምርኮኞች ግን በተኻለ እንክብካቤ ይያዛሉ። እንዲያውም ጣሊያኖቹን ሥልጣን እየሰጡ አስተዳደር ላይ ሲያስቀምጧቸው ከኢትዮጵያውያን ጋር በሚፈጠር አለመግባባት ተደማጭነት የነበራቸው እነሱ ሆነው ተገኙ። አንድ ጊዜ ጣሊያኖቹ እንግሊዞቹ ፊት ሰባት ኢትዮጵያውያንን በጥይት ሲገድሉ ምንም አልተደረጉም። በዚህ ቅሬታ ሱዳን ውስጥ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያንና የብሪታንያ ባንዲራ ይዘው ሠላማዊ ሰልፍ በካርቱምና በሌሎችም ከተሞች ስላደረጉ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤት እንዲበረበር ተደርጎ የግል ንብረታቸውን በወታደሮች ተዘርፈዋል[17]።

[17] ያቺ ቀን ተረሳች ከሕይወት ጎዳና



በኬኒያ የነበሩትን የኢትዮጵያ ስደተኞች እንግሊዞች እያሰሩ መንገድ ያሠሯቸው ነበር። በኋላም አገራቸውን ነፃ ለማውጣት ሲሰበሰቡ እንግሊዞች በየወሰናቸው ላይ ጣሊያኖች እያጠቁ መሬት መያዝ ጀምረው ነበርና መጀመሪያ የእንግሊዝን ጦርነት ኢትዮጵያውያን እንዲዋጉላቸው አድርገው ካጠናቀቁ በኋላ አብረዋቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲዘምቱ አድርገዋል። በጠቅላላው ስንመለከተው እንግሊዞች ሊረዱን ይሁን ከጣሊያኖች ተረክበው ሊገዙን የመጡበት አኳኋን ግልጽ አልነበረም።

ጣሊያኖች ከተሸነፉ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ብሪታንያ በየቦታው የፖለቲካ መኮንኖች በመሾምና በጦርነት ወቅት ምክትል አስተዳዳሪ የነበሩት ብርጋድዬር ላሽ ጃንሆይን ቢሮአቸው ድረስ እንዲመጡ እንደማዘዝም ሞክረው ነበር። እንረዳለን ብለው የመጡት እንግሊዞች የኢትዮጵያን መንግሥት ምሥረታ ዕውቅና ላለመስጠት የጠላት ይዞታ አስተዳደር (Enemy Occupied Territory) በማለት እየጠሩ ራሳቸው አስተዳደሩን ሊያዙበት ፈልገው ነበር። ከቃላቶቹ እንደምንረዳው የመጡት እኛን ለመርዳት ሳይሆን ጣሊያን በወቅቱ የእነሱ ጠላት ስለነበረ እሱን በኢትዮጵያ ምድር ለመውጋት ነበር።

ከዚህም በላይ የተሾሙት የብሪታንያ ኦፊሰሮች ንብረት መዝረፍን ትልቅ ዓላማ አድርገው ይዘውት ስለነበረ በተለይ የማርትሬዛ ብርና ወርቅ ሲገኝ ለመውሰድ ይታገሉ ነበር። በተጨማሪም አዲስ አበባ ውስጥ የግሪክ ዝርያ ያላቸውን ሰብስበው አንድ "የዘበኛ ኃይል" የሚባል ጓድ ፈጥረው በየሰው ቤት በኃይል እየገቡ የጠላት ንብረት ነው በማለት የቤት ዕቃ ይወስዱ ነበር [18]። ይሁንና በየቦታው በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ኃላፊነት የተሰጣቸው ሹሞች የተቻላቸውን ያህል ተከላክለው አድነዋል።

ከታሪክ ማኅደር እንደምንረዳው ትልቁ አሌክሳንደር ንግሥት ሕንደኬ ሦስተኛን ሊያገባ ድርድር ጀምሮ ጋብቻው ሳይሳካ ሞተ። በዚህ ምክንያት ተፈጥሮ በነበረው መግባባት ግሪኮች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ መልክ በብዛት አክሱም ላይ ተንሰራፍተው ነበር። በአክሱም ቤተ መንግሥትም የግሪክ ቋንቋ ተለምዶ ነበር።

[18] ያቺ ቀን ተረሳች ከሕይወት ጎዳና



ጃንሆይ ከእንግሊዝ የጦር መኮንኖች ጋር

ራስ ተፈሪ መኮንን በአልጋ ወራሽነት በ1916 ዓ.ም ኢየሩሣሌምን በመጎብኘት ላይ እያሉ "ግሪኮች በጎልጎታ ውስጥ ብዙ ክፍል ቦታ አሏቸው ማለትን ስለሰማን ከዚሁ አንድ ክፍል ለኢትዮጵያ መነኮሳት መቀደሻ ርስት አድርገው እንዲሰጡልን አዲስ አበባ በሚኖረው በግሪክ ቆንሲል ጄኔራል በዶክተር ዘርቦስ በኩል በኢየሩሣሌም ያሉትን የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ አቡነ ድምያኖስን ብንጠይቅ የአብርሐም ገዳም ከሚባለው አንድ ክፍል ርስት አድርገን እንሰጣለን ስላሉ እኛም በበኩላችን ለግሪክ ገዳም ጥቅም የሚሆን ቦታ ኢትዮጵያ ላይ እንሰጣለን ብለን በሃሳቡ ተስማምተንና ተዋደን ቀጥሎ ያለውን ውል ተጻጽፈን ተፈራረምን…ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሳይሆን ቀርቶ ይህ ውል ወደ ፍጻሜ አልደረሰም" የሚለው በሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ገጽ 64 እስከ 66 ላይ ይገኛል። በዚህ ባልጸደቀው ውል መሠረት ለግሪክ መነኮሳቶች ሳይሆን አገር



ውስጥ ለገቡ ግሪኮች ሁሉ አዲስ አበባ ከራስ መኮንን ድልድይ አንስቶ በአርበኞች መንገድ እስከ ገፈርሳ ድረስ መሬት እየተሰጣቸው የበረዶ፣ አረቄና የሻክላ ፋብሪካዎች እየከፈቱ ሃብታም መሆን ጀመሩ። ቀጥሎም በአምቦ መስመር ነቀምትና አልፎም ደምቢ ዶሎ ድረስ መሬት ተመርተው መኖር ጀመሩ። እነሱም ተስፋፍተው ኢሉባቦር፣ ጋምቤላ፣ አሶሳና ቤኒ ሻንጉል ድረስ ገቡ።

ግሪኮች በማይጨው ጦረነት ላይ ቀደም ብሎ ለጣሊያን በስላይነት፣ በወረራውም ወቅት እንደገና ተንሰራፍተው በመነገድ፣ እንግሊዝም ሲገባ እሱ ባቋቋመው የዘበኛ ኃይል ውስጥ በመሰለፍ በዘረፋ ተሰማርተዋል። ከጦርነቱ በፊትም ሆነ በኋላ ደርግ ንብረታቸውን እስከውረሰባቸው ጊዜ ድረስ ንግዱን በመቆጣጠር ነጋዴዎች በመሆን በሠላም ኖረዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ከኢትዮጵያ ወጥተው ሄደው ጣሊያን አገር እንደገና ሹመታቸውን እንዲያጸድቅላቸው ደጅ ጥናት ላይ ነበሩ። በመጨረሻ ስላልተሳካላቸው አገራቸው ግብጽ ሄደው ተቀመጡ። ጦርነቱ ሲያልቅ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ግን ኩባዊው ኮሎኔል አልኸንድሮ ዴል ባዬ ከራስ ሙሉጌታ ጋር ዘምቷል። ስዊድናዊው ካርል ጉስታቭ ቮን ሮዝን መጥተው በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ሥር አባ ቃኘው የሚባል የቀይ መስቀል ፎከር አይሮፕላን ተረክበው ቁስለኞች በማመላለስ አገልግሎት አበርክተዋል። ከወረራው በኋላም የኢትዮጵያን አየር ኃይል አቋቁመዋል። በደርግ ዘመነ መንግሥትም አገራቸው ስዊድን እያሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ረሃብ ሲገባ ተመልሰው መጥተው ዕርዳታ ላይ ተሠማርተው ጎዴ ውስጥ ከመቶ አለቃ ዳዊት ኃይለ አብና የስዊድኑ ፓይለት ሚስተር ክርስቲያን ክርስትንሰን ጋር በአይሮፕላን አደጋ ጎዴ ውስጥ ሞቱ።

የሩሲያው ንጉሥ ዳግማዊ ኒኮላስ እ.ኤ.አ. በ1917 ተገድሎ ሥልጣኑን ኮሚኒስቶች ሲረከቡ የአርመን ዜጎች በዓለም ተበተኑ። ኢትዮጵያ ውስጥም ብዙ አርመኖች መጥተው አገሬ ነው ብለው ተቀመጡ። የኢትዮጵያ መንግሥትም ከእንግሊዝ ኤምባሲ አንስቶ እስከ ራስ መኮንን ድልድይ ድረስ ግራና ቀኙን መሬት መርቷቸው በንግድ ሥራ ተሠማርተው ይኖሩ ነበር። ከቀን ብዛት ብዙዎቹም አማርኛ

አቀላጥፈው መናገር በመቻላቸው በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የታወቁ ከበርቴዎች ሆነው ነበር። የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን፣ ትምሕርት ቤትና የስፖርት ክበብ አቋቁመው ይኖሩ ጀመር። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ አርመኖቹና ሌሎችም በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ሕንዶች፣ ፓኪስታኖችና እሥራኤሎች ንብረታቸውን በደርግ መውረስ ሳቢያ ወደ ሌሎች አገሮች ተሰደዱ።

በዙዎች የውጭ አገር ሰዎች ከኢትዮጵያዊ ሴቶች ልጅ ይወለዱ እንጂ ሴቶቻቸው ግን ኢትዮጵያዊ ባል አያገቡም ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎች ከአርመኖች፣ ከሕንዶች፣ ከግሪኮችና ከአረቦች መካከል ለኢትዮጵያ ነፃነት የታገለ አልተገኘም። ዶክተር ጂ. ዳሲዮስ የሚባለው ግሪካዊ ግን በዓለም ቀይ መስቀል አባል በመሆን ከስዊድኖች ጋር በመምጣቱ ዶክተር ነኝ ብሎ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ከጦርነቱም በኋላ በዚሁ ሙያ ሲኖር የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር የነበሩት ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ በአገር ውስጥ ያሉትን የነጭ ህክምና ዶክተሮች ማስረጃ ሲያስመረምሩ እሱም ሆነ ከሌሎቹ ነጮች መካከል ብዙዎቹ ዶክተር ሆነው አልተገኙም።

በተጨማሪም እንግሊዞች የጣላትን (የጣሊያንን) ንብረት መዝረፍ ብቻ ሳይሆን ነባር የኢትዮጵያን ንብረቶችንም እየነቀሉ መውሰድ ሲጀምሩ ከአርበኞች ጋር በተፈጠረው ጠብ እስከ ጦር መማዘዝ ተደርሶ ነበር። የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን መሣሪያዎች ነቅለው ሊወስዱ ሲሉ አርበኞች ራስ መኮንን ድልድይ ሥር መሣሪያ ጠምደው በማድፈጥ አስጥለዋቸዋል። ዘረፋው የግል መኪናዎችንና ሊንቀሳቀስ የሚችልን ብረታ ብረት ሁምር ያካተተ ነበር። ይባስ ብሎ አዲስ አበባ ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ጣሊያኖች በሙሉ መኪናቸውን እያሽከረከሩ ጃንሜዳ እንዲሰበሰቡ ካደረጉ በኋላ ቁልፉን መኪናው ላይ እየተው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አዝዘው መኪናውን ወደ ኬንያና አልፎም እስከ ደቡብ አፍሪካ ድረስ አግዘውታል። ሊወስዱት ያልቻሉትን መኪናና ብረታ ብረት ኢትዮጵያ እንዳትጠቀምበት በባሕር ውስጥ ጨምረዋል። በየቦታው ባሉ ሃይቆችና ኩሬዎች በተለይ በአዋ ወንዝና በቢሾፍቱ ሃይቅ ውስጥ የከተቱት በርካታ ያለ መኪናና ብረታ ብረት አሁንም እንደሚገኝ ይታመናል።



በኤርትራ ውስጥ ያደረጉት ዘረፋና ውድመት ደግሞ በጣም የከፋ ነበር። አሁን የኵምድሩማን ሬዲዮ ጣቢያ ከኤርትራ ነቅለው የወሰዱት ሲሆን በምሥራቅ አፍሪቃ በጣም ትልቁና ዘመናዊው ዳቦ መጋገሪያ ከምጽዋ ተነቅሎ ተወስዷል። ከምጽዋ አሥመራ የተዘረጋው የዕቃ ማመላለሻ ቴሌፌሪክ የሽቦ መስመር ወላልቆ ሲወሰድ የቀረውም እንዳይሠራ ተበጣጥሷል። ሊወስዱ ያልቻሉትን ብረታ ብረት ቀይ ባሕር ውስጥ ጨምረውታል። ተንሳፋፊ የመርከብ መውረጃና መውጫ ከኤርትራ ወደብ ተነቅሎ ወደ ኤደን ተወስዷል። በአስገራሚ ሁኔታ በብረታ ብረት ብቻ ሳይወሰኑ በአይሮፕላን እያሳደዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የዱር አራዊቶች ወደ ኬኒያ ነድተዋቸዋል።

በወቅቱ በነገሩ ያልተከፋ ሰው አልነበረም። በብሪታኒያ ዘረፋና አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ መግባትን የጠሉ አርበኞች የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት አይደለንም እንዋጋለን ብለው መሣሪያቸውን መወልወል ስለጀመሩ ከድል መልስ ከአንድ ዓመት በኋላ ነገሩ ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ ንጉሠ ነገሥቱ አስግቷቸው በሬዲዮ ለሕዝቡ ንግግር በማድረጋቸው ውጥረቱ በረደ። ከዚህም ደባ ለመከላከል ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዞች ሳያውቁ በድንገት ማልታ ሄደው ከአሜሪካን ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት ጋር መክረው እንግሊዞች እንዲወጡና በምትካቸው አሜሪካኖች እንዲገቡ አደረጉ። ለማንኛውም እንግሊዞች እስከ 1937 ዓ.ም ድረስ ጣልቃ መግባታቸውን አላቆሙም ነበር።

ለአራት ዓመት ያህል የብሪታንያ አምባሳደር ልክ እንደ አገረ ገዥ ከሌሎች አምባሳደሮች በላይ ሆኖ ይታይ ነበር። ዳኞች፣ የባንክ ሠራተኞችና ወታደር አሠልጣኞች እንግሊዞች ሆኑ። ፖሊስና የጸጥታ ሠራተኞች በእነሱ ቁጥጥር ስር ዋሉ። መኪና ቀደም ብሎ በቀኝ በኩል ይነዳ የነበረው በግራ በኩል ኾነ። የውጭ አገር ትምህርት የሚሰጠው አስቀድሞ በፈረንሳይኛ የነበረው ሙሉ በሙሉ እንግሊዝኛ ኾነ። በትምህርቱ መካከል የእንግሊዝ ታሪክ በከፍተኛ ደረጃ ይሰጥ ነበር።

በተጨማሪም ጀኔራል ዊንጌት የሚባለውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በማቋቋም ከየትምህርት ቤቱ በራሳቸው መመዘኛ ተማሪዎችን እየሰበሰቡና ነፃ የትምህርት ዕድል እየሰጡ ለወደፊት አገሪቱን የሚመሩትን የእንግሊዝ አፍቃሪ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት በዘመኑ ስውር ደባ ሲሠሩ ኖረዋል። ስለኾነም ብዙዎቹ ተማሪዎቻቸው የመንግሥት

ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በመሆንና የሚኒስትርነትና የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ቦታዎች ለመያዝ ችለዋል። ነገር ግን በትምህርት ቤቱ ከተማሩት መካከል አገር ወዳዱ ስለበዛ ዓላማቸው እጅግም አልተዋጣለትም። ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ድግሞ ትምህርት ቤቱ ለኮሌጅ ያበቃቸው ተማሪዎች ከኮሌጁ በመጀመሪያው ዓመት ከሚባረሩት መካከል በአማካይ ቁጥራቸው ይበልጥ ነበር። ይህ የሚያሳየው ትምህርት ቤቱ ተማሪዎቹን በቋንቋ፣ በብሪትሽ ታሪክና ሥነልቦና መቅረጽ እንጂ ዕውቀትን በማስተላለፍ በኩል ጥረት የማያደርግ መሆኑን ነው። አንዳንድ ግብዞች በዚያ ትምህርት ቤት ስለተማሩ ብቻ ራሳቸውን እንደተለዩ ብልህ ሰዎች በማድረግ የሚኩራሩበት አልታጡም።

እንግሊዞች አገሪቱን ለመከፋፈል ባይሆንላቸውም ኤርትራንና ኦጋዴንን እንደያዙ ቀሩ። ኤርትራ ከአፄ ዮሐንስ ሞት ጀምሮ የባልያን ቅኝ ግዛት ስለነበረች ከእናት አገሯ ጋር እንዳትቀላቀል ኢትዮጵያን ልንረዳ መጣን ያሉት እንግሊዞች ተሽቀዳድመው ኤርትራን ለይተው ማስተዳደር ጀመሩ። ኦጋዴን ግን የጉልበት ነገር ሆኖ እንጂ የኢትዮጵያ አካል ስለነበረች ከመቆየት በስተቀር ምንም ሕጋዊ መብት ስላልነበራቸው እስከ 1947 ዓ.ም ድረስ ወታደራቸውን አስቀምጠው ቆዩ።

ይኸም እንደውለታ ተቆጥሮ አዲስ አበባ ውስጥ በእንግሊዝ መኮንኖች፣ በመሣፍንቱና በወቅቱ በነበረው ጠቅላይ ሚኒስትር ስም የተሰየሙ ብዙ የመታሰቢያ መንገዶች አሁን ድረስ እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህም ቸርችል፣ ካኒንግሃም፣ ስመትስ፣ ኤደን፣ ኪንግ ጆርጅ፣ ንግሥት ኤልሳቤጥ፣ ወዘተ.. የሚባሉት ጎዳናዎች ናቸው። የኢትዮጵያ አርበኞች ላደረጉት ተጋድሎ የተሰየሙላቸው መንገዶች ቢኖሩም ሰዋራና ትናንሾች ስለሆኑ ሕዝቡ የሚያስታውሰው ስም የራስ አበበን መንገድና በደርግ ጊዜ የተሰየመውን የበላይ ዘለቀን መንገድ ብቻ ነው። በእንግሊዞቹ ስም የተሰየሙት መንገዶች በዚያው ስም መቅረታቸውን እንደ ጨዋነት የሚቆጥሩት አልታጡም። እነሱ ግን ብሪስቶል ኢንግላንድ ውስጥ የኢትዮጵያ መንገድ በሚል ስያሜ የተለጠፈውን ናዚ ጀርመን በቦንብ ካፈራረሰው በኋላ ያንን ስም መልሰው መንገዱ ላይ ለመለጠፍ ስለ አልፈለጉ ሙዚየም ውስጥ አስቀምጠውታል።



# ምዕራፍ ፳፬

## አዲስ ዘመን

ንጉሠ ነገሥቱ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከስደት መልስ አዲስ አበባ ሲገቡ ባደረጉት ንግግር መጪው ዘመን አዲስ ዘመን መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበሥረው ነበር። ኢትዮጵያም አዲስ በተቋቋመው የዓለም መንግሥታት መሥራች አባል አገሮች ውስጥ አንዷ ኾነች። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደገና በአዲስ መልክ ሲዋቀሩ ሌሎች አዳዲስ ተቋሞች እንደየአስፈላጊነታቸው ተቋቋሙ። በ1936 ዓ.ም አዲስ ገንዘብ በንጉሠ ነገሥቱ ምስልና በይሁዳ አንበሳ ቅርጽ ተዘጋጅቶ በዓመቱ ሥራ ላይ ዋለ።

እንደ ክብር ዘበኛ፣ የጦር ሠራዊት፣ የአየር ኃይል የወታደር ማሠልጠኛዎችን፣ ፖሊስ፣ ፊናንስ፣ የአየር መንገድ የመሳሰሉ ተቋሞችን አደራጁ። ከኤርትራ መዋሃድ በኋላም የባሕር ኃይል ተመሠረተ። በተለይ ከትምሕርት ቀጥሎ አንዱ ከፍተኛውና ሊመሰገኑበት የሚገባ ሥራ የአየር መንገድንና የንግድ መርከብን በቀለጠፈና በዘመናዊ ሁኔታ መመሥረታቸው ነበር። ሆስፒታሎችም በቂ ባይሆኑም በዘመናዊ መልክ ተሠሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ለአዲስ ሥራዎች መሠረት መጣል፣ የተጠናቀቁትን መመረቅ፣ አንዱና ትልቁ ሥራቸው ኾነ። አዳዲስ ሚኒስትሮች በየመሥሪያ ቤቶቻቸው ሥራቸውን ማቀላጠፍ ቢጀምሩም የአገሪቱንና የሕዝቡን ችግር በዘላቂነት የሚፈታ ነገር ሊሠራ ግን አልተቻለም። በእርሻ በኩል ሠርቶ ማሳያና ማሠልጠኛዎች ቢቋቋሙም የመሬት ይዞታው ላይ መሻሻል ስላልተደረገ ለውጡ አልታይ አለ።



የኢትዮጵያ የባሕር ኃይል መኮንኖች

እንደዚሁም ከአዲሱ ዘመን አስተዳዳሪዎች መካከል ከፊሎቹ ራሳቸው ዘራፊ እየሆኑ ገበሬውን ማስቆጣት ጀመሩ። አንዳንድ አገረ ገዥዎች ደግሞ ጥንት የቀረውን አሳሽ የሚባሉ ሹሞች በየአውራጃው እየሾሙ አልዘረፍ ያለውን በራሳቸው ሥልጣን ማጉላላት ጀመሩ። በአርበኝነት ወይም በስደት ያልተሰማራውንና ልጆቹን ላሳድግ ብሎ የተገኘውን ሥራ እየሠራ የኖረውን ሕዝብ ሁሉ እንደ ባንዳ በመቁጠር ርስቱን መንቀል፣ እምቢ ካለም ማንገላታት ጀመሩ። ትንሽ ቆየት ብሎ በኃላፊነት ሥልጣን ላይ ያሉትም ሰዎች የሃብት ማጋበስ በሽታ እየተጠናወታቸው ስለሄደ በሚሾሙበት ቦታ ሁሉ ዘመዶቻቸውን እያስቀመጡ የመንግሥትን ገቢ ለራሳቸው ማስቀረት ጀመሩ። መታያና ጉቦ በመጠየቅም ከሕግ ውጭ ፈቃድ ö ቆጠት ወይም መከልከል አንዱ መጥፎ አሠራራቸው ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ በሚቋቋሙ ኩባንያዎች ያለምንም ክፍያ አክስዮን ካልሰጠኸኝ ፈቃድ አልሰጥም እስከማለት ደርሰው አገር ውስጥ ሊቋቋሙ የሚችሉ ፋብሪካዎች ወደ ጎረቤት አገር እንዲሸሹ አደረጉ። በገጠርም ለም የእርሻ መሬቶችን ባለሥልጣኖች መሻማት ጀምረው ወሰን



ትገፋሁ፣ ርስቴን ተነጠቅሁ፣ የሚለው አቤት ባይ እየተበራከተ ሄደ። በተለይ እንደ ጅማና አርሲ ባሉ ጠቅላይ ግዛቶች የመሬት ሽሚያው ዓይን ያወጣ ዘረፋ እየሆነ በመሄዱ ሕዝብና መንግሥት ሆድና ጀርባ እየሆኑ ሄዱ። በተለይ በአርሲ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነባር ደኖች ለየሚኒስትሮች ስለተከፋፈሉ ዛፉን እየቆረጡ በመሸጥ ባለሃብት ሲሆኑ የአገሪቱን ደን አራቆቱ።

ሌላው አከራካሪ ነጥብ የጠላት ንብረት ሁኔታ ነበር። ይህንን ንብረት እንዲመዘግብና እንዲቆጣጠር የተቋቋመው መሥሪያ ቤት ቀጥታ በጃንሆይ ቤተ ርስት በሚሰጥ ትዕዛዝ በመመራት፣ አስተዳደሩ መልክ ያልያዘ ነበር። በቦታ አደላደልም ላይ አሠራሩ በዘፈቀደና ውስ በማይታወቅ መልኩ ከመሆኑም በላይ ሲያስፈልግም የግለሰብ ንብረት በትንሽ ጥፋት ይወረስ ነበር።

አፄ ምኒልክ የግል መሬት እንዲይዙ ተብለው ሲመከሩ “መላው ኢትዮጵያ የማን ሆነና እኔ በግሌ መሬት እይዛለሁ?” ብለው በመመለሳቸው በምኒልክ ስም የተያዘ አንድም መሬት አልነበረም። የእናታቸውን የዘር ርስት ወራሽ ቢሆኑም ገበሬው እያረሰ ሲኖር በግብር ምክንያት ከምስለኔው ጋር ተጋጩ ተው ጉዳዩ አፄ ምኒልክ ዘንድ ሲቀርብ “ፈጣሪዬ የመላ ኢትዮጵያ አባት ስለአደረገኝ እሱም ከልጆቼ አንዱ ስለሆነ በስሙ ሊገብር ይችላል” ብለው መረቁለት። እንዲያውም እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ የነበሩት ንጉሦች የግል መሬት የሚባል አልነበራቸውም። ነገር ግን ቦታዎች ለየመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ይደለደሉ ነበር። በአዲሱ ዘመን ግን ብዙዎቹ ለግል ሰዎች በግዴለሽነት በመሰጠታቸው የዞታው ቀንሷል። ለምሳሌ የቤተ መንግሥት ከብት የሚደልብበት የወረገኑ መሬት እንዶዴ የሚባል ቦታ አሁን ቦሌ ተብሎ የሚጠራው ላይ ነበር። መሬቱም ባለቤትነቱ በራስ አሥራተ ካሣ ስም ዞሮ እሳቸውም ሸጠው ተጠቅመውበታል።

እላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች በትግራይ፣ በጎጃምና በባሌ ሽፍትነት ተጀምሮ ወታደር ጸጥታ ለማስከበር ሲላክ ባላገሩን እስቆጥቶ ይመለስ ጀመር። ከነዚህም ሌላ በጃንሆይ መሰደድ ያማረሩና ቂም የያዙ ሰዎች ንጉሡን ለመገልበጥ ማሤር ጀመሩ። እነሱም ዓላማቸው ሳይሳካ እየቀረ ተይዘው እየተፈረደባቸው ይታሠሩና ይጉላሉ ጀመር።

ይኸ ሁሉ ሲሆን በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የጸጥታ ጥበቃ ሥራ ላይና የንጉሠ ነገሥቱን ዝና በማስተጋባት ፍጹም የኾነ አስተዳደር እንደነበረ ይሰብኩና ያሳምኑ ጀመር። አድር ባዮችም የንጉሡን ዝና በማራገብ ተጠቃሚ ለመሆን ሲሉ ሕዝቡን ግራ አጋብተውታል። ምሁሮች ምንም ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት አላቋረጡም። የፖሊሱና የጸጥታ ሠራተኛው በሙሉ አገሪቱን ሳይሆን የሚጠብቀው መሪውን ብቻ ስለኾነ ብዙ ሰዎች ተጎዱ። ፖሊስ ወገኑን ደብድብ! ግደል! ሲሉት ሳያንገራግር በያዘው መሣሪያ ሁሉ መቀጥቀጥ ልምዱ አደረገው። አንዳንዴ የፖሊሱ ኃይል ሲያንስ ወታደርም እየተደረበ ትዕዛዝ እስከተሰጠው ድረስ ወገኑን ማሰቃየት ግዴታን እንደመፈጸም ይቆጥረው ጀመር። አንዳንድ አገሮች ወታደሩ በራሱ ሕዝብ ላይ እንዳይዘምትና የዴሞክራሲ መብቱ ላይ ባልቃ እንዳይገባ ሕገ መንግሥታቸው ይከለክላል።

አንዳንድ ሹሞች ምንም ቢሠሩ የማይመሰገኑና በጥፋት ጊዜ ግን የሚወቀሱ ነበሩ። በዚህ የተነሳ በሕዝቡ ዘንድ 'ንጉሠ ነገሥቱ ምንም ጥፋት ቢያደርጉም ጥፋተኞቹ ሚኒስትሮቹ ናቸው' እየተባለ በሰፊው ይነገር ነበር። ከሚኒስትሮችም ሌላ የታወቁ እንደ አባ ሃና ያሉ ሹማምንት ነበሩ። አባ ሃና ጂማ የጃንሆይን የግል ንብረት ከመቆጣጠር በተጨማሪ የንጉሠ ነገሥቱን ደህንነት ለመጠበቅ የራሳቸው የስለላ ድርጅትም አቋቋመው እንደነበረ ይታወቃል። ለዚህም አገልግሎታቸው የመንግሥት ፕሮቶኮል ከሚያውቃቸው ብዙ ባለሥልጣኖች ይበልጥ ይከበሩና ይፈሩ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና ሲቋቋም ባሊያን መሥርቷቸው የሄደውንም፣ በራሳቸው በእንግሊዞችም ዕርዳታ የተቋቋሙት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ዘመናዊ የኾነ አሠራርን ጀምረው ሕዝቡ ተስፋ አድርጎና በተገኘው ድልም ረክቶ ንጉሠ ነገሥቱን እያመሰገነ መኖር ጀመረ። አገሪቱን ሌሎች አገሮች የደረሱበት የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሚችለው ተባብሮ መሥራቱን ቢያያዘውም መንግሥቱን የሚመሩት ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ የራሳቸው የኾነ ችግር ስለነበረባቸው በተፈለገው የሥልጣኔ እርምጃ ለመግፋት አልተቻለም። ጃንሆይን የከበቧቸው ባለሥልጣኖችም አብዛኞዎቹ ስደተኞችና ባንዳዎች በመሆናቸው በአርበኞች ይተቹ ስለነበረ ደስተኛ አልነበሩም።



ጃንሆይ በፊትም የልጅ ኢያሱን ሥልጣን አወሳሰዳቸውና በኋላም የስደት አካሄዳቸው ስላልተወደደላቸው መልሰው ሥልጣናቸውን ለማጠናከር ቀደም ብለው የሰጡትን መብት መንፈግ ጀምረው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በክብር ዘበኛ፣ ልዩ ካቢኔ፣ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሥር ፖሊስና ብዙ ግለሰቦችም ለስለላ እየተመለመሉ ተሰማሩ። እንዲያውም ጃንሆይ ደህና የጀመሩትን የሥልጣኔ ጎዳና ሕዝቡ በንቃት እንዳይገፋበት ራሳቸው መልሰው መግታት ጀመሩ። የንግግር ነጻነትን እንደማደፋፈር ጃንሆይን ሰድበሃል እየተባሉ ሰዎች በአደባባይ ይገረፉም ጀመር። ስለ ጃንሆይ ጥሩ መናገር እንጂ በመጥፎ ስማቸውን ማንሳት የሚያስፈራበት ወቅት መጣ። ስለኾነም ንጉሡን የሚተች ኢትዮጵያን እንደከዳ እየተቆጠረ ሁሉም ሆዱ እያወቀ ለመኖር ሲል ብቻ በመፈራራትና በመተማማት ኑሮውን ቀጠለ። በዚህም ምክንያት አገሪቱ በሥልጣኔና በምጣኔ ኃብት ወደ ኋላ እየቀረችና የተወሳሰቡ ችግሮች ውስጥ እየገባች ሄደች። ብዙ ተቋሞች ጥራት ባለው አደረጃጀት ይመሥረቱ እንጂ መስፋፋት ግን አልቻሉም። የቀለጠፈ አሠራር ዘርግተው ቢያካሂዱም ጠቀም ያለ አገሪቱን ከድህነት ሊያወጣ የሚችል የጎላ ዕድገት አልታየም። ምክንያቱም መንግሥት ገንዘብ ስላልነበረው ነው ቢባልም ይኸ ጉዳይ በተለይ ራሱን የቻለ የሚያነጋግር ነጥብ ነው። ለምሳሌ ለየክብረ በዓሉ ከመጠን ያለፈ ወጭ፣ ለጉብኝትና ለእንግዶች ማስተናገጃ የሚፈሰው ገንዘብ፣ በድርጎ መልክ የሚሰጥ ገንዘብ፣ ለየወይዛዝርቱ የክብር መጠበቂያ እየተባለ ሳይሠሩ የሚከፈል ደሞዝና የመሳሰሉት አላስፈላጊ ወጭዎች ነበሩ።

በቀረጥ የሚሰበሰበው ገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ እየተረሳ ልክ እንደንጉሠ ነገሥቱ የግል ኃብት ስለሚቆጠር መንግሥትን ለመምራት በተሰጣቸው ኃላፊነት የሚያደርጉት ማናቸውም ነገር በግላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ውለታ እንደዋሉለት ይቆጠር ነበር። የትምህርት ታክስ ሕዝቡ እየከፈለ ጃንሆይ ልጄን አስተማሩልኝ ብሎ እንዲያስብ ተደረገ። ሆኖም ጃንሆይ የትምህርትን ሁኔታ ቅድሚያ ሰጥተው በጣም ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ በማድረጋቸው ይመሰገናሉ። ያም ሆኖ ግን በአጠቃላይ የተጠበቀውን ያህል ዕደገት በወቅቱ ባለመታየቱና በተደጋጋሚ በተከሰቱ በደሎች የሕዝቡ ቅሬታ ተባብሶ የጃንሆይን መንግሥት እስከ ማናጋት ደረሰ።

ዳሩ ግን አሁንም ብሆን ሳይጠቀስ የማይታለፈው ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ለማፍራትና ክብሯን ከፍ ለማድረግ ብዙ ሥራ መሥራታቸው ነው።

1ኛ) በ1939 ዓ.ም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በሰብል መበላሸት ምክንያት በብሪታንያ ረሃብ በመግባቱ በኢትዮጵያ ስም ጃንሆይ አንድ ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ ዕርዳታ ለግሰዋል።

2ኛ) ደቡብ አፍሪካን ከአፓርታይድ ነፃ ለማውጣት ለሚታገሉት ብሔርተኞች መጠለያ ከመስጠት ሌላ ብዙ ዕርዳታ ተደርጓል። ለስደተኞች በትምህርት ሚኒስቴር ሥር በየክፍለ አገሩ በአስተማሪነት ከመቀጠር ሌላ ለታጋዮች የወታደር ሥልጠናና ዕርዳታ ይሰጥ ነበር። በተለይ ለትግሉ መሪዎች ደመወዝ በመስጠትና እቴጌ ሆቴል በማስቀመጥ እንክብካቤ ተደርጎላቸዋል። ከመካከላቸው ሚስተር ኔልሰን ማንዴላና ሌሎችም ኮልፌ በፈጥኖ ደራሽ ተቋም ውስጥ ሠልጥነዋል።

3ኛ) ናምቢያ ነፃነት ከመውጣቷ በፊት በነበረው ውዝግብ ኢትዮጵያና ላይቤርያ ለሁለት ጠበቃ አቁመው ለዘጠኝ ዓመት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሲከራከሩ ቆይተዋል።

4ኛ) የኬንያ የማኦ ማኦ (ሰው ሰው ነው) ሕቡዕ ነፃ አውጭ ድርጅት መሪ ለነበሩት ሚስተር ጆሞ ኬኒያታ ሰባት ዓመት ሙሉ ታስረው በነበረ ጊዜ ለሴት ልጃቸው በየወሩ 250 ሺልንግ በኢትዮጵያ ጄኔራል ቆንሲል አማካይነት ይሰጥ ነበር።

5ኛ) ኬኒያ ላይ ደርሶ ለነበረው ረሃብ ማስታገሻ እንዲሆን በኬኒያ የብሪታኒያ ተወካይ ለነበሩት ለሰር ሃምፍሬይ 250 ሺህ ሺልንግ ዕርዳታ ተሰጥቷል።

6ኛ) በቀዳማዊ ኢድሪስ ጊዜ ሊቢያ በደረሰባት ረሃብ የተነሳ የኢትዮጵያ መንግሥት ዕርዳታ አበርክታለች።



7ኛ) የገናሌና የዋቤ ሸበሌ ወንዞች ሶማሊያን ባጥለቀለቁበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር ኃይል አይሮፕላኖች ምግብ በማድረስና ሰው በማዳን ሥራ ላይ ተሰማርተው አገልግሎት ሰጥተዋል።

8ኛ) በተባበሩት የዓለም መንግሥታት ውሳኔ መሠረት ከ22 አገሮች መካከል የክብር ዘበኛ ወታደሮችን በቃኘው ሻለቃ ስም ኮሪያ ላይ በማዝመት ኢትዮጵያ ታላቅ ኃላፊነቷን በጀግንነት ተወጥታለች።

9ኛ) ለአፍሪካ ያለባትንም ኃላፊነት ለመወጣት ስትል ኢትዮጵያ ጦር ሠራዊቷን በተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ሥር ኮንጎ ከማዝመቷም ሌላ በጦር ኃይሉ አዝማችነትና መሪነት አገልግሎት ሰጥታለች።

10ኛ) የአፍሪካን አገሮች ለመርዳትና ለማቋቋም ለብዙ ተማሪዎች የነፃ ትምህርት ዕድል በምስጥት በአየር ኃይል፣ በሐረር ጦር አካዳሚ፣ በዩኒቨርስቲ፣ በአየር መንገድ እየተቀበለች ለብዙ አፍሪካውያን ውለታ ሠርታለች።

11ኛ) በቢያፍራና በናይጄሪያ መንግሥት መካከል የተነሳው የመገንጠል ጥያቄ ያስከተለውን የእርስ በእርስ ጦርነት ለማስቆም በአስታራቂነት ንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

12ኛ) በደቡብና በሰሜን ሱዳን የነበረውን ጦርነት በአስታራቂነት ንጉሠ ነገሥቱ ገብተው ጦርነቱን ለማስቆም ችለው ነበር።

13ኛ) በስሃራዊ ድንበራቸው ምክንያት አልጄሪያና ሞሮኮ በተጣሉ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ የአስታራቂነት ተግባር አከናውነዋል።

14ኛ) የአፍሪካ አገሮችን ሰብስበው ማኅበር በመፍጠር እንዲዋሃዱና በአንድነት ተደራጅተው ኃይል እንዲያገኙ ንጉሠ ነገሥቱ አስተባብረው ጽሕፈት ቤቱንም አዲስ አበባ እንዲሆን አድርገዋል።

14ኛ) ለታንዛኒያ የንቅናቄ መሪ ለሚስተር ኒሬሬ የወር ደመወዝ ተቆርጦላቸው ይከፈላቸው ነበር። በዚህ ውለታ ከነፃነት በኋላ የውጭ አገር ሰዎች ከታንዛኒያ ሲባረሩ 600 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ከሊማንጃሮ ተራራ አጠገብ በግብርና የመኖር መብታቸው ተጠብቆላቸዋል።

15ኛ) ከኬኒያ መንግሥት ጋር በነበራቸው ጥብቅ ግንኙነት ሳቢያ በኢትዮጵያ መንግሥት ለኬኒያ ኤምባሲ የሚሆን 10ሺህ ሜትር ካሬ መሬት ተሰጥቷቸዋል። እነሱም በምትኩ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ መሥሪያ የሚሆን ቦታ ሰጥተዋል።



# ምዕራፍ ፳፫

## የኤርትራ ታሪክ ዳሰሳ

የኢትዮጵያ ንጉሥ ካሌብ በነገሡበት በ6ኛው ክፍለ ዘመን የየመን ክርስቲያን ሕዝብ ከፍልስጥኤም በፈለሱ አይሁዶች ጥቃት ሲበባበትና በሰንዓ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ማፈራረስ ሲጀምሩ በአካባቢው ከነበሩ ክርስቲያኖች ዕርዳታ መጠየቅ ጀመረ። የዚህን ጊዜ የግብፁ የአሌክሳንድርያው ፓትርያርክ የኢትዮጵያውን ንጉሥ ካሌብን 'እባክህ ለየመን ክርስቲያኖች እርዳታ ላክ' ብለው ስለጠየቁት ሰባ ሺ ወታደር ይዞ ዘመተና ድል አድርጎ ክርስቲያኖችን አዳናቸው። ከዚያም አፄ ካሌብ ባለሚሉን አብርሃን ከአሥር ሺ ወታደር ጋር የመን ላይ ትቶት ተመለሰ።

አብርሃ ከቀን ብዛት ራሱ የየመን መሪ ሆኖ ለአፄ ካሌብ መታዘዝ አቆመ። በመሃሉ ንጉሥ ካሌብም ሥልጣኑን ለወራሹ ትቶ መነነ። ከእርሱም በኋላ የተነሱት የመንግሥቱ ወራሾች በኃይል ማነስና በውስጥ ችግር ሲወጠሩ የመን የቀሩት ኢትዮጵያውያኖች የየመንን አገር ለመቶ ዓመት ያህል ማስተዳደር ቀጠሉ። የየመን ሰዎች አረብ ባልኾነ መሪ መገዛትን ያልወደዱት ብሔርተኛ አረቦች ከፋርስ (ኢራን) ሰዎች ጋር ተመሳጥረው የመን ላይ ይዘምቱና ኢትዮጵያውያንንና ክርስቲያን አረቦችን ፈጁዋቸው። በዚህ ወቅት ክርስቲያን አረቦችና ሃበሾች የሞተው ሞቶ የቀረው ወደ ኢትዮጵያ፣ ሳውዲ አረብያና ወደ ሌላ አገሮች ተበተኑ። በተለይ ወደ ሳውዲ አረብያ የተበተኑት በሠላምና በመግባባት ሲኖሩ አልፈው ተርፈው መካን ከወረራ ለማዳን በውትድርና ማገልገል ጀምረው ነበር። ሳውዲ አረብያ ገና በባእት የሚያመልኩ ከበርቴ ነጋዴዎች የተንሰራፉበት አገር ስለነበረች የክርስትናና የአይሁድ ሃይማኖት ጭቅጭቅ መነሳት ሲጀምር ሁለቱንም ላለመቀበል ሲከላከሉ ረጅም ዘመን አሳልፈዋል። በዚህ ግብግብ አካባቢው ሲታመስ ቆይቶ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን መካ ከተማ በነቢዩ ሙሐመድ የሚመራ

የእስላምና ሃይማኖት ንቅናቄ ይነሳና የአዲሱ ሃይማኖት አማኞች ባእት አምላኪዎቹን ፈርተው ወደ መዲና ይሸሻሉ። በዚያኑም ወቅት ነቢዩ ሙሐመድ የቅርብ ቤተሰቦቻቸውን ለደህንነታቸው ወደ ሃበሻ አገር ንጉሥ ይልካሉ። መጨረሻ ላይ ሙስሊሞቹ ከመዲና ተነስተው መካ በድል አድራጊነት ከገቡ በኋላ በዚያ አካባቢ ሌላ ሃይማኖት ያለው ስለሚገደል ወይም ለመኖር የፈለገው ሁሉ ስለመ።

በአሥር ዓመት ውስጥ እስልምና የአረብን አገር በሙሉ አጥለቅልቆ ወደ ፍልስጥኤምና ግብጽ ተዛመተ። በቀይ ባሕርም ላይ ሌላ እስላም ያልኾነ ኃይል እንደበፊቱ መንቀሳቀስ ተቸገረ። ከ8ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ምጽዋና አዱሊስ በእስላሚ በቱርክ ተያዙ። በተለይ ቱርኮች የኢትዮጵያን የባሕር ዳርቻ መቆጣጠር ሲጀምሩ የኢትዮጵያ መርከበኞች ስለተቸገሩ በየቦታው እየሄዱ ዘረፋ ጀመሩ። በተለይ ዛሬ ጄዳ የሚባለውን ከተማ የኢትዮጵያ መርከበኞች አከታትለው ስለዘረፉት አረቦቹ ፈርተው ሃበሾች የአረብን አገር ወረው የነቢዩ ሙሐመድን አጽም ወስደው ሊያቃጥሉ ነው ብለው ስላስወሩ ሁሉም ተረባርቦባቸው መርከበኞቹ ተፈጁ።

ነቢዩ ሙሐመድ ዘመዶቻቸውን በክፉ ቀን ከለላ የሰጠችውን አገር ሙስሊሞች እንዳይወሩ ወይም የጅሃድ ጦርነት እንዳያደርጉባት አዝዘው ስለነበረ የቀይ ባሕር ድንበረተኛ የነበረችው ክርስቲያኗ ሃበሻ ወይም ኢትዮጵያ ባትወረርም ደካማ ሆና ቀረች። ሌላውን የአካባቢ አገር ቱርክ እያሸነፈች ስታስገብር ምጽዋንና አዶሊስን አልፋ ለማስገበር የማይሆንላት ስለኾነና ባሕሩ ላይ ኃይል ስላላት ዝም ብላ ቁጭ አለች። በጊዜ ብዛት በቀይ ባሕር መካከል ያሉትን የዳህላክ ደሴቶችን ስም በሙሉ ለውጣ የአረብኛ ስም ሰጠች። የአፋርን ሕብረተ ሰብ ሃይማኖት እስላም አድርጋ ወደ መሃል ኢትዮጵያ በተንቀሳቃሽ ነጋዴዎች መስበክ ጀመረች። የሃበሻና የሶማሌ ሙስሊም ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ለማስጨበጥ ቱርኮች ግራኝ ሙሐመድን እየረዱ የውስጥ ብጥብጥ አስነሱ። የኋላ ኋላ ግን ቱርኮች እየደከሙ ሲሄዱ ምጽዋን ለግብጾች ጥለው ሄዱ። ግብጾች የሚመሩት ከቱርክ ዘር በሆኑ ንጉሦች ስለነበረ ብዙም አልገደዳቸውም። መጨረሻ ላይ ግብጾች በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥር ሲወድቁ የግብጽ ግዛት ሁሉ የእንግሊዞች ሆነና ምጽዋም ላይ ማዘዝ ጀመሩ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከምጽዋ ከተማ ሌላ ግዛቱ በሙሉ የኢትዮጵያ እንጂ ማንም ወደ ውስጥ ገብቶ ለማስገበር አልቻለም። ወደ ምጽዋ በሚወስደው መንገድ ነፋሲት ወረዳ አርብ ዕሮብ መንገድ ላይ



የሚገኘው የደብረ ቢዘን ገዳም በቁጥር መንግሥት የኢትዮጵያ አካል ለመሆኑ ተመዝግቦ ይገኛል።



አፄ ኃይለሥላሴና ክቡር አቶ አክሊሉ ሃብተወልድ

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት እንግሊዞች የፈረንሶዮችንም መስፋፋት ለመገደብ ጣሊያኖችን ምጽዋ አስገብተዋቸው ቦር ስላሉ ጣሊያኖች ቀላል መስሏቸው በተደጋጋሚ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ በዙ ሙከራ ቢያደርጉም ከሽፎባቸዋል። በአንድ ወቅት ግብጾች ደጋው ላይ ወጥተው ስለተገኙ ተፈጁ። ግብጾችም በ19ኛው ክፍለ ዘመን 15 ጊዜ ጦርነት ከፍተው በኢትዮጵያውያን ተሸንፈዋል። ከዚህም ጦርነት አንዱ የአፋር ሰዎች አድብተው የግብጽን ወታደሮች በአዳል በርሃ መፍጀት ነበር። በዚህ መካከል ግብጾች ለ11 ዓመት ሰርገው ገብተው ሐረርን አስተዳድረዋል። የሐረር ሰዎች ሙስሊም ስለነበሩ የግብጾችን ሙስሊምነት ብቻ በመመልከት የውጭ ጠላት መሆናቸውን ዘንግተው ምንም ሳይከላከሉ ተቀበሉዋቸው። በኋላ ግን ግብጾች በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል በአፄ ዮሐንስ ስለተሸነፉና ኃይላቸውም ስለተመናመነ በሠላም እንደገቡ ሁሉ በሠላም ሐረርን ለቀው ወጡ። ያ ግብጾችን እያጨበጨበ

ምኒልክም ቀደም ብለው የጀመሩትን የአውሮፓን ሥልጣኔ ወደ አገር ውስጥ ማምጣት ገፋበት። አፄ ምኒልክ አድዋ ላይ ድል ከአደረጉ በኋላ ኤርትራን ባለማስለቀቃቸው እስከ አሁን ድረስ የኤርትራና የትግራይ ሰዎች ቅሬታ አላቸው። ምክንያቱም የባሕር ነጋሽን አሸንፈው ቢጠቀልሉት ኖሮ የትግርኛ ተናጋሪዎች ሲያብሩ ኃይል ስለሚያገኙ መንግሥቴን ይወስዱብኛል ብለው ነው ጦርነቱን ያልገፉበት ብለው ጠርጥረዋል። በነበረው ሁኔታ ገፍተው ቢሄዱ ኖሮና ቢሸነፉ ውጤቱ ጎጂ ሊሆን እንደሚችል አስቀድመው በማወቃቸው እንጂ ሌላ ዘዴ ሊያገኙለት ለሚችሉት ለውስጥ የሥልጣን ትግል ብለው አንድ ግዛታቸውን በቀላሉ የሚለቁ ንጉሥ አይመስሉም።

ጣሊያኖች በአድዋ ድል መመታት ተቆጭተው ስለነበርና ጣሊያን በፋሽስት ብሔርተኞችና በዱቼ ሙሶሊኒ መሪነት ኃይል ተሰምቷቸው ስለሄደ ከአርባ ዓመት በኋላ ነገር እየቀሰቀሱ ጦርነት ከፈቱና ኢትዮጵያን በ1928 ዓ.ም ወረሩ።

የጣሊያን መንግሥት ከጀርመን ጋር አጋር በመሆን በእንግሊዝና ፈረንሳይ ላይ ጦርነት ስለከፈተ ወዳጆቻቸው የነበሩት የቅኝ ገዥዎች አሁን የኢትዮጵያ ረዳት ሆኑና ጣሊያኖች ተሸንፈው ኢትዮጵያ ነጻነቷ ሲመለስ ለዕርዳታ የመጣው እንግሊዝ ቶሎ ብሎ ኤርትራን ይዞ ማስተዳደር ጀመረ።

ከድል በኋላ የጣሊያን የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ለድርድር ሲቀርብ ኢትዮጵያ ኤርትራን ግዛቴ ነች ትመለስልኝ ብላ መከራከር ጀመረች። አስማሚዎቹ ካቀረቡዋቸው የተለያዩ ሃሳቦች መካከል አሰብን ያለምንም ችግር ኢትዮጵያ ትውሰድና ስለሌላው እንወያይ ቢባልም ኢትዮጵያ ግን የአሰብ ጉዳይ ከመላው የኤርትራ ጉዳይ መለየት የለበትም ብላ ሰላሳሰበች የአሰብ ጉዳይ ሞተ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በኤርትራ ውስጥ በተፈጠረው "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ትግልና በእነ አቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ዲፕሎማሲ ትግል ታህሣሥ 2 ቀን 1943 ዓ.ም ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን ለአሥር ዓመት እንድትዋሃድና ከአሥር ዓመት በኋላ ምርጫ እንዲደረግ ተወሰነ። የፌደሬሽኑ ወቅት ሲያልቅ በኤርትራ ምክር ቤት ውስጥ ውሳኔ ተላልፎ ከመስከረም 1 ቀን 1952 ዓ.ም ጀምሮ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ተዋሓደች።



አንድን ውሳኔ መቼም መቶ በመቶ ሁሉም ስለማይደግፈው ጥቂት የፓርላማው አባሎች አጉረምርመው ወደ ጎረቤት አገር ሄደው ለኤርትራ ነጻነት ለመዋጋት እንቅስቃሴ ጀመሩ። ሕዝቡ በየወረዳው ድምጽ አልሰጠበትም ብለው የሚከራከሩም ነበሩ።

ከፌዴራሽን ጀምሮ ለአንድነት ሲታገሉ የነበሩት ሰዎች በሹመት መካስ ሲገባቸው በአንጻሩ ሲወላውሉና ሲያስቸግሩ ለነበሩት ከበሬታውና ሥልጣኑ ስለተሰጠ የተከፉ ሰዎች በቤት ውስጥ ሲነጫነጩ፣ ልጆቻቸው በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጭፍን ጥላቻ እያቆሩ አደጉ። በተጨማሪም በእንደራሴነት ከመሃል አገር የሄዱት ራስ አንዳርጋቸው መሳይና ራስ አሥራተ ካሣን የመሳሰሉት የሃብት ዘረፋ ውስጥ ገብተው ስለነበረ ኢትዮጵያዊነት ላይ የነበረውን የሰዉን አመለካከት ለወጡት ተብሎ በወቅቱ ተገምቷል። ጃንሆይም ኤርትራን ለማስመለስ የተደከመውን ያህል ለማፍረስ ሰዎች ሲጥሩ ምንም ሳይመስላቸው ከማለፋቸው ሌላ እንዲያውም ነገሩን በሹም ሽር አባባሱት። ከዚህም ሌላ ከውጭ በተገኘ ብድር የአሰብ ወደብ ተሠራና የምጽዋ ወደብ ሥራ ፈታ።

በአሥመራና በደጋው ኤርትራ የተሠማሩ ሠራተኞች በአካባቢው ኢኮኖሚው ስለደከመ ወደ መሃል አገር ቢመጡና ቢያመለክቱም ችግራቸውን ዞር ብሎ የሚመለከት ባለሥልጣን ጠፋ። ስለሆነም ብዙዎች ኤርትራውያኖቹ ተቸገሩ። በወቅቱ በስርቆትና በማጭበርበር በአዲስ አበባ ውስጥ ማጅራት መቺው ስለበዛ ለማስፈራራት በየቦታው የአጠና መስቀያ ተተክሎ ብዙ ሰው በስቅላት የሚቀጣበት ጊዜ ስለነበረ ተስፋ ሲቆርጡ በየጎረቤት አገር ሥራ በመፈለግ ተሰደዱ። በአገር ውስጥም ባሉት ኤርትራውያኖች ውህደቱ ባመጣባቸው አኗኗር ተስፋ መቁረጥ ተጀምሮ እንዲያውም የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ብ. ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት ወገኖቼን ሳጉላላ የኖርኩት ለዚህ ኖሯል ወይ ብሎ በመጸጸት ራሱን ገደለ ተብሎ ተወሳ። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች


ብ.ጄኔራል ተድላ ዕቁቢት

የለም ቢሮው ውስጥ ተገድሎ ነው የሚሉም አሉ። ይሁንና ቅር ተሰኝቶ እንደነበረ ይታወቃል። በጠቅላላው ኤርትራውያኖች ከኢትዮጵያ መለየትንና የኤርትራን መንግሥት ለመመሥረት ወሰኑ።

ይህ ሁሉ ተዳምሮ የነጻ አውጪ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ሲጀምሩ ጸጥታ ሊያስከብር የሄደውን ወታደር ከየተሰማራበትና ከሚፋለምበት ቦታ "ተዋቸውና ተመለሱ!" እያሉ የሚገቷቸው ባለሥልጣኖች ተፈጠሩ። በተጨማሪም በሙስሊም የነጻነት ተዋጊ መሪዎችና በክርስቲያን ጀሌዎች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ሌላ በክርስቲያኖች የሚመራ ነጻ አውጪ ድርጅት ተቋቋመ። በዚህ ወቅት አዲሶቹን መሪዎች የመንግሥት ባለሥልጣን የሆኑት ይረዷቸውና ያበረታቷቸው ጀመር። የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሚያበረታቷቸው ለሁለት ነገር ነበር። አንዱ በሙስሊሞች የሚመራውን ነፃ አውጭዎች አዳሉ በክርስቲያኖች የሚመራው ነፃ አውጭ እንዲቋቋመውና ሚዛን እንዲጠብቅ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ በመሃል አገር በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉትን የሚቀናቀን ነፃ አውጭ እንዳይኖሳ ለፖለቲካ መጠቀሚያ እንዲሆኑ ነበር። በዘመኑ በቃኘው ሻለቃ ስም የአሜሪካን ጦር ሠፈር አዛገሮችም ለ.ፃ አውጭዎቹ በመጠኑ እርዳታ አልነፈጓቸውም ይባላል። ምክንያቱም እንደተለመደው ኢትዮጵያ ግዙፍ አገር እንዳትሆን ለመከላከል በሚደረገው የእንግሊዞች ደባ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ይመስላል።

በመሃሉ የ1966 ዓ.ም አብዮት ፈንድቶ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊቶች የበታች መኮንኖች ሥልጣን ሲይዙ ተደጋጋሚ ስህተቶች መሥራት ጀመሩ። አንዱ ስህተት ኤርትራዊ የኾነውን ተወዳጅ ጄኔራል ርዕሰ ብሔር አድርገው ከሾሙ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ለሥልጣን ሽሚያ ሲሉ በስበብ አስባቡ ስለገደሉት የብዙ ኤርትራውያንን ልብ አሸፈቱ። ቀጥለውም የተማሪው ኃይል ሥልጣናችሁን ለሕዝብ ስጡ እያለ ሲያስቸግራቸው "ዕድገት በሕብረት" የሚል ዘመቻ አውጀው ተማሪውን በውድም በግድም በመላው ኢትዮጵያ ሲያዘምቱ የኤርትራ ተማሪዎች ግን ሸሽተው ከነፃ አውጭ ጋር በማበራቸው 1,500 ብቻ የነበረው የሽምቅ ተዋጊ ጦር ወዲያው 45,000 ሆኖ ታላቅ የተቃዋሚ ኃይል ተፈጠረ። ደርግ የሾመው ኮሎኔል ዘነበ አስፋው የሚባል እሥመራ ውስጥ የነበረውን ወጣት ስላስበረገገው ሙሉው ብሎ ወደ ነፃ እውጭዎች ገባ። ይባስ ብሎ



እነሱን ለማደን ተዘጋጅቶ የነበረው የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ የኮማንዲስ ጦር በደርግ ችላ ስለተባለ ለሽማቂዎቹ ገብቶላቸው ትልቅ ኃይል ሆኑ። በተጨማሪም ነጻ አውጭዎቹ በአስታራቂ እጅ ለመስጠት ወደ ከተማ ሲመጡ ወታደሮቹ መንገድ ጠብቀው ስለተኮሱባቸው አምርረው በትግላቸው ቀጠሉ። የኤርትራ ተወላጅ የሆኑትን ከባሕር ኃይልና ከአየር ኃይል ሰብስበው አዲስ አበባ አራተኛ ክፍለ ጦር ሲያስሩ የኤርትራ ሕዝብ ቁርጥ ውሳኔ አድርጎ በሙላ ኃይሉ ለነፃነቱ መታገሉን ቀጠለበት። እንደ ዶክተር በረከት ሃብተ ሥላሴ ያሉ በሹመት ያልተደሰቱ ምሁሮች በመሰደድ በውጭ አገርም ስለኤርትራ ፕሮፓጋንዳ በመንዛትና እስከ መጽሐፍ ድረስ በመጻፍ የኤርትራን ነፃነት በሚችሉት ለቀረው ዓለም በማሳመን ግፊቱ እየበረታ ሄደ።

በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን መንግሥት ሊወገድ የሚችለውን የነፃ አውጭ ድርጅት ባለሥልጣኖች እንዲጠፉ ስለማይፈልጉ ወታደሩ ተከታትሎ ሊመታቸው ሲቃረብ 'ተመለስ!' እየተባለ የሚባለው አሠራር በደርግም ጊዜ በመቀጠሉ ጥቂት ወታደሮች ነገሩ ይመራቸውና በኋላ ለይ ከፋኝ በሚል ስያሜ ሸፈቱ። ራስ አሥራተ ካሣ እንደራሴ በነበሩበት ጊዜ የጦር መማሪያ የመንግሥት ሹሞች ለነፃ አውጭዎቹ ሲያቀብሉ በጸጥታ ሠራተኞች ስለተደረሰበትና ይህንን ጉዳይ ብ/ጄኔራል ተሾመ እርገጡ ሲከታተሉት እያሉ በመሃሉ በነፃ አውጭዎቹ ተገደሉ። ይኸ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ ኮማንደር እስክንድር በተለይ ደግሞ ራስ አሥራተ ካሣ በግልጥ መኪና ያለአጃቢ ከምጽዋ አሥመራ ብቻቸውን ይጓዙ ነበር። በጊዜው ሰዎች የሰጡት ትርጉም እንደራሴው ከነፃ አውጭዎቹ ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው አድርጎ ነው። ሆኖም ራስ አሥራተ ካሣ ከቦታቸው መሻራቸው አልቀረም። የጃንሆይ መንግሥት ሲለወጥ ዋና የመማሪያ አቀባይ የክፍለ ሃገሩ የፖሊስ ጄኔራል እንደነበረ ተደርሶበታል።

የአብዮቱ መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባንዲራ በመሳም አገር ወዳድ እየመሰሉ የኤርትራን ጦርነት በሥልጣን ላይ ለመቆየት ተጠቀሙበት። በመጀመሪያ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጦር ሠራዊት ቦይስካውት በነበሩ ጊዜ የባሕር ኃይል ወታደር በሚመለምልበት ወቅት ከጓደኞቻቸው መካከል ብዙዎቹ ሲመለመሉ እሳቸው በተፈጠረው አለመግባባት ስለተመለሱ በባሕር ኃይል ላይ የግል ቂም ነበራቸው። ሃምሳ አለቃ ለገሠ አስፋው የደርግ አባል

አውራዎች ሕልማቸው እንደሚሰምር አረጋገጡ። ስለኾነም የኤርትራን ሕዝብ መገንጠል ያመቻቹት የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች መሆናቸው ግልጽ ነው።

በሌላም በኩል የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት በኤርትራ ነፃ አውጭ ሽምቅ ተዋጊዎች በመታገዝ ሽሬ ላይ ወታደሩን ድል አደረገው። የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩት የደርግ ተወካይ ባለሥልጣን በፊት የቀይ ሽብር የበላይ አስፈጻሚ የነበሩት የሻምበል ለገሠ አስፋው ዕውቀትም ብልጠትም ያልነበራቸውና ባልገባቸው ኮሙኒዝም የሰከሩ ስለነበሩ በ1981 ዓ.ም ትግራይን ለቀው ጦሩንና የመንግሥት ሠራተኞችን ወደ ወሎ አስተዳደር እንዲሄዱ አደረጉ። እሳቸውም ሸሽተው አዲስ አበባ ገቡ።

አፄ ዮሐንስ መሞቻቸው ሲቃረብ አንድ ቀን አፄ ምኒልክ በቅኗቸው ላይ ሲፈናጠጡ በሕልማቸው ስላዩ ዘውዱ ወደ ሸዋ መሄዱን አውቀው ነበር። ታዲያ አፄ ዮሐንስ ሰዎች ሰብስበው "ዘውዱ ወደ ሸዋ ይሄዳል ግን ከመቶ ዓመት በኋላ ይመለሳል" ብለው ትንቢት ተናገሩ ይባላል። እንደ ትንቢቱም እሳቸው በ1881 ዓ.ም ሲያርፉ በ1981 ዓ.ም ደግሞ ሕውሓት ትግራይን ያዘ።

ከ1981 እስከ 1983 ዓ.ም የትግራይን አስተዳደር ደርግ ለሕውሃት ስለተወላቸው እነሱም ወታደር የሚመለምሉበትና የሚደራጅበት ሰፊ አካባቢ አግኝተው በሰፊት ተዘጋጅተው የተማረኩ ወታደሮችን በማደራጀትና ሌሎች ነፃ አውጭዎችን በማስተባበር ኢሐዴግ የሚል ፓርቲ መሥርተው ወደ መሃል አገር በመግፋት አዲስ አበባን ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም ያዙ። ለአገሬ እሞታለሁ እያሉ ይደነፉ የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ለአምስት ዓመት ስደት መሄድ ለፖለቲካ ጥቅም ሲሉ የስም ማጥፊያ ዘመቻ እንዳላደረጉ ሁሉ በአይሮፕላን ወደ ብላቴ ለጉብኝት የሚሄዱ በማስመሰል ወደ ኬንያ ሸሹ። ከአገር ከወጡ በኋላ መኮብለላቸው ተገለጸ። አትፍረድ ይፈረድብሃል እንደሚባለው ኮሎኔል መንግሥቱም ተሰደዱና ይኸው እሳቸው ከንጉሠ ነገሥቱ የስደት ዘመን ከእጥፍ በላይ ቆዩ። ገና ስንት ዓመት በስደት እንደሚኖሩም ለማወቅ ያዳግታል። ቀደም ብለው ገንዘብና ንብረት ምንጣፍ እንኳን ሳይቀር አሸሽተው ወታደሩን በትነው መጥፋታቸው



የኢትዮጵያን ሕዝብ በመሪዎቹ ላይ ዕምነት እንዲያጣ አድርጎታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ የሚናገሩትና የሚሰጡት ትችት እያስናቃቸው እየመጣ ነው።

የሚገርመው ነገር ስለ ኮሎኔል መንግሥቱ ወሬ ሲነሳ "እሱ አገር ወዳድ ነው! ቆራጥ ነው! ምንም ገንዘብ አይነካም! ብዙ ሥራ ሠርቷል!" የሚሉ ሰዎች መኖራቸው ነው። አንድ ሰው እንደምንም ብሎ የመሪነትን ሥልጣን ለመያዝ ከቻለ ደጋፊ፣ አድናቂ፣ ወይም አምላኪ እንደሚኖረው ብዙ አጋጣሚዎች አሳይተውናል። አገር መውደድ ማለት ባንዲራ መሳም ነው ወይስ አገር አስገንጥሎ መጥፋት ነው ወይስ ላይሞቱ እሞትልሻለሁ ብሎ መደንፋት ነው? የፖለቲካ ሰዎች ብዙዎቹ አይታወቅባቸውም እንጂ ሰውን ከማግኘት አያርፉም። አሜሪካን አገር በምርጫ ወቅት ልጆችን ከእናቶቻቸው ጉያ እየተቀበለ የማይስም ምረጡኝ ባይ የለም። ከተመረጠ በኋላ ግን ልጅ ያለበት ቦታ አይደርስም።

አገር ወዳድነትስ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የነበሩት ባለሥልጣኖች ላይ በብዛት ታይቷል። አንዳቸውም እንኳን በንብረት ከአገር በማሸሽ አልተወነጀሉም። ብዙዎቹ እስር ቤት ኾነው ያሳስባቸው የነበረው ጉዳይ የእነሱ በግል እንደታሰሩ መገደል ሳይሆን በተፈጠረው የተዘበራረቀ የመንግሥት አስተዳደር ኤርትራ ትገነጠል ይሆን ብለው መጨነቅ ነበር። ደርግ ሁሉም ነገር በዘመቻና በኮሙኒስት አስተሳሰብ ብቻ የሚመራ ስለሚመስለው የኤርትራን ችግር በኃይል እፈታዋለሁ ብሎ ስላሰበ ጅቡቲን አስረክቢኝ ብሎ ከፈረንሳይ ጋር እንደመከራከር ለተባበሩት መንግሥታት አሳልፎ ሰጣት። አምባሳደር አቶ አሃዱ ሳቡሬ በወቅቱ በጅቡቲ የኢትዮጵያ በአምባሳደር ደረጃ ቆንሲል ጄኔራል የነበሩት ደርግ የጅቡቲን ጉዳይ እንዲያዘገይ ቢመክሩ ከሥልጣናቸው ተነስተው ታሰሩ። ጅቡቲን ፈረንሳይ ለኢትዮጵያ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ሆና ሳለ የኢትዮጵያ ኮሙኒስት መሆን ነገሩን ያበላሸ ይመስላል። የተባበሩት መንግሥታት በቅኝ ገዥዎች የተቋቋመ የእነሱን ሕልም የሚፈታ፣ የእነሱን ተግባር ሕጋዊ የሚያደርግ፣ ድርጅት መሆኑን እንኳን ባለመጠርጠር ደርግ የወሰደው እርምጃ ኢትዮጵያ ከነበራት ዕድል አንዱን አጣች። በመጨረሻም ኤርትራን ያስገነጠለው የደርግ መንግሥት ነው የሚባለው ወታደሩ የተበተነውና አገሪቱ የተገነጠለችው በደርግ ውድቀት ምክንያት ስለኾነ ነው።

ኤርትራውያኖች ወደድንም ጠላንም ኢትዮጵያዊ መሆናቸው የተፈጥሮ ሁኔታ እንጂ የፖለቲከኞች ጉንጎና ወይም የኃይል ማነስ የሚያስቀረውም ወይም የሚሰጠውም ፀጋ አይደለም። ስለዃነም አንድ ሕዝብ እንደመሆናቸው መጠን ወቅቱን ጠብቆ መዋሃዳቸው አይቀርም። ሶማሌዎች እንኳን ምንም የደቡብ ሕንድ ጎሣ ደም በመጠኑ የተደባለቀባቸው ቢሆኑም ከኢትዮጵያ ጎሣዎች አንዱ እንጂ የሶማሌ መንግሥት በቅኝ ገዥዎች የተፈጠረና የአንድ የጥቁር መንግሥትን ለመቦጫጨቅና አቅመቢስ መንግሥቶች እንዲኖሩ የጎነጎኑት ዘዴ ነው። ስለዃነም ጠቅላላው የአፍሪካ ቀንድ በጥቅሉ አንድ ኢትዮጵያ ተብሎ በሠላምና በመግባባት በጥሩ አስተዳደር አንድ ላይ እንደሚኖር አያጠራጥርም። አንዳንድ ግለሰቦች ሲቆጩ፥ የሚከተለውን ግጥም በመዝናኛ ቦታ ላይ ለአዝማሪ ይሰነዝራሉ።

እኛ እንደተማርነው በታሪክ ሲጣራ
ጅቡቲም የኛ ናት እንኳንስ ኤርትራ።

እንዲህ ዓይነቱ አባባል የራሱ ችግር ቢኖርበትም፣ ውስጠ ምስጢሩ ጅቡቲም ኤርትራም የኢትዮጵያ አካል መሆናቸውን ለመግለጽ ነው።



# ምዕራፍ ፳፮

## የሕዝብ ቅሬታዎች

የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን እንደሚወድ በብዙ አጋጣሚዎች ይንጸባረቃል። በአገር ውስጥ ያሉ ይቅርና በውጭም አገር የተደላደሉት ኢትዮጵያውያኖች ፖሊቲካው ላይ እጅግም ባይጠቅሙም ሲከራከሩ የሚውሉት ስለ አገራቸው ነው። አገር ተወረረ ሲሉት ኢትዮጵያዊ ሀሉ ውድ ሕይወቱን ለመሰዋት አያወላውልም። ነገር ግን አገሪቱ ለእያንዳንዱ ዜጋ የምታደርገው ነገር በአንጻሩ ሲታይ ለዜጎችዋ ከምትሰጠው የነፃ ትምሕርት ሌላ እጅግም ነው። ሌሎችም ልማቶች በጣም ውስን ስለሆኑ ሕዝቡ እርካታን አላገኘበትም። እንዲያውም በሕዝቡ አመለካከት መንግሥት በግብር ስም ሕዝብን እየገፈፈ የሚኖር አካል አድርጎ ይመለከተዋል።

ቀደም ባለው ዘመን ወታደር የሚሞትለት ለአገሩ ሳይሆን ለአሳዳሪው ነበር። አሳዳሪው ከከዳ አብሮ ይከዳል፣ አሳዳሪው ከጠላት ከወገነ አሱም አብሮ ይወግናል። በዚህም አስተሳሰብ ይመስላል በጦርነት ላይ አሳዳሪው ከወደቀ ወታደሩ ይበተናል። ለምሳሌ አፄ ዮሐንስ ስለቆሰሉ ድል በማድረግ ላይ የነበረው ወታደር ሸሽት ጀምሮ ራሱንም አገሩንም ጎዳ። ጃንሆይ ከማይጨው ተመልሰው ወደ ውጭ አገር ሰለሄዱ ወታደሩ ተበተነ። እንዲሁም በቅርብ ዘመን ኤርትራ ውስጥ ለኮሎኔል መንግሥቱ ታማኝ ለመምሰል የጦር አዛዡን የጄኔራል ደምሴ ቡልቶን ራስ ቆርጦ ሲዞር የነበረው ጦር አሳዳሪው ኮሎኔል መንግሥቱ ሲኮበልሉ ተፈታ።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ከአሳዳሪው አገር ትበልጣለች የሚል አስተሳሰብ በወታደሩ ልብ የሠረፀ ስለነበረ አሳዳሪውን ወንጅሎ ኢትዮጵያን ለማዳን ወታደሩ በዕውነተኛ አገር ወዳድነት ተነስቶ ነበር። ነገር ግን ሠራዊቱ ተመልሶ በሌላ አሳዳሪ እጅ ስለወደቀ የአዲሱ አሳዳሪ መገልገያ መሣሪያ ሆኖ ኖሮ መጨረሻ ላይ ተፈረካከሰ።

አገርን ከሁሉ በላይ አድርጎ የሚመለከትና ሲታገልም የኖረ ብዙም መከራ የተቀበለ ትክክለኛ ግን ብስለት የሚያንሰው ቡድን የተማሪ ኃይል ብቻ ነው። የተማሪ ኃይል ዕውነትንና አገርን መርህ የሚያደርግ አካል ስለኾነ ሁል ጊዜ ይኖራል ይታገላልም። አዲስ አሳዳሪ በመጣ ቁጥር የሚያጉላላውም ተማሪውን ነው። ተማሪው ግን መጀመሪያ ዴሞክራሲን በራሱ ላይ ቢያሰፍን ከተለያዩ የርዕዮተ ዓለም፣ የኀማና የፖለቲካ ድርጅቶች መማሪያነት ይድናል። ይኸንን ካላደረገ ግን አገርንም ወገንንም ከመጥቀም ይልቅ ጎጂ ይሆናል።

## ሥራ ፈትነት

በንጉሠ ነገሥቱ የመጨረሻው ዘመን ተምሮ ለሥራ ዝግጁ የሆነው ሥራ ለማግኘት ካለመቻሉም በላይ ከባላገር ወደ ከተማ የሚገባውና ከተማ ውስጥም አድጎ ለሥራ የሚደርሰው የሚቀበለው ድርጅትም ኾነ ግለሰብ ስለታጣ ሥራ ፈቱ እየበዛ ሄደ። በተለይ ከየባላገሩ የሚመጡት ወጣት ሴቶች የተዘጋጀላቸው ሌላ ሥራ ስላልነበረ መጠጥ ቤትና የዳንስ ቤቶች በብዛት ስለተከፈቱ እዚያው ሥራ ላይ ይሰማራሉ። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ አስረሽ ምችው እየበዛ የሴተኛ አዳሪው ቁጥር ከመጨመሩም በላይ የአባለዘር በሽታ በጣም ተስፋፋ። መንግሥት የሴተኛ አዳሪን መኖር በይፋ ባይቀበለውም ትልቅ መቅሰፍት እየኾነ መጣ። ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ይህንን መቅሰፍት ለማጥፋት የጉልበት እርምጃ መውሰድ ጀምሮ ነበር። የኤኮኖሚን መቅሰፍት በቅጣት መቋቋም የማይቻል ስለኾነ የተሻሻለ ነገር አልተገኘም።

በዚሁ የመጨረሻ ዘመን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ብዙ ተፈታኝ ሲኖር አልፈሃል እየተባለ የሚነገረው ተማሪ ብዛት ዩኒቨርሲቲው ሊቀበለው የሚችለውን ቁጥር ያህል ብቻ ስለነበረ የወዳቂው ቁጥር ከሚያልፈው በጣም ጨመረ። ተማሪ ከፈተና ሲወድቅ የራሱም ኾነ የቤተሰቡ ክብር ስለሚነካ ሕይወታቸውን ያጠፉ ልጆች ብዙ ነበሩ። በኋላ ላይ ነገሩ ለሁሉም ግልጽ ሲሆን ራስ ላይ አደጋ ማስከተሉ ቀረ። አልፈሃል ግን ዩኒቨርስቲው ሊቀበል የሚችለው ከዚህ በላይ ያገኙትን ብቻ ነው እንደማለት መንግሥት ሲግደረደር የብዙ ልጆች ሞራል ተነካ። ለወዳቂዎቹም ሥራ የሚባል ነገር ሊገኝ አልተቻለም።



የኢትዮጵያ ትልቁ የኤኮኖሚ አውታር እርሻ ስለኾነ የመሬት ይዞታው ቢሻሻል ኖሮ ለብዙ ሰው ሥራ እንደሚፈጥር አያጠራጥርም። መንግሥት ግን የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም፣ ሕዝቡን ለመቆጣጠር ሲል የመሬትን ይዞታ ኢትዮጵያ ውስጥ ለዝንት ዓለም አልለቅም በማለቱ ድህነት ያማቀቀው ሕዝብ እንደኾነ ይኖራል። ደርግ ለችግሩ መፍትሄ የሚሰጥ መስሎት ጥቂት ባለርስቶችን ወርሶ በጠቅላላው የኢትዮጵያ መሬት ሁሉ የመንግሥት በመሆኑ እንዲያውም ጭራሹኑ ሕዝቡ መብት የሚባል ነገር እንዳይኖረው አደረገ።

## ኤምባሲዎች

የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በውጭ አገር የመሪዎችን ዝና ለማስተጋባት እንጂ የኢትዮጵያዊ ግለሰቦችን ችግር ለማቃለል ወይም የአገሪቷን ጥቅም ለመጠበቅ ተብለው የተመሠረቱ አይመስሉም። ስለሆነም አንድ ኢትዮጵያዊ ፓስፖርቱ እንዲታደስ ሲጠይቅ ከማደስ በስተቀር ኢትዮጵያዊውም ወደ ኤምባሲው የሚሄድበት ምክንያት የለውም፣ ኤምባሲውም እንዲመጡበት አይፈልግም። ኢትዮጵያውያን ኤምባሲዎች በሊሉባቸው አገሮች እንደሚኖሩና የመኖሪያ ፍቃድና የፓስፖርት ማሳደስም ችግር እንዳለባቸው እየታወቀ ፓስፖርቱ ለአምስት ዓመት መታደስ ሲችል ከሁለት ዓመት በላይ በምንም መልኩ አይታደስም። እንዲያውም አንድ ኢትዮጵያዊ በሌሎች ብዙ አገሮች የሌለ ችግር ተጥሎበት እንደ እስረኛ ከአገሩ ለመውጣት ቪዛ ያስፈልገዋል።

በንጉሡ ዘመን ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በጣም ያነሰ ስለነበረ ይህ ሃቅ አይታወቅም ነበር። ብዙ ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን በጨረሱ ማግስት ወደ አገራቸው ስለሚመለሱ አንዳንድ በመርከብ ተደብቀው ከሄዱ ኢትዮጵያውያን በስተቀር እጅግም የሚያሳስብ ብዛት ያለው ውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ አልነበረም። በጎረቤት አገሮች በአረብ ነጋዴዎች በባርነት ተዘርፈው የሚሸጡትን ኢትዮጵያውያን ቁጥር ለማወቅም ኾነ ነገሩን ለማንሳት የፈለገ የመንግሥት አካል አልነበረም። አንድ ኢትዮጵያዊ በሌላ አገር ውስጥ ቢበደል መንግሥት ለግለሰብ ብሎ ከሌላ መንግሥት ጋር ውዝግብ ውስጥ አይገባም። ስለሆነም ኢትዮጵያውያን በጎረቤት

አፍሪካና በየአረቡ አገር እንደተጉላሉ ነው። ብዙ አገሮች ግን ስለዜጋቸው መብት ትግል ያደርጋሉ። በተለይ እሥራኤልና አሜሪካ ለአንድ ዜጋ መብት ብለው ጦርነት እስከማንሳት ይዳዳቸዋል።

በጠቅላላው የኤምባሲ ሰዎች ሊያደርጉ የሚችሉትን ያህል እንኳ ለማድረግ ቅንነቱ የላቸውም። አቶ ሕይወት ኅዳሩ "ያቺ ቀን ተረሣች" በምትለው መጽሐፋቸው ላይ በሳቸው የደረሰውን በገጽ 7 ላይ እንደሚከተለው አትተዋል። "መጋቢት 16 ቀን 1924 ዓ.ም በአሥመራ ወደ ቆንስላችን ሄጄ በፓስፖርቱ ላይ ወደ ሱዳን ለመግባት የሚያስችለኝ ይጻፍልኝ፣ ለአሥመራ ባለሥልጣኖችም እንዲጻፍልኝ ይደረግልኝ። እዚያ ሄጄ ትምሕርቴን ለመቀጠል እፈልጋለሁ ብላቸው ቆንሲሉ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ "ወደ አዲስ አበባ ብትሄድ ይሻላል" ሰላሉኝ• "አዲስ አበባ የሚያደርስ ገንዘብ የለኝም" ብላቸው "ልብስህን ሽጠህ ሂድ" ያሉኝም ትዝ አለኝ" ብለው አውስተዋል። አሁንም ቢሆን ከዚህ የተለየ ነገር ከኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አይጠበቅም።

ኤምባሲዎቹ የመሪውን ፎቶግራፍ በግርግዳ ላይ ከመስቀላቸው በስተቀር ስለአገሪቱ ለመመራመር የሚፈልግ ሰው እንኳን ቢጎበኛቸው የሚያሳዩት ምንም ነገር አብዛኞዎቹ የላቸውም። የኤምባሲው ሠራተኞችም ቀርበው የሚያነጋግሩት እንኳን ራሱን የቻለውን ኢትዮጵያዊ እንጂ ሊላውን አያቀርቡትም።

የየኤምባሲዎቹም የውስጥ ይዞታ የሚያኮሩ አይደሉም። በእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ የሚደረደሩት መቀመጫዎች መናኛ ከመሆናቸውም በላይ በጣም ያረጁ ወይም የወላለቁ ናቸው። ክፍሉ ንጽሕናው በሥርዓት አይጠበቀም። የመዋኛ ቦታ ያላቸው እንኳን ውሃውን በንጽህና መያዝ ስለማይችሉ ገንዳውን ባዶ ይደረጋሉ። የሠራተኞቹም ቋንቋ ችሎታ በውጭ አገር ላለ ኤምባሲ ሠራተኛነት እንደማይመጥኑ ያስረዳል። የሌላ አገር ዜጋ የኤምባሲው ሠራተኞችም ሁኔታዎችን በማገማመት ኢትዮጵያውያን ሲመጡ አለባበሳቸውን አገናዝበው እስከመከልከል ይደርሳሉ። ስለሆነም ካልተገደደ በስተቀር አንድ ኢትዮጵያዊ ወደ ኤምባሲው የመሄድ ሕልም እንኳን የለውም። ብዙ ኢትዮጵያውያን ለጉብኝት አንድ አገር ሲሄዱ ምናልባት የኢትዮጵያ አየር መንገድን ቢሮ ወይም ዛሬ ጊዜ



ደግሞ የባህል ምግብ ቤትን ሄደው ይጎበኙ እንደ ኾነ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የት ነው ብለው እንኳን አይጠይቁም።



በ1922 ዓ.ም የተሾሙ አምባሳደሮች በማዕረግ ልብሳቸው
በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ ፊትለፊት (አሁን የግብጽ ኤምባሲ)

ይህን ሁኔታ ደርግ ሥልጣን ሲይዝ ያለፈውን መንግሥት ለመውቀሻ ተጠቅሞበታል። ነገር ግን ደርግ የባሰውን ሰው ማሸሽ ጀመረ እንጅ ያሻሻለው ነገረ አልነበረም። እንዲያውም በውጭ አገር ነዋሪው እየበዛ የሄደው ደርግ በሰው ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን ስቃቃ በመሸሽ ስለነበረ ኤምባሲው ዘንድ የሚመጡት ኢትዮጵያውያኖች ሁሉ የመንግሥት ጠላት እየመሰሏቸው ሠራተኞቹ ይሸሹ ነበር። ቀደም ብሎ ሌሎች አፍሪካውያኖች ኢትዮጵያዊ ነን ማለት እንዳልሞከሩና ኢትዮጵያዊነት እንዳላኮሩ ሁሉ በደርግ ዘመን አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ያለውዴታቸው ፓስፖርታቸውን እየመለሱ የሌላ አገር ዜግነት የወሰዱትም ኢትዮጵያዊነታቸው ሊያስከብራቸው ባለመቻሉ ይመስላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በውጭ እየበዛ ሲሄድ የታየው ሁኔታ በአገሩም በውጭ አገርም መብቱ አለመከበሩን ነው።



አፈንጉሥ ገብረ መድኅን ከሃያ ሰባት ዓመት እሥር በፊትና በኋላ

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ያለፍርድ የታሠሩና የተገደሉ ሰዎች ቁጥር በርካታ ነበር። በተለይ የባላባት ልጆች ይፈሩ ስለነበረ አደብ ገዝተው ያልተቀመጡ ተገድለዋል። ለምሳሌ የራስ ኃይሉ ልጅ የነበሩት ፊታውራሪ አድማሱ ኃይሉ ያለፍርድ ታሥረው እግራቸውም ተቆርጦ በእንግልት ኖረው ሞተዋል። ፊታውራሪ አድማሱ ኃይለኛ ሰው እንደነበሩና ጃንሆይ የታሠሩበት ቦታ ሊጠይቋቸው ቢሄዱ "ምን ልታደርግ ነው የመጣኸው!" ብለው በንዴት አጠገባቸው የነበረውን የአምቦ ውሃ ጠርሙስ ወርውረው ስተዋቸዋል። "እህያ ማሠሪያዋን በጠሰች የምትግጠውን ሳር አሳነሰች" እንዲሉ ሰውየው ርቀው እንዲታሠሩ ተደርጎ በዚያው ሞቱ። በልጃቸው ጠንቅም ራስ ኃይሉ ለሚሊዮን ብንዳ ሆነው ከተወረሰው ንብረታቸው የቀረችውን እንደገና ስለተወረሱ መጨረሻ ላይ በድህነትና በሃዘን ኖረዋል። ራስ ኃይሉ አንድ ቀን እንደሚከተለው አንጎራጎሩ ይባላል።

እኔ ተው እያልኩህ አንተ እየተቆጣህ
ለኔም መቀመጫ ላንተም መቆሚያ አጣህ





# ምዕራፍ ፳፯

## ራስ ተፈሪያን

በጃማይካ ደሴት የሚኖሩ ጥቁሮች በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ አንድ አፍሪካዊ ንጉሥ ይመጣል የሚል ከአካባቢያቸው ፖለቲካ ጋር የተቀላቀለ ሃይማኖት መስበክ ጀምረው ነበር። ለነገሩ ከፖለቲካ የጸዳ የሃይማኖት አመራር በምድር ላይ የለም።

እምነቱ ብሉይ ኪዳንን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ ከመናገራቸውም ሌላ እኛ ጥቁሮች ሃጢያተኛ አይሁዶች ነን፤ እግዚአብሔር እንደገና የፈጠረን ሊቀጣን ፈልጎ ሲሆን በሚልክልን ንጉሥ አማካይነት ወደ ገነቷ አፍሪካ በነፃነትና በምሕረት እንመለሳለን ብለው ያምናሉ። እንዲሁም ራስ ተፈሪ ሕያው አምላክ ናቸው ይላሉ። ጥቁሮች ወደ ቃል ኪዳን ምድራቸው ኢትዮጵያ መመለሳቸው አይቀሬ ቢሆንም የመመለሻው ጊዜ የሚወሰነው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ነው ብለው ይጠባበቃሉ። ኢትዮጵያ በሚለው ስያሜ ላይ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች በመስጠታቸው በመካከላቸው ልዩነት አለ። ከፊሎቹ ኢትዮጵያ እናት አገራቸው መሆንዋን ሲያምኑ የተቀሩት ደግሞ ኢትዮጵያ ማለት ያው መላው አፍሪካ ማለት ነው ይላሉ። በጠቅላላው የሚስማሙበት ጉዳይ ግን ኢትዮጵያ የተስፋ ምድር መኾንዋን ነው። የአመላለሱ ሁኔታ ለእውነተኞቹ አማኞች ካልሆነ ለተቀረው ሕዝብ ምስጢር ነው። ይሁንና ጃንሆይ ሻሸመኔ አካባቢ ለራስ ተፈሪያን አማኞች መሬት ሰጥተው እዛው ኑሮ የጀመሩ እንደአሉ የታወቀ ነው።

የአፍሪካ አገሮች በሙሉ በቅኝ ገዥዎች ተይዘው በነበሩ ጊዜ ነፃ አገር ተብለው የሚታወቁት ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ብቻ ነበሩ። ላይቤሪያ ከአሜሪካ የሚመለሱ ጥቁሮች የሚሰፍሩባት አገር ስለነበረች የቅኝ ገዥዎች ሊይዟት አልደፈሩም። ኢትዮጵያ ግን የመጣውን የነጭ ኃይል ድል አድርጋ ወግና ሥርአቷን ጠብቃ ከነክብሯና ማዕረጓ የምትኖር

ከመሆኗም በላይ እንደሌሎች ጥንታዊና ታሪካዊ አገሮች የራሷ የኾነ የንግሥና ወግ ያላት የጥቁር መንግሥት ሆና ተገኘች።

በ1916 ዓ.ም ራስ ተፈሪ መኮንን የአውሮፓን አገሮች በመጎብኘታቸው የተነሳ ስማቸውም እየታወቀ ሲሄድና እንዲሁም ንግሥና በኢትዮጵያ ታሪክ ከእሥራኤል ንጉሦች ከዳዊትና ሰሎሞን ጋር በመያያዙ በጀማይካ ያሉት የአዲሱ ፖለቲካዊ ሃይማኖት ምሁሮች 'ይህ የምንጠብቀው መሲህ ራስ ተፈሪ ነው፣ እኛም የራስ ተፈሪ ተከታዮች ነን' ብለው ማስተማር ጀመሩ። በተለይ የሃይማኖቱ ንቅናቄ መሪ ማርክስ ጋርቬይ ሲሆን ሌሎችም አስተማሪዎች ተነስተው ዕምነቱን በማስፋፋት ከጀማይካ ድንበር አልፎ በሌሎች አገሮችም ተስራፉ።

ከሥርዓታቸውም አንዳንዶቹ የምግብ ሕግ ሲሆን ሥጋ አለመብላትን ይጨምራል። ጠጉርንና ጢምን ማሳደግና ጋንጃ ብለው የሚጠሩትን ሃሺሽ (ዕጸ ፋሪስ) ማጨስ ይፈቅዳል።


ማርክስ ጋርቬይ

ራስ ተፈሪያኖች በጥሩው ዘፈናቸው ስሜት ያነሳሳሉ። ስለኾነም የታወቁት የጀማይካ ዘፋኞች ቦብ ማርሊንን ጨምሮ ራስ ተፈሪያን ናቸው።

ማርክስ ጋርቬይ የንጉሡ ነገሥቱ በጣልያን ጦር ተሸንፈው መሰደዳቸው በጣም ያስቆጣው ነገር ነበር። እንደገና በድል ከተመለሱም በኋላ እንዲሁ እንዳወገዛቸው ሕይወቱ አለፈ።

ጃንሆይ የጀማይካን አገር ለመጎብኘት በሄዱ ጊዜ ዝናብ ጠፍቶ ክርሞ ልክ እሳቸው ከአይሮፕላን ሲወርዱ ስለዘነበ ሕዝቡ ዕውነትም ቅዱስ ናቸው ብሎ በበለጠ እምነቱን አጠናከረ። በዘመኑ ጀማይካ በእንግሊዝ ሥር ስለነበረች አገረ ገዥው አይሮፕላን ውስጥ ገብቶ ለጃንሆይ "ሕዝቡ በእርስዎ መለኮትነት ያምናል። ስለኾነም መለኮት አለመሆንዎንና ሰው መሆንዎን ይናገሩ" ቢላቸው "ተዋቸው በፈለጉት ይመኑ" ብለው ነገሩን ዘግተውታል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአሜሪካንን አገር ሲጎበኙ በራስ ተፈሪያን አማኞች እንደመሲህ በመታየታቸው ምክንያት



ጋዜጠኞች "ነቢይ ነዎት?" ብለው ቢጠየቁዋቸው አለመሆናቸውን ተናገሩ።

በጀማይካ ጉብኝት ወቅት እሳቸውን ለመቀበል በተደረገው ሥነሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በብዛት ሲውለበለብ ዓይተው የእምነቱ ተከታዮች መለያ ቀለም ቀይ ብጫና አረንጓዴ እንዲሆን አድርገውታል። በቅርቡ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን በመመልከት አረንጓዴውን ከላይ ማድረግ ጀምረዋል። የኢትዮጵያ ባንዲራ እስከ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ቀዩ ከላይ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ አረንጓዴውም ከላይ ቢሆን ሁለቱም ተቀባይነት ነበራቸው። ራስ መኮንን ጣሊያን አገር ሄደው በነበረበት ወቅት ሦስቱ ቀለማት ተለያይተው መውለብለባቸው ቀርቶ በአንድነት መያያዝ እንዳለባቸው ተገንዝበው ወደ ሐረርጌ ሲመለሱ አረንጓዴውን ከላይ አድርገው በአንድነት ሦስቱን ቀለሞች በመስፈፋት ማውለብለባቸው በአፄ ምኒልክ ዘንድ ተሰማ። አፄ ምኒልክ ይኸንኑ በመቀበላቸው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ፣ በጫና ቀይ ሆነ። ከጊዜ ብዛት የቦሊቪያ ባንዲራ ቀዩ ከላይ መሆኑ ሲታወቅ ኢትዮጵያ በምትመዘገብበት የዓለም አቀፍ ማኅበሮች ሁሉ ይኸው አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ረድፍ የጸና ሆኗል።

ጃንሆይ በመሠረቱ የኢትዮጵያ ባንዲራ በሌጣው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ መሆኑን አምነውበት ቀጥለውበታል። ይህም ማለት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ብቻ እንደነበረ ነው የምንረዳው። የጃንሆይ መንግሥት ለብዙ ተቋሞች ዓርማ፣ ምልክትና ሰንደቅ ዓላማ ሲሰጥ ለቤተ መንግሥቱ የይሁዳ አንበሳ ምልክት በቢጫው ቀለም ላይ ተደረገ። ስለሆነም ቤተ መንግሥት ውስጥና ጃንሆይ መኪና ላይ የሚውለበለበው ሰንደቅ ዓላማ ላይ የአንበሳውን ምስል በቢጫው ላይ ማድረግ ተጀመረ። በዓለም መንግሥታት በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማነት የተመዘገበውና የሚታወቀው ግን ሦስቱ ቀለማት ብቻ ነው። ደርግ ግን ዋናው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሕብረተ ሰብዓዊት ኢትዮጵያ መንግሥትን ዓርማ ጨመረበት። እንደዚሁም ኢሕአዴግ ደግሞ የደርግን ምልክት አንስቶ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥትን ዓርማ አደረገበት። ስለኾነም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያለው ዓርማ የባንዲራው አንዱ አካል ተደርጎ ስለሚቆጠር ሌላ አገር ሦስቱን ቀለም ብቻ በሌጣው የእኔ ሰንደቅ ዓላማ ነው ብሎ ቢነሳ ለመከላከል ያስቸግራል። ለምሳሌ የቦሊቪያና የጋና ሰንደቅ ዓላማ አንድ ዓይነት

ሲሆኑ የጋናው ከቦሊቪያው የሚለየው መሃከሉ ባለው ጥቁር ኮከብ ብቻ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ከነበሩት አቡነ ባስልዮስ እስከ አቡነ መርቆርዮስ ድረስ ምልክታቸው አረንጓዴ ቀለም ላይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከነፈረሱ ይሳልበትና ዙሪያው በወርቅ አዘቦ መርገፍ የተከበበ ስለነበረ በመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ ጽሕፈት ቤትና መኖሪያ ቤት እንዲሁም መኪናቸው ላይ የሚውለበለበው ይኸው ባንዲራ ነበር።

በ1967 ዓ.ም ንጉሡ ነገሥቱ ከሥልጣን ወርደው ታስረው ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ተገድለው፣ ቀብራቸው በምስጢር ከመፈጸሙ የተነሳ የራስ ተፈሪያን አማኞች መሲሁ አልሞተም፣ አልተቀበረም፣ አረገ እንጂ፣ ብለው ያምናሉ። ለሚከራከራቸውም ከብሉይ ኪዳን ይጠቃቅሳሉ። ዛሬ እጅግ የተዋበ የንጉሡ ነገሥቱ ፎቶግራፎችና የይሁዳ አንበሳ ያለበት የኢትዮጵያ ባንዲራ በብዛት የሚሰራጨው በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በካሪቢያን ደሴት አገሮች ተንሰራፍተው በሚገኙት በራስ ተፈሪያን ሱቆች ውስጥ ነው።

በጃማይካኖችና በኢትዮጵያውያን መካከል በዚሁ አዲስ ሃይማኖት ምክንያት መቀራረብና መወያየት ስለተጀመረና ኢትዮጵያውያን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሰውነት ሰበዓዊ ፍጡርነት አበክረው በማስገንዘባቸው ለማይጠራጠሩ ብዙ ጃማይካኖች ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በመቀየር በክርስትና ሃይማኖት እየተጠመቁ ይገኛሉ። ቤተክህነት ግን የቅዱስ ያሬድን ቅዳሴ በእንግሊዝኛ ባለማዘጋጀቷ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት በሌላው ዓለም ለማስፋፋት ያላሰበችበት መሆኑን ያሳያል።





# ምዕራፍ ፳፫

## ሃይማኖትና ንጉሠ ነገሥቱ

ተፈሪ መኮንን የተወለዱት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ቤተሰብ ነው። በዘመኑ ይደረግ እንደነበረው አንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ቤተ ሰብ ልጁን ትምሕርት የሚያስጀምረው በሃይማኖት አባት መምህርነት እንደመሆኑ መጠን ተፈሪም በራስ መኮንን መኖሪያ ቤት አባ ወልደ ኪዳን የሚባሉ መምህር ተቀጥረውላቸው ፊደል ቆጥረውና የጸሎት መጽሐፍቶችን በአማርኛና በግዕዝ ማንበብና መጻፍ ተምረዋል። አሥር ዓመት ሲሞላቸው አባ ሳሙኤልና ዶክተር ቪታሊያ በተባሉ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች የፈረንሳይኛ ቋንቋ ደህና አድርገው ተማሩ። ተፈሪ ወደ መንግሥት ሥልጣን ላይ የወጡት የሁለት ዓይነት ዕምነት ተከታይ አስተማሪዎች በትምሕርት ካነጿቸው በኋላ ነው።

ጃንሆይን በአንድ ወቅት ታዋቂው ጋዜጠኛ አሳምነው ገብረ ወልድ ቃለ መጠይቅ ሲያደርግላቸው ማኪያቬሊን የሚያደንቁት እንደኾነ መግለጻቸው ይታወሳል። ማኪያቬሊ ደግሞ ለመሪዎች ከሰጣቸው ምክር አንዱ "ሃይማኖተኛ ምሰል" የሚል ነው። ስለኾነም መሪዎች ዋንኛው ሃይማኖታቸው ሥልጣናቸው መሆኑን ሳንዘነጋ በኢትዮጵያ ታሪክ ግን ብዙዎቹ ንጉሦች የሃይማኖት ትምህርትን ይማሩ ስለነበረ፣ ዕምነታቸው ከመመሰጣቸው የተነሣ መጨረሻ ላይ ሥልጣናቸውን ለልጆቻቸው እየተው የመነኮሱ ነገሥታት ከአጼ ካሌብ ጀምሮ ብዙ እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል።

ይኸ እንዳለ ሆኖ ጃንሆይ በሥልጣን ላይ እንደወጡ በቤተ መንግሥቱ የፖለቲካ ንቅናቄ ስለነበረ ጠላትም ወዳጅም ማፍራት ስለጀመሩ

ጠላቶቻቸው ስማቸውን ለማጥፋት “ተፈሪ ካቶሊክ ነው” እያሉ መናገር አብዝተው ነበር። ይህንንም ያሉበት ምክንያት ተፈሪ በካቶሊክ አስተማሪዎች ይማሩ እንደነበረ ስለሚያውቁ ነው። ከዚህም በላይ ጃንሆይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሐዋርያው ጳውሎስን ትምህርት መጥቀስ ያዘወትሩ ስለነበረ ነው።


ጃንሆይ ከአንድ ባህታዊ ጋር

ተፈሪ የዚህ ትርጉሙ ምን እንደኾነ የተገነዘቡ ስለ ነበሩ ለጠላቶቻቸው ዕድል ላለመስጠትና ኦርቶዶክስ መሆናቸውን ማንም እንዳይጠራጠር ለማድረግ በቤተ ክርስቲያን በዓላት ላይ አዘውትረው ይገኙ ጀመር። እንዲያውም ሥልጣን ሲይዙ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ የማሾሙን ጉዳይ ተከታትለው ዳር ስላደረሱት ጭራሽ ተመስገኑበትና የተቃዋሚዎቻቸው ፕሮፓጋንዳ እንደተኮላሸ ቀረ።

እንግሊዝ አገር በስደት በነበሩበት ወቅትም ዳዊት ደጋሚያቸውን አባ ሃናኛና የንስሐ አባታቸውን እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስን አስከትለው ስለነበረ የሃይማኖቱን ነገር ችላ አላሉትም። እንዲያውም ከኢየሩሳሌም የመድኃኔ ዓለምን ታቦት አስመጥተው እንግሊዝ አገር በመኖሪያ ግቢያቸው ስዕል ቤት ውስጥ ጸሎት ይደረስ ነበር። ከስደት እንደተመለሱ ታቦቱን አስመጥተው ቤተ ክርስቲያን አሠርተውለታል። ይህ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ምስካዬ ሕዙናን ወይም ስደተኛው መድኃኔ ዓለም የሚባለው ከስድስት ኪሎ በስተሰሜን ተፈሪ መኮንን (እንጦጦ አጠቃላይ) ትምህርት ቤት መግቢያ ላይ ያለው ነው።

ጃንሆይ ባለማቋረጥ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በየንግሡ በዓሉ ይገኙ ነበር። የሃይማኖት ሰዎችንም ያከብሩ ነበር በቤተ ክርስቲያን ከቅዳሴ በፊት ገብተው ከተቀመጡና ትንሽ ጸሎት ካደረሱ በኋላ ባለሥልጣኖቻቸውን እየጠሩ ስለመንግሥት ሥራ ይወያዩሉ። ከቀድሞዎች ንጉሦች የሚለዩት ታቦት ወጥቶ በቆመ ጊዜ እሳቸው ወንበር



ተደርጎላቸው መቀመጣቸው ነው። ከዚህም ልምድ በመነሳት ይመስላል በአሁኑ ወቅት ጳጳሶችም መቀመጥ ጀምረዋል።

በመጀመሪያ ኢትዮጵያ የእራሷን ተወላጅ ፓትርያርክ አድርጋ እንድትሾም ከእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ጋር ስምምነት ሲደረስ የመጀመሪያው ፓትርያርክ የንጉሡ ነገሥቱ የንስሐ አባት እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ግብጽ አገር ሄደው ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ተብለው ተሹመው መጡ። እሳቸውም በሞት ሲለዩ ምክትላቸው ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ተብለው በሲኖዶሱ ተሾሙ። አቡነ ቴዎፍሎስ የተማሩና ዘመናዊ ስለነበሩ ብዙዎች ካህናት እንዲሾሙ አለመፈለጋቸውንና እንዲሁም ጎጃሜ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ቅብዓት ናቸው ተዋህዶ አይደሉም እያሉ አስቸገሯቸው። እሳቸው ግን ይህን ሁኔታ ሲቃወሙ ራሳቸው ተዋህዶ መሆናቸውንና የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ኮፕት መባል እንደሌለበት በይፋ አስታውቀው ነበር። ተቃዋሚዎቻቸው ካህናት ሹመታቸውን ባይፈልጉም የጃንሆይ ግፊት በዘመኑ ቀላል ስላልነበረ አቡነ ቴዎፍሎስ መጨረሻ ላይ የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ተቀበሉ። ምንም እንኳን የሃይማኖት መሪዎች አመራረጥ ላይ መንግሥት እጁን ማስገባት ባይኖርበትም የአገሪቱ መሪዎች የአብዛኛውን ሕዝብ የሃይማኖት መሪዎችን አሿሿም ችላ ብለው አያውቁም። ስለሆነም


አቡነ ቴዎፍሎስ

አቡነ ባስልዮስ ለንጉሡ ነገሥቱ ታማኝ መሆናቸው የታወቀ ስለሆነ የሹመታቸው መሠረቱ ይኸው መሆኑ በንግግራቸው ተንጸባርቋል። “እኔ አባ ባስልዮስ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሊቀ ጵጵስና ተመርጬ ጃንሆይ ሹመቱን ፈቅደውልኝ አሁን በግርማዊነትዎ ፊት ቀርቤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለግርማዊነትዎ አገልጋይ መሆኔን ስገልጥ በፊትዎ የታመንኩ አገልጋይ ነኝ። ሃይማኖትና ዕውነት ይመሰክሩልኛል” በማለት ጉዳዩን አደባባይ አወጡት።

ከዚህም በተጨማሪ ጥንት የጄስዊትስ ሰባኪያን ኢትዮጵያን በሃይማኖት ሲያምሱ ኖረው መጨረሻ ላይ ከተባረሩ ከብዙ ዘመን በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል። እንዲያውም ራሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱ የተማሩት በካቶሊክ ፍሬሮች ስለነበረ እንደልብ በየቦታው ሚሲዮናቸውን ለማስፋፋት ዕድሉ አልተነፈጋቸውም። እነዚህ የጄስዊትስ ሰባኪያን መንግሥቱን የካቶሊክ ሃይማኖት እንዲቀበል ለማድረግ ባደረጉት ጥረት ንጉሥ ሱስንዮስን መለወጥ ችለው ነበር። ስለሆነም ለስምንት ዓመት በዚህ ሽኩቻ የሕዝብ እልቂት ተካሄዷል። መጨረሻ ላይ ሲባረሩ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ለሁለት ከፍለው አንዱን የፀጋ ልጆች ሌላውን ቅብአት ብለው አስተምረውና ኢትዮጵያ ውስጥ መርዝ ተክለን ብለው ፎክረው ከሄዱ በኋላ በዚሁ ምክንያት የኦርቶዶክስ ተከታዮች ሲቸገሩበትና ሲጋደሉበት ኖረዋል።

ከክርስትና ሃይማኖት ውጭ በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት መሠረት የጣለ ሃይማኖት ባሃይ ነው፤ በሃይ ሃይማኖት ከእስልምና ሃይማኖት የፈለቀ፣ ከመቶ ሰማንያ ዓመት በፊት የተፈጠረ ሳይንስን ያገናዘበና ለምሁር ቶሎ የሚመስጥ ሃይማኖት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተዋወቀው በተግባረ ዕድ ትምሕርት ቤት አስተማሪ የነበረው ፓኪስታናዊ ሚስተር ሙናጅም ነው። ስለሆነም ብዙ የተማሩ አማኞች ለማግኘት ችሏል።

በሌላ በኩል ወደ 35 % አካባቢ አማኝ ያለው የእስልምና ሃይማኖት የሚገባውን ድጋፍ ከንጉሠ ነገሥቱ አላገኘም፤ የሕዝቡ በትምሕርት አለመግፋት ለጃንሆይ በሃይማኖት በኩል የተስተካከለ አስተዳደር ለመፈጸም አዳግቷቸዋል። ስለኾነም "ልጅ ኢያሱን ዓይተህ ተቀጣ" ከሚለው የተማሩ ይመስል በዚህ ጉዳይ የተቆጠቡ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፳፱

## ያለፉትን ማስታወስ

መንግሥት ተለውጦ በሌላ ሲተካ ተተኪው ከበፊቱ መንግሥት የከፋ ከሆነበት ሕዝቡ ያለፈውን መንግሥት ግፉም እንደ ነበረ አድርጎ ያቀርበዋል። ደርግ የበለጠ ጨቋኝ ነው ለማለት ተማሪ "ኃይልዬ ማረኝ! ማረኝ!" እያለ ዘምሯል። ይኸ ማለት ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጥሩ ነው ለማለት አልነበረም። ሁለቱን ሲያወዳድር ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይሻል ነበር ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን የሚይዘው መንግሥት መልካም ነገሮችን መሥራት ሲያቅተው ያለፉትን መውቀስና በእነሱም ላይ ድክመትን ማላከክ እንደ ልማድ ሆኗል። ይኸ የጎላው በደርግ ዘመነ መንግሥት ነው። ደርግ ያለፈውን መንግሥት የተሻለ ሁኔታ ሕዝቡ እንዳይገነዘብ ሥነ ልቦናውን ለመቀየር ብዙ ጥሮ ተሳክቶለትም ነበር። በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት የነበረው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው። ጃንሆይን ታላቅ መሪ ለማስመሰል ያለፉትን ባለታሪኮች መዘንጋት ሲሆን በዚያው መጠን የአገር ውስጥ ባለታሪኮችን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር መሪዎችንም ማጋነን በተዘዋዋሪ መንገድ የተከለከለ ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ ጥንት የጀስዊትስ ሰባኪያን ኢትዮጵያን በሃይማኖት ሲያምሱ ኖረው መጨረሻ ላይ ከተባረሩ ከብዙ ዘመን በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን እንዲገቡ ተፈቅዶላቸዋል። እንዲያውም ራሳቸውም ንጉሠ ነገሥቱ የተማሩት በካቶሊክ ፍሬሮች ስለነበረ እንደልብ በየቦታው ሚሲዮናቸውን ለማስፋፋት ዕድሉ አልተነፈጋቸውም። እነዚህ የጀስዊትስ ሰባኪያን መንግሥቱን የካቶሊክ ሃይማኖት እንዲቀበል ለማድረግ ባደረጉት ጥረት ንጉሥ ሱስንዮስን መለወጥ ችለው ነበር። ስለሆነም ለስምንት ዓመት በዚህ ሽኩቻ የሕዝብ እልቂት ተከሂዷል። መጨረሻ ላይ ሲባረሩ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ለሁለት ከፍለው አንዱን የፀጋ ልጆች ሌላውን ቅብአት ብለው አስተምረውና ኢትዮጵያ ውስጥ መርዝ ተክለን ብለው ፎክረው ከሄዱ በኋላ በዚሁ ምክንያት የኦርቶዶክስ ተከታዮች ሲቸገሩበትና ሲጋደሉበት ኖረዋል።

ከክርስትና ሃይማኖት ውጭ በጃንሆይ ዘመን መንግሥት መሠረት የጣለ ሃይማኖት ባሃይ ነው፡ በሃይ ሃይማኖት ከእስልምና ሃይማኖት የፈለቀ፣ ከመቶ ሰማንያ ዓመት በፊት የተፈጠረ ሳይንስን ያገናዘበና ለምሁር ቶሎ የሚመስጥ ሃይማኖት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስተዋወቀው በተግባረ ዕድ ትምሕርት ቤት አስተማሪ የነበረው ፓኪስታናዊ ሚስተር ሙናጅም ነው። ስለሆነም ብዙ የተማሩ አማኞች ለማግኘት ችሏል።

በሌላ በኩል ወደ 35 % አካባቢ አማኝ ያለው የእስልምና ሃይማኖት የሚገባውን ድጋፍ ከንጉሠ ነገሥቱ አላገኘም፡ የሕዝቡ በትምሕርት አለመግፋት ለጃንሆይ በሃይማኖት በኩል የተስተካከለ አስተዳደር ለመፈጸም አዳግቷቸዋል። ስለኾነም "ልጅ ኢያሱን ዓይተህ ተቀጣ" ከሚለው የተማሩ ይመስል በዚህ ጉዳይ የተቆጠቡ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፳፱

## ያለፉትን ማስታወስ

መንግሥት ተለውጦ በሌላ ሲተካ ተተኪው ከበፊቱ መንግሥት የከፋ ከሆነበት ሕዝቡ ያለፈውን መንግሥት ግፉም እንደ ነበረ አድርጎ ያቀርበዋል። ደርግ የበለጠ ጨቋኝ ነው ለማለት ተማሪ "ኃይልዬ ማረኝ! ማረኝ!" እያለ ዘምሯል። ይኸ ማለት ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጥሩ ነው ለማለት አልነበረም። ሁለቱን ሲያወዳድር ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ይሻል ነበር ለማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን የሚይዘው መንግሥት መልካም ነገሮችን መሥራት ሲያቅተው ያለፉትን መውቀስና በእነሱም ላይ ድክመትን ማላከክ እንደ ልማድ ሆኗል። ይኸ የጎላው በደርግ ዘመን መንግሥት ነው። ደርግ ያለፈውን መንግሥት የተሻለ ሁኔታ ሕዝቡ እንዳይገነዘብ ሥነ ልቦናውን ለመቀየር ብዙ ጥሮ ተሳክቶለትም ነበር። በጃንሆይ ዘመን መንግሥት የነበረው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው። ጃንሆይን ታላቅ መሪ ለማስመሰል ያለፉትን ባለታሪኮች መዘንጋት ሲሆን በዚያው መጠን የአገር ውስጥ ባለታሪኮችን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር መሪዎችንም ማጋነን በተዘዋዋሪ መንገድ የተከለከለ ነበር።

ወሰን ትምህርት ቤት" ተብሎ ተጠራ። ሕዝቡ በጥንት ስሙ መጥራቱን ስለቀጠለ እንደገና በ1937 ዓ.ም የበፊት ስሙ ተመለሰለት።

በ1939 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ጃንሆይ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አዳሪ ተማሪዎችን ሲጎበኙ ምግብ ቤቱ ግድግዳ ላይ የአፄ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱን ምስል ተሰቅሎ ሲያዩ በንዴት "ይኸ እንዲነሳ!" ስላሉ ጃንሆይ እዚያው በመጎብኘት ላይ እያሉ የሁለቱ ምስል ተነስቶ የእሳቸውና የእቴጌ መነን ምስል ተሰቀለ። ይባስ ብሎ ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የተራው ሰው ልጆች በተፈሪ መኮንንና በቀኃሥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የመሳፍንትና የመኳንንት ልጆች ይገቡ ነበር። በዚህም ምክንያት በተፈሪ መኮንንና በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም መካከል በመጠኑ የመከፋፈል ሁኔታ ተነስቶ ነበር። ሠልፍ በሚወጡበት ወቅት የትምህርት ቤቶቹ የሙዚቃ ባንዶች የክበር (ታንቡር) አመታቶችን ትርጉም እየሰጡና እየተስዳደቡበት ይተላለፉ ነበር። አልፈው ተርፈው የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪዎች የሚከተለውን ግጥም በየምክንያቱ በመድረክ ይዘምሩ ነበር።

> ተፈሪ መኮንን ሐር ከሚያለብሰኝ
> ዳግማዊ ምኒልክ ደበሎ ያልብሰኝ

ተማሪዎችም ላይ የነበረው አመለካከት አንድ ዓይነት ስላልነበረ በየምክንያቱ ለየትምህርት ቤቶቻቸው እየወገኑ ከሌላው ጋር ይደባደቡ ነበር። የባላባት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና የኮተቤ (ቀኃሥ) ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎቸ ስታዲዮም ላይ ተደባድበዋል። የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መጥተው በመደባደብ ተማሪ ሞቷል። የጄኔራል ውንጌትና የባላባት (መድኃኔ ዓለም) ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተደባድበው አንድ ልጅ ሞቷል።

የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥትን ለማሠራት በሥራ ሚኒስቴር በኩል ኢትዮጵያዊው አቶ አፈወርቅ ዮሐንስና እንግሊዛዊና፣ ስዊድናዊ መሃንዲሶች የቤተ መንግሥት ፕላን ሠርተው አቀረቡ። ውድና ቅምጥል ስለሆነና ሥራውንም ለመጨረስ ብዙ ጊዜ የሚወስድ ሆኖ ስለተገኘ በምትኩ ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት በ1948 ዓ.ም በ20 ሚሊዮን ብር ተሠራ። ቤተ መንግሥቱ ላለመሠራቱ ሌላውና ትክክለኛ የሚመስለው



ምክንያት ግን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአፄ ምኒልክን ዝና ከፍ የሚያደርግ ሥራ እንዲሠራ ስለማይፈልጉ ነው እንጂ ሌላ ፕላን ተሠርቶ የምኒልክ ቤተ መንግሥት ሊታደስ ወይም በአዲስ መልክ ሊሠራ በተገባ ነበር።

አሌክሳንደር ፑሽኪን የተባለ ሩሲያዊ ባለቅኔ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ነበረው ስለተባለ የሁለቱን አገሮች ሕዝብ ያስተባብራል ተብሎ የሩሲያ የባህል ማዕከል እንደተሰየመለት ይታወቃል። አልፎ ተርፎም በቅርቡ ሐውልት እንደተሠራለት አይተናል። ፑሽኪን ከመወለድ ሌላ ለኢትዮጵያ ያደረገላት ነገር የለም። ነገር ግን ስንትና ስንት ለዚህች አገር የተሰውላትና ባለቅኔዎች እያሉ ለፑሽኪን ሐውልት መሠራቱ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ግራ ያጋባል። የተመረጠውም አደባባይ ሌላ የራሱ ታሪክ ያለው ሲሆን ለብዙ ዓመታት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሎበት የቆየ ነው። በአጭሩ የፑሽኪን ሐውልት እንደ ሌኒን ሐውልት የሚያገኘው ሩሲያን እንጂ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሐውልት የሚያስቆም ገድል ያለው አይመስልም።

ሊላው ለታላቁ የምኒልክ ቤተ መንግሥት የተደረገለት ነገር ቢኖር ዙሪያውን በብረት አጥር ቀኃሥ በሚል ምህጻረ ቃል መታጠሩ ብቻ ነው። ደርግ ቀኃሥ የምትለውን አርማ ለማፍረስና እንደገና በሌላ ለመተካት ብዙ ወጭ ስላስፈለገው አጋጣሚውን ሲጠብቅ ራሱ ወረደ። ቢያሠራው ኖሮ ማጭድና መዶሻ ምልክቱን ያደርግ ነበር ብሎ መገመት አያዳግትም። የሚያጠያይቀው ተከታዩ መንግሥት ማርክሲስት ካልኾነ እንደገና ያፈርሰው ነበር ወይስ ይተወዋል? የሚለው ነው።

አጼ ምኒልክ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ብልህ፣ ሥልጣኔ የሚወዱና ለሚቀጥለው ትውልድ የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት የሚጥሩ ነበሩ። አፄ ምኒልክ ያቋቋሚቸውን አዳዲስ መሠረተ ልማቶች ማስፋፋትና ማደስ ሲገባ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ከእሳቸው በፊት ለተሠሩት ነገሮች እድሳትና መስፋፋት እንዲደረግላቸው ተገቢውን ትኩረት አይሰጧቸውም ነበር። በተለይ የአፄ ምኒልክን ሥራና ስም የያዘ ተቋም አይወደድም። በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በአዳሪነት የሚማሩት ተማሪዎች እንኳን ከሌሎች ትምህርት ቤት አዳሪ ተማሪዎች በተለየ የሚሰፋላቸው ልብስ ኬንዳ ሲሆን የሚመገቡበት ሳህንና ሻይ የሚጠጡበት ጋቤጣ ኒኬል ነበር። ስለሆነም ብዙ ተማሪዎች ወደ ሌላ የመንግሥት ትምህርት ቤት መዛወርን ይመርጡ ነበር። እዚያ ትምህርት ቤት የተማሩ ተማሪዎቹም ብዙዎቹ ወታደርነት እየገቡ መኮንኖች በመሆን አገራቸውን ከማገልገላቸውም

እንደነበረው ይወሳል። መታያ ጥቅም ለማግኘት የሚሰጥ እጅ መንሻ ማለት ነው። ለምሳሌ:

| | |
|---|---|
| ለወረዳ አስተዳዳሪነት ለመሾም | 3,000 ብር |
| ለአውራጃ አስተዳዳሪነት ለመሾም | 5,000 ብር |
| ለአገረ ገዥነት ለመሾም | 10,000 ብር |

በቤተ መንግሥት ራሱን የቻለ የመታያ ቢሮ እንደነበረ ይታወቃል። መታያ የሚሰጡ ሰዎች ሹመት ፈላጊዎች ካልሆኑ አንዳንድ ጊዜ ተጠርተው ምን እንደሚፈልጉ ይጠየቁና ጉዳያቸው ይፈጸምላቸው ነበር። አልፎ አልፎም መታያ የሚከፈለው ታማኝነትን ለማረጋገጥም ጭምር ነው።

ቀደም ብሎ አንድ አገረ ገዥ የሚያስገባው ግብር የራሱ ይሆንና እሱ ደግሞ በተራው ለዋናው ማዕከላዊ መንግሥት የሚጣልበትን ያስገባል። በተለያዩ አካባቢዎች የአገረ ገዥው የክብር መጠሪያ ንጉሥ ወይም ባላባት ወይም ማንኛውም የባህል ማዕረግ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመንግሥት የተሾመ ባለሌላ ማዕረግ ባለሥልጣን ነው።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት ሁሉ ገቢ ለመንግሥት ቀጥታ እንዲገባ ሲደረግ አገረ ገዥዎች ደሞዝ ተቆርጦላቸው እንዲያስተዳድሩ ይላኩ ነበር። በይፋ በደሞዝ ብቻ እንዲኖሩ ይደረግ እንጅ እነሱም በተራቸው ከደጀ ጠኚውም ከባለጉዳዩም ሁሉ መታያ መቀበሉን ቀጠሉበት። ስለሆነም ሕጋዊ ባልሆነ መልኩ ግን በይፋ የሚያስከፍሉት ጉቦ መሰል ንጥቂያ እንደነበረ ይታወቃል። አንዳንዶቹ ሹሞች ከመሻራቸው በፊት ቶሎ ለመክበር መታያውን እያበዙ ብዙዎችን ያጉላሉ ስለነበረ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚባል መጥፎ ባህል ሥር መስደድ ጀመረ።

ክቡር አቶ መኮንን ደስታ በጣም የተማሩና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። በውልደትም የጎጃሙ የደጃች ተድላ የልጅ ልጅ ናቸው። ከወረራው በኋላ የመጀመሪያው የትምህርት ሚኒስትር ነበሩ። ከእንግሊዞች ጋር በተደረገው ድርድር የፈረማው ዕለት ራስ ሆቴል ግብዣ ተደርጎ የእንግሊዙን መልዕክተኛ መጠጥ አወሳሰድ ተመልክተው ያዘጋጁትን ሌላ ውል በማስፈረም አገሪቱ ሳትወድ በተጽዕኖ ልትዋዋል የነበረውን በተቃራኔው እንዲሆን አድርገዋል እየተባለ ይወራላቸዋል። የወለጋ አገረ ገዥ በነበሩበት ጊዜ የአዶላ


ወርቅ ሙሉ በሙሉ ወደ ቤተ መንግሥት ይገባ ነበርና በከፊል ወደ መንግሥት እንዲገባ ሲደረግ 75% በመቶው ለቤተ መንግሥት 25% በመቶ ለመንግሥት ሲባል አይቻልም ብለው ከለከሉ። በኋላ ቤተ መንግሥት ተጠርተው አስተምረን አስተምረን እኛ 75% ከመቶ እንዳንወስድ ታውካለህ እንዴ ብለው ጃንሆይ ሲቆጡ የለም "ወርቃዊው ስምዎ በወርቅ እንዳይጎድፍ በመቆርቆሬ ነው" ብለው ነገሩን አብርደው 50% ለመንግሥት 50% ለቤተ መንግሥት እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደረሰ። ከዚህ ወቅት ጀምሮ ወርቁ ግማሹ ወደ ቤተ መንግሥት ግማሹ ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት እዚያው የተመረተበት ቦታ ተከፋፍሎ ይላካል። ታዲያ አንዳንድ ጸሐፊዎች ስለወርቁ ጉዳይ ሲያትቱ ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት ብቻ ስለገባው ያወሱና ነገሩን ይሸፋፍኑታል።

ሹሞች ምናልባት መታያ የሚቀበሉት ለመኖሪያ የሚከፈላቸው ደሞዝና ያለባቸው የሥራ ጫና ከሚላኩበት ቦታ ርቀት አንጻር ተመጣጣኝ ስላልነበረና ልምድም እየሆነ ስለመጣ ነው። ከግዛት ግዛት የሚገኘው ጥቅም ይበላለጥ ነበር። ለምሳሌ ተወዳጅ የሆነ ሰው ከፋ ላይ ሲሾም ተወዳጅ ያልሆነ ሰው ግን ጋሞ ጎፋ ላይ ይሾም ነበር። ከፋ የቡና አገር ከመሆኑም በላይ ለም ስለሆነ ብዙ ጥቅም ሲገኝበት በተቃራኒው ጋሞ ጎፋ ሩቅና መንገድም ስላልነበረው ጥቅም የሚገኝበት አልነበረም። በተጨማሪም ባለሥልጣኖች የሚጋዙበት ቦታ ስለነበረ አንድ ሰው እዚያ ሲሾም እንደተወረወረ ያህል ይቆጥረው ነበር።

በሌላ መልኩ መታያ ወይም ጉቦ መቀበልና መስጠት በአንዳንድ አውራጃዎች የተለመደ ወግ ነበር። ለምሳሌ በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አንድ አቶ ኃብተ አብ ባይሩ የሚባል የተማረ ወጣት ከፋ ውስጥ ቦንጋ አውራጃ ተሹሞ ጉቦ ባለመቀበሉ የአገሩ ሕዝብ ገንዘባችንን ካልወደደ እኛንም አይወደንም ማለት ነውና አንፈልገውም ስላሉ ተሸረ።

ጃንሆይ በቀድሞው አሠራር መሠረት ሁሉም ገቢ ለንጉሠ ነገሥቱ፣ በየግዛቱ ያለውም ለአገረ ገዥው መሆኑ ቀርቶ ለመንግሥት እንዲሆን በማድረግ የአገሪቱን አስተዳደር ቅርጽ ለውጠዋል። ይህን ካደረጉ በኋላ መልሰው የግል ንብረትንና የመንግሥት ንብረትን በማደባለቅ በፍጹማዊ ሥልጣናቸው በሚሰጡት ትዕዛዝ የተመሰቃቀለ ሁኔታ ተፈጠሮ ነበር። ሲፈልጋቸው የመንግሥት ንብረት የሆነውን ለግለሰብ ይሰጣሉ፣ መልሰውም በመንግሥት ወጭ እንዲገዛ ያደርጋሉ። ስለግል



# ምዕራፍ ፴፩

## መሠረተ ልማት

ጥንት ያልነበረ ዘመናዊ ህክምናና ክትባት በአገሪቱ እየተስፋፋ ሲሄድና ሰውም እየተማረ ራሱን መጠበቅ ሲጀምር የሕዝብ ቁጥር እንደሚጨምር ግልጽ ነው። የቁሳቁስ ፍላጎትም ሰው እየሠለጠነ ሲሄድ በዛው ልክ ይጨምራል። ቢያንስ ያለጫማ አይሄድም፣ ለምሳሌ የአዲስ አበባ ነዋሪ ውስጥ በባዶ እግር የሚሄድ መገኘት ያቆመው ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ስለሆነም ከአዲስ አበባ ነዋሪ መካከል አብዛኛውን የመንጠቆ ትል (HOOK WORM) አይዘውም። የሽንት ቤትና የአካባቢ ጽዳት ተሟልቶ ቢሆን ኖሮ በሽታው የሚይዘው ሰው ጨርሶም አይገኝም ነበር። የጥርስ መፋቂያ መጠቀም ትቶ ብሩሽና ሳሙና ይፈልጋል፣ ጥሩ ለመልበስና ለመመገብ ይጥራል፣ እስከተቻለ ድረስ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ የተመቻቸ ሁኔታዎችን ለማግኘት ይጽጽጣል።

በ1950ዎቹ ዓመታት አንድ ሰው ሚስት ሲያገባ ዛሬ መኪና እንደሚዋሰው ያኔ ሰዓት ይዋስ ነበር። በ1990ዎቹ ዓመታት ሰዓት የሌለው ሰው በከተማ ውስጥ ቢኖርም ቁጥሩ ጥቂት ነው። ታዲያ አገሪቱ የተማሩ ልጆች እያፈራች ስትሄድ ሌሎችም የተመጣጠኑ የግንባታና የምርት ብዛት ስለሚያስፈልጋት መንግሥት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር የራሱን ኃላፊነት መወጣት ይገባዋል።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን በመጠኑም ይሁን እንጂ ብዙ ነገር ተሞክሯል። ግን ዘለቄታ ያለውና ለመሠረተ ልማት የሚረዱ ነገሮች ላይ የገንዘበ ወጪ ተደርጎ የሕዝቡን ኑሮ የሚያሻሽል ሥራ አልተሠራም። ስታሊን ከአምስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ፈጅቶ ለአገሩ ግን ጠቃሚ የሆኑ የመሠረተ ልማት ተቋሞች ትቶ ስለሄደ ያን ያህል አልተጠላም። በማእደን ፍለጋ ህገድ ያላቋረጠ ክንት ል መዱ ሊማ —



ነበረበት። ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ በውዳሴ ከንቱ የዚህች የድሃ አገር ገንዘብ እየባከነ ከድህነት አውጥቶ በኤኮኖሚ ሊያቆናጥጣት የሚችል ሥራ አለመሥራቱ ነው።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከ**19000** ሰው በላይ አልቆበት ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የተዘረጋው የባቡር አገልግሎት በጃንሆይ **58** ዓመት ሥልጣን ጊዜ እንኳን ተስፋፍቶ አገሩን ሊያዳርስ ቀርቶ የሚሰጠውም አገልግሎት ከዓመት ዓመት እያዘቀዘቀ በመሄዱ ሊጠቅም የሚገባውን ያህል አገልግሎት ለአገሪቱ አልሰጠም። የባቡር ሃዲዱ አቃቂ ደርሶ ስለነበረ ጃንሆይ ያደረጉለት ነገር ቢኖር ከአቃቂ እስከ ለገሃር 12 ኪሎ ሜትር ማስረዘማቸው ብቻ ነበር። አፄ ምኒልክ ባቡሩን ከአዲስ አበባ እስከ ነገሌ፣ ወሊጋና ጅማ ለማገናኘት ያቀዱት ሃሳብ ቀርቶ አንዴ ወደ አሰብ ሌላ ጊዜ ወደ አዋሳ ይዘረጋል እየተባለ በወሬ ቀረ። አዲስ አበባም ውስጥ ቢስፋፋ ኖሮ ለከተማው ሰው መጓጓዣ ያገለግል ነበር። አሜሪካና ህንድ በባቡር ምን ያህል ሥልጣኔያቸው ወደፊት እንደገፋ መመልከቱ ጥሩ ነው። የዓለም ሰዓት በሥርዓት ውሳኔ አግኝቶ ሥራ ላይ የዋለው በባቡር ምክንያት ነው።

ስልጣኔን ያመጣሁት እኔ ነኝ ለማለት ካልተፈለገ በስተቀር የቀደመው መሪ የጀመረውን ቀጣዩ ካልጨረሰውና መሪ በተለዋወጠ ቁጥር የነበረውን አፈራርሶ የራሱን ሌላ አዲስ መገንባት ከኾነ ተጎጂው ሕዝብና አገሪቷ መሆኗ ነው።

ሕግና ደንብ በማውጣት እንኳን ከብዙ ችግር መላቀቅ ይቻል ነበር። መሬትን በስፋት መያዙን የአገር መሪዎች ሁሉ ለሥልጣናቸው መቆያ ስላደረጉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍዳውን ያየበት ነገር ነው። ደርግ እንኳን መሬት ወርሶ ሕዝቡን ጭሰኛ አደረገ እንጅ ለሕዝብ አላከፋፈለም። የሕዝቡ ጥያቄ መሬት ለአራሹ እንጂ መሬት ለመንግሥት አልነበረም።

እርግጥ የመሬት ይዞታ ተስተካክሎ ቢሆን ኖሮ አብዛኛው ሕዝብ የምርት ውጤቱ አድጎ የኢኮኖሚ መሻሻልና እመርታ በታየ ነበር። ሆኖም ከሕዝቡ 85% ገበሬ ሆኖ ከሁለት ሺ ዓመት በፊት በሚታረስበት ዘዴ በበሬ ከማረስ ባለመላቀቁ የትም አይደረስም። ስለሆነም ብዙ ሥራ የሚከፈትበት ሁኔታ መመቻቸት ነበረበት። በአደጉት አገሮች ከሕዝቡ ከ2% እስከ 5% ብቻ እያረሠ አገሩን ሁሉ አጥግቦ ወደ ውጭ መሸጥ ችሏል።

የከብት ርባታም ቢሆን በየቤቱ የሚረባው አመርቂ ካለመሆኑም በላይ የአፈር መሸረሸርን ያበረታታል። ስለ እርሻ ከተነሳም ዝናብ ጠብቆ በሰፊው ለማረስ ስለማይቻል በመንግሥት ጥረት ግድቦችና የመስኖ ልማት መስፋፋት ነበረበት። በርካታ ኢንጂኔሮች ያስተማረው የኢትዮጵያ ገበሬ አሁንም የሚያርሰው በፊት በለመደው በጥንቱ ሞፈርና ቀንበር ነው።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት 40% ያህሉ በደን የተሸፈነ ኹኖ እያለ ከአውስትራልያ ባሕር ዛፍ አስመጥተው ተክለዋል። ሆኖም አሁን ወደ 3% ያህሉ ስለቀረና የሰሃራ በረሐም እየሰፋ ስለመጣ በርትቶ ዛፍ እንደመትከል ፈንታ ጭራሽ ለማውደም ርብርቦሽ ይደረጋል። በየአሥር ዓመት ይደጋገም የነበረው ድርቅ በየሦስትና አራት ዓመት እየተመላለሰ ስለመጣ አገሪቱ ለሰው መኖሪያ ተስማሚነቷ እየቀነሰ ነው። በቀኃሥ የመጨረሻ ዘመን ሚኒስትሮችና መኳንንቶች የዛፍ ደን እየተሰጣቸውና እየቆረጡ ሸጠው ባለገንዘብ መሆን ጀምረው ነበር። በተለይ በአርሲ የተደረገው የደን ጭፍጨፋ የሚያስተዛዝብ ነበር። ደርግ ደግሞ ሥልጣን ሲይዝ ካድሬዎቹ ዛፉን ጨፍጭፈው በገንዘቡ ፈነጠዙበትና አገሪቱ አረንጓዴ መሆንዋ ቀርቶ ቢጫ መሆን ጀመረች። በኋላ ለይምሰል በአዲስ አበባ እንጦጦና የካ ጋራዎች ላይ ተማሪን ሰብስበው ዛፍ እንዲተክሉ ሲያስገድዱ ተማሪዎቹ ደግሞ ችግኙን በመዘቅዘቅ እየተከሉ ሲቀልዱ ከርመዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፊደላችንን ለብዙ ዘመን ጠብቃ እንደኖረችው ሁሉ አሁንም በየአድባራቱና በየገዳሙ ዛፎቻችንን በመጠበቅ አስተዋጽኦ እያደረገች ትገኛለች። ይሁን እንጂ ከዚያው ጎን ለጎን ሌሎችም ጥፋቶች እየተስተዋሉ ነው። ለምሳሌ በ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቅርሳ ቅርስ ባለ አደራ ጽሕፈት ቤት እንጦጦ ማርያም አጠገብ የሚገኙትን ዛፎች በመሸጥ ዛፉን ሁሉ አስቆርጦ በምትኩ እንዲተከል አላደረገም። በመሃሉ አፄ ምኒልክ በመጀመሪያ እንጦጦ ላይ የተከሉትን አምስት ዛፎች የቆረጠው ማን እንደሆነ አልታወቀም። እንዲሁም ቀሩንዮ የነበረው በንጉሥ ኃህለ ሥላሴ የተተከለው ዛፍም ተቆርጦ ጉቶው ብቻ ቀርቷል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ ከዋናው ቤቱ ይበልጥ ለአጥር ያለው ስሜት (Fence Mentality) ትልቅ ነው። አጥሩ ሦስት ሜትር ርዝመት ላይ ከመድረሱም በላይ• ጥድ፣ አጋምና ኮሽም እየተከለ መንገድ



ከማጣበቡም ባሻገር በግቢው የሚበላ ፍሬ የሚሰጥ ወይም የደን መመናመንን ለመግታት የሚያግዝ ዛፍ ሲተክል አይታይም። በአሁን ጊዜ የሚሠሩት የአጥር በሮች ከከባድነታቸው ሌላ ቁመታቸው ከሦስት ሜትር ይበልጣል። ፋሽን እየሆነም ስለመጣ አጭሩን አሮጌ በር እየለወጡ በአዲሱና በረጅሙ በር በመተካታቸው ከተማው ሰፊ እስር ቤት ከመምሰሉም በላይ እንደ መካከለኛ ምስራቅ አገሮች ኋላ ቀርነታችንን ያሳያል። አጥር ለከፋ ቀን ከምንም እንደማያስጥል በቀይ ሽብር ዘመን ታይቷል። ቀደም ብሎ የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የአጥር ቁመት ከ25 እስከ 50 ሳንቲ ሜትር እንዲሆን የውስጥ ደንብ ነበረው። የራሱን የግቢ አጥር ግን ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በብረት አሳድጎታል።

ከአገልግሎት አውታር መንገድን በተመለከተ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ጣሊያን በአምስት ዓመት የወረራ ዘመን የሠራቸው መንገዶች ደረጃውን ባልጠበቀ እድሳት ብቻ አገልግሎታቸውን ሲቀጥሉ ዘላቂነት ያለው የመንገድ ሥራ አልተሠራም። የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን ድርጅት ለነዚህ መንገዶች የጥገና ሥራ ያፈሰሰው ገንዘብና የሥራው ውጤት አይመጣጠንም። ያስመጣቸውንም መሣሪያዎች በዘዴ የተገለገለባቸው አይመስልም። ለዚህም ዋናው ምክንያቱም መጋዘን አጣብበው ሊቀመጡ ባልተገባም ነበር የሚለው ግምት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ኤኮኖሚውን የሚያሻሽል ምንም አመርቂ ሥራ ባለመሠራቱ ተምሮ ለሥራ የተዘጋጀው ኃይል ሥራ ፈት እየሆነ አገሪቱ ከቅኝ ግዛት በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት ነጻ የወጡት የአፍሪካ አገሮች እየበለጧት ሲሄዱ ያለፈን ታሪክ ብቻ እያወሩ በመኮፈስ ጊዜ ተቃጠለ። ታሪክ ያለው ሕዝብ ሥነ ልቦናው ከፍ ያለ መሆኑ አያጠራጥርም። ልንኮራበትም ይገባል። ግን እየተራብንና በአሁኑ ዘመን ያለነው እንደበፊተኞቹ አባቶቻችን ጠንክረን ሳንሠራ ዘመናችንን ማሳለፍ አይገባም። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ሄደው ለጃንሆይ "ከአፍሪካ አገሮች በሥልጣኔ ወደ ኋላ ቀረን" ብለው አቤት ሲሉ ጃንሆይ "ኢትዮጵያን ማወዳደር ያለባችሁ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ጋር ነው" ብለው ሲናገሩ ተማሪዎቹ በነገሩ ስቀው ተመለሱ። ይኸ የሚያሳየው በገዥውና በተገዥው መካከል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ነበር።

ቀደም ብለን ቀዋሚ ሥራ ባለመሥራታችን ዛሬ ልጆቻችን በየዓረቡ አገር ለግርድናና ለአሽከርነት ለመሄድ በሚያደርጉት ጥረት የተሳካላቸው

በአጠቃላይ የመንግሥትን ሁኔታ ለመረዳት አዲስ አበባን በመመልከት ብዙ መረዳተ የቻላል። በተለይ አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የንግድ፣ የመገናኛ ማዕከል ስለሆነች አዲስ አበባ ቁጭ ብሎ ስለጠቅላላው አገር ብዙ መረዳት ይቻላል። አዲስ አበባን ብቻ በመመልከት አገሪቷ ራዕይ እንደሌላት እንረዳለን።

## የአዲስ አበባ ከተማ አመራር

የመጀመሪያው የአዲስ አበባና የጎንደር ከተሞች ከንቲባ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጎሹ በ1901 ዓ.ም የአዲስ አበባ ማኅበር የሚባለው እንደተቋቋመ ማስተዳደር ጀመሩ። ብላቴን ጌታ ኅሩይ በ1912 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆነው ሲሾሙ ስሙን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አሉት። ማዘጋጃቤት ለሚለው ቃል በእንግሊዝኛ የሰጠነው ትርጉም ሚዩኒሲፓሊቲ (Municipality) የሚለውን ነው። በመሠረቱ ሚዩኒሲፓሊቲ ማለት ራስ ገዝ የሆነ ከተማ ወይም ማኅበረ ሰብ ማለት ነው። ሚዩኒሴፕ ደግሞ የሚዩኒሲፓሊቲ ነዋሪ ማለት ነው። ዋናው አስተዳዳሪም ከንቲባ (Mayor) የሚባል ማዕረግ ይኖረዋል። የከንቲባነት ማዕረግ የከተማውን ክብር ከፍ የሚያደርግ ስለነበረ የከንቲባዎች ልዩ ልብስም ነበር። በተለይ ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ልብሳቸውን ለብሰው የከተማውን ቁልፍ ለክብር እንግዶች ሲያበረክቱ ያኮሩ ነበር።

ከ1942 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ አበባ የዓለም ከተሞች ማኅበር አባል ነበረች። በዚህም ምክንያት ከተማዋ በቻርተር የምትተዳደር በመሆኗ ከንቲባዎቹ በየዓመቱ በሚደረገው የዓለም አቀፍ ከተሞች ስብሰባ ላይ ይገኙ ነበር። ከተማው የሚተዳደርበት ቻርተር ስለነበረው የከተማው ምክር ቤት በሕዝብ ተመርጦ ምክር ቤቱ በተራው ሦስት ዕጩ ከንቲባዎች ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርብና ጃንሆይ አንዱን መርጠው ይሾማሉ ይላል። ይሁንና ይህ አሠራር ተፈጻሚነት ነበረው ይባል እንጂ በዘመኑ ጃንሆይ ከመጠን በላይ ይፈሩ ስለነበረ እሳቸው የፈለጉትን ይሾሙና ይሽሩ ነበር እንጂ ዴሞክራሲው በጋዜጣ ለሕዝብ ከመደለያነት አልፎ ተፈጻሚነት አልነበረውም። አንዱ ባለሥልጣን ከሌላ የመንግሥት ሥልጣን ላይ ተነስቶ ሲሾም በፈለጉት ሰዓት ደግሞ በቦታው የነበረውን ከንቲባ ሌላ ሹመት ሰጥተው ያነሱታል። •





ከንቲባ ዘውዴ ገብረሕይወት

ከጠላት ወረራ በኋላ ደጃች ውቤ መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደገና የተቋቋመው የማዘጋጃ ቤት ባለመታደል በነቀዘ አስተዳደር የተደቆሰ ቤት ነበር። ከመነሻው በብዛት የቤተ ክህነት ሰዎች፣ በደርግ ጊዜ ካድሬ የሞላበት ሲሆን በሹመት ከተመደቡት ከንቲባዎች መካከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት የነበሩት ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ ዕቅዶችን በማዘጋጀት፣ ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ቋሚ ሥራዎችን በመሥራት፣ ከንቲባ ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ ለከተማው የእግር መንገዶች አቅድ በመስጠት፣ ከንቲባ ዘውዴ ተክሉ ከተማው ውስጥ መሠረተ ልማትን በማቋቋምና በማሠራጨት ይታወቃሉ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዘውዴዎች በተደጋጋሚ የከንቲባነት ሹመት አግኝተዋል። ከሌሎችም ከንቲባዎች የሚታይ ሥራ የሠሩት ዘውዴዎቹ ነበሩ። እዚህ ላይ ሊታወስ የሚገባ ነገር ቢኖር አሁን

በመሠራት ላይ ያለውን የቀለበት መንገድ ያቀዱት ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ እንደ ነበሩ ይታወቃል።



ከንቲባ ዶ/ር ኃ/ጊዮርጊስ ወርቅነህና ባለቤታቸው ዶ/ር ጀምበር

ለመወደድ ሲል ደርግ በጊዜያዊነት በነጭ ሊስት እየፈረሙ ይሠሩ የነበሩትን ጊዜያዊ ሠራተኞችን በጅምላ ቋሚ ሠራተኞች አደረገ። ዕድሜያቸው ከ55 እስከ 85 ዓመት የነበሩ ሁሉ አነስተኛ ዕድሜ በማስመዝገብ ስለተቀጠሩ በሥራው ላይ ከፍተኛ በደል አድርሰዋል። ለምሳሌ በወረዳ 5 የጽዳት ዘበኛ የነበሩት በ1975 ዓ.ም ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ወድቀው በመሞታቸው ዕድሜያቸው 83 ዓመት መሆኑ ታወቀ። ዳሩ ግን በመሥሪያ ቤቱ ፋይል ውስጥ የተመዘገበው ዕድሜያቸው 48 ዓመት ነበር። እንዲሁም በወረዳ 2 የአራዳ አትክልተኛ የነበሩት ዕደሜያቸው 78 ዓመት የሆነው አጭሩና ጎበጥ ያሉ የነበሩት ያስመዘገቡት ዕድሜያቸው 52 ዓመት ሆኖ በሥራ ላይ



ሞተዋል። የማዘጋጃ ቤት አትክልተኞችና ተላላኪዎች በዚህ መልኩ በመሠማራት አዛኝ ቅቤ አንጓች የነበረው ደርግ የሥራ ዲሲፕሊን በአገሪቱ እንዳይኖርና አስመሳይ ካድሬዎቹን እየሰገሰገ የአገሪቱን ዕድገት አወላገደው። አስተዳደሩ ለአዲሱ ተቀጣሪዎች የደንብ ልብስ ሲያሰፋና ስለፖለቲካ ውይይት ሲያደርግ ኖረ እንጂ ምንአልባትም ለከተማው ከአብዮት አደባባይ በስተቀር ጠቃሚ ሥራ አልሠራም።



ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሥላሴ በከንቲባ ልብስ ከሚኒስትሮች ጋር ሆነው ጃንሆይን ሲጠብቁ

በ1967 ዓ.ም የደርግ መንግሥት ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ በዴሞክራሲ መንገድ ተመርጠዋል ብሎ የቀበሌ ካድሬዎችን አስቀመጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የከንቲባ የክብር ልብስ መለበሱ አቋረጠ። እንዲያውም የመንግሥት ፖሊሲ የነበረው ከተማውን በመተው ወደ ባላገር ያተኮረ ስለነበረ አዲስ አበባ የሕዝቡ ቁጥር ቢጨምርም ውጥንቅጡ የወጣ ከተማ ሆነች። ይህ ፖሊሲያቸው የተዋቀረው በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች "ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ብቻ አይደለችም" ብለው ያነሱትን መፈክር መሠረት በማድረግ ይመስላል። ተማሪዎቹ ያሉት ሊላውንም አትርሱት ነበር እንጂ አዲስ አበባ አትሻሻል ወይም አተገንባ አልነበረም። ባገኙት ክፍተት ከንቲባ ዘውዴ ተክሉ

ከጥቂት ሥራ ወዳጆች ጋር ብቻ በመሆን መሠረተ ልማትን እንደምንም ለመሥራት ጥረዋል። እነዚህም በየቦኑ የከነማ ፋርማሲና ዳቦ ቤቶች እንዲቋቋሙ ምድረጋቸውና በተጨማሪም በየቦኑ የፍራፍሬና አትክልት መሸጫዎች ለማቋቋም ሞክረው ውጥናቸውን ሳይጨርሱ መሥሪያ ቤቱ ወደ አዲስ አበባ አስተዳደር ደረጃ ዝቅ አለና ሥራው ቀርቶ ፖለቲካ ማናፈስ ተጀመረ።

በ1928 ዓ.ም የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፒየር ላቫል ስለወልወል ግጭት ጉዳይ በሚወያይበት ጊዜ አዲስ አበባ የሚለውን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰማ “አበባ እንዴት ያለ ደስ የሚል ስም ነው” ‘A-be-ba. Que c'est chic, ça. A-be-ba.’ ብሎ አደነቀ። አሁንም ብዙ የውጭ አገር ሰዎች ስሙን በጣም ያደንቁታል። ፈገግ የሚያሰኘው አዲስ አበባ የሚለው ስያሜ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በይፋ የምትታወቅበት ስም ሆኖ እያለ በመንግሥት ሚዲያ ጭምር በሌላ ስም መጥራት ትክክል አይመስልም። አዲስ አበባ ባንትይቀጡ የሚባሉ የታወቁ የሥጋ ደዌ በሽተኛ የሚታጠቡበትን ፍል ውኃ ፊን እያለ ከመሬት የሚወጣበትን አካባቢ ባንትይቀጡ፣ ፊንፊኔ ወይም ፍልውኃ ብለው ሰዎች የሚጠሩት ከደካ አራራ ጉብታ ወረድ ያለ ሥፍራ ነበር። አዲስ አበባ የሚባለው አገር በውስጡ ጉለሌ፣ ኮልፌ፣ ኮተቤ፣ እንጦጦ፣ ቀጨኔ፣ ገፈርሳ፣ አዲስ ከተማ፣ አራዳ፣ ረጲ፣ የካ፣ ፍልውኃ ወይም ፊንፊኔና ከዚያም በላይ በርካታ ቦታዎችን ያጠቃልላል። እየሰፋ ሲሄድም ቃሊቲ፣ ገርጂ፣ ላፍቶ፣ ኢንዶዴ(ቦሌ)፣ ቀራንዮ፣ ታክለውበታል። ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ የሱስ የአፄ ምኒልክ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው የአዲስ አበባ የበፊት ስሙ ፊንፊኔ ነበር ብለው ስለጻፉ በርካታ ሰዎች ይህንኑ በመከተል ሲያስተጋቡ አቶ በሪሁን ከበደ ደግሞ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው እንዶጥና ይባል ነበር በማለት ጽፈዋል። የኦሮሞ ተወላጆች ግን ሸገር እያሉ ይጠሩት ነበር። አዲስ አበባ በመሠረቱ ግን አጠቃላይ ስም የነበራት አይመስልም። መጀመሪያ የተሠፈረበትን ስፍራ የከተማው ስም ለማድረግ ከተፈለገ እንጦጦ ቅድሚያ ይኖረዋል።

በተረፈ የውጭ አገር ሰዎች ስለ አዲስ አበባ ከተማ ሲገልጹ መላቢስ ከተማ መሆንዋ እንደሚገርማቸው ነው። ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት የአዲስ አበባን ከተማ ሥርዓት ለመስጠት ያልሞከሩት ነገር አልነበረም። ዶሮ እንኳን ወደ ገበያ ስትመጣ እንዳትንጠለጠል የከለከሉ ሰው ነበሩ። ጋሪን፣ ከብቱን ከከተማ ያወጡና አሁን ያለውን የማዘጋጃ ቤት



ሕንጻ ያሠሩ ሰው ናቸው። በተረፈ እሳቸው ለአዲስ አበባ የሠሩትን ለመዘርዘር ቢሞከር ራሱ አንድ መጽሐፍ ይፈጃል። ከተማው ግን ከእሳቸው በኋላ ስንት ሕጻናት፣ ሽማግሌዎችና እርጉዞች በሚዘዋወሩበት መንገድ በሬ አስደንብሮ የሚነዳባት ከተማ ሆናለች። ደንብ ቢወጣም አስፈጻሚ አካል ስለሌለ ደንቡ ራሱ የሚሰጠው ጥቅም አይኖርም። በጃንሆይ ዘመን መንግሥት ሥነ ሥርዓት አስከባሪ ፖሊስ ለጥቂት ጊዜ እንደነበረ ይታወሳል። መንገድ ዳር ሰዎች ሲጸዳዱ ይዘው የሚያስቀጡ የታወቁና የሚፈሩ የማዘጋጃቤት ሥርዓት አስከባሪዎች ተመድበውም ይሠሩ ነበር።

በመሠረቱ ብዙ አገሮች እንደሚያደርጉት ዋና ከተማው ከነአካባቢው ተከልሎ በራሱ የሚተዳደርና የሁሉም ዜጋ ንብረት የሆነና የተለየ አካባቢ መኖር ይገባው ነበር። ስለሆነም መደረግ ያለበት አዲስ አበባን ከ75 ኪሎ ሜትር ባላነሰ ራዲየስ ከልሎ በሰሜን እስከ ደብረ ሊባኖስ፣ በምስራቅ ሞጆን፣ በደቡብ ቡኢና ቱሉቦሎን፣ በምዕራብ ግንጪን ጨምሮ የአዲስ አበባ ክልል ማድረግ የመጨረሻ ችግር ፈቺ ይሆናል። ምክንያቱም ለከተማው ነዋሪ ቆሻሻ መጣያ፣ ለመጠጥ የዝናብ ውኃ ማጠራቀሚያ፣ የደን ቦታ፣ የአትክልት ቦታ፣ መዝናኛ፣ የዱር አራዊት ክልል፣ የከብት ማደለቢያ፣ የተፈጥሮ ገጽታ፣ የፋብሪካ መንደር፣ የምርምር ስፍራ፣ የመቃብር ክልልና ከተማው ወደፊት የሚስፋፋበት መጠባበቂያ አብሮ መታሰብ አለበት። ሰው የሚኖርበትን አካባቢ ብቻ አዲስ አበባ ብሎ ከልሎ መጥራት አንድ ስፌ እስር ቤት እንደመፍጠር ይቆጠራል። እያንዳንዱ ክልላዊ መንግሥት የኢትዮጵያን ዋና ከተማ ልውሰድ ብሎ ከታገለ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድነትን በአእምሮው አያስርጽም። ስለሆነም ለአንድነት ሲባል ጉዳዩን በወቅቱ እልባት መስጠቱ ተገቢ ይሆናል። የፌዴራሉ ዋና ከተማ በክልሉ መኖር ለክልሉ ክብርና ምገስ ከመሆኑ ሌላ የኤኮኖሚ አስተዋጽኦ አለው።

ናይጄሪያ ፌዴራል ካፒታል ቴሪቶሪ የሚባል ክልል አዘጋጅታ በውስጡ የአቡጃን ከተማ ዋና ከተማዬ ብላ ሠርታለች። ይህ ክልል ማንም ወገን የኔነው የሚለው ሳይሆን ማንም ናይጄሪያዊ በአንድነት የሚኖርበት አገርና ከተማ ነው። ሌሎችም አገሮች እንደ ብራዚልና አውስትራሊያ ያደረጉት ይህንኑ ነው።

አይደለንም ግን ገንዘባችንን ስናጠፋ ወደፊት ለሚጠቅመንና ኃብታም ለሚያደርገን ካላጠፋነው ነዳጅ እንኳን ቢወጣ ከድህነት አንወጣም። ነዳጅ እያላቸው ድሃ የሆኑ አገሮች በርካታ ናቸው። ለመጥቀስ ያህል ናየጀሪያ፣ ካሜሩን፣ ትሪኒዳደና ቶቤጎ፣ ቬኔዙዌላ፣ ወዘተ.. ናቸው። አስተዳደሩ ሳይሻሻል ነዳጅ ባይወጣ ይሻላል ብለው የሚከራከሩም አሉ። ምክንያቱም የመጭው ትውልድ የምድር ውስጥ ኃብት እንዳይባክን ለማለት ነው።

የአ.አ. ማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ነባር መንገድ ላይ አፈር ወይም ድንጋይ ቆልለው ወይም መንገዱን ቆፍረው ሲሄዱ ተገቢ ምልክት እንኳን ሳያደርጉ በመሄዳቸው አደጋ ሲደርስ በማግስቱ ተሰበስበው አደጋውን እያዩ 'ሾፌሩ ሰክሮ ይሆናል!' እያሉ ይሳለቃሉ። ለምልክት የፕላስቲክ ኮን እንኳን ማስቀመጥ አልተቻለም። በአዲስ አበባ የአደጋ መከላከያ ምልክት ድንጋይ ሆኗል። እንደ ደቡብ አፍሪካ ባሉ አገሮች የባላገር መንገድ እንኳን ሲታደስ መብራት የተቀመጠበት በርሜል ለብዙ ኪሎ ሜትር ያህል ይደረደራል። አስፋልት መንገድ ላይ ሰዎች በክረምት ለቤት መሥሪያ ጭቃ ሲያቦኩበት በበጋ በርበሬ ወይም ጌሾ ሲያሰጡበት የሚከለክል ኃላፊ የለም። የውስጥ መንገዶችን የፈለገ በድንኳን ሲዘጋው ወይም የእጣቢ ማፍሰሻ አየሆን ሲሄድ የሚናገር የለም። ወለሉን ያልጠበቀ ክፍት ቦይ በየመንገዱ ዳር ስለሚሠራ የከተማን ኑሮ አደገኛ እያደረገው ነው። ተላላፊ በሽታ ገብቶ ሕዝቡን ቢጨርሰው የራሱ ጠላት ራሱ መሆኑን እንኳን ሳይገነዘብ እንዳያልቅ ያሰጋል።

መቼም የአገሪቱ መንግሥትም ኾነ ማዘጋጃ ቤት ለመሥራት የሚፈራው ነገር ቢኖር ድልድይ ነው። አዲስ አበባ ደግሞ ተራራማ በመሆንዋ ያለድልድይ ሥራ በምንም መልኩ ልትሻሻልና ልታምር አትችልም።

## የመንገድ ሥራ

የመንገድ አዘረጋግ ሥርዓትን ለማሻሻል ብዙ አብነቶች ሊነሱ ይችላሉ። አራተኛ ክፍለ ጦር ፊትለፊት የጥንቱ መሿለኪያ (Overpass or Flyover Bridge) አጠገብ ከቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት አንስቶ እስከ አራተኛ ክፍለ ጦር አጥር ማለቂያ ድረስ አፈር ተቆልሎ የመኪናው መንገድ ከባቡሩ ሃዲድ ጋር እንዲገናኝ ተደረጎ ተሠራ።



መንገዱ ከተሠራ ጀምሮ እስከ አሁን በርካታ የሰው ሕይወትና ንብረት ተጎድቷል። ስድስት ወይም ስምንት ምሰሶ ተተክሎ ባቡሩ ላዩን፣ መኪኖች ሥሩን፣ እንዲሄዱ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ የትራፊክ መጨናነቅና አደጋም አይኖርም ነበር። የመንገዱም ትክክለኛ ወለል ይታወቅ ነበር።

የአንድ መንገድ ወለል ካልታወቀ በመንገዱ ዳር የሚሠሩት ቤቶች በዕቅድ ሊሠሩ አይችሉም። የፍሳሽም መሄጃ በዕቅድ ሊሠር አይችልም። የወለል ነገር ከተነሳ የአዲስ አበባ መንገዶች ወለላቸው በጭራሽ አይታወቅም። እያንዳንዱ የአዲስ አበባ መንገድ ሲታደስ አስፋልት በጠጠር ተቦክቶ ይደረብበታል። አቀበት መንገድ ላይ የሚደረበው ጠጠርና አስፋልት ፀሐይ ሲመታው እየተሽበሸበ መኪና ይሰብራል። ከሁለት ዕድሳት በኋላ የመንገዱ ጠርዞች ሲዋጡ ተቆፍረው ይወጡና ከፍ ይደረጋሉ። ውኃ ማስተላለፊያ ጉድጓዶች እየሰመጡ አደገኛ ይሆናሉ። በዚህ ዓይነት ከሃምሳ ዓመት በኋላ በየመንገዱ ዳር ያሉት የምድር ቤቶች ውስጥ ሰው የሚገባው በመስኮት ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው አገር ለአካል ጉዳተኞች ብዙ እንክብካቤ በሚደረግበት ዘመን እኛ አገር ግን ዓይነ ስውሮች በየመንገዱ ዳር ባለው በሰው ሠራሽ ጉድጓድ እየገቡ ተጨማሪ የአካል ጉድለት ሲደርስባቸው እንመለከታለን። ደንቡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ከንቲባው በሕዝብ የተመረጠ ቢሆን ኖሮ ሥራ መልቀቅ ይኖርበት ነበር። ችግሩ ከንቲባዎቹ የመንግሥት ሹሞች ስለሚሆኑ ሕዝቡን አይፈሩትም። ነዋሪው "ለማን አቤት ይባላል" ሲል የሚያሰማው ምሬት ብዙ መልዕክት እንዳዘለ ሥልጣን ላይ ያሉት የሚገባቸው አይመስልም።



ሙሴ ሚናስ

## የከተማ ዕቅድ

የአዲስ አበባ መሪ (ማስተር) ፕላን እየተባለ የሚወራው ለሕዝብ የተደበቀ ግን ሰውን ውዥንብር ውስጥ የሚከት ነው። የልምዱ

መሃንዲስ ሙሴ ሚናስ በየመኳንንቱ ቤት ሲደርሱ መንገዱን አጠፍ እያደረጉ የተቻላቸውን ጊዜው በሚፈቅደው መሠረት ሠርተዋል። ሰውየው በጣም የታወቁ ስለነበሩ ሕዝቡ ከዚህ በታች ያለውን ገጥሞላቸዋል።

ጣሊያንም መጣ ሄደ ተመለሰ
እንግሊዝም መጣ ሄደ ተመለሰ
ሚናስ ብቻ ቀረ ቤት እያፈረሰ።

አስቀድሞውኑ ሁሉ ነገር በዕቅድ ቢሠራ ኖሮ ቤት ማፍረስን ምን ያመጣው ነበር። ከሙሴ ሚናስ በኋላ የነበሩትም መሃንዲሶች መንገድ ብቻ ሳይሆን ድልድይም አጣምመዋል። ከጉለሌ ወደ ቀጨኔ የሚወስደው መንገድ ሲሠራ የወይዘሮ ጅፋሬ ቤት ላይ የሚያልፈውን መንገድ ለማሸሽ ድልድይ ማጣመም ነበረባቸው። የወሎ ሰፈር መንገድም ተጣሞ የተሠራው በዘመኑ በነበረ ባለሥልጣን ተጽዕኖ ነው ተብሎ ተወርቷል። በደርግ ዘመን የነበሩት መሃንዲሶች ከተማው ሳይሆን ራሳቸው ያለ ይሉኝታ ብዙ ተጠቅመዋል ይባላል። የሚያሳዝኑት ንጹህና ችሎታ ያላቸው መሃንዲሶች አብረው መወቀሳቸው ነው። መሪ ፕላን የሚባለው ለሕዝብ ይፋ ሆኖ ስሜት ያለው አጥንቶት ቢተችበትና ውሳኔ መጨረሻ ላይ ቢደረስ ይሻል ነበር። ይህ ሆኖ ቢሆን ኖሮ በየጊዜው መሪ ፕላኑ እየተሻሻለ ነው እየተባለም ምክንያት አይሰጥም ነበር።

አዲስ አበባ ራዕይ የሌለው ከተማ ስለሆነ ከስንት ዓመት በኋላ ኦሊምፒክ እንደሚካሄድበት፣ ከስንት ዓመት በኋላ የሕዝቡ ብዛት ስንት ሚሊዮን እንደሚሆን፣ ሕዝብ በምን ማመላለሻ ወደፊት እንደሚጓጓዝ፣ አይታወቅም። ለሕዝብ መናፈሻና ለፓርክ የተከለሉ ቦታዎች ለግለሰብ መኖሪያ እየተሰጡና እየተሸጡ አልቀዋል። ልክ አፄ ምኒልክ ጃንሜዳን እንደከለሉት ጣሊያንም ወደ ኮልፌ በሚወስደው መንገድ በስተቀኝ ያለውን ከአሁኑ አወቶቡስ መናኸሪያ በላይ ያለውን ቦታና የኳስ ሜዳ እየተባለ የሚታወቀውን ለጥ ያለ ሜዳ ከልሎ ለሕዝብ መናፈሻ ያስቀመጠውን ሕዝብ ተመርቶት አሁን ችም ችም ያለ መንደር ኾኗል።

ቀደም ብሎ ከለገሃር እስከ ቦሌ የተዘረጋው የሃዲድ መስመር ሊያገለግል ሲችል መዘጋቱ የማን ጥፋት ወይም ችላ ባይነት ነው? መንግሥት ራሱ የሕዝብ ማመላለሻ ስላልሠራ ኃላፊነቱን ለባለታክሲዎችና ለአንበሳ አውቶቡስ በመተው መሃል ከተማዎች መናኸሪያ እየሆኑ ነው። አደባባዮችም የአወቶብስ ጣቢያና ጋራዥ



እየመሰሉና የከተማው ውስጥ የመኪና አነዳድም በግራ ይሁን በቀኝ ግራ እያጋባ ነው። የምኒልክ አደባባይና ለገሃር የሞዓ አንበሳ አደባባይ የአውቶብስ ጋራዥ ሆነዋል። ኢትዮ ፍሩት የእግር መንገድ ላይ ድንኳን ተክሎ አትክልት ሲሸጥ መንገድ ዘግቶሃልና ተነስ የሚለው የለም። ከንቲባ ዘውዴ ገብረ ሕይወት ያስወገዱትን የእግር መንገድ ላይ ሱቆች የኮካ ኮላና ፔፕሲ ኮላ ሱቆች እንደገና ተደርድረውበት መንገድ እያጣበቡ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ስለ እግረኛ መንገድ ከማንሳቱ መተው ይሻላል። የትራፊክ መብራቶችን ሲገጥሙ እንኳን ስለ እግረኛ የሚታሰብበት አይመስልም። በዓለማችን ካሉ ትልልቅ ከተሞች መካከል ሕጻን ልጅ በጋሪ (Perambulator or Pram or Push Chair) እየገፉ የማይወጡበት ከተማ አዲስ አበባ ነው።

ለእሳት አደጋ የሚያገለግል ግፊት ያለው ውሃ አዲስ አበባ ውስጥ በየዋና መንገዶች ዳር ለመግጠም ታልሞ አያውቅም። በአሁን ሰዓት የሚሠራው ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ያለው ብቻ ነው። የእሳት አደጋውም ድርጅት ከከተማው ዕድገት ጋር አብሮ የሚሄድ አይመስልም። አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ የውሃ ጉድጓድ በነበረ ጊዜ ልጆች ሲገቡበት የእሳት አደጋ ይጠራና ሲመጣ ይዞ የሚመጣው ነገር ቢኖር ሬሳውን ዘንጥሎ የሚያወጣ መንጠቆ እንጂ ኦክሲጅን ተሸክሞ ጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ ልጁን በሕይወት ለማውጣት ሲሞክር ታይቶ አይታወቅም። የአዲስ አበባ ነዋሪ ከክፉ ነገር ሰውረኝ እያለ መኖር ልምዱ ሲሆን አሁን ደግሞ አትመመኝ ማለት ጀምሯል። ምክንያቱም ለድንገተኛ ህክምና የተዘጋጀ ሃኪም ቤት እየጠፋ ስለሄደ ነው።

የፎቆች ከፍታ እያደገ ሲሄድ የእሳት አደጋ ድርጅትም እስከ ሄሊኮፕተር ድረስ የመጠቀም ልምድ ማዳበር ይጠበቅበታል። ትልቅ እሳት በተነሳ ቁጥር የአቪዬሽንን የእሳት አደጋ እርዳታ እየጠበቀ የከተማው የእሳት አደጋ ክፍል ሊቆይ አይገባውም። እስከ አሁን የሚታየው ቤት ሲቃጠል አመዱ ላይ ውሃ አፍስሶ መመለስ እንጂ ቤቱን ከእሳት ቃጠሎ የማዳን ችሎታ ድርጅቱ ያለው አይመስልም።

አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ልትሆን ዕድሉ ነበራት። እኛ ግን ጠንክረን ወንዞቻችንን የሚያሻግር ድልድይ እንኳን ለመሥራት ስላልተባበርን ዕድሉን አፈር እየቆለሉ ድልድይ ለሚሠሩት የናይጀሪያ ዋና ከተማ ለእነአቡጃ ሳናስረክብ አንቀርም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ብልፅግና ከጅምሩ ስለተበላሸ እስካለንበት ዘመን ድረስ እያሽቆለቆለ እንጂ እየተሻሻለ ሲሄድ አልቻለም። የኒው ዮርክ ከተማ የምትታወቀው

በተለይ አገሪቷ ገና ያልተነኩ ብዙ ዕጽዋቶቿ ባለቤት ስለሆነች የባህል መድሃኒቶችን ለመመርመር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። እንዲያውም የበቁ ሰዎች "መድሃኒቱ እደጃችሁ ነው" እያሉ በመሮህ ላይ ናቸው።

ይህች ዓለም የቻለ የሚኖርባት (survival of the fittest) መሆንዋን ማወቅ ይኖርብናል። አለበለዚያ እንደ ቀይ ህንዶች ወይም እንደ አቦርጂኒስ እኛ አልቀን ሌሎች ሕዝቦች ይህችን ድንግል መሬት ይኖሩባታል።





# ምዕራፍ ፴፪

## ጃንሆይና ዴሞክራሲ

ዴሞክራሲን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት አብርሃም ሊንከን ያብራሩት እንዲህ ብለዋል።

"Democracy is the government of the people, by the people for the people."

ትርጉሙም "ዲሞክራሲ የሕዝብ ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ የሆነ መንግሥት ነው"

ይሁንና ዲሞክራሲ ብዙ የሚያጠቃልላቸው ጉዳዮች ስላሉት በዚህ ትርጉም ብቻ ለመወሰን ያስቸግራል። መንግሥት የሕዝብን መብት እየገፈፈ ግዴታውን ብቻ እንዳይቆልል ይወስናል። በጠቅላላው ውስጠ ሚስጥሩ ሥልጣንን የሕዝብ ማድረግ ነው።

የመንግሥት መዋቅር ሕዝብ በሚመርጣቸው ሳይፈልጋቸውም በሚሽራቸው ባለሥልጣኖች የሚገነባ መሆን ሲኖርበት ውሳኔም የሚሰጠው በአብዛኛው ድምጽ የሚደገፍ ሲሆን ነው። ያምሆኖ ግን የድምጽ ብዛታቸው ትንሽ ነው ተብሎ የጥቂቶችም መብት አይደፈርም። የሥልጣን መፍለቂያ ሕዝብ ሲሆን አስፈጻሚዎችን እንደሚመርጥ ሁሉ ሕግ አውጭዎችንም ይመርጣል።

ምንም እንኳን ጥንታዊው የንጉሠ ነገሥት መንግሥት በጥንቱ ሥርዓት መሠረት በውልደት ወይም በውርስ ሥልጣን ላይ የሚወጣበት ሥርዓት ስለነበረ በልምድ ትክክል ነው ተብሎ በወቅቱ በሕዝብ በመታመኑ እንደ ሥርዓት ሲሠራበት ኖሯል።

የዴሞክራሲን ሥርዓት በተግባር ለመተርጎም አስቸጋሪ ቢሆንም በቅን ልቡና ወደእሱ የሚወስድ መንገድ የከፈተ መሪ ሊመሰገን ይገባል። አዲሱ ሥርዓትም ሙሉ በሙሉ ያለ እንከን በትክክል ይሠራል ብሎ መጠበቅም ችኩልነት ይሆናል። ለመጀመሪያ ጊዜ ሚኒስትሮችን በ1898 ዓ.ም የሾሙትና የመንግሥትን ሥራ አከፋፍሎ ለመሥራት የሞከሩት አፄ ምኒልክ ነበሩ። ምንም እንኳን በ1911 ዓ.ም በመሃል ሰፋሪዎች አድማ ሚኒስትሮቹ ቢሻሩም ተመልሶ ሕግና ደንብ ወጥቶ አዳዲስ ሚኒስትሮች በጃንሆይ ተሹመዋል። አሠራር ላይ ሚኒስትሮቹን እንዲረዷቸውና እንዲያማክሯቸው የውጭ አገር ሰዎች ተቀጥረውላቸው ነበር። ከጣላት ወረራ በኋላ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንደገና ሲቋቋሙ ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሚኒስትሮች እየተሾሙ ሥራቸውን ማካሄድ ጀምረዋል።

ይህ አጀማመሩ ጥሩ ሆኖ የነበረው እርምጃ እየዳበረና እየተሻሻለ መሄድ ሲገባው ከጣላት ወረራ በኋላ ሕዝቡ ብዙ ሲጠብቅ መልሶ የንጉሡ ነገሥቱ ፍጹማዊነት እየጎላ በመሄዱ ምንም የተመቻቸ ሁኔታ ቢኖርም ሥልጣኔውን መልሶ መግታት ተጀመረ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ታይቶ ከሳቸው ዘመን በኋላ እንደገና ደብዛው ጠፍቷል። ምንም እንኳን ፍጹማዊ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ቢሆንም በየመሥሪያ ቤቶች የተመደቡት ሚኒስትሮች ባጀታቸውን ካስፈቀዱ በኋላ ሥራቸውን በነጻነት ይሠሩ ነበር። ስለሆነም እያንዳንዱ ሚኒስትር የነበረው ማዕረግና ክብር ነጻነት እንደነበረው ያስረዳ ነበር።

ከንጉሡ ነገሥቱ ዘመን በኋላ የነበረው የወታደር መንግሥት በየመሥሪያ ቤቱ አንዳንድ ቋሚ ተጠሪ መድቦ በተጨማሪም በሌላ የሚታዘዙ ካድሬዎች በመሰግሰግ ሚኒስትሮቹ ጥላ ቢሷቸው ለሥራው ሁሉ ወሳኝ ጠፍቶ አገሪቱ ወደፊት እንደመሄድ ባለህበት ሂድ ተጀመረ። የብዙ ሚሊዮን ብድር በአገሪቷ ስም የሚፈርሙት ሚኒስትሮቹ ሳይታመኑ ቀርተው የሚኒስትሩ መኪና በሾፌሮች ቁጥጥር ሥር እንዲውልም ተደርጎ ነበር።

በሙያ ማኅበራት በኩል የሄድን እንደ ኾነ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት እያንዳንዱ የሙያ ማኅበር ራሱ በመረጠው ወኪሉ ይንቀሳቀስ ነበር። በደርግ ዘመን መንግሥት ግን የገኘው ወገኖች



ተመርጠው የመንግሥት አፈቀላጤ ይሆኑና አሽከርነቱ ሲመራቸው መጨረሻ ላይ አገር ጥለው ይጠፉሉ፣ ሲዘላብዱ ተይዘው ይታሰራሉ፣ ወይም ይገደላሉ።

ተማሪዎች የንጉሡ ነገሥቱን መንግሥት እንደሚቃወሙ እየታወቀ ከሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች አንስቶ እስከ ዩኒቨርስቲ የየራሳቸውን ማኅበራት ሥራ አስኪያጆች እየመረጡ ዲሚክራሲያዊ እንቅስቃሴን ይለማመዱ ነበር። በደርግ ዘመን ግን በከፍተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች ቀርቶ በዩኒቨርሲቲዎች የዴሞክራሲያዊ ማኅበሮች ሊቋቋሙ አልቻሉም።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት ለፓርላማ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ተመራጮች እየዞሩ ለመራጮቹ ዓላማቸውን እያስረዱ ይወዳደሩ ነበር። ከሳቸው ዘመነ መንግሥት በኋላ የተመራጮች ፎቶግራፍ በየቦታው ይለጠፍና ዓላማቸውንም ለመራጮቹ ሳያስረዱ ይመረጣሉ። አመራረጡ ላይም መራጩ ሕዝብ ቅሬታ ነበረው። ሕዝቡም አንዳንዴ ያልመረጠው ሰው እንደሚመረጥ ያውቃል።

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ሊቋቋም ያልቻለው የፖለቲካ ፓርቲ ነበር። በደርግ ዘመን ፓርቲዎች ተመሥርተው መጨረሻ ላይ በኮሙኒስት ሥርዓት አገሪቱ ስለምትመራ አንድ ፓርቲ አገሩን ሲያስተዳድር ቆየ። እሱውም የገዥዎች ስብስብ ስለሆነ ወዛደሩን እወክላለሁ ቢልም የሚያጅበው ስላነሰ በመንግሥት ሥልጣን ከአንድ እርከን በላይ ያሉ ባለሙያዎች ሁሉ በግድ አባል ካልሆኑ ከሥራቸው ይነሱ ነበር። መጀመሪያ ላይ ተቋቁመው የነበሩት ማወናበጃ ፓርቲዎችም ከሰሙና አባሎቹ በአሐዳዊ ፓርቲው በኢሠፓ ተዋጡ።

ብዙውን ጊዜ ስለዴሞክራሲ የሚወተውቱ መንግሥታት ዴሞክራት አለመሆናቸውን ነው የሚያመለክቱት። ለምሳሌ ምሥራቅ ጀርመን ዴሞክራት ነን ለማለት የጀርመን ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ተብለው ሲጠሩ የምዕራብ ጀርመን ግን የጀርመን ሬፑብሊክ ተብለው ይታወቁ ነበር። እንዲሁም የሰሜን ኮሪያ አሁን ድረስ የኮሪያ ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ ሲባሉ የደቡብ ኮሪያ ግን የኮሪያ ሬፑብሊክ ተብሎ ይጠቀሳል። ኮሙኒዝም በዴሞክራሲ የሚያምን ፍልስፍና ሆኖ አመራሩን የጨበጡት በተግባር ላይ በዴሞክራሲ ላይ በማሾፋቸው ከብዙ ደም መፍሰስ በኋላ የተገኘው ውጤት ተቀለበሰ። ይህም የሚሆንባቸው ምክንያቶች

ክፍለ ጦር ወታደሮች ደርሰውባቸው ልጅ በላይና ጥቂት ሰዎች ተያዙ። ፊታውራሪ አድማሱ ግን እጃቸውን ሳይሰጡ የተደበቁበት ዋሻ ውስጥ የሚያቋርጥ ነስር ሰለፊሰሳችው ሕይወታቸው አለፈ። በዚሁ ጥፋቱ ችሎት ላይ ቀርቦ የሞት ፍርድ ስለተፈረደበት አዲስ ከተማ የዚያን ጊዜ በግ ተራ አሁን የአዲስ ከተማ ትምሕርት ቤትና አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ ቅዳሜ ጥር 5 ቀን 1937 ዓ.ም በስቅላት ተቀጣ። የተሰቀለበት ገመድ በአንገቱ በስተጀርባ በመሆኑ ምክንያት ብዙ ተሰቃይቶ ሞተ። ቅጣቱን ያስፈጸሙት ኮሎኔል መንግሥቱ ንዋይ ነበሩ።

ከሞት ቅጣቱ በኋላ መንግሥት የአርበኝነቱን ውለታ ለመክፈል ጎሹን፣ ባሕሩንና መልአኩ በላይ የተባሉትን ወንድ ልጆቹን በነጻ አዳሪ ትምሕርት ቤት ከማስገባቱም በላይ የኪስ ገንዘብ በየወሩ 30.00 ለእያንዳንዳቸው እየሰጠና በዓመት ሁለት ሙሉ ሱፍ ልብስ እያለበሰ አስተምሯቸዋል።

የበላይ ዘለቀ ተቆርቋሪዎች ብዙ እንደሆኑና በየጊዜውም በየዘፈኑ ስሙ ይታወስ እንደነበረ ይታወቃል። ስለሆነም እንደተሰቀለ የሚከተለው ተገጠሞለታል።

ተሰቀለ ቢሉኝ ሽጉጡ ነው ብዬ
ተሰቀለ ቢሉኝ ጠመንጃው ነው ብዬ
ለካስ በላይ ኖሯል ትልቁ ሰውዬ

አከታትሎም ዘፈን ቢዘፈንለትም በይበልጥ የጃንሆይ ሥልጣን መውረጃ ገደማ ላይ "በላይዬ! ጀግናው በላይዬ!" እየተባለ በሰፊው ይዘፈን ነበር።

## አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ

አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ የራጉኤል ዲያቆን የነበሩና በኋላም አባታቸው አለቃ በነበሩበት ወጨጫ ማርያም በድቁና ያገለገሉ ሲሆን በየጋዜጣው ላይ በሚጽፏቸው ጽሑፎች ጃንሆይ አውቀዋቸው የመንግሥት ሹመት እየሰጧቸው ሲሠሩ የነቀዙ ባለሥልጣኖችን እያሳጡ በንጉሡ ይደነቁ ነበር። መጨረሻ ላይ ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከሁሉ ተጣልተው የማይችሉ መሆናቸውን ስላወቁና ከተያያዙት ንቅዘትን የመዋጋት ተግባር ንቅንቅ እንደማይሉ ስለታወቀ በአምባሳደርነት



ተሹመው ወደ ውጭ እንደተወረወሩ ሲረዱ የጃንሆይንም አስተዳደር ጠሉት። በመጨረሻ ስደተኛ ሆነው የጃንሆይን መንግሥት በመቃወም ኖረው ብዙ ጽሑፎችም ሲጽፉ ቆይተው በአሜሪካን አገር አርፈዋል።

አሜሪካን አገር በስደት ሲኖሩ የደርግ መንግሥት ሥልጣን ይዞ ንጉሠ ነገሥቱን መውቀስ ሲያበዛ ተመልክተው ለርዕሰ ብሔሩ ለጄኔራል ተፈሪ በንቴ የጽሑፍ መልዕክት አስተላለፉላቸው። ጽሑፉም:-



አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ከአሜሪካን ፕሬዚደንት ኬኔዲ ጋር

እያደረጉ ተማሪውን ትምሕርት ሲያቆም እየተቆጡና ምሕረት እየሰጡ ወደ ትምሕርት ገበታቸው እንዲመለሱ ያዝዙ ነበር። በ1962 ዓ.ም እንደተለመደው ንጉሡ ነገሥቱ ንግግር ካደረጉ በኋላ "የአዋጁ አዋጅ" የሚል ለንግግራቸው መልስ ተጽፎ ተበተነ። ጽሑፉን ያረቀቀው ከተማሪው የኮሙኒስት ቡድን መካከል ታዋቂ የነበረው ዋለልኝ ነው ተብሎ ይታመናል። ጃንሆይ በዚህ በተበተነው ወረቀት ክብራቸው ስለተነካ ሕዝቡ በየድርጅቱና በየአውራጃው እየተሰባሰበና እየተወከለ ጃንሚዳ ድንኳን ተተክሎ ከመላው ኢትዮጵያ እየመጣ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ እየቀረበ ታማኝነቱን እየገለጸ ይቅርታ ጠየቀ።

ዋለልኝ መጨረሻ ላይ የሞተው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ ላይ ከዘጠኝ ጓደኞቹ ጋር ሆኖ የተሳፈሩበትን አይሮፕላን ለመጥለፍ ሲሞክሩ በጸጥታ አስከባሪዎች ተተኩሶበት ነው። አንድ የፖለቲካ ቡደን ለጸጥታ ኃይሎች ጠቋሚባቸው ነው ለሞት የበቁትም እየተባለ በሰፊው ተወርቷል።





# ምዕራፍ ፴፱

## የጃንሆይ ወዳጆች

ጃንሆይ ጠላት እንዳላቸው ሁሉ ብዙ የልብ ወዳጆች ነበሩዋቸው። ለረጅም ዘመን አገሪቱን በማስተዳደራቸው የተነካ አብዛኛው ሕዝብ ከልብ የሚወዳቸውና የሚያፈቅራቸው ግርማ ሞገስ የተላበሱ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ። ሕዝቡ ከፍቅሩ የተነሣ ጃንሆይ ተነኩ ማለት ኢትዮጵያ እንደተነካች አድርጎም ይመለከት ነበር። በግልም የንጉሠ ነገሥቱ ሃቀኛና የመንግሥታቸው ጠባቂ የሆኑ ብዙ ወዳጆች ነበሩዋቸው። እነዚህ ሰዎች የጃንሆይን ዘመነ መንግሥት ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሆነዋል። በሌላ በኩል የጃንሆይን ከሥልጣን መውረድ የሚከላከሉት ለራሳቸውም ደህንነት በማሰብም ጭምር ነበር። ከነዚህም ሰዎች መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

### ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ



ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ

ልዑል ራስ ካሣ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሁለት በኩል ይዛመዳሉ። የልዑል ራስ ካሣ እናት ወይዘሮ ትሰሜ ለአባታቸው ለራስ መኮንን የአጎታቸው የራስ ዳርጌ ልጅ ሲሆኑ ለጃንሆይ በእናታቸው በኩል ደግሞ የአያታቸው የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ልጅ ናቸው ወይም ለእናታቸው ለወይዘሮ የሺ እመቤት እህት ናቸው። በዝምድና ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት ልዑል ራስ ካሣ ጃንሆይን

የንግድ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ነበሩ። በኢትዮጵያ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ታሪክ የመጀመሪያው ዋና ዲሬክተር እሳቸው መሆናቸው ነው። በዋና ዲሬክተርነታቸው ጊዜ ጉምሩክንም ያዝዙ ስለነበረና የግሊያንም መምጣት ስደትን እንደሚያስከትል ቀደም ብለው አውቀው ስለነበረ ገንዘብና ወርቅ ወደ እሥራኤል አገር ይልኩ ነበር ይባላል። ከማይጨው መልስ በአገር ውስጥ ከነበሩት የውጭ አገር ቆንሲሎች ጋር በመመካከር ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ የመሄዳቸውን ሃሳብ ካቀረቡት ሰዎች አንዱ ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ አብረው ከተሰደዱትም ባለሥልጣኖች አንዱ ናቸው።

መኮንን ኃብተ ወልድ በ1927 ዓ.ም በልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴ የክብር ፕሬዚዳንትነት የአገር ፍቅር ማኅበር ሲቋቋም ምርጥ ጸሐፊዎችንና ተናጋሪዎችን እየጋበዙ ለሕዝብ ስለወቅቱ ሁኔታ ማብራሪያ ይሰጡ ነበር። ለማይጨው ዘመቻ ማኅበሩ ስንቅ በማሰባሰብና ስለ አገር ጉዳይ ንግግር እያደረገ "የጠቅል አሽከር!" እየተባለ ይፎክርና ይሸልል ነበር። መኮንን ኃብተ ወልድ ከስደት መልስም ይኸንኑ ማኅበር እንደገና አደራጅተው ዘፈን፣ ውዝዋዜና ቲያትር ይታይበት ጀመር።

መኮንን ኃብተ ወልድ አገር ወዳድና ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ከመሆናቸው በላይ ከስደት መልስም በመንግሥት ሥራ ላይ ከፍተኛ አገልግሎት የሰጡ ሰው ናቸው። ከባድ ሠራተኛ ከመሆናቸው የተነሳ የዕረፍት ጊዜ እንኳን አያውቁም ነበር። ከሠሯቸው ትልልቅ ሥራዎች አንዱ የኢትዮጵያ ብር በ1937 ዓ.ም ከወጣ በኋላ ነጋዴዎችን ሰብስበው እንደማርያቴሬዛ ያሉትንና ሌሎች ገንዘቦችን እንዳይለዋወጡባቸው ቃል አስገብተው ከገበያ ያስወጧቸውና አዲሱን ብር በስፋት ሕዝቡ እንዲቀበለው ማድረጋቸው ነው። ሁለት ወንድሞቻቸውም ሚኒስትር ደረጃ ደርሰው በአንድ ወቅት ሦስት ወንድማማቾች በጃንሆይ ካቢኔ ውስጥ ነበሩ።

የእርሻ የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ በ1943 ዓ.ም አራዳ መካከል ዚንጎኒ ፊትለፊት የልዑል ራስ ካሣ ቤት የነበረው ውስጥ የታክሲ ደርሚ (የደረቀ የእንስሳት ገላ) የታየበት የመጀመሪያውን ኤግዚቢሽን ኢትዮጵያ ውስጥ ለአንድ ሳምንት አሳዩ። ቀጥሎም አራዳ መካከል በሚገኘውና በዘመኑ የልማት ባንክ ሕንጻ በሚባለው ላይ "ጥጥ ትክሉ ፍተሉ" የሚል ተንቀሳቃሽ ጽሑፍ እስለጥፈው ሕዝቡን ለሥራ ያነሳሱ ነበር። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለየግላቸው ሁሉንም



ነገር በሚሠሩበት ወቅት ብዙ መዝረክረክ መኖሩን እንደተገነዘቡ ማዕከላዊ የዕቃ ግዢ፣ የሒሳብ አሠራርና ቁጥጥር ከማቋቋማቸው ሌላ የኮንትሮባንድ መከላከያ አደራጁ።

የችርቻሮና ቀላል ሥራዎችን ለአገር ተወላጅ ብቻ እንዲሆን ወጥነው እግብ ሳያደርሱት ሞት ቀደማቸው። ክቡር አቶ መኮንን ኃብተ ወልድ ስለ አገር ወዳድነታቸው ምንም ጥርጥር የሌለው ከመሆኑም በላይ ብዙ ጠቃሚ ሥራ ለመሥራት ወደ ኋላ የማይሉ ሰው ነበሩ። አቶ መኮንን ኃብተ ወልድ በከንቱ ስለሚጠሉ በሁሉም ነገር ላይ ቁጠባ ያደርጋሉ። ስለሆነም ደሞዝ ለሠራተኛ ሲቆርጡ በተቻለ አነስ ያድርጉ ነበር። ገንዘብም ያለምክንያት አትወጣም። በዚህ ምክንያት ሰዎች የሚከተለውን ገጥመውባቸዋል።

መኮንን ኃብተ ወልድ የመከረው ምክር
የበርታ ይብላ የደከመ ይቅር የሚል ነበር።


መኮንን ኃብተ ወልድ

የኾነው ሆኖ ክቡር አቶ መኮንን ኃብተ ወልድ የስለላ መረብ ዘርግተው ጃንሆይን ከአደጋ ሲጠብቁ የነበሩ ከመሆናቸው በላይ በአገር ፍቅር ማኅበር የሚታየው ቲያትርና የሚዘፈነው ዘፈን ንጉሠ ነገሥቱን እንዲያሞግስ ሆኖ ነበር። በመጨረሻ በታኅሣሥ 1953 ዓ.ም ያልተሳካ የመንግሥት ግልበጣ ላይ ከተረሸኑት ባለሥልጣኖች አንዱ ነበሩ።

በተረፈ ወንድማማቾቹና ዘመዶቻቸው በተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶችና አውራጃዎች በአገረ ገዥነት ሹመት ለጃንሆይ ቅን አገልጋይ ሆነው ቆይተዋል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ባለሥልጣኖችን እየጠራ በሚያስርበት ወቅት በተለይ ፀሐዩ ዕንቆ ሥላሴ እጄን አልሰጥም ብለው ተታኩሰው መሞታቸውን የሰማ ሁሉ ድሮም ጀግና እንደነበሩ አስመስክሩ እያለ አሞገሳቸው። እናታቸው ወይዘሮ ፍቅርተ እንኳን በሠፈራቸው የእኔ ልጅ ጀግና ነው እጁን አይሰጥም እያሉ ይፎክሩ ነበር።

በማሊያን ጊዜ ጅሩ ላይ ተሰብስበው የመጀመሪያውን የጀግኖች ማኅበር ከመሠረቱት መካከል ፀሐዩና ተስፋዬ ዕንቆ ሥላሴ፣ ጀኔራል ተድላ፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ደጃዝማች አሉላ በቀለና ሌሎችም መሆናቸው ይታወቃል።


ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

## ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ

ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአባታቸው የአክስት የልጅ ልጅ ከመሆናቸውም በላይ ከተፈሪ ጋር አብረው አፈር እየፈጩ ያደጉ ታማኝ ዘመዳቸውና ወዳጃቸው ናቸው። በማይጨው ጦርነት ጊዜ ጥሩ አድርገው በስሜን በኩል የዘመተውን የጐጃምንና የጎንደርን ጦር የመሩ አዝማች ነበሩ።

በሰላሙም ዘመን በአገረ ገዥነት፣ በተለያዩ አገሮችም የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል። በተጨማሪም ለጃንሆይ የልብ ወዳጅ ከመሆናቸው የተነሳ "በቃዎት ሥልጣንዎን ለልጅዎ ያስተላልፉ" ብለውም በወቅቱ መክረዋቸዋል።



ራስ እምሩ ከሌሎቹ መኳንንቶች የሚለዩት ኃብት ማጋበስን የማይወዱና የነበራቸውን መሬት ለሕዝብ ያከፋፈሉ፣ ቁጥብና ሕዝብ በጣም የሚወዳቸው ነበሩ። ደርግ ለሥልጣኑ የማያስጉት ስለነበሩና በሕዝብም ዘንድ በጣም ተወዳጅ መሆናቸውን እግንዛቤ በማስገባት ምንም ዓይነት ጉዳት አላደረሰባቸውም።

## ራስ መስፍን ስለሺ


ራስ መስፍን ስለሺ

ጠላት ከመግባቱ አስቀድሞ ከሆለታ ገነት ጦር ትምሕርት ቤት ተመርቀው ለሻለቃነት ማዕረግ የበቁና ከዚያም በወረራው ጊዜ በጣም ስመጥር አርበኛ ነበሩ። በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ ሽሮ ሜዳ የሚባለው ሠፈር የነበረውን የጣሊያን ካምፕ ቀን ቀን እንቁላል እየሸጡና እየሰለሉ ሌሊት ሌሊት ሲያተራምሱት ያድሩ ነበር። በኋላም በአምቦ መንገድ መናገሻ ከተማ አጠገብ 'ሴኮንዶ ማይጨው' በተባለው ቦታ የጣሊያንን ጦር ፈጅተው ወደ ጎጃም ተሻግረው ከአርበኞች ጋር ብዙ ጀብዱ ሠርተዋል። ጃንሆይ በስደት በነበሩ ጊዜ አስፈላጊ የሆኑና የሚታመኑ መረጃዎች በማቀበል አገራቸውን ጠቅመዋል። ጃንሆይ ሲመለሱም አርበኞችን በማስተባበር ብዙ የሚያኮራ ሥራ ሠርተዋል።

ከድል በኋላ በአራዳ ዘበኛ ኃላፊነት፣ በአ.አ. ከተማ ከንቲባነትና በአገረ ገዥነት ያገለገሉ ሰው ናቸው። አባታቸው ስለሺ የራስ መኮንን ባለሟል የነበሩና ልጅየውም ምስፍን ስለሺ በጃንሆይ ዘንድ ፍጹም ታማኝ ነበሩ።

ራስ መስፍን ስለሺ ዩኒፎርም በጣም ስለሚወዱ አንድ ጊዜ የሌፍትናንት ጀኔራል ልብስ ለብሰው ጃንሆይን "ይመርቁልኝ" ብለው ስለጠየቁና ጃንሆይም ስለተስማሙ ሌፍትናንት ጀኔራል ሆነዋል። ሆኖም በባህል

የሀማች ሹመት የመጨረሻውን እርከን በመቀዳጀት በ1948 ዓ.ም ራስ ተብለዋል።

በየአካባቢው መሬት መያዝ ይወዱ ስለነበረ የመሬት ከበርቴ ምሳሌ ከመሆናቸውም በላይ ሁኔታው ከብዙ ሰው ጋር አጋጭቷቸዋል። ደርግ ሥልጣን ላይ እንደወጣ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን እጃቸውን የሚሰጡበትን ሰዓት ወስኖ በነበረበት ጊዜ ራስ መስፍን ከከተማ ውጭ ስለነበሩ ሰዓቱ ያለፈ እንደሆን ርስታቸው እንዳይወረስ ሰግተው ስልክ ደውለው መጣሁ በማለታቸውና ሁኔታው በወቅቱ በሬዲዮ ይተላለፍ ስለነበረ ብዙ ሰው በሁኔታው ተገርሟል። በመጨረሻ ርስታቸውም ተወረሰ፤ እሳቸውም ከተረሸኑት ከስልሳ አንዱ ውስጥ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፴፫

# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባህርይና ትክለ ሰውነት

## ትክለ ሰውነት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተፈጥሮአቸው አጭር ሲሆኑ ቁመታቸው አንድ ሜትር ከስልሳ ሴንቲ ሜትር (1.60 ሳሜ)፣ ክብደታቸውም ሃምሳ ኪሎ ግራም (50 ኪግ)፣ የእግራቸው መጫሚያ ትልቅና የቀኙ ወደጎን የሚረግጥ ነበር። ጃንሆይ መልከ ቀና፣ ቀይ፣ ጥርሰ ፍንጭት፣ ትላልቅ ጆሮና አፍንጫ ያላቸው፣ ጠጉራቸው ከግንባራቸው ገባ ያለ፣ ጎፈሬያማ፣ ባለ ሙሉ ጢምና ትልቅ የቅንድብ ጠጉር ያሏቸው ነበሩ። ምንም አጭር ቢሆኑም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ካሉት ንጉሦች ሁሉ ንጉሥ ሲኖረው የሚገባው ግርማ ሞገስ ነበራቸው።

አማርኛ ተናጋሪ ቢሆኑም በተጨማሪ አደርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ በመጠኑ ደግሞ ጀርመንኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ያውቁ ነበር። ሲናገሩ አንዳንድ የሚጫኑዋቸው ቃላቶች የነበሩና የምታስቸግራቸውም ድምጽ "ረ" ስትሆን ድምጻቸው ጎርናና ነበር።

ከማጠራቸው የተነሣና ለክብራቸውም ሲባል ወንበር ላይ ሲቀመጡ ብዙ ጊዜ እግራቸው ሥር ትራስ ይደረግ ነበር።

## ባህርይ

በጠባይ በኩል የሁለት ተፈሪዎችን ስብዕና የተላበሱ ነበሩ ለማለት ይቻላል። አንደኛው ተፈሪ ትሁት፣ ሩህሩህ፣ ለጋስ፣ ሲሆን ሁለተኛው ተፈሪ ደግሞ ቁጡ፣ ጨቋኝ፣ ቂመኛና አናኳሽ ነበሩ። በጠቅላላው ግን ተፈሪ በኅብረት ኩሩ፣ ጨዋ፣ ደፋር፣ ራስ ወዳድ፣ የማስታወስ ችሎታ

# ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን

ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ሐምሌ 20 ቀን 1908 ዓ.ም ተወለዱ።



ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንና ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ

እሳቸውም የራስ ሥዩም መንገሻን ልጅ ልዕልት ወለተ እሥራኤልን አግብተው ልዕልት እጅጋየሁን ወልደዋል። ልዕልት ወለተ እሥራኤል ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ከመጋባታቸው በፊት ከአድዋው ተወላጅ ከደጃች ገብረ ሥላሴ ደጃዝማች ዶክተር ዘውዴ ገብረ ሥላሴን ወልደዋል። ልዕልት እጅጋየሁም እንግሊዝ አገር እንዳሉ የተዋወቁትን የወለጋውን ባላባት የደጃች ሃብተ ማርያምን ልጅ ፍቅረ ሥላሴን አግብተው ሲኖሩ መጨረሻ እስር ቤት እንዳሉ ታመው ሞቱ።

ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ከልዕልት ወለተ እሥራኤል ጋር ከተፋቱ በኋላ ከልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ ጋር ተጋብተው

| | |
|---|---|
| 1 | ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ |
| 2 | ልዕልት ማርያምሥና |
| 3 | ልዕልት ስሂን |
| 4 | ልዕልት ሥፍራሽ ወልደዋል። |



ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ በ1966 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥቱ አልጋ በተነቃነቀበት ወቅትና ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰንም ታመው እንግሊዝ አገር በነበሩበት ጊዜ ተጠባባቂ አልጋ ወራሽ ተብለው ሐምሌ 16 ቀን ተሾሙ።

ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን በስደት እያሉ አምኃ ሥላሴ ተብለው መንገሣቸውን ይፋ ቢያደርጉም ኮሎኔል መንግሥቱን በግል ከማስደንገጡ በስተቀር ምንም ለውጥ አላመጣም። ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ልጃቸው ተጠባባቂ አልጋ ወራሽ ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ በጤና ጉድለት ምክንያት ሊተኳቸው አልቻሉም።

ልዕልት ማርያምሥና የአርበኛውን የደጃዝማች ዘውዴ ጥላሁንን ልጅ አቶ ሰይፉ ዘውዴን አግብተው ብዙ ልጆች ወልደዋል።

ጃንሆይ ልዑል አልጋ ወራሽን እንደ ልዑል መኮንን አያስጠጉም ነበር። እንዲያውም አይወዱዋቸውም እየተባለ በሕዝብ ዘንድ ይወራ ነበር። የማይወዱበትም ምክንያት በሰዉ ዘንድ የሚወራው የልጅ ኢያሱ ልጅ ናቸው ብለው ስለሚጠረጥሩ ነው። ነገር ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ጃንሆይን በቁመት፣ በእርጋታ፣ በአረማመድና በድምጽ ይመስሏቸዋል። እነመንግሥቱ ንዋይ አስገድደው ያስነበቧቸውን አዋጅ ለሰማ ሰው ከጃንሆይ ጋር የድምጻቸውን ተመሳሳይነት በማዳመጥ ልጃቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይቻላል።

ምንም እንኳን ልዑል አስፋ ወሰንን አልጋ ወራሻቸው አድርገው አፄ ኃይለ ሥላሴ ቢሾሙዋቸውም እምብዛም ስለማያፈቅሯቸው በመካከላቸው አለመግባባት ነበር። ሕዝቡ በሙሉ 'አልጋ ወራሽ አይነግሡም' እያለ እንደዘበት ይናገራል። ይሁንና ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ የወሎ ገዥ ከመሆናቸውም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ በአገር ውስጥ በማይኖሩበት ወቅት የመንግሥቱን ኃላፊነት ይዘው ይጠብቁ ነበር። ጃንሆይ አልጋ ወራሻቸውን ወደ ኋላ ላይ ንጉሥ ብለው ለመሾም ቀርቶ እስከመጨረሻው ድረስ በካቢኔያቸውም እንኳን አላሳተፏቸውም። በዚህም ምክንያት ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ደስተኛ አልሆኑም።

ይህንን ዑኔታ የተረዱ ባለሥልጣኖች በጃንሆይና በአልጋ ወራሹ መካከል የነበረውን ክፍተት ለማሰፋት ሞክረዋል። አንድ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ለሁለት ወር ጉብኝት ላይ በነበሩ ጊዜ ልዑል አልጋ ወራሹ

የተወዘፉ ሥራዎችን አጠናቅቀው ሚኒስትሮችን በደንብ ተቆጣጥረው መልካም ሥራ ሠሩ። ይህንን ሁኔታ ያልወደዱት በተለይ ክቡር አቶ መኮንን ሃብተ ወልድ የአገር ፍቅር የበላይ ስለነበሩ "ጠቅል ቶሎ ና. ጠቅል ቶሎ ና" የሚል ዘፈን ያዘፈኑት በዚያን ጊዜ ነበር።

ልዑል አልጋ ወራሽ ፍርድ አዋቂና ቁጥብ ሰው ነበሩ። የወሎ አገረ ገዥ ሆነው ሁሉም ሰው 'አስፋው ወሰን ይሙት!' እያለ ሲምል ለሕዝቡ ግን ያደረጉት ነገር አልነበረም። እንዲያውም ብዙ ንብረት እንደገፈፉ ተደርጎ ይታሙ ነበር። የወሎ ረሃብ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ወቅት ንጉሠ ነገሥቱ ሰምተው ወሎን ሲጎበኙ የረሃቡን ፅናት ሲመለከቱ ልዑል አልጋ ወራሽን በኃይል ተቆጡ። በዚህም ቁጣ አልጋ ወራሽ ተከፍተው ስለነበረ ከጉብኙቱ በኋላ ደብረ ዘይት ለዕረፍት ሄደው የደም ግፊቱ ስለባሰባቸውና በሽታቸውም አስጊነት የተነሳ ለህክምና ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው እዚያው እንዳሉ መንግሥት ተገለበጠ።

ባለቤታቸው ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ ጎበዝና ሥነ ሥርዓት ያላቸው ልዕልት ከመሆናቸውም ባሻገር ልጆቻቸውን በሥርዓት ያሳደጉ እናትም ናቸው።

ተፈሪ መኮንን ትልቁ ልጃቸው
አልጋውን ለመውረስ ያሰባል ልባቸው
የኋለ የኋላ ሐቲማም የላቸው
ሸዋ ክፉ ሰው ነው ተሥር ነቀላቸው
ዳግሚያ እንዳይነሱ ተነልጅ ልጃቸው
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

## ልዕልት ዘነበ ወርቅ

ልዕልት ዘነበ ወርቅ ሐምሌ 18 ቀን 1909 ዓ.ም. ተወለዱ። ልዕልት ዘነበ ወርቅ ከአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ቆይተው በወሊድ ሞቱ። ልዕልት ዘነበ ወርቅ ከሞቱ በኋላ 'የልጃችንን የወግ ዕቃ አምጥተህ አስረክበን' በመባሉ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ቅሬታ አቁሮ ይኖር ነበር። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ቅምጥል የነበረ በጠላት ወረራም ወቅት ጣሊያኖች ትግራይን በሙሉ



ለእኔ ይሰጡኛል ብሎ ለጣሊያን ያደረ ሲሆን ከጣሊያን ድል በኋላ በግዞት አሊባቦር ከዚያም በቋም እስር አምቦ ላይ ቆየ። በደርግ ጊዜ ከተፈታ በኋላ የተፈጥሮ ሞት ሞተ።

## ልዕልት ፀሐይ

ልዕልት ፀሐይ ጥቅምት 2 ቀን 1912 ዓ.ም. ተወለዱ። ልዕልት ፀሐይ ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ስለነበራቸው ከጣሊያን ወረራ በፊት በአስተርጓሚነት አባታቸውን አገልግለዋል። በጣሊያን ጊዜ ከአባታቸው ጋር በስደት እንግሊዝ አገር ሄደው የነርስነት ሙያ ተምረዋል። ከስደት መልስ በዚሁ ሙያ ሲያገለግሉ ቆይተው ነቀምት ሆስፒታል ውስጥ በወሊድ ሞቱ። ባለቤታቸው ጀኔራል ዓብይ አበበ በደርግ ከተረሸኑት ባለሥልጣኖች አንዱ ናቸው።



ልዕልት ፀሐይ ከወንድማቸው ከልዑል መኮንን

ለልዕልቲቷ መታሰቢያ ተሰይሞላቸው የነበረውን የልዕልት ፀሐይ ሆስፒታልን ደርግ የጦር ኃይሎች ሆስፒታል ብሎ መጠሪያውን ለውጦታል።

## ልዑል መኮንን

ልዑል መኮንን ጥቅምት 5 ቀን 1916 ዓ.ም ተወለዱ። ልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴን አባታቸው ከእንጀት የሚወዷቸውና ከልጆቻቸውም መካከል የሚያቀርቧቸው ስለነበር የሚደፍሯቸውና አንተ የሚሏቸው ልጃቸው ነበሩ። የሐረር ገዥ አድርገው ሾመዋቸው እንደ እንግሊዞች አጠራር 'የሐረር ዱክ' እያሉ ይጠሯቸው ነበር። ሐረር ከተማን ከሚከበው አጥር ላይ ካሉት አምስት በሮች መካከል አንዱ በእሳቸው ማዕረግ ዱክ በር በመባል አሁንም ይታወቃል።

ከልዕልት ሣራ ግዛው ጋር ተጋብተው አምስት ወንዶች ልጆች ወልደዋል። ልጆቹም



ወይዘሮ ምሕረት መኮንን

- ልዑል ወሰን ሰገድ
- ልዑል ሚካኤል
- ልዑል ተፈሪ
- ልዑል ዳዊት (መኮንን መኮንን)
- ልዑል በዕደ ማርያም ናቸው

ልዕልት ሣራ ግዛው የጥላሁን ግዛው ታላቅ እህት ናቸው። ጥላሁን የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ፕሬዚዳንት ሆኖ በአንድ የክብር ዘበኛና በአንድ የፖሊስ መኮንን ቅንብር በጥይት በ1962 ዓ.ም ተገደለ።

ልዑል መኮንን ከጋብቻ ውጭ ወይዘሮ ምሕረትንና አቶ እስክንድርን ወልደዋል። ምንም እንኳን ስለ ወይዘሮ ምሕረት የራሳቸው የጃንሆይ ልጅ ናቸው የሚል ሃሜት ቢኖርም ባለቤታቸው ጄኔራል ግርማ መንግሥቱን አነጋግሬ አስተባብለውልኛል። አቶ እስክንድር ሕመምተኛ ስለነበሩ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ልዑል መኮንን ቸርና በጣም ደግ ሰው እንደነበሩ ተጋንኖ ይወራላቸዋል።



ልዑል ወሰን ሰገድ መኮንን

በ1949 ዓ.ም ጃንሆይ ሲዳሞ ለጉብኝት በሄዱበት ወቅት ልዑል መኮንንም ወደ ሲዳሞ በመኪና ከራስ መስፍን ጋር ሲሄዱ ሞጆ ላይ አደጋ ደርሶባቸው ሞተው ታላቅ ሃዘን በኢትዮጵያ ውስጥ ተደረገ። በዚህም ሃዘን ሳቢያ ወንዱ ጥቁር ጨርቅ ሴቶች ከል እንዲለብሱ ፖሊስ አልፎ አልፎ ያሳስብ ነበር። በሃዘኑ ምክንያት የመንግሥት የጽሕፈት ወረቀቶች በሙሉ በጥቁር የተከበቡ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዘፈንና በመዝናኛ ሙያ የተሰማሩ ሁሉ ለስድስት ወራት ሥራቸውን ማቋረጥ ግድሆኖባቸው ነበር።



ስለ ልዑል መኮንን አሟሟት ብዙ ቢወራም በመኪና አደጋ ለመሞታቸው እርግጠኛ መሆኑን በማጣራት ለማወቅ ችያለሁ።

ከልዑልነታቸው ሞት በኋላ ለስማቸው መታሰቢያ ሆስፒታል ማሠሪያ አዋጡ ተብሎ ብዙ ገንዘብ ተሰበሰበ። በተለይ ደሞዝተኛ የኾነ ሁሉ የአንድ ወር ደሞዙን በአሥራ ሁለት ወር እንዲከፍል ስለተወሰነ 10% ከከፈሉት ከአየር ኃይል ሠራዊት በስተቀር ሁሉ ደሞዝተኛ ከፍሏል። በተጨማሪም ገበሬውም፣ ነጋዴውም ሳይቀር የተቻለውን ያህል በውዴታ እንዲከፍል ተደርጓል። በተሰበሰበው ገንዘብ ቀድሞ የራስ ቢትውደድ ተሰማ ናደው ወይም ስኳር ሜዳ ይባልየነበረው በኋላ ለዩኒቨርስቲ በተከለለው ቦታ ላይ በልዑል መኮንን ስም ሆስፒታል ተሠራ። መጨረሻ ላይ ግን በዩጎዝላቪያና በስዊስ (በስዊትዘርላንድ) መንግሥቶች ከፍተኛ ዕርዳታ ጭምር ሆስፒታሉ አልቆ ተከፈተ።

ደርግ ሥልጣን እንደጨበጠ የንጉሡ ነገሥቱንና የቤተሰቦቻቸውን ስም ለማስወገድ ባደረገው ዘመቻ ሆስፒታሉን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብሎ ሰየመው። ሆስፒታሉ በሕዝብ መዋጮ የተሠራ ሲሆን መንግሥት ወርሶ ባለቤት መሆኑና ስሙን ያለሕዝቡ ፈቃድ መቀየሩ ለብዙ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ ቅሬታ እንዳሳደረባቸው ነው። ሌሎችም በልዑሉ ስም ተሰይመው የነበሩትን ትምሕርት ቤቶቸ ደርግ ስማቸውን ለውጦታል። አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን የልዑል መኮንን ት/ቤት 'አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት' ብሎታል። በሐረርና እንዲሁም በሌላ ቦታ በልዑሉ ስም የተሰየሙትን ትምሕርት ቤቶችም ደርግ ስማቸውን ቀይሮታል።

ጃንሆይ ልዑል መኮንንን እንደሚወዱ ሁሉ አምስቱን የልዑል መኮንንን ወንዶች ልጆች በአባታቸው ዓይን እየተመለከቷቸው በጣም ይወዷቸው ነበር። ልጆቹም ጃንሆይን በእንግሊዝኛ ትልቁ አባባ (Grand Pa) ይሏችው ነበር። መንግሥት በተለወጠበት ወቅት ያለጥፋታቸው በመወሰድ ብቻ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ድረስ ታስረዋል። ከአምስቱ ልጆች መካከል የመቶ አለቃ መኮንን መኮንን በስደት ላይ ሞቷል። ሌሎቹም በአገር ውስጥና በውጭ አገር በትምሕርትና በሥራ ላይ ይገኛሉ። ከልዑል መኮንን ልጆችም ኾነ ከንጉሣውያን ቤተሰብ ልጆች መካከል ልዑል በዕደ ማርያም በአስተዋይነቱ ሞዓ አንበሳ ለንጉሥነት ከሚመርጣቸው አንዱ ተወዳዳሪ እንደ ኾነ ይወራል።

## አቶ ኪዳኔ ተፈሪ

ከንጉሡ ነገሥቱ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ከጋብቻ ውጭ የተወለድሁ ልጃቸው ነኝ የሚሉት አቶ ኪዳኔ ተፈሪ ብቅ ብለው ስለአወላለዳቸው የሚከተለውን ገልጸዋል። አቶ ኪዳኔ ተፈሪ የተወለዱት ቤተ መንግሥት ውስጥ ከሚሠሩት ከወይዘሮ ይመኙሻል ክብረት መሆኑ ባይካድም ጃንሆይ ክብራቸውን የሚጠብቁ ስለሆኑ ከሴትየዋ ጋር የመገናኘታቸው ዕድል አይኖርም በማለት ነገሩን የሚያጣጥሉት ብዙ ናቸው። ነገር ግን አንድ አጋጣሚ ይጠፋል ብሎ መደምደም የዋህነት ነው። ነገሩን ችላ ለማለት ደግሞ አንድ በመሃሉ የተወለደ ልጅ ስላለ ለአባቱ ክብር ተብሎ የሱን ያላባት መቅረት ችላ ማለት በደል ስለሚሆን ነገሩ መነሳትአለበት።



አቶ ኪዳኔ ተፈሪ

ፎቶግራፋቸውን የተመለከተ ሰው "ይህ ሰው ዕውነትም ይመስላቸዋል" የማይል የለም። ያደጉትም እስከ ሰባት ዓመታቸው ቤተ መንግሥት ውስጥ ሲሆን ከሰባት ዓመት በኋላ ራስ እምሩ ቤት እንደነበርና ባለመስማማት ምክንያት እናታቸው እህት ዘንድ ሄደው ማደጋቸውን አስረድተዋል። አንድ ልጅ ያላቸውና ደርግ በጠራው ዘመቻ ላይ ተሳትፎ ሁለት እግሩን ተመቶ እሳቸው ዘንድ በፊት በቀለም ቀቢነት በሚያገኙት በኋላ ግን በእርጅና ዘመን ደግሞ በልመና የሚያገኙትን እየተካፈለ እንደሚኖር አስረድተዋል። ግንቦት 27 ቀን 1994 ዓ.ም በሰባ ዓመታቸው ሞተው በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን አስከሬናቸው አርፏል።



## መንግሥቱ ግርማ



አቶ መንግሥቱ ግርማ

አቶ መንግሥቱ ግርማ ግንቦት 13 ቀን 1936 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። አባቱ አቶ ግርማ ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ግቢ ይሠሩ የነበሩ ናቸው። እናቱ ከአርመናዊ አባትና ከኢትዮጵያዊት እናት የተወለዱ ሲሆኑ መልከ መልካም ነበሩ። እንደሚባለው አቶ መንግሥቱ ግርማ የተወለደው ከጃንሆይ ሲሆን እንዲያውም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት አሁን የውል ክፍል የሚባለውን ቤት ጃንሆይ ለልጅሽ ማሳደጊያ ይሁንሽ ብለው ለእናቱ የሰጧቸው ነው ይባላል። ሕዝቡ ግን የአልጋ ወራሽ ልጅ ነው እያለ ይንሾካሾክ ነበር። መንግሡቱ ግርማ መልከ መልካምና ቀይ ሲሆን ያደገው በራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ስለነበረ በመሃል አራዳ የታወቀ ልጅ ነበር። በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሲሠራ ኖሮ መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ መሥሪያ ቤት የፔርሶኔል መምሪያ ኃላፊ በመሆን አገልግሏል።

አቶ መንግሥቱ ግርማ በድንገት ጥቅምት 13 ቀን 1987 ዓ.ም አርፎ በቅዱስ ዮሴፍ መካነ መቃብር አስከሬኑ አርፏል። በአሁኑ ወቅት ባለቤቱ ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ግረማና ሦስት ወንዶች ልጆቹ የሚኖሩት አሜሪካን አገር ነው።

## ትዕግሥት ካሣና ቴዎድሮስ ካሣ

ወይዘሮ አስገደች አበራ የሚባሉ ሊሞቱ ሲሉ ንስሓ ልግባ ብለው ዘመድ ሰብስበው ልጆቼ ትዕግሥት ካሣና ቴዎድሮስ ካሣ የተወለዱት ከጃንሆይ ስለኾነ እስከ ዛሬ በመፍራት ሳልናገር ቆይቻለሁ። አሁን ግን ትክክሉን ይወቁት ብለው ተናገሩ። ወይዘሮ አስገደች የሚሠሩት በቤተ መንግሥት የቤት ዝግጅት ከመሆኑም በላይ ጃንሆይ ወደ ውጭ አገር ለጉብኝት በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ አብረው ይመላለሱ ነበር። ባለቤታቸው አቶ ካሣ ገበየሁ በዩጋንዳ ኤምባሲ የሚሠሩ ከወይዘሮ

አቶ መክብብን ያሳደጉት ጄኔራል ወርቁ ዘውዴ ናቸው። የሚጠራው ግን በወይዘሮ ንጋቷ ታደሰ ባለቤት ወይም በእንጀራ አባቱ በአቶ አበበ ወልዴ ሲሆን እሳቸውም ዳኛ ነበሩ። በዚሁ ልጅ መወለድ ምክንያት በነበረው አለመግባባት ባልና ሚስቶቹ ተፋቱ። ከተፋቱም በኋላ አቶ አበበ ቂም ቋጥረው በደርግ መንግሥት ጊዜ ሴትየዋን ወንጅለው ነበር።

መክብብ የጃንሆይ ልጅ መሆኑን ቢያውቅም እንዳንዶች ገነ እሳቸውን ትመስላለህ እንደሚሉት ይናገራል። መጨረሻ ላይ ግን በደንብ የጃንሆይ ልጅ መሆኑን የተረዳው ወይዘሮ ትዕግሥት ቢሆነኝ በግልጽ ስለነገሩትና ወንድሞቹም ከአቶ ተሰፋዬ ወልደ ሥላሴ ከሚባሉ የቤተ መንግሥት ሠራተኛ ሰምተው ስላረጋገጡለት ነበር።



በግራ በኩል የቆሙት ወ/ሮ ንጋቷ ታደሰ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር

ይህንን ሁኔታ እንደተረዳ አንድ ቀን "ልዕልት አይዳን ይሁን ልዕልት ሰብለን አላውቅም አንደኛቸው ቤት ድንገት ዘው ብዬ ገብቼ ማነጋገሬን አስታውሳለሁ" ብሏል። ሁኔታውን ሲገልጽ ደነገጡና "ግን እኛ የምናውቀው ነገር የለም ምን እናድርግ" ብለው መልሰውለታል።



"ለልዑል ኤርሚያስ ደብዳቤ ጽፌ መልስ አላገኘሁም" ብሎም ተናግሯል።

## ሁለት ልጆች

በሰበታ መንገድ ቤተ ስሊሆም የምትባል የሴቶች ገዳምን ለመጎብኘት እቴጌ መነን ሲሄዱ አንዲት ቅጠል በመልቀም ላይ ያለች ልጅ እጇን እያውለበለበች ሠላምታ ስትሰጣቸው ጊዜ ወደዋት ወሰዷትና እቴጌ መነን ትምህርት ቤት አስገቧት። እዚያ በመማር ላይ እያለች ለልዑል መኮንን ልጆች ሞግዚት እንድትሆን ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰደች። ይህች ልጅ ስሟ ፀሐይ መገርሣ ይባላል። ቤተ መንግሥት ውስጥ እያገለገለች ስትኖር በመካከሉ ሁለት ልጆች ወለደች። በኋላም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ለነበሩት ለአቶ ሐጎስ ባህታ ተዳረች። ሠርጉም የተካሄደው በጊዮን ሆቴል ሲሆን በዓይነቱ የተለየ ስለነበረ ልዕልት ተናኘ ወርቅ በጉዳዩ ያልተደሰቱበትም ምክንያት በተለይ አባታቸው ጃንሆይ ሙሽሮቹን እስከ ሰበታ ድረስ በመሸኘታቸው ነበር። በመጨረሻም ወይዘሮ ፀሐይ ከነባለቤታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ በሥራ ተዛውረው ሄደዋል። ሃሜቱ ሁለቱ ቤተ መንግሥት የተወለዱትን ልጆች የጃንሆይ ናቸው የሚል ነው። በንብረት በኩል ወይዘሮ ፀሐይ በአሮጌ አይሮፕላን ማቢያ አካባቢ መሬት ተሰጥቷቸው ቤት እንደሠሩበት ይታወቃል።

## ሰሎሞን ሠርፀ ወልድ



ሰሎሞን ሠርፀ ወልድ

ወይዘሮ የውብዳር ድፋባቸው የሚባሉ የአቶ ሠርፀ ወልድ ባለቤት የቤተ መንግሥት ሠራተኛ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ዕድሜያቸው 82 ዓመት ነው ተብሏል። ከበርካታ ልጆቻቸው መካከል ትንሹ ወንድ ልጃቸው ሰሎሞን የጃንሆይ ልጅ ነው ይባላል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ በህመም ምክንያት ንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታል ገብቶ እያለ የጃንሆይ ልጅነቱ በሆስፒታሉ ውስጥ በሰፊው ስለተወራ

እንዲት ነርስ ስጋት ገብቷት ቤተሰቦቹን በማሳሰብዋ ልጁ ሳይድን ከሆስፒታል ወጥቶ በድብቅ ታክሞ ለመዳን በቅቷል።

እያደር ሰሎሞን ሥርፀ ወልድ የጃንሆይ ልጅ መሆኑ በሰፊው ስለታወቀ እንደምንም ብሎ ወደ አሜሪካን አገር ሄዶ አሁን ድረስ እዚያው ይኖራል።

ከቤተሰቦቹ ለማረጋገጥ እህቱንና ወንድሞቹን ብናነጋግራቸውም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ የጃንሆይ ልጅነቱን ለማረጋገጥ አልፈለጉም። እንደተረዳነው ዘመዶቹ ጥቅም ለሌለው ነገር ሰሎሞንን ከአብሮ አደግ ወንድሞቹና እህቶቹ ላለመነጠልና ለደህንነቱ በማሰብ የጃንሆይ ልጅነቱን ላለመቀበል የወሰኑ ይመስላል። ይሁንና ሰሎሞን በልጅነቱ በቤተ መንግሥት ማደጉና መልኩም እንደሚታማው ጃንሆይን መምሰሉን ደርሰንበታል። እናቱም ለልጁ ማሳደጊያ ወርሃዊ የገንዘብ ድጎማ ያገኙ ነበር ተብሏል።

በአጠቃላይ ስለተለያዩ ሌሎች ልጆች ብዙ ቢባልም በከፊል እንኳን ተአማኒነት የሚያሳድር ፍንጭ የሌለው ስለሆነ አልፌዋለሁ።



# ምዕራፍ ፴፯

# የውዳሴ ከንቱ አስተዳደር

## በጎ አድራጎት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከ1913 ዓ.ም ጀምሮ በየወቅቱ የዕርዳታ ድርጅቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ የጡረታና የነዳያን መርጃና መማሪያ ድርጅቶችን ሲያቋቁሙ ኖረው መጨረሻ ላይ በ1945 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት በሚል ስም ተጠቃለው አንድ ተቋም ተመሠረተ። ለነዚህም ድርጅቶች የገንዘብ ምንጭ የሆኑት የግል ርስት፣ የግል ገንዘብ፣ ግለሰቦች የሚያበረክቱት ዕርዳታ፣ የውጭ አገር ሰዎችና ድርጅቶች ስጦታ፣ ከብሔራዊ ሎተሪ፣ ከመንግሥት ወጪ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ የልደት ስጦታ ወዘተ.. ናቸው።

አንድ ንጉሥ ወይም ንጉሠ ነገሥት የመንግሥት ቋንጮ ሠራተኛ እንጂ ነጋዴ ወይም ሃብታም ገበሬ ወይም ከብት አርቢ አይደለም። ከ13 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ የአስተዳደር ሥራ እየሠራ የኖረ መሬት ካልነጠቀ፣ ወይም የመንግሥቱን ገቢ ወደ ግል ሃብትነት ካላዞረ፣ የጠላት ንብረትን ለግሉ ካልወሰደ፣ ወይም ከመንግሥት ካዝና እያዘዘ ካልሰጠ፣ እንዴት ከበርቴ ሊሆን ይቻላል ብሎ ስለሚያስብ፣ ጃንሆይ በየወቅቱ ከግል ሃብታችን ይኸን ሰጠን ቢሉም ለተማረው ክፍል አልተዋጠለትም። እንዲያውም እንዴት ዘርፈውን ኖሯል የሚያሰኝ አስተሳሰብ ላይ ጥሎታል።

ሰው ሁሉ በአንድ ዓይነት ሊያስብ አይችልም። አንዳንዶች በንጉሡ ችሮታ ሲረኩ አንዳንዶች እንዴት ይቀለድብናል ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ስለሆነም ይሻል የነበረው ድርጅቱን በንጉሠ ነገሥቱ ስም ሰይሞ፣ አንድ የመንግሥት አካል አድርጎ፣ በበጀትና በዕርዳታ አሰባሰብ ቢተዳደር የተሻለ ነበር። በየልደት በዓላቸውም ውስጡን ግዴታ ላዩን በፈቃድ ስጦታ

## የሽልማት ድርጅት

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ከተቋቋመ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በቀለጠፈና ባልተዛባ መስፈርት ሽልማቶችን በዓላማው መሠረት ይሰጥ ነበር። የድርጅቱ አሠራር ምንም የማይወጣለት ሆኖ እያለ ብዙ ሰዎች የውዳሴ ከንቱ ሥራ ነው እያሉ ማናናቃቸው አልቀረም። ለዚህ አባባል የነበረው ምክንያት ሦስት ነው። አንደኛው አገሪቱ ድሃ መሆንዋ እየታወቀ ለስጦታ ገንዘብና የሰው ጉልበት ለምን በሽልማት ይባክናል። ሁለተኛው አስተሳሰብ ልክ የራሳቸውን ሐውልት እንደሚያሠሩ ዲክታተሮች በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ለምን የሽልማት ድርጅቱ በስማቸው ተሰየመ የሚል ነው። ሦስተኛው የድርጅቱ የገንዘብ ምንጭ ልክ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካና ከንጉሠ ነገሥቱ የግል ርስት ላይ የሚገኘው ሰብል ተሸጦ ስለኾነ በገንዘቡ ምንጭ ላይ ብዙ ሰዎች ነቀፌታ ስላላቸው ነው።

ጃንሆይ በ58 ዓመት ለሠሩት ማስታወሻ የሽልማት ድርጅቱ በስማቸው መሆኑ ያንሳቸው እንደ ኾነ ነው እንጂ አይበዛባቸውም ነበር። ግን የሽልማት ድርጅቱ መሰየም የነበረበት ከሕይወት ዘመናቸው በኋላ በተከታዩ ትውልድ ውሳኔ በኾነ ኖሮ ጥሩ ነበር።

## የዘፈቀደ አስተዳደር

ጃንሆይ ምንም እንኳን ሕገ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰጡ ቢሉም ራሳቸው ከሕግ በላይ የሆኑ አስተዳዳሪ ነበሩ። አሠራራቸው ከደንብና ከሥርዓት ውጭ እንደፈለጋቸውና እንዳሰኛቸው ነበር።

ከጣሊያን አገር የ150 ሚሊዮን ዶላር ብድር እንዳይቀበሉና በተደረገላቸው የጉብኝት ጥሪ መሠረት ጣሊያን ኢትዮጵያን ይቅርታ ሳትጠይቅ ለጉብኝት እንዳይሄዱ ተብለው ቢከለከሉም የግል ውሳኔ አድርገው ጥቅምት 27 ቀን 1963 ዓ.ም የጣሊያንን አገር በይፋ ጎበኙ። በዚህም ጉብኝት የቫቲካንን ጳጳስ ሄደው ዓይተዋል። የቫቲካን ጳጳስ የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ሲወርር ሲመጣ መድፉን ሳይቀር የባረከ ሲሆን በመንበሩ የተተካው የዘመኑ ጳጳስ እስከ አሁን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ አልጠየቀም።



እንደዚሁ ሁሉ የአገራችን የጀግኖችና የባለውለታዎች የክብር ማዕረጎችን በማቅለል ወግና ልማዱን ሽረዋል። በዘመናዊ የወታደር ደንብ ውስጥ የሹመት ማዕረግ እስከ ሻለቃ ድረስ በሥርዓት ሲሠራበት ከዚያ በላይ ያሉት እንደ ኮሎኔልና ጄኔራል ያሉ በእንግሊዝ ቃላቶች በመተካት እንደ ፊታውራሪና ደጃዝማች ያሉትን ለነጋዴና ለገበሬ እየሰጡ አቀለሏቸው። አልሆን ብሏቸው እንጂ ዱክ የሚባለውን የእንግሊዝ ሹመት ለልጃቸው ለልዑል መኮንን ሰጥቶ ለማስለመድ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። አንዳንድ ሰዎች ዓለማቀፋዊ የማዕረግ ስም ነው ይሉ ከሆነ ለምን ሌፍትናንት የሚለው የመቶ አለቃ ተባለ ለምንስ ኪንግ እያለ ንጉሥ ይባላል እንደማለት ነው። ማዕረጎቹ በመቃለላቸው ምክንያት የጃንሆይ መንግሥት ሲለወጥ ሹመት የተሰጣቸው ሰዎች መቀለጃ መሆን ጀምረው ነበር። ሌሎች ደግሞ የአድር ባይነት ጠባይ የነበራቸው በፊት ለምነው ያገኙትን ማዕረግ አንፈልግም በማለት በይፋ አቶ በሉን ብለው አስታውቀዋል።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አንድ ሰው ለኢትዮጵያ ምን ጠቀመ ሳይሆን ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ነው የሚለው ጥያቄ የበለጠ ሚዛን የሚደፋ ነበር። ስለሆነም በመጀመሪያ አንድ ግለሰብ መታወቅ ሲጀምር እጅ እንዲነሳ ይጠየቃል። ይህንን ሁኔታ በሥርዓት ካልተከታተለ የግለሰቡ ለአገር ጠቃሚ መሆኑና መታወቁ ጭራሽ ያስጠቃዋል እንጂ አይጠቅመውም።

## ውዳሴ ከንቱ

ጠቅላላውን ስንመለከተው ንጉሠ ነገሥቱ ሁለት ዓይነት አስተዳደር ይመሩ እንደነበረ ነው የምንረዳው።

1ኛ መደበኛው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
2ኛ የቀ.ኃ.ሥ የውዳሴ ከንቱ አስተዳደር

ሰው ደካማ ፍጡር ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ሰው እንደ መሆናቸው ሁሉ ብዙ ደካማ ጎኖች ነበሯቸው። ከነዚሁም አንዱ ውዳሴ ከንቱ ያበዛሉ። እወደድ ባዮችም ይኸንን ድክመት ነገዱበት። እነዚህም የአንድን አገር መሪ ታሪክ የሚያበላሹ ስግብግብና አስተሳሰባቸው ሁሉ የዕለቱን

ጥቅማቸውን ብቻ የሚመለከት ነው። ጠንካራ መሪ ከደካማው የሚለይበት ብርታት አንዱም እበላባዮችን መቋቋም ሲችል ነው።

የጃንሆይ ልዩ ረዳት (ኤዲሲ) የነበሩት ጄኔራል መኮንን ደነቀ አንዴ ንጉሠ ነገሥቱ 'ምስጋናውን ሁሉ ለራሳቸው ያደርጉታል' ብለው ስለተናገሩ ሰው ሁሉ ገሸሽ አደረጋቸው። ያማ ባይሆን ኖሮ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ስለ ኤርትራ ውህደት ለደከሙት ድካም ጃንሆይ ኤርትራ ሲሄዱ ባደረጉት የይፋ ንግግራቸው ላይ ስማቸውን ጠቅሰው ባመስገኑዋቸው ነበር። ራስ አበበ በብዙ ምክንያቶች ወደ አውሮፓ እንዲሄዱ ሲታቀድ ጃንሆይ ያስቀሩዋቸው እንደነበረ ይታወቃል። ጄኔራል መኮንን የተናገሩት ውሸት ሆኖ ሳይሆን ሁሉም ልቡ እያወቀ የንጉሠ ነገሥቱ ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት ሲል ነው።

ለዚህ ምስኪን ሕዝብ የተቻላቸውን ያህል ቋሚና ኑሮውን የሚያሻሽልበት ሁኔታ ትተውለት ማለፍ ሲችሉ የነበረውን ረጅም የሠላም ወቅት በውዳሴ ከንቱ ዝናና ራስ ወዳድነት ላይ በማተኮር አባክነውታል። በመሠረቱ ቀኃሥ አገሩን ይገዙ የነበሩት ለራሳቸው ተድላና ደስታ እንጂ ለሕዝቡ ብለው እንዳልነበር የሚያስረዱ ድርጊቶች አሉ። አንደኛ ትተውለት የሄዱት ጠቃሚ ነገር ካለመኖሩም ሌላ ሥልጣናቸውን በሠላም ለራሳቸው ልጆች እንኳን ማስተላለፍ አልፈቀዱም። እንዲያውም ከሳቸው በፊት ዝነኛ መሪ እንዳልነበርና ወደፊትም እንዳይፈጠር አበላሽተው በማለፋቸው ከዘመናቸው በኋላ ያለው ትውልድ ደምቶበታል። በሕይወት ዘመናቸው 101 ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች፣ 20 የክብር ዲግሪ በፍልስፍና፣ በግብርና፣ በሕግና በሥነ ጽሑፍ ተለግሰዋል። እንዲሁም ከእንግሊዝ መንግሥት የፊልድ ማርሻል ማዕረግ አግኝተዋል። ከአገር ውስጥና ከውጭ አገሮች 100 የተለያዩ ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል። 167 አገሮች ሲጎበኙ በዘመናቸው የ63 አገር መሪዎች ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል። የአገራቱን ምጣኔ ኃብት ሲመለከቱት ከላይ የተጠቀሰው ግርግር ያበረከተው ጠቀሜታ ኢምንት ነበር። እንዲያውም ለዚህ ግርግር ወጭ የሆነው ገንዘብ ጠቃሚ ሥራ ላይ ውሎ በሆን መልካም ነበር ያሰኛል።

ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ሁሉ በመንግሥት በኩል በቀለጠፈና በተስተካከለ መልኩ መሥራት ሲቻል በተወሳሰበ አኳኋን ሲሠሩ ብዙ ባለሥልጣኖችን ለንቅዘት አስተዳደር ጋበዙ። አንዱ የድህነት ዋና



ምክንያት የባለሥልጣኖች ንቅዘት እንደሆነ አይካድም። ስለሆነም በዚህ አይነት አሠራር ለሕዝቡ ድህነትንም አውርሰዋል ማለት ነው።

ጃንሆይን እንወዳቸዋለን እናከብራቸዋለን ግን እንተቻቸዋለን። እሳቸውን ያዋረዱ ራሳቸው ወራዳ ስለነበሩ ይሄው አሁን ተዋርደዋል። አንዳንድ የተሠሩም ነገሮች ላይ የሚደነቁባቸውና የሚመስገኑባቸው እንዳሉ ዕሙን ነው። ምንም እንኳን ብዙ ዓመት በሠላም የማስተዳደር ዕድልና በዘመናቸው የምዕራባውያን ስልጣኔ ተጋፍቶ የመጣበት ጊዜ ቢሆኑም ያስገቡት ስልጣኔ ሰዎችን በከፊል ሲያረካ ከፊሎችን ደግሞ አላረካም። የረኩት ያላዩትን ስላዩ ተደስተዋል ያልረኩት ግን ከሌሎች ተመሳሳይ አገሮች ሁኔታ ጋር በማስተያየት አገራችን ሊገባ የሚችለው ስልጣኔ አልገባም ነው የሚሉት። ሁለቱም ልክ ናቸው። የሚያሳዝነው ግን የሚያግባባውም ራሱ ስልጣኔ ስለሆነና ይሄኛው ስልጣኔ ደግሞ በለመግባቱ ሀለቱ ወገኖች ሊግባቡ አልቻሉም። የንግግር ነፃነት ኖሮ ሕዝብ ስለራሱ መንግሥት አስተዳደር በይፋና ሳይፈራ መወያየት ቢችል ኖሮ የማይግባባበት ምክንያት በጠፋ ነበር። የንጉሠ ነገሥቱን ስልጣን መጠበቅ ብቻ ተቀዳሚ ጉዳይ ስለነበረ ችግር ውስጥ ተገብቶ ብዙ ጥፋት ተፈጸመ። ከዚህ ሁሉ በኃላ አስተዳደሩ ግሩም ስለነበረ ራሳቸው እያደነቁ ያንኑ አሠራር አድንቁ ብለው የሚታገሉ ተላላ የሆኑ ሰዎች አሁንም አሉ።

ከላይ ያሉትን መዘርዘር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ለወደፊቱ በኃላፊነት ላይ የሚቀመጡ ሁሉ ተቀዳሚ ተግባራቸው ለአገራቸው ሕዝብ ሠላምን፣ ዕድገትን፣ መግባባትን፣ ብልጽግናና ጤናነትን አውርሰው ማለፍ እንጂ ለጊዜያዊ ተድላና ደስታ በብልጣ ብልጥነት ኃብትንና ጊዜን እንዳያባክኑና ምን ትቼ ልለፍ ብለው ኃላፊነት እንዲሰማቸው ለማስገንዘብ ነው።

## የአንድነት ስሜት

ንጉሠ ነገሥቱ ለዓላማቸው ጎበዝ፣ ብልህ፣ ዘዴኛ፣ የነበሩ መሆናቸው አይካድም። በዛው ልክ ደግሞ ውዳሴ ከንቱ የሚያበዙና በዚህ በረጅም የሥልጣን ዘመናቸው ሊሠሩዋቸው የሚችሉትን ብዙ ሥራዎች ሳይሠሩ ማለፋቸው ይታወቃል። ጃንሆይ ራስ ወዳድ እንጂ የጎሣ ወይም ወገናዊነት አይታይባቸውም ነበር። ስለሆነም አስተዳደራቸው ውስጥ ኢትዮጵያን በአንድነት አስተሳስብ ለማስተዳደር አልተቸገሩም።

በሚመሩት የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ሥልጣን አሰጣጥ ላይ የግለሰቡን ሁኔታ እንጂ የጎሣው ምንነት ስፍራ አይሰጠውም ነበር። ስለሆነም በዘመናቸው የጎሣ ልዩነት እየመነመነ ሄዶ ኢትዮጵያ አንድነቷ የጎለበተበት ወቅት ሆኖ ነበር። የጃንሆይ አስተዳደር አንዱ ውርስ ኢትዮጵያን መገንባት መፍትሄው አማራነት፣ ትግሬነት፣ ጉራጌነት፣ ወላይታነት፣ ሶማሌነት፣ አፋርነት፣ ወዘተ.. ብሎ ማሰብ ሳይሆን ጎሣው ምንም ይሁን በቅድሚያ ኢትዮጵያዊነት ብቻ መታየት ያለበት መሆኑን ነው። እንዲያውም ጃንሆይ ኤርትራውያኖች ምንም እንኳን አገራቸው በውጭ ኃይል ተይዞ ለብቻው የሚተዳደር የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያን ብለው የመጡትን ኤርትራውያኖች በማስተማርና ሥልጣን በመስጠት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኩል መብታቸውን በማክበር በሲቪልም እስከ ሚኒስቴርነት በወታደርም እስከ ጄኔራልነት ስፍራ ይሰጧቸው ነበር።

ያም ሆኖ ግን አንዳንድ ያለፉ የአስተዳደር ስህተቶችን በአማራው ላይ ለመጣል አንዳንድ ሰዎች ይሞክራሉ። ለነገሩ የሚሠራ ሁሉ ይሳሳታል፤ ይወቀሳልም። የማይሠራ ብቻ ነው ሊወቀስ የማይችለው። ስለሆነም አስተዳደሩ በወቅቱ ያለውን ሥልጣኔ፤ አስተሳሰብና ችግር ያገናዘበ ስለሚሆን ከመውቀስ በፊት ሁኔታዎችን በሥርዓት ማስተዋል ያስፈልጋል። ይሁንና የአማራው አንጻራዊ የተሻለ የአስተዳደር ችሎታ ላለፉት 700 መቶ ዓመታት ተሳትፎ ባገኘው ልምድ የተመረኮዘ ስለኾነ አሁን ሌሎች ጎሣዎች አልፎው አልፎው በሚከሰቱ ምክንያቶች የአማራውን የአስተዳደር ችሎታ የመሰከሩበትም ሁኔታ አለ። ሌሎች ጎሣዎችም በአስተዳደሩ መግባታቸው ወቅታዊና መሆንም ያለበት ሲሆን፣ እነሱም አልፎው አልፎው ስህተት ቢሠሩም ማጉላቱ አይበጅም።

አንድ ትልቅ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት አንድ ጎሣ ብቻ እንዲያስተዳድር መፍቀድ በመሠረቱ ስህተት ነው። ለዚህች አገር እያንዳንዱ ጎሣ እኩል መስዋዕትነት እንዲከፍል ስለሚጠበቅ በሠላሙ ጊዜ እኩል ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል። የራሱን ጎሣ ጥቅም ብቻ የሚጠብቅ ሌላውን ጎሣ አስተባብሮ ማስተዳደር ይቸግረዋል። ጀርመኖች ኃይል እያላቸው አውሮፓን እንኳን አሸንፎ ይዞ ማስተዳደር አልቻሉም። ምክንያቱም አስተሳሰባቸው ከጀርመን ዝርያ የበላይነት ዕምነት ባሻገር ሊሄድ ስላልቻለ ነው። በመሠረቱ በየትም ዓለም ሕዝብ ጥሩና የዋህ ነው። ከመካከሉ ግን በየዋህነቱ ለመጠቀም



የሚሯሯጡ ጥቂቶች ውሳኔውን በማሳት ችግር ውስጥ ሲከቱት በተደጋጋሚ ታሪክ አሳይቷል። በሌላ በኩል ለእኩልነት የሚደረግ ትግል ሁሉ መደገፍ ሲኖርበት በእኩልነት ስም ለበላይነት መታገል ግን በፊት በበላይነት ለተሠሩት ስህተቶች ትክክለኝነት ማረጋገጫ ይሆናል።

እውነት ለመናገር ከሆነ አማራውና ትግሬው ወደ ኋላ የቀሩት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ነው። ኤርትራ ውስጥ በየመንደሩ ትምሕርት ቤት ሲከፍቱ፣ በሌላው አካባቢ ፋብሪካዎች ሲያቋቁሙ፣ በትግራይና በአማራው አገር ላይ ጦር ሲያዘምቱ በአይሮፕላን ሲያስደበድቡ ኖሩ እንጂ በተለየ የሠሩለት ነገር አለ ለማለት አያስደፍርም። አንድ ሕዝብ የሚገነባው በተለያዩ ጎሣዎች ሲሆን ሁሉንም በእኩልነት ማስተዳደር ሲገባ በተለያዩ መክንያቶች ማበላለጥ ግን ቀጣዩን ተውልድ የተዛባ አመለካከት ውስጥ ይከተዋል። በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደበላልቆ አንድ ኢትዮጵያዊ ብሔር ይሆናል ተብሎ ይገመታል እንጂ በየጎሣው እየተከፋፈለ ለረጅም ዘመን አይኖርም። ምክንያቱም የሕዝቡ መደባለቅ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ስለኾነ ነው። በየሠርግ ወረቀቱ ላይ ያውም በስም መለየት የተቻለውን ብቻ በመመልከት በጋብቻ የመደባለቁ ሁኔታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ማጤን ይቻላል።



# ምዕራፍ ፴፰

# ሁለት ሉሉዎች በቤተ መንግሥት

ጄኔራል ሉሉ እንግሪዳ የሚባሉ የአፋር ተወላጅ ከወፍራሙ ግራዝማች ቡመር ዲንጎ ቀጥሎ የጃንሆይ ሾፌር የነበሩት በቤተ መንግሥት የታወቁና የተከበሩ ሰው ነበሩ። ጃንሆይን በሾፌርነት ሲያገለግሉ ኖረው በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ጃንሆይ በእስር ሲወሰዱ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ቆማ የነበረችው የጄኔራል ሉሉ የግል ቮልክስዋገን ቢትልስ መኪና ጃንሆይ እንዲሳፈሩባት ተደርጎ ከሄዱባት በኋላ መኪናዋም ታስራ ለረጅም ዓመት ቆይታ ለቤተሰቡ ተመልሳ በአሁኑ ወቅት ይገለገሉባታል።

ሌላዋ ሉሉ የታወቀችው የጃንሆይ ድንክ ውሻ ነበረች። ይህች ድንክ ውሻ አቶ ጃማነህ አላብሰው ተማሪ በነበሩበት ጊዜ በ1942 ዓ.ም ለጃንሆይ ያበረከቷት ነች። በተበረከተችበት ጊዜ ጃንሆይ "ስሟ ማነው" ብለው ቢጠይቁ ግለሰቡ ያልተዘጋጁበት ጉዳይ ስለነበረ አፋቸው ላይ እንደመጣ "ሉሉ ነው" ብለው መለሱላቸው። ከዚህ ወቅት አንስቶ የውሻዋ ስም ሉሉ ሆኖ ቀረ።

ይህች ድንክ ውሻ የተለየችና አቶ ጀማነህ ከየት አምጥተው እንዳሳደግዋት በእርግጥ የሚያውቅ ሰው አልተገኘም። ይሁንና የነቃችና ብልህ ውሻ ስለነበረች ለብዙ ጊዜ ሉሉን በውጭ አገር ጉብኝታቸው ጭምር ሳያስቀድሙ ንጉሠ ነገሥቱ አይሄዱም ነበር። ጃንሆይ ሉሉን ሳያስከትሉ የሚሄዱበት ቦታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበር። ጃንሆይ አውስትራሊያን ለመጎብኘት ሲሄዱ የአገሩ ሕግ እንስሳ እንዲገባ ስለማይፈቅድ ሉሉ ልትገባ ባለመቻልዋ አንድ የቤተ መንግሥት



ባለሥልጣን ሉሉን ይዞ ወደ ሚቀጥለው የጎበኙት አገር ደቡብ ኮርያ ሄዶ ጃንሆይ እዚያ ሲደርሱ አስረክቧል።

ጃንሆይ ከአይሮፕላን ከመውረዳቸው በፊት ሉሉ ትወርድና የራሷን ጉብኝት ታደርጋለች። ውድድር ለመመልከት ወደ ስታዲየም ሲመጡ ቀጥ ብላ ኳሱ ሜዳ መካከሉ ድረስ ትሄድና ተመልሳ እስራቸው ትተኛለች። በተለይ በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል በ1954 ዓ.ም በተደረገው የሦስተኛ የአፍሪካ ዋንጫ የመጨረሻ ግጥሚያ ዕለት ሜዳው ውስጥ ገብታ እንዲያውም ጎል ማግቢያው ድረስ ሄዳ መመለሷን እንደ ትልቅ ነገር የሚያወሱ ሰዎች አሉ። ይኸን ሁሉ የሚመለከት ሰው ይህች ውሻ ነገር ያላት ናት እያለ ይናገራል።

ሉሉን የሚወዷት ሰዎች የመኖራቸውን ያህል የሚጠሏትም ብዙዎች ነበሩ። በተለይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጃንሆይ ለምርቃት በዓል ሲመጡ የእሷ አብሮ መምጣት አይጥማቸውም ነበር። እሷም መካከላቸው እየገባች ታነፈንፍ ስለነበረ አንድ ዓመት ላይ አንድ ምሩቅ ሰው ሳያየው ረገጣትና ጮኸች። በዚህን ጊዜ አጃቢዎች ረጋጩን ተማሪ ለመለየት ብዙ ቢሞክሩም ሌሎቹ ተማሪዎች ስለሸፈኑት ተማሪው ሳይለይ ነገሩ እንዲሁ በቀረታ ታለፈ።

"ባለቤቱን ካልናቁ ውሻዋን አይነኩም" እንደሚባለው ጃንሆይን ካልናቁ ወይም ካልጠሉ ውሻዋን አይነኩም በሚል ውሻዋን ሁሉ ሰው ያከብር ነበር። አንድ ጊዜ ኮለኔል ተከሉ ገብሩ ሻምብል በነበሩበት ወቅት ተግባረ ዕድ ትምሕርት ቤት የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን ትምሕርት ሲማሩ ጃንሆይ ትምሕርት ቤቱን ለመጎብኘት ሲመጡ መኮንኑ እግር ስር ሉሉ መጥታ ስላስቸገረቻቸውና ጃንሆይም በቅርብ ስለነበሩ ውሻዋን 'ወይጅ!' ማለት ስለፈሩ 'ወይዱ!' ስላሉ ጓደኞቻቸው ወይዱ! የሚል የቅጽል ስም ሰጥተዋቸው ነበር።

ሉሉ የወር ደሞዝ ተቆርጦላት በወር የአንድ ሻምበል ደመወዝ ብር 175.00 ታገኝ እንደነበረ የታወቀው ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ለገሃር በሚገኘው የጦር ካምፕ እስር ላይ በነበሩበት ወቅት ለአንድ ሻንበል 'እኔ እዚህ ችግር ውስጥ የገባሁት ያንተን ደሞዝ ከአንድ ውሻ ደሞዝ እንዲሻል ለማድረግ ብዬ ነበር' ብለው በመናገራቸው ነው።

ሞት አይቀርምና ሉሉ ስትሞት ቤተ መንግሥት ውስጥ ተቀብራ መቃብሯም በዕብነ በረድ ስለተሠራ ጃንሆይ ከተወቀሱበት ነገር አንዱ ሆኗል። በአገራችን ለእንስሳት ክብር ሐውልት መሥራት ያልተለመደ ሆኖ ነው እንጅ አገልግሎት ለሰጠ እንስሳ ማስታወሻ ማድረጉ አይከፋም ነበር። በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥትም በትግል ዘመን ታሪክ ለሠራች አንድ የሃምሳ አለቃ ደሳለኝ ለምትባል አህያ ሐውልት ተሠርቷል። ስለሆነም ሉሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ሐውልት ከተሠራላቸው እንስሶች በታሪክ የመጀመሪያዋ መሆንዋ ነው።



# ምዕራፍ ፴፱

# ንጉሠ ነገሥቱ በአጠቃላይ ዕይታ

ንጉሠ ነገሥቱ በተፈጥሮ ብልህ፣ የውጭ አገር ትምሕርት የቀሰሙና ተራማጅ እንደ ነበሩ ይወሳሳቸዋል። ሆኖም ከ 58 ዓመት የሥልጣን ዘመናቸው በኋላ የአመራራቸው ውጤት እንደሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል።

## መልካም ሥራዎቻቸው

1 ኢትዮጵያን የዓለምና የአፍሪካ መንግሥታት ማኅበሮች አባል አደረጉ
2 ዘመናዊ ትምሕርትን አስፋፉ
3 ቋሚና ዘመናዊ የመንግሥት ወታደር ገነቡ
4 ምክር ቤት አቋቋሙ፣ ሕግና ደንብ እንዲወጣና ሥራ ላይ እንዲውል አደረጉ
5 ማዕከላዊ መንግሥትን አጠናከሩ
6 ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር አዋሃዱ
7 አነስተኛ ተቋሞችን በሁሉም መስክ አቋቋሙ
8 ከግብጽ ጋር የነበረውን የሃይማኖት ችግር መፍትሄ ሰጡ።

## የተወቀሱባቸው ሥራዎች

1 በዘመናቸው ኢትዮጵያ በጦርነት ተሸንፋ ጠላት አገርን ወረረ
2 አመርቂ የኤኮኖሚ ዕድገት ሳያመጡና የመሬት ይዞታን ችግር በወቅቱ መፍትሄ ሳይሰጡ ቀሩ
3 ፍቅረ ንዋይ፣ የግል ድሎትና ውዳሴ ከንቱ አበዙ
4 የሚተኳቸውን ሳያዘጋጁ አለፉ።

በመሠረቱ ኢትዮጵያን ከጥንታዊ ሥርዓት አሸጋግረው ዘመናዊነትን ያስፋፉ ስለሆኑ በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ይኖራቸዋል።

በሌላ መልኩ የኢትዮጵያን ንጉሣዊ ሥርዓትም እንዲገረሰሰ ያመቻቹ ራሳቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ብዙ ዘመን አገሪቱን በማስተዳደራቸው ምክንያት በሕዝብ ተቀባይነትና ክበሬታ ስለነበራቸው ከጣሊያን ወረራ በፊት የጀመሩትን አሠራር ከወረራውም በኋላ ቀጥለው ሥልጣናቸውን በወቅቱ አስረክበው ቢሆን ኖሮ አገሪቱም እሳቸውም ተጎጂ ባልሆኑ ነበር። በተለይ ከ1953 ዓ.ም የታህሣሥ ግርግር በኋላ በእርጅናና በግትርነት ለአሥራ ሦስት ዓመት የሕዝቡን ፍላጎት ችላ በማለትና በማን አለብኝነት፣ በግል ድሎትና በውዳሴ ከንቱ ጊዜ ማጥፋታቸው ለውድቀታቸው ዋና ምክንያት ኾነ። የተማረው ወጣት ሥራ አጥ ሆኖ፣ ሕዝቡ በድህነት እየተጉላላ፣ ደጋግሞ በሚመታው ድርቅ ባስከተለው የረሃብ አለንጋ እየተገረፈ፣ እሳቸው ግን በእርጅና ዘመናቸው እንኳን የሥልጣን ጥማቸውን ብቻ በማርካት ላይ እንዳሉ በመጨረሻ ላይ የመጣውን የሕዝብ እንቅስቃሴ ለማቆም ሳይችሉ ቀሩ።

ስለዚህ ያለምንም ማመንታት ለውድቀታቸው ምክንያት የሆነው የራሳቸው የተፈጥሮ ባህሪያቸው ነው ለማለት ይቻላል። አንደኛ ሞትን የማይቀበሉ ስለነበሩ የ80 ዓመት ልደት በዓላቸውን አክብረው ሥልጣን ላይ ንቁግ ስለነበሩ አልጋ ወራሻቸውን እንኳን ንጉሥ ብለው ለማለማመድ ቀርቶ ካቢኔያቸው ምን እንደሚሠራ እንኳን እንዲያውቁ አላደረጉም። ሁለተኛ በእሳቸው ዘመነ መንግሥት እንዲፈጸሙ ያልፈለጓቸው ሥር ነቀል ለውጦች የሆኑት የመሬት ይዞታን የሚያሻሽልና መሠረተ ልማት የሚያመጡ ታላላቅ ሥራዎች ማስፈጸም አልፈለጉም። ሦስተኛ ውዳሴ ከንቱ ስለሚያበዙ የሠላም አባት ተብለው የኖቤል ሽልማትን ለማግኘትና በዓለም ላይ ተደናቂ ለመሆን ሲሉ ለአገራቸው ታላላቅ ሥራ የሚሠሩበትን ጊዜና የሰው ኃይል አባከኑ። የከበቧቸው ሰዎች የተማሩትም ያልተማሩትም በንጉሡ ነገሥቱ የሚያመልኩና አገር ወዳድ ሆነው መጭውን መገመት የተሳናቸው ስለነበሩ ራሳቸውንም አገራቸውንም ጎዱ።

ተፈሪ ክፉ ነው ልቡም አይገኝ
ለሰው ይመስለዋል ይናገራል ቀኝ
ኋላ እንዲህ ሊዋረድ ፍጻሙን ሊያገኝ
ሼህ ሁሴን ጅብሪል





# ምዕራፍ ፵

# ተፈጥሮና የሰው ልጅ

ሰው በቀላሉ አይረዳውም እንጂ ተፈጥሮ ሰውን ያነጋግራል። ጥቂት ሰዎች አንዳንዴ እየገነገኑ የተፈጥሮን ቋንቋ ሊረዱ ይሞክራሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሰው ከቤቱ ሲወጣ ባዶ እንስራ ከገጠመው ፍርድ ቤትም የሚሄድ ከኾነ እረታለሁ መንገድም የሚሄድ ከኾነ ለሚመጣው ሁሉ ይጠነቀቅና ምናልባትም አንድ አነስተኛ ችግር በመካከሉ ከገጠመው በዚሁ ይለፍልኝ ብሎ ለፈጣሪው ይማለዳል። ፈረንጅም ጥቁር ድመት ካቋረጠው ወይ ወደ ቤቱ ይመለሳል ወይም ጥንቃቄ ያደርጋል። በአንጻሩም በስኮትላንድ ለዘመን መለወጫ (New Year) አንድ ሰው ቤት የዓይኑ ብሌንና ፀጉሩ ጥቁር የሆነ እንግዳ በመጀመሪያ በር አንኳክቶ ቢመጣ ሀብታምና ጤነኛ እንደምንሆን ምልክት ነው ብለው ስለሚያምኑ ደስታቸው ወሰን አይኖረውም።

እግዚአብሔር ምድር ቢወርድና ሰውን ቢያነጋግር የእያንዳንዱን አገር ሕዝብ በየቋንቋው ያናግራል እንጂ በእንግሊዝኛ፣ በሃረማይክ፣ በኤስፔራንቶ፣ በአረብኛ፣ በግዕዝ ወይም በቻይንኛ ሊያነጋግር አይችልም። ተፈጥሮም ሲያነጋግረን በየራሳችን ባህልና ቋንቋ ወይም በሚገባን ዘዴ ነው። የሚገርመው ደግሞ እንዲገባን ካልፈለግን ሌላ እንዲገባን የሚያስችል መላ ይፈጥራል። እርግጥ ይህን ቋንቋ አንዳንዶች ሱፐርስቲሽን ነው ብለው አይቀበሉትም። አንዳንዶች ደግሞ በዚህ ቋንቋ ይመሰጡና የሚገጥማቸውን ሁሉ ትርጉም እየሰጡ ሲጨነቁ ይታያሉ። ሳይበዛ ግን በስፋት ሰው የሚመለከተውንና ትርጉም የሚሰጠውን ማጤን ክፋት የለውም።

ጣሊያን ሊገባ ሲል ብዙ ሰዎች ምልክቶችን ዓይተው ነገሩ በቅድሚያ የገባቸው ነበሩ። ዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ አካባቢ ያኔ ጋን ተራ ነበር

ብዛት እየለወጠ መተርጎሙ እያዳገተ ሄዶ ብዙ ሰዎች አልገባ እያለቸው ነው። በአገራችንም በአፄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ ዘመን ይኖሩ የነበሩትና በግጥም የተነበዩት በተለይ በተፈሪ ዘመነ መንግሥት የሚሆነው ቁልጭ ብሎ እንደታያቸው ያሳያል። ሼህ ሁሴን ጅብሪል በ1908 ዓ.ም. ከመሞታቸው በፊት የተናገሩት አብዛኛው ሲደርስ ወደፊት ደግሞ ይፈጸማል ተብሎ የሚጠበቅም እነሆ ከዚህ በታች ይታያል።

በመካ አንድ ንጉሥ ባረብ ሦስት ቲቀሩ
ሐበሻና ሶማል ታይገጥሙም አይቀሩ

ሼህ ሁሴን ይኸን ካሉ ወደፊት ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ትዋሃዳለች ማለታቸው ይሆን? ዘመኑስ ደርሶ የለም? ምክንያቱም አሁን ያሉት የአረብ ንጉሦች ሦስት ብቻ ሲሆኑ እነሱም የሞሮኮ፣ የዮርዳኖስና የሳውዲ አረብያ ናቸው። ይኸን ጉዳይ በተመለከተ ጋዜጦች በቅርቡ ማውሳት ጀምረዋል። ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ ሃበሻ ነን ብለው የሚያምኑት ኤርትራውያኖችን አስገንጥሎ ስለሶማሌ መዋሃድ ማውራት እምብዛም አልታየውም። ሆኖም ግን ቀኑ ደርሶ ትንቢቱ ዕውነተኛ ከኾነ በቅርብ ይታያል ማለት ነው።

በየትኛውም ዓለም የመንግሥትን ኃላፊነት ይዘው የሚኖሩ ሰዎች ጭንቅ ስላለባቸው የወደፊቱን እናውቃለን የሚሉ ሰዎችን ያዳምጣሉ። አጭበርባሪውም በዛው ልክ ስለኾነና ግራ ስለሚያጋባ ይኸንን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎች ይመድባሉ። ባሊያን ሊመጣ አካባቢ የውጭ አገር ሰላዮች በገንዘብ ሰዎችን እየገዙ አጉል ትንቢት እንዲበትኑ አድርገዋቸው "ኑጭ ይመጣል እያሉ" ይናገሩ ነበር። ሂትለር ዓለምን ለመግዛት ሕልም ስለነበረውና የሙሴን ጽላት የያዘ ጦር ሁል ጊዜ አሸናፊ ነው የሚለውን ነገር ስለሰማ እሱን ለማስፈለግ ግብጽ አገር አንድ ቡድን ልኮ እንደነበረ ይነገራል። ይህንን መሠረት በማድረግ ነው የሆሊውድ ሰዎች "ዘ ሎስት አርክ" የሚለውን ፊልም የሠሩት።

በአገራችን በቤተ መንግሥት ውስጥ ሊቀ መባኔ የሚባል ሹመት ተሰጥቷቸው ይህንን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ትንቢት የሚናገሩትን ሁሉ እያዳመጡ ነገሮችን እያበጠሩ ለንጉሦች ያቀርቡ ነበር። ጃንሆይ ከሥልጣን ሊወርዱ አካባቢ ብዙ ሰዎች መልዕክትም የላኩና ንጉሡም ዘንድ አድርሱን ብለው መልዕክታቸው



ሳይደርስ የቀሩ አሉ። እነዚህም ሰዎች ባሕታውያን፣ ሼሆች፣ አንዳንድ በዕድሜ የገፉ ሰዎች ናቸው።

እንደሊላው የመንግሥት ባለሥልጣን ሁሉ ለጃንሆይም ባህታውያኖች የሚልኩባቸው መልዕክት እንደነበረ ይነገራል። ከመናንያን ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ የታወቁ አበ ጉኒና የሚባሉ መነኩሴ ግቢ ገብርኤል በርካታ ሰዎች የሚያውቋቸውና ትንቢት የሚናገሩ እንደ ነበሩ ይታወቃል። ከንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት በኋላ በደርግ ቤተ መንግሥትም የዚህን ጉዳይ የሚመሩና የሚከታተሉ ሰው እንደነበሩ ይነገራል። መጨረሻ ገደማ በደርግ መንግሥት ላይ እናውቃለን የሚሉ ሁሉ ብዙ የማይወደድ ነገር ማውራት ሲጀምሩ የማጥፋት ዘመቻ ተደርጎ ብዙዎች ተገድለዋል። ከነዚህም መካከል ቀኛዝማች ታየ (የአሩሲዋ እመቤት ልጅ) ከናዝሬት መኖሪያ ቤታቸው ተይዘው ታስረው ደብዛቸው ጠፍቷል። ደርግ የከፋው ኤቤዴ ጎዳ በጣም ታዋቂ የነበሩትን ከቦንጋ ወደ ጅማ አስመጥቶ ረሸናቸው ይባላል። ወልዮዎችንም ከወሎ፣ ሌሎችንም ከየቦታው ሰብስቦ ፈጅቷቸዋል።

አንዳንድ ሁኔታ ላይ ሕዝቡ የተደጋገመ ትንበያ ሲያደርግ ይሰማል። ለምሳሌ "አልጋ ወራሽ አይነግሡም" እያለ ማንም ሰው እንደዘበት ይናገር ነበር። ዕውነትም ሳይነግሡ ቀሩ። ወደፊት የሚሆነውን ደግሞ ሰዎች ሲናገሩ "ጥሩ ጊዜ ይመጣል" ይላሉ። አልፎ ተርፎም "አሁን ዲቪ. እየተባለ ወደ አሜሪካ እንደሚኬደው ወደፊት ዲቪ. ወደ ኢትዮጵያ ይሆናል" የሚሉም አልጠፉም። "አንድ ሽበቶ ባለከዘራ ኢትዮጵያን በሥርዓት ያስተዳድራታል፤ ከእሱ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያዊ መሆን የማይገኝ ጸጋ ይሆናል" እያለ በሰፊው ሰው ይናገራል። ምን ታይቶት ይሆን ብሎ ከመጠበቅ ሌላ ለው በምን መሠረት እንዲህ እንደሚል ለማወቅ ይቸግራል። ምናልባት ከበቁ መነኮሳትና ወልዮች እየሰማ ይሆን?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለወደፊቱ በሰፊው እንደሚናገር የታወቀ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጣ ፍካሬ ኢየሱስ የሚባል የትንቢት መጽሐፍም አለ። በተጨማሪም የሰው ልጅ ስለወደፊቱ ለማወቅ የውስጥ እጅ ያያል፣ ከብት አርዶ ሞራውን ያነባል፣ ቡና ጠጥቶ ስኒውን ያጠነፍፍና ይመለከታል፣ ኮከብ ይቆጥራል፣ የበቁ ሰዎችን፣ መጽሐፍ ገላጮችንና አዋቂዎችን ይጠይቃል። ይህ ሁሉ ጥረት የነበረና የሚኖርም ነው።



# ምዕራፍ ፵፩

# ሪፑብሊክና ሞናርኪ

## የሥልጣን ኮርቻ

ዴሞክራሲ የሚባለውን ቃል ዘመናዊ ፖለቲከኞች እንደሚጠቀሙበት ሁሉ ቀደም ብሎ የነበሩት ነገሥታት ሃይማኖትንና የዘር ግንድን ለሥልጣን ኮርቻነት ይጠቀሙበት ነበር። ይህ የቋንቋና የዘዴ ልዩነት እንጂ ዓላማውና ግቡ አንድ ነው። ሕዝብ ቀድሞም ቢሆን አሁንም የሚፈልገው ከወገኑ አንድ ሰው መርጦ እንዲያስተዳድረውና ሥራውንም መሥራት ባቃተው ጊዜ ወይም በሞት ሲለይ በሌላ ለመተካት ነው። ሥልጣኑን የጨበጠው ሰው ግን ከያዘው ስፍራ ላለመነቃነቅ እንዲያውም ሲሞት ልጁን ለመተካትና የዘር ዘሩ በሥልጣን እርካብ ላይ እንደተፈናጠጠ እንዲቆይ በሚሸርበውና በሚሠራው ተንኮል ሕዝቡ ለመሪዎቹ መገልገያ መሣሪያ እየኾነ እንዲኖር ይገደዳል። አልፎ ተርፎም አንዳንድ ሸረኛ አበላባይ ምሁሮች ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በምን ዘዴ ዘመናቸውን ማራዘም እንደሚችሉ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ብዙ መላ ያሳዩዋቸዋል።

በዚህ የታወቀው ጣሊያናዊው የቤተክህነት ሰው ማኪያቬሊ የሚባለው ፈላስፋ ነው። እሱም እሾማለሁ ብሎ በዘመኑ ለነበረው የጣሊያን ንጉሥ መሥፍን "The Prince" የሚል የሥልጣን ዕድሜውን ሊያራዝም የሚችልበትን የሚጠቁም መጽሐፍ ጽፎ ይሰጠዋል። መጽሐፉ ከፋፍለህ ግዛን የመሳሰሉ እርኩስ ሃሳቦችን የሚያስተምር ነበር። ንጉሡ መጽሐፉን አስቀርቶ የተመኘውን ሹመት ግን ሳይሰጠው ቀረ። ስሑል ሚካኤል 'ንጉሥ በስለት አይገደልም' ስለሚባል እንዴት እንደሚያደርግ ሲጨነቅ አንድ አበላባይ ጠጋ ብሎ ንጉሥን በሻሽ አንቆ መግደል የሚቻል መሆኑን ስለነገረው ይህንኑ ፈጽሟል።



እንግሊዞች በማኪያቬሊ ፍልስፍና የዓለምን ሕዝብ በያንዳንዱ አገር ላይ ጠንቅ እየጣሉ ሄደው ይኸው የደም ጎርፍ ብዙ ቦታ ይፈሳል። ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ እንደ ፓኪስታንና ባንግላዳሽ ያሉትን ከሕንድ ገንጥለው መንግሥት በማድረጋቸው አዲሶቹ መንግሥቶቸ አሁንም እንደተፋጠጡ ይኖራሉ። ሁለት የማይጣጣሙ ሕዝቦች የሚኖሩባትን ፓለስታይን የምትባለውን አገር ለአንዱ ብቻ ሰጥተው ሄደው ዘለዓለም ደም እየፈሰሰ ነው። ጆርዳን የሚባል መንግሥት ያለመኖሩ እየታወቀ እንግሊዞች የፍልስጥኤም ሕዝብ የሚኖርበትን መሬት ቆርጠው ከሳዑዲ ዓረቢያ ነገሥታት አምጥተው በፍልስጥኤም ሕዝቦች ላይ አዲስ መንግሥት ሾመው ሄዱ። ፍልስጥኤሞች እ.ኤ.አ. በ1969 ዓ.ም ጆርዳን ውስጥ የመንግሥት ግልበጣ ሞክረው ስላልተሳካ 185,000 ፍልስጥኤማውያን በሰይፍ ታርደዋል።

በኢትዮጵያ እንኳን አንዱ ጎሣ በሌላው ጎሣ ላይ ዕምነት እንዳይኖረው አቃቅረው የሄዱት እንግሊዞች ናቸው። ሶማሊዎች በመሠረቱ የኢትዮጵያ አንድ ጎሣ መሆናቸው እየታወቀ አንድ ትልቅ ኤምፓየር እንዲመሠርቱ ታላቋ ሶማሊያ ብለው ባንዲራቸው ላይ አምስት ኮከብ እንዲያደርጉ (ሮ)ከሩዋቸው እንግሊዞች ናቸው። ኤርትራን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከመጨረሻው ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር በአንድነት እንዳትኖር ያደረጉ እንግሊዞች ናቸው። እንዲያውም ለመጀመሪያ ጊዜ ኤርትራ ውስጥ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ሕዝቡ እርስ በርሱ ደም የተቃባው በእንግሊዞች ሤራ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኤርትራ ውስጥ በየምክንያቱ ደም ይፈሳል።

ንጉሡ ወይም መሪው የአገሪቱ መሆን ሲገባቸው፣ በተቃራኒው ሕዝቡም አገሪቱም በጠቅላላ የንጉሦች ወይም መሪዎች ለልጆቻቸው የሚያወርሷቸው ሃብትና መገልገያ ለመሆን ተገደዋል። ከዚህ ዓይነት ማነቆ ሕዝቡን ለማውጣት ጥቂት በጥቂት ብልህ የሆኑ ሰዎች በሞከሩ ቁጥር በተናጠል ይመታሉ ወይም እንደ እርኩስ ይወገዛሉ። ሥልጣን ላይ ያሉ ሁሉ በጣም የሚጠሉት ነገር ቢኖር እንደዚህ ዓይነት ሙከራን ስለኾነ ለሰላዮች፣ ለልዩ ጠባቂዎቻቸውና ዝናቸውን ከፍ ለሚያደርግ ፕሮፓጋንዳ የሕዝቡን ሃብት ያባክናሉ። የሕዝቡን ልጆችም ለወታደርነት በመመልመል ብዙ ጥፋት ያደርሳሉ። ቀስ በቀስ በዓለም ውስጥ ንጉሦች ጠፍተው በሕዝብ በተመረጡ አስተዳዳሪዎች የሚተኩት ለዚህ ነው። ችግሩ ግን አዲሶቹም ተመራጮች ዘዴና የማዕረግ ስም ለውጠው

ሥርዓታቸው ከንጉሦቹ አልተለየም። ስለሆነም ይህች ዓለም ለሰው ልጅ ያማረ ኑሮ መኖርያ መሆን ሲገባት የፍዳና የመከራ ዓለም ሆና እስከ አሁን ቀጥላለች። ዴሞክራሲ የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ ሰውን ውኸርንብር ውስጥ የከተተና ትርጉሙም እየተዛባ የሚገኝ ሆኗል።

## ሞናርኪ (ንጉሣዊ መንግሥት)

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሥ አገዛዝ የሚያምን (ሞናርኪስት) የኾነ ሞዓ አንበሳ የሚባል ፓርቲ ተደራጅቶ ይገኛል። በመሠረቱ ማንኛውም ዓይነት ፍልስፍናን የሚከተል ፓርቲ መመሥረት፣ መደራጀት፣ ማኅበርተኛ ማብዛት፣ ፍልስፍናውን ማስተማርና በምርጫም የመሳተፍና ካሸነፈም በፍልስፍናው መሠረት አገሪቱን ማስተዳደር መብቱ ነው። ስለሆነም የሞዓ አንበሳ መኖርና መንቀሳቀስ ተገቢና የሚደገፍ ነው። ማኅበርተኛም ባይሆኑ ብዙ የንጉሣዊ አስተዳደርን የሚደግፉ ሰዎች አሉ። ይሁንና ፍጹማዊ የንጉሠ ነገሥታ መንግሥት (Absolute Monarchy) ይኑር ለማለት የሚደፍር ሰው በአሁኑ ወቅት ቢኖርም ቁጥሩ በጣም አነስተኛ ነው።

ለኢትዮጵያ የንጉሣዊ መንግሥት አስተዳደር ይሻላታል ብሎ መከራከርና መታገል ዓላማው ስለኾነ ሌሎች ፓርቲዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ሕዝብ ፊት እየቀረበ ውይይት ማድረግና ፍልስፍናውን ማሳመን ይኖርበታል። ዓላማው ቢሳካና በምርጫ ፓርቲው ቢያሸንፍ ንጉሥ እንደሚያነግሥ ዕሙን ነው። ነገር ግን ለንጉሠ ነገሥትነት የሚመረጠው ሰው መሠረቱ ታሪካዊ ቅርስነቱ ስለኾነ መንገሥ ያለበት ትክክለኛው ንጉሥ መሆኑ ተጣርቶ መቅረብ ያለበት በመጀመሪያ በፓርቲው አባሎች በድምጽ ብልጫ ነው። ቀጥሎም ንጉሥነቱ ለመላው ኢትዮጵያ ስለኾነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ ተወያይቶበት፣ የታሪክ ተመራማሪዎች ተችተውበት በፓርላማ መጽደቅ ይገባዋል። እንዲያውም ይህ ፓርቲ ንጉሥ ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል ብሎ ከሕዝብ ጋር መወያየት ዋናው ዓላማው መሆን አለበት እንጂ እንደሌሎች ፓርቲዎች የእኔ ፓርቲ አገሪቱን ያስተዳድር ብሎ መሳተፍ ዓላማው መሆን የለበትም። ምክንያቱም ፓርቲው አሸንፎ ሥልጣን ቢይዝ የሚሾመው ንጉሥ ፓርቲው በምርጫ ከሥልጣን የወረደ ዕለት ንጉሡም ይወርዳል ማለት ይሆናል። ስለሆነም ፓርቲው አሰባሳቢና አስረጅ ፓርቲ ስለሚሆን



ሕዝብ መካከል መግባትና የሌሎች ፓርቲ አባሎችንም ማስረዳትና ማሳመን ይኖርበታል። ሞናርኪን እቀበላለሁ ያለውን ፓርቲ በምርጫ ጊዜ የሞዓ አንበሳ አባሎች ድምጽ በመስጠት እንዲደግፉና አልቀበልም ያለውን ፓርቲ እንዳይደግፉ ዘመቻ ማድረግ ይችላል፣ ኃይሉም ይኸው ብቻ ይሆናል። አንድ ጊዜ ሕገ መንግሥት ውስጥ የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ንጉሥ መሆን አለበት የሚል አንቀጽ ከገባ በኋላ ፓርቲው አሠራሩን ቀይሮ የቅርስ ወይም የባሕል ጠባቂ አካል መሆን ይኖርበታል።

የፓርቲው አሠራር ከላይ እንደተጠቀሰው መሆን ሲገባው ፓርቲው በአላስፈላጊ ሽኩቻ ጊዜ እያባከነ ይመስላል። አንድ ጊዜ የልዑል ማህለ ሥላሴ ልጅ ልዑል ኤርምያስ ቀጣይ ንጉሥ ይሁኑ የሚል ቡድንና የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን ወገን የሆኑ ሲጨቃጨቁ በዘመኑ የፓርቲው ዋና ጸሐፊ የነበሩት አምባሳደር ዶክተር ጌታቸው መካሻ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን በሚገፋ ወንበር እየተንቀሳቀሱና መናገር ሲቸገሩ እየታየ "ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን በሙሉ ጤንነት ይገኛሉ" ብለው በይፋ ተናገሩ። በአሁኑ ሰዓት ደግሞ መንገሥ ያለበት የልዑል መኮንን ልጅ ልዑል በዕደ ማርያም ነው ብለው የሚከራከሩት ከልዑል ኤርሚያስ ደጋፊዎች ጋር በውዝግብ ላይ ናቸው ይባላል። የውስጥ ሹቅሹቅ የሌለው ቡድን ወይም ፓርቲ ያለመኖሩ ባይካድም ትችቱ የሚያተኩረው ግን ጊዜየቸውንና ገንዘባቸውን የሚያጠፉት ዓላማቸውን ግብ በሚያደርስ ጉዳይ ላይ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ስለሪፐብሊክ አገዛዝ ደፍረው የተናገሩት ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሃዋርያት ብቻ ነበሩ። ሌላው ይኸ ነገር ነሳበት 'ኧረ ዝም በል እንዲህ ዓይነት ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖ አይችልም' ይል ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለንጉሥ መመለስ ሲነሳበት 'አዬ ከእንግዲህስ ወዲያ ሊሆን አይችልም' ይላል። እንዳይሆን የምንፈልገው ሥልጣን በአንድ ሰው እጅ ብቻ እንዳትገባ እንጂ ንጉሥም፣ ፕሬዚዳንትም፣ ጠቅላይ ሚኒስትርም ኾኑ ሥልጣኑ በአንድ ሰው እጅ እስከገባ ድረስ የዴሞክራሲ አስተዳደር ሊሰፍን አይችልም። የሚሻለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ሥልጣኑ በሕዝብ እጅ እንዲገባ ለማድረግ መጣጣር እንጂ አንድ ሰው በወኪልነት

ቢቃወጥ ተግባሩ ውሳኔን በተጠያቂነት መፈጸም ሲሆን የተቀረው ወግ ነው።

የንጉሣዊ ሥርዓት ለአገሪቷ የሚበጅበትን ሁኔታ ለሕዝብ ማሳወቅና ያለፈውን ስህተት እያረሙ ለወደፊት የሚሻለውን አስተዳደር መቅረጽ እንደ አማራጭ ማቅረብ ነው። የንጉሦች አገዛዝ በይፋ እየተወገዘ ባለበት ወቅት ሞዓ አንበሳ በይፋ በፓርቲነት መሳተፍ ካልደፈረ እንደ እርምጃ ጎታች ቡድን ስለሚታይ በሕዝብ ዘንድ ይናቅና ፓርቲውም ፍልስፍናውም ቀስ በቀስ ይከስማሉ። ማንም ይንገሥ የፓርቲው ተቀዳሚ ዓላማ ግለሰቡ ሳይሆን ፍልስፍናውና ባህል መሆን ይኖርበታል። ቀደም ብሎ ንጉሡ ነገሥቱ የሠራው ጥፋት ካለ የሚቀጥለው ጥሩ የማይሠራበት ምክንያት የለም። ንጉሥ ሱስንዮስ ሃይማኖቱን ለውጦ ስምንት ዓመት ሙሉ ሕዝብ ካፋጀ በኋላ ልጁ ፋሲል ነግሦ ወደ ጥንቱ ሃይማኖት ተለውጦ ሠላም ስለወረደ ብዙ ሥራ መሥራት ችሏል። በመሠረቱ የአንድ ሰው ኃብቱ እንጂ ወንጀሉ አይወረስም።

ኢትዮጵያ ንጉሥ ቢኖራት ጥሩ የሚሆኑባቸው ምክንያቶችም ይኖራሉ። የሰው ልጅ እንደ ንብ ዓይነት የተፈጥሮ ጠባይ ስለአለው መሪውን ይወዳል፣ ይከተለዋል፣ በሱም መወከልን ይመርጣል። አንድ ሰው ፕሬዚደንት ተብሎ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከሚቀመጥ ባህልን መሠረት ያደረገ ብዙ ታሪካዊ ወጎችን የሚከተል ንጉሥ ቢኖረው መልካም ይሆናል። በዘመናችን ቅርስና የቱሪስት መስህብም ነው። አንድ ሰው ላይ የተጫነውንም የሥልጣን ኃላፊነት ሊጋራ ይቸላል። ለምሳሌ በርዕሰ ብሔርነት አገሪቱን ከመወከል በተጨማሪ የፍትሕን ሥራና የምርጫ ኮሚሽንን ሃላፊነት ሊሸከም ይችላል። ለአገሪቱ አንድነት ከፕሬዚደንቱ የተሻለ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ብሪታኒያ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድን፣ ኔዘርላንድና ስፔይን የተሰደዱትን ንጉሦቻቸውን መልሰው በቦታቸው አስቀምጠዋል። ጃፓን ንጉሥ ስላላት ትኮራበታለች እንጂ ሥልጣኔዋን አልገታውም። አፍሪካ መተባበርን ዓላማ እያደረገች ስለመጣች አንድ የጥቁር ንጉሥ ቢኖራት እንደ ክብር ስለምትቆጥረው በዚህም መስመር ነገሩን ተመልክቶ እንደ አማራጭ መዘጋጀት ጥሩ ይመስላል። የሴንትራል አፍሪካ ሬፑብሊክ መሪ ቦካሳ በነገሡበት ጊዜ የሰጡት ምክንያት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲሞቱ የተካቸው ስለሌለና ለአፍሪካ ንጉሥ ስለሚያስፈልጋት እኔ መንገሥ አለብኝ የሚል ነበር።



ንጉሥ በሚነግሥበት ጊዜ በሃይማኖት ሥርዓት ይከናወን ስለነበረ ንጉሥ ይንገሥ ቢባል የሃይማኖት ጉዳይ መነሳቱ አይቀርም። እያንዳንዱ የሃይማኖት ቡድን የራሱን ሃይማኖት ብቻ የአገሪቱ ሃይማኖት ለማድረግ እንደሚፈልግ ደግሞ ግልጽ ነው። ስለሆነም ለጊዜው የሃይማኖት ጭቅጭቅ የንግሥና አፈጻጸም ላይ እንዳያውክና ሁሉም በኅብረት ንጉሡን ወኪላቸው፣ ጌጣቸውና ቅርሳቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ ያስፈልጋል። የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች እስከ ኤዛና ድረስ በቤተ ክርስቲያን ወግ እንዳልነገሡ ይታወቃል። በአጠቃላይ ስለንጉሡ ሃይማኖት በአሁኑ ሰዓት ችግር መፍጠር ለንጉሡ ሹመት እንቅፋት ስለሚሆን ለጊዜው እንደበፊቱ አከናውኖ ምናልባት ስለዚህ ጉዳይ ወደፊት በተረጋጋ ምንፈስ በምክር ቤት መወያየትና ሁሉንም የሚያስደስት ሕግ በሕብረት ማውጣት ይቻላል። ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲህ የክርስቲያን፣ የእስላም፣ ወይም የቡድሃ ሃይማኖት አገር ነች ብሎ መመደብ አይቻልም። ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን አገር ነች ተብላ መጠራት ብቻ ነው ያለባት። ምክንያቱም ሃይማኖት የግል፣ አገር የጋራ ነውና።

ጃንሆይ በዘመናቸው አሻፈረኝ አሉ እንጂ ሕዝቡማ ይደረጋል ብሎ የጠበቀው ለሕገ መንግሥቱ የሚታዘዝ ንጉሠ ነገሥት እንዲኖርና አገሪቱ በሕዝብ በሚመረጥ ጠቅላይ ሚኒስትር እንድትተዳደር ነበር።

ይሁንና ሕዝቡ በሰፊው ተወያይቶ ንጉሥ አያስፈልግም ብሎ ከወሰነ ኢትዮጵያ ሬፖብሊክ መሆን ይኖርባታል። ምናልባት እንኳን በንጉሥ መተዳደር የሚመረጥ ከኾነ ንጉሡ ሥራ ስለሚሠራ ደሞዝ ቢቆረጥለትም የንጉሣዊ ቤተሰቦችን ልዩ ፍጡር አድርጎ መመልከትና ሳይሠሩ የክብር መጠበቂያ ደሞዝ መክፈል ተገቢ አይሆንም።

ተቴዎድሮስ አንስቶ ተፈሪ ድረስ
ዘመኑ ይበቃል የዘውድ ንጉሥ
ንጉሥ አለ ብለህ አትወሳወስ
በምርጫ ታልኾነ የለም የሚነግሥ
ግን ሕልቁን አየሁት ብዙውን ቲያለቅስ
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

መሪ ለመሆን ግርማ ሞገስና ችሎታ ያለው ተወዳዳሪ እየጠፋ ፓርቲዎች ሰው ለማቅረብ የሚቸገሩበትም ጊዜ አለ።

በሂንዱ ሃይማኖት ላይ ተንተርሶ ዶክተር ራቪ ባትራ የሚባል ኤኮኖሚስት "ዘ ግሬት ዲፕሬሽን ኦፍ 1990" በሚለው መጽሐፉ ሲተነትን የሰውን ልጅ በአራት ይከፈለዋል። እሱውም ጦረኛ፣ ገበሬ፣ ሠራተኛና ምሁር ናቸው ይላል። እንደ ፍልስፍናው ገበሬም፣ ሠራተኛም፣ ምሁርም፣ መሪ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ ይደመድማል። መሪነትን ለጦረኛ ወይም ለወታደር የሚከልለው እየተዋጋ የማስተዳድር ኃላፊነቱን የሥራ ክፍሉ አድርጎ ስለሚያየው ነው። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል የአገራችን ታሪክ ደጃች እገሌ የዚህ አገረ ገዥ በዚህ ጦርነት ድል መቱ ወይም ተሸነፉ በሚል የተሞላው። ስለሆነም ተማሪ ወይም በአሁኑ አጠራር ምሁር በጦረኛው ጥላ ስር ኃይሉን ያደራጅና የሚፈልገውን እያሳመነ ያስፈጽማል። ጦረኛውም ለምሁሩ ሳይስማማው የቀረ እንደ ኾነ ምሁሩ ጦረኛውን ገዝግዞ ይጥለዋል።





# ምዕራፍ ፴፫

## የተማሪ ንቅናቄ

ተማሪ ሕዝብ ሲበደል፣ አገር ሲጎዳ፣ ግፍ ሲሠራ፣ ዓይቶ ዝም ብሎ ማለፍ አይችልም። በተለይ ዘመናዊው ትምህርት በኢትዮጵያ መስፋፋት ከጀመረ አንስቶ ተማሪዎች ነገሮች አልጥም እያሉዋቸው በተለያዩ ጊዜዎች ተቃውሞዎች አድርገዋል። በ1923 ዓ.ም. በማኅበር ደረጃ ነገሮችን ለማስተካከል ተደራጁ። ደግነቱ ,ያኔ አትሰብሰቡ የሚል ሕግ ስላልነበረ ለመሰብሰብ የሚያስፈራ ነገር አልነበረም።

በ1928 ዓ.ም. ጠላት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ማኅበር ሊኖር ቀርቶ የተማረ ሰው ሁሉ እየታደነ ይፈጅ ስለነበረ ተማሪዎቹ ተበታተኑ። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ግን በውጭ አገር የኢትዮጵያ የተማሪዎች ማኅበር በነገርማሜ ንዋይ ተመልሶ አቆጥቁጦ ነበር። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ውስጥ የንግግር ነፃነት ስለነበረ ተማሪዎች እንደልባቸው የፈለጉትን ቢናገሩ፣ ባለሥልጣንንም ይሁን ድርጅት ቢተቹ አይከሰሱም ነበር። በአንድ ወቅት ቀኃሥ ለአዲስ አበባ ኮሌጅ ክብረ በዓል መጥተው በነበረ ጊዜ የግጥም ውድድር አሸናፊዎች



ጥላሁን ግዛው

ግጥማቸው ሲነበብ አሽሙር በቀላቀለ ቋንቋ ተችተዋቸዋል። ንጉሠ ነገሥቱም ከዚህ ወቅት በኋላ በየዓመቱ ለክብረ በዓሉ መገኘቱን ተውት። ተማሪዎቹ የራሳቸውን የተማሪ መማክርትና ተወካዮች በመምረጥ ጉዳያቸውን መከታተልና ጋዜጦችም ማዘጋጀት ጀምረው ነበር። የተማሪ ንቅናቄ በስፋት የተጠናከረው ግን ከታኅሣሥ 1953 ዓ.ም ግርግር ጀምሮ ነው። የታህሣሥ 1953 ዓ.ም የመንግሥት ግልበጣ መሪ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በግልበጣው ወቅት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል ተገኝተው "እኛ መስኮቱን ከፍተናል በሩን የምትከፍቱት እናንተ ናችሁ" በማለት ለተማሪው ንቅናቄ መቀጣጠል ልዩ አስተዋጽዖ ያበረከተ ንግግር አደረጉ።

ቀጥሎም ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ብቻ የተሰጣቸውን ነፃነት በመጠቀም ያሳቸውን ቅሬታ ቢገልጹም ምንም ፋይዳ ስላልነበረው ሕዝቡን ለመቀስቀስ በየምክንያቱ ከተማ ውስጥ ሠላማዊ ሠልፍ ያደርጉ ጀመር። ሠላማዊ ሠልፍ ሲያደርጉ ፖሊስ ይታዘዝና ሲያግዳቸው ድንጋይ መወራወር ይጀመርና ከፖሊስ ጋር ግጭት ይፈጠራል። በተማሪና በፖሊስ መካከል በሚፈጠረው አምባጓሮ አንድ ወይም ሁለት ልጅ በተኩስ ይገደልና ነገሩ ሕዝብን ካስደነገጠ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በራዲዮና በቴሌቪዥን ንግግር አድርገው እንደገና ትምሕርት ይጀመራል። ይህ ሁኔታ በተደጋጋሚ ለ**13** ዓመት ሳያቋርጥ ቀጥሏል።

ሌላው የተማሪዎችን የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሰው ጉዳይ ለ**200** የአፍሪካ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተሰጣቸው የነፃ ትምህርት ነው። የአፍሪካ ተማሪዎች የመጡት አፍሪካ ውስጥ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ መውጣት በተጀመረበት ወቅት ስለነበረና የተማሪ ንቅናቄ ልምድም ስለነበራቸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከእነሱ ብዙ ነገር ቀሰሙ። ምናልባት ጃንሆይ ለዝና ብለው ያደረጉት ችሮታ ተማሪውን አስገንግኖ የራሳቸው ጠላት እንዲሆን አፋጠነው ማለትም ይቻላል።

እነመንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት ግልበጣ ሞክረው ከከሸፈ በኋላ ወጣቱ ትውልድ የንጉሠ ነገሥቱ ተቃዋሚ መሆኑ ስለታወቀ አንድ እበላባይ ጋዜጠኛ 'ገርማሜ ንዋይ ኪስ ውስጥ የተገኘ ወረቀት ከ40 ዓመት ዕድሜ በላይ የኾነ ሰው ሁሉ እንዲገደል ይላል' ብሎ በሬዲዮ አስነገረ። በዚህን ጊዜ ራሱ መንግሥቱ ንዋይ ዕድሜው 44 ዓመት ነበር። በዚህ ምክንያት



ዕድሜያቸው ከፍ ባሉ ሰዎችና በወጣቱ መካከል መቃቃር ተጀመረ። ይኸው አስተሳሰብ ቀጥሎ በደርግ ዘመን መንግሥትም በሂሆን ወጣቱ በዕድሜ በገፉ ሰዎች በጥርጣሬ ዓይን ይታይ ስለነበረ በሚያካሂደው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ላይ የአዛውንቶችን ድጋፍ ተነፍጓል። ጋዜጠኛው ለትንሽ ሹመት ብሎ የረጨው መርዝ የአገሩን ሕዝብ መርዞ በአንድ ልብ እንዳይቆም አድርጎታል።

የኾነው ኾኖ የአገሪቷ በስልጣኔ ወደ ኋላ መቅረትና በኤኮኖሚ አለማንሰራራት በተማሪዎች አሳሳቢነት ሕዝቡን እያስገነገነ እኩራፊ እየበዛ ሄደ። የተማሪው ግብግብም ከመንግሥት ጋር እየጨመረ ሄደ። አስከትሎም የተማሪውን ኃይል ለማስደንገጥና የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ መንግሥት እርምጃዎችን ወሰደ። ከእርምጃዎቹም መካከል የልዑል መኮንን ባለቤት ታናሽ ወንድምና በወቅቱ የተማሪዎች ፕሬዚዳንት የነበረውን ጥላሁን ግዛውን የፀጥታ ኃይሎች አድብተው ማታ የሴት ጓደኛውን ከወንድሙ ከመኮንን ጋር ሲሸኝ ሲወጣ በጥይት ገደሉት። እንደሚባለውማ ልጅቷ ራሷ እሱ ሳያውቀው በፍቅር እንድታጠምደው የተላከችበት ወዳጁ እንደነበረች ነው። በጥይት እንደተመታ ደጃች ባልቻ ሆስፒታል ውሰዱኝ እያለ ሲል ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (የካቲት 12) ሆስፒታል ተወሰደ። ተከትሎት የሄደው ብዛት ያለው ተማሪ ቁስለኛው ከነበረበት አዳራሽ ተባሮ ያጣጥር የነበረው ልጅ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሕይወቱ ማለፉ ተነገረ። በዚህ ምክንያት በማግስቱ ዩኒቨርስቲው



ልጅ ካሣ ወልደ ማርያም

ቅጥር ግቢ ውስጥ ታላቅ ብጥብጥ ተነስቶ በወታደሮች ተኩስ ብዙ ተማሪዎች ሲሞቱ የበለጠ ቁጥር ያለቸው ተማሪዎችም ቆሰሉ።

ተማሪዎቻቸውን ከጥቃት ለማዳን ይታገሉ የነበሩት የቀድሞው የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ልጅ ካሣ ወልደ ማርያም በዶክተር አክሊሉ ሃብቴ ተተክተው ስለነበረ አዲሱ ፕሬዚዳንት ግን ያሁሉ ተማሪ ጉዳት ሲደርስበት ባለመከላከላቸው ሕዝቡ አዝኖባቸዋል። ሆኖም የፊተኛው ፕሬዚዳንት የባላባት ልጅ የነበሩና

አዲሱ ግን የድሃ ልጅ ስለነበሩ ሞክረውም ቢሆን የሚስማቸው እንደማይገኝ ግልጽ ነበር።



ዶክተር አክሊሉ ግብቴ

በተማሪው ንቅናቄ መሃከል ዩንቨርስቲው ውስጥ ክሮኮዳየል በመባል የሚታወቅ የኮሚኒስት ቡድን ተደራጅቶ የተማሪውን እንቅስቃሴ መጨረሻ ላይ በድርጅታዊ አሠራር ለመቆጣጠር ቻለ። ድርጅታዊ አሠራርን ለቀጣዩ መንግሥት ያስተማረ የኸው ቡድን መሆኑ ይታወቃል። በዘመኑ የነበረው ተማሪና ወጣት ለውጥ ፈላጊ ብቻ እንጂ የምንም ርዕዮተ ዓለም አራማጅ ስላልነበረ በአገር ፍቅር ስሜት እየተገፋፋ የተሻለ አስተዳደር በለውጥ እንዲመጣ ሲመኝና ሲታገል ኮሚኒስቶቹ ላለሙት ግብ መሣሪያ አደረጉት። ለዴሞክራሲ እንዋጋለን የሚሉት የኮሚኒስት ቡድኖች ራሳቸው የተማሪውን የዴሞክራሲ መብት ነጥቀው እነሱን የተቃወመውን ሁሉ የሕዝብ ጠላት አስመስለው ማቅረብ ጀመሩ። ለውጡ ዕውን መሆን ሲጀምርና የንጉሡ ነገሥት ሥልጣን ወደ ወጣት መኮንኖች መዞር ሲጀምር የተማሪዎች ንቅናቄ ከአገር ውጭ መከፋፈል ጀመረ። ወታደሮቹ ሥልጣን ሲይዙ እነሱን እንደግፍ ወይስ አንደግፍ በሚለው ላይ ውዝግብ ተነስቶ አብዛኛው ተማሪ አንደግፍም በማለት በራሳቸው አገላለጽ "ምንም ቢሆን ወታደር ፋሽስት ነው" ብለው ሲስማሙ የድምጽ ብልጫ ያላገኙት ወገን ዘለው አዲስ አበባ በመግባት ከወታደሩ ጋር አብሮ ለመሥራት ተቀላቀሉ። ደጋፊዎቹ የኮሙኒስቱ ቡድን መኮንኖቹን የሚመጣው ችግር ሳይገባቸው ኮሙኒስት ነን ብለው እንዲያውጁ አደረጓቸው።

ሌላው ወገን ወታደሩ የያዘውን ሥልጣን በአብዛኛው ተማሪው እንዳይቀበለው ስላደረጉ መኮንኖቹ አጋር ሲያገኙ እሾክን በሾክ ነውና የጸጥታ ሠራተኞችን ለደጋፊዎቹ ረዳት ስላደረጉዋቸው እነዚህ ወዶ ገባ ተመሪዎች ዋና ጠላት አድርገው የያዙት የተማሪውን ንቅናቄ ስለኾነ በውጭ አገር አብዮቶች ላይ እንደተደረጉት ዓይነት ጥቃቶች በወጣቱና በተማሪው ላይ ዘረጉ። እነዚህም ጥቃቶች ሽብር፣ ፕሮፓጋንዳ፣ ስም



ማጥፋት፣ ሰልፍ፣ እስር፣ ግርፊያ፣ በከተማና በገጠር በየመንደሩ ውስጥ ያሉ ቦዘኔዎችን እየሰበሰቡና እያደራጁ መሣሪያ በማስታጠቅ ወጣቱን ማሰቃየት ተያያዙት። ወጣቱም ከስቃይ ብዛት የተነሳ ራሱን ለማዳን የከተማ ጦርነት (ነጭ ሽብር) አውጆ ደጋፊዎችን በተናጠል እያደነ መግደል ጀመረ። አብዮቱን ለማዳን በሚል ሽፋን በደጋፊዎች ላይ የተከፈተውን ጦርነት ለመቋቋምና መልሶ ለመምታት በማለት ሌላ (የቀይ ሽብር) ዘመቻ በመንግሥት ተፈቅዶ የሰው መግደል መብት ድረስ በአዋጅ ስለሰጡዋቸው በየመንደሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተፈጸመ የወንጀል ዓይነት አልነበረም። አብዛኛው ተቃዋሚ ተማሪ በጥቂት ደጋፊዎች ከመንግሥት እገዛ ጋር ሲመታ የተጎጂውን ብዛት መገመት ይቻላል። የሞተው ሞቶ በዙዎችም በአማራጭ ከአገር ውጭ መሰደድ ተገደዱ። ደጋፊዎቹም መጨረሻ ላይ ከመኮንኖቹ ጋር ስለተቃቃሩ በተራቸው እነሱም ተመቱ። አገሪቱ ስታስተምርና ስታሠለጥን የቆየችው የተማረ ወጣት ኃይል ከሁለቱም ወገን ከመፈጀቱም በላይ በስደት ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ አገር መኮብለልን ተለማመዱት። ይኸንንም ክስተት የውጭ አገር ጸሐፊዎች 'እንድ የተፈጀ ትውልድ' (The Lost Generation) በማለት ገልጸውታል።

መሥራት ባልቃ ገብነት ነው። የአሜሪካ መንግሥት ከንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ጀምሮ እጁን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ያስገባ ስለነበረ በታሕሣሥ ግርግር በአስታራቂነት በሁለቱ ጦር መሪዎች መካከል ይሯሯጥ ነበር። በወቅቱ የአሜሪካን አምባሳደር የነበሩት ሚስተር አርተር ሪቻርድስ የአስታራቂነቱን ቦታ ይዘው ጊዜ ያባክኑ ነበር። እኚሁ ሰው በቺሊ የአሊንዴን መንግሥት ማስገልበጥም ችለዋል። ደርግም ከሥልጣን በወረደ ጊዜ አንተ ግባ፣ አንተ ውጣ፣ የሚለው የአሜሪካ ባለሥልጣን ሚስተር ኮሄን ነበር። ይህም የሚያመለክተው ወደፊትም ቢሆን በአገራችን ጉዳይ አሜሪካኖች ባልቃ እየገቡ ማስቸገራቸው የማይቀር መሆኑን ነው። የዛምቢያ መሪ ኬኔት ካውንዳ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እየገቡ ይዘባርቁ እንደነበረ ብዙ ጊዜ ታይቷል። ጃንሆይን 'በመካከላችን እንደ ፀሐይ የሚያበራ ንጉሥ' ባሉበት አፋቸው በኮሎኔል መንግሥቱ ጊዜ 'አንድ አገር ስል ኢትዮጵያ በሉ!' 'አንድ መሪ ስል መንግሥቱ በሉ!' ብለው ሕዝቡን ሲያስጨበጭቡ ነበር።

ሸሽተው የነበሩት እነ መንግሥቱ ንዋይ ከሳምንት በኋላ ተደርሶባቸው በተኩስ ልውውጥ ሲገደሉ ጄኔራል መንግሥቱ ግን ቆስለው ተያዙ። ከተያዙም በኋላ "እንዴት አርበኞችን ትገላላችሁ ተብለው ሲጠየቁ "እኛ የገደልነው የ 5 ዓመት አረበኛ የ 25 ዓመት ቀማኛን ነው" ብለው መለሱ። ከተረሸኑት ባለሥልጣኖች መካከል አንዳንዶቹ በብዙ ጉዳይ ላይ ቢወነጀሉም ከፌሎቹ ኋላ ቀር ስለነበሩ በገዛ እጃቸው ትዝብት ላይ የሚጥላቸው ብዙ የትምክህተኛ ስህተቶችም ፈጽመው ነበር። ለምሳሌ እንደሊላው ሕዝብ የመብራት፣ የውሃና የስልክ ፍጆታቸውን ለማስከፈል የሚመጣውን ገንዘብ ሰብሳቢ እንኳን ላለመክፈል ሲሉ "ባቀናነው አገር! ደግሞ ማነው የሚያስከፍለን!" በማለት ያባርሩ ነበር።

ከ1953 ዓ. ም. የታህሣሥ ግርግር አንስቶ በጃንሆይ መንግሥት ላይ በየዓመቱ የተማሪው ረብሻ ለ**13** ዓመት ባለማቋረጥ ይደረግ ስለነበረ በአዲስ አበባ ውስጥ የከተማው ሱቆች ዝርፊያ እየፈሩ በጊዜ መዝጋት ጀመሩ። የፖለቲካ ስሜት ያላቸው ሰዎች ሁሉ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ስህተት በማጉላት ሲናገሩ ሥልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች ግን የጉዳዩ ክብደት ሊታያቸው አልቻለም። ንጉሠ ነገሥቱ ግን ነገሮችን ለማስተካከል ምንም እርምጃ ባይወስዱም ግንዛቢያቸው



የተሻለ ነበር። አንድ ቀን ተቆጥተው "ምንድነው ይኼ ነገር!" ብለው ሲጠይቁ "አይ ትንሽ ተማሪዎች ናቸው" ሲሏቸው "ተማሪም እኮ ሕዝብ ነው!" ብለው ተቆጡ ይባላል። ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ በ**1966** ዓ.ም ከእስር ተፈተው ቅዱስ ዮሴፍ ለቀብር ማርሴዲስ መኪናቸውን እየነዱ መጥተው አንድ ወዳጃቸው "ምነው ይህንን መኪና ለጊዜው ብታስቀምጠው፣ ዓይን አስገብቶሃል!" ብሎ ሊመክራቸው ቢሞክር "ምን እንዳይሆን ብለህ ነው! አይምሰልህ!" ብለው መለሱ። ከጥቂት ቀን በኋላ እንደገና ታሥረው የሚመኩበት መንግሥት ፈራረሰ።

የሕዝቡ እሮሮ በመብዛቱ ጊዜውን ጠብቆ እንቅስቃሴ ተነሥቶ መንግሥት እስከ ተገለበጠ ድረስ ሊገታ አልቻለም። በ**1966** ዓ.ም ጃንሆይ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሄደው በንግግራቸው ላይ ሁል ጊዜ 'የምንወደውና የሚወደን ሕዘባችን' የሚሉት ሕዝብ ቲማቲም ወረወረባቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ጥር **12** ቀን 1966 ዓ.ም ለቃና ዘገሊላ የካ ሚካኤል ታቦቱ ሲገባ ከራሽያ ከመጡት ጳጳስ አቡነ ፒሜንን ጋር ሄደው ድንጋይ ተወረወረባቸው። ጥቂት ቆይቶ የቤንዚን ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ባለታክሲዎች ሥራ አቆሙ። አስተማሪዎች በዚያን ወቅት ሥራ አቁመው ስለነበረ ተማሪው ሁሉ መንገድ ላይ ነበር። በመሃሉ አውቶቡሶች ሕዝቡን እያመላለሱ ባለታክሲዎች ሥራ ፈተው በሚንገዋለሉበት ጊዜ አውቶብሶችን መስበርና ማስቆም ተጀመረ። ከአውቶብስ በኋላ የግል አሽከርካሪዎች ላይም ድንጋይ መወርወር ሲጀመር አንዳንድ ሰዎች ከአደጋ ራሳቸውን ለመከላከል እየተኮሱ የአዲስ አበባ ከተማ ተናወጠች። አስከትሎም ተሽከርካሪዎች ቆመው ሰው ሁሉ እግረኛ ሆነ።

በመሃሉ ነገሌ ቦረና ያለው ጦር በደል ስለነበረበት አመጸና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትን ጄኔራል ከበደ ገብሬን እንዲመጡ ቢጠራም በምትካቸው የምድር ጦር ዋና አዛዥ የነበሩት ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ተልከው ቢሄዱ አሠራቸው። ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ያንኑ ቦታ ከዓመት በፊት ሲጎበኙ የነበረውን ሁኔታ ተመልከተውና ነገሮችን ለማስተካከል ቃል ገብተው ከተመለሱ በኋላ ምንም ሳያደርጉ ከርመው እንደገና ሲላኩ ሮጠው የሄዱት ትዕዛዝ ለመፈጸም እንጂ ራሳቸውም ከመጀመሪያው ምንም እንደማይፈይዱ ያውቁት ነበር።

ጄኔራል ድረሴን ለማስፈታት የተላኩት የአየር ኃይሉ አዛዥ ጄኔራል አበራ ወልደ ማርያም ጠሩን አግባብተው እስረኛውን ጄኔራል አስፈትተው ተመለሱ። ነገሩ ተቀጣጥሎ በየቦታው ያሉት ወታደሮች በሙሉ መገናኛነት ጀምረው አቤቱታቸውን በአሥመራ ሬዲዮ በኩል በይፋ ዘረዘሩ። አስከትሎም ወኪሎቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ልከው ሳለ የአክሊሉ ካቢኔ በድንገት መውረዱ ተገለጸና አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ተሾሙ። ወታደሮች የተሻሩትን ሚኒስትሮች ልቅምቅም አድርገው አስረው ንጉሠ ነገሥቱን ሠላምታ እየሰጡ ታማኝ መሆናቸውን አሳወቁ።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን አዲስ ካቢኔ አቋቋሙ። የወታደሮቹም ኮሚቴ ፈርሶ በሌላ ኮሚቴ ሲተካ መጨረሻ ላይ ያለው ኮሚቴ እራሱን ደርግ ብሎ አንድነቱን ከሁሉም የጦር ኃይሎችና ፖሊስ ሠራዊት ጋር አጠናክሮ ለጃንሆይ መንግሥት ታማኝ መሆኑን እያስታወቀ ባለሥልጣኖችን ማሰሩና ማሻር ጀመረ። በመሃሉ ተፈተው የነበሩትን ሚኒስትሮችም እንደገና መልሶ አሰረ። ይህ ሁሉ ሲሆን ጃንሆይ ከወታደሩ ጋር እንደገና በአዲስ መልክ አገሩን አስተዳድረዋለሁ በሚል ሃሳብ ወይም እኔ እስካለሁ ድረስ ለመግዛት ልሞክር ካልሆነልኝም ከእኔ ወዲያ ሰርዶ አይብቀል በሚል ከወታደሮቹ ጋር እየተስማሙ እስከ መጨረሻው ቆዩ።

አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ልጅ እንዳልካቸው መኮንንን ተማሪ አስቀድሞም ቢሆን አይወዳቸውም ነበረና ገና ሲሾሙ "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" ብሎ ተቃወማቸው። ከዚህ በኋላ እሳቸውም ፋታ ስጡኝ እያሉ ቢወተውቱም ከየድርጅቱ የሚቀርበው አቤቱታ ከልክ በላይ ሆነና ሰላማዊ ሠልፍንም ጋበዘ። በተለይ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባዘጋጁት ሰላማዊ ሠልፍ ላይ ክርስቲያኑም ስለተደመረበት በጣም ብዙ ሰው ተሠልፎ ባለሥልጣኑን ሁሉ አናወጠው። በመጨረሻም ደርግ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንንን እንደሌሎቹ ባለሥልጣኖች ወደ ማረፊያ ቤት ወሰዳቸው። ሚኒስትሮችና የጦር ባለሥልጣኖች ከየሠፈራቸው ሲለቀሙ ሕዝቡ እየተሰበሰበ ደስታውን ይገልጽ ነበር።

ቀጥሎም ልጅ ሚካኤል እምሩን ደርግ ጠቅላይ ሚኒስትር አስኝቶ በንጉሡ አሾመ። ራሱ ደርግ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ሕዝቡን እያነሳሳ መሠረቱን አጠናከረ። የወሎ ድርቅ ተደብቋል ብሎ መንግሥትን አሳጣ። የኮንጎ ዘማቾች የተባበሩት መንግሥታት የሰጠን ገንዘብ በባለሥልጣኖች ተመዝብሯል ብለው አቤት ስላሉ ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው ሲነጋገሩ ንጉሡን



"ሊባ!" ብለው ደፈሩ። ጃንሆይ ወታደሩ የማይነካቸው መስሏቸው ከርመው ወደ መጨረሻ ላይ ነገሩ እየገባቸው ሲሄድ አልጋ ወራሻቸው በጠና ታምው ለህክምና ውጪ አገር ስለነበሩ ቀኃሥ ሐምሌ 16 ቀን 1966 ዓ.ም የልደት በዓላቸውን ባከበሩ ቀን የአልጋ ወራሹን ወንድ ልጅ ልዑል ዘርዓ ያዕቆብን ምክትል አልጋ ወራሽ ብለው ሾሙ። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ የሚወያየው ስለሕዝባዊ መንግሥት ስለነበረ በአዲሱ ሹመት ሳቀ እንጂ እንደ ቁምነገር አልቆጠረውም። አዋጁ የተነገረ ዕለት ማታ አዲስ አበባ የታወቀው ጅማ ባር አጠገብ አንድ ወፈፌ "በአንደ አገር ሁለት አልጋ ወራሽ!" እያለ በመሳለቅ በለዉ አእምሮ የነበረውን አንጸባረቀ ።

ከቀን ወደ ቀን ባጠገባቸው ያለው መኳንንት ሁሉ እየታሠረ ብቻቸውን እየቀሩ ሲሄዱ በቅርባቸው የተገኙት ራስ እምሩና ደጃዝማች ከበደ ብቻ ነበሩ። ሌሎቹ ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅና በአገር የቀሩት የልዑል መኮንን ልጆች ነበሩ።

መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም የእንቁጣጣሽ ዕለት ማታ የኢትዮጵያ ሕዝብና ራሳቸው ጃንሆይም ተጋብዘው በቴሌቪዥን ጆናታን ድምብልቤይ የሚባል የእንግሊዝ ጋዜጠኛ በድብቅ ያነሳው የወሎ ረሃብ ፊልም በቴሌቪዥን ለሕዝብ ተላለፈ። የተላለፈበትም ምክንያት ሆን ተብሎ ንጉሠ ነገሥቱ በሕዝቡ እንዲጠሉ የተደረገ የፕሮፓጋንዳ እርምጃ ነበር።

በማግስቱ ጠዋት መስከረም 2 ቀን**1967** ዓ.ም የኢትዮጵያ ሬዲዮ የንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን መውረድና በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መተካት ደጋግሞ አወጀ። የሥራ ቀን ስለነበር ሁሉም ሰው ወደየመሥሪያ ቤቱ ሲሄድ ተማሪዎች ወታደር ሥልጣን መውሰዱን በመቃወም አንዳንድ

ቦታ ላይ ሠልፍ ለማድረግ ሲሞክሩ ፖሊሶች አሁንም ያባርሯቸው ጀመር። ማታ ግን በርቀት የተነሳውን የሠልፉን ፊልም ተማሪዎች የደርግ ሥልጣን መያዝን እንደ ደገፉት ተደርጎ በቴሌቪዥን ተላለፈ። ይህ ዜና ምናልባትም በደርግ ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያው የሃሰት ዜና ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።

በኋላ የተሰማው ወሬ ግን የደርግ አባሎች ቤተ መንግሥት ሄደው ራስ እምሩ በተገኙበት ንጉሡን አስቀምጠው ከሥልጣን መውረዳቸውን የሚያስረዳ ጽሑፍ ከደርግ አባሎች በአንዱ በሻለቃ ደበላ ዲንሳ ለንጉሡ እንደተነበበና ቀጥሎም በሾፌራቸው በጄኔራል ሉሉ የግል ቮልክስዋገን ቢትልስ መኪና ወደ ማረፊያ ቤት እንደተወሰዱ ነው። በዚያን ጊዜ ትናንሽ ልጆች ቤተ መንግሥቱ አጠገብ ወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ "ተፈሪ ሌባ" እያሉ ይጮሁ ነበር። ንጉሡም አንገታቸውን ጠጋ አድርገው ልጆቹ የሚናገሩትን ለመስማት ቢሞክሩ ስላቃታቸው "ምንድነው የሚሉት" ብለው ቢጠይቁ "ሌባ! ሌባ! ነው የሚሉት" ብለው ቢነግሯቸው "እውነታቸውን ነው ንጉሣቸውን ሠርቃችሁ ስትሄዱ" ብለው ተናገሩ ይባላል።



ወሎ በራብ አልቆ ሞት የበዛ እንደሆን
ተፈሪ የዛን ቀን ምን ይውጠው ይሆን
የጁን ነው የሚያገኝ የዛን ቀን ሰው አይሆን

ሼህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፵፰

# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መጨረሻ

አንድ የዝቋላ ባሕታዊ የታያቸውን በጽሑፍ ለጃንሆይ በአንድ የቤተ መንግሥት ሰው በኩል ይልካሉ፤ መልዕክቱም እንዲህ ይላል። "እንግዲህ ያንተ መንግሥት አብቅቶለታል፣ ምንም የሚደረግ ነገር የለም፣ መጸለይ ብቻ ነው። ከምሥራቅ የሚመጣ ጥቁር ሻለቃ መንግሥትህን ይወስደዋል። ከሥልጣኑ ለማውረድ ብዙ ሰዎች ይሞክራሉ፣ ግን ለጥፋት የመጣ ስለኾነ ምንም አይሳካላቸውም።ጊዜው ሲደርስ እዚህ ገባ ሳይባል ይጠፋል። ዕድሜው እንዲያጥር መጾም መጸለይ ብቻ ነው"[21]።

መቼም ንጉሥ ዘንድ አዋቂ ነኝ የሚል ሁሉ ለመሸለምና ለመታወቅ ሲል የታየውን ትንቢት ዕውነቱንም፣ ውሸቱንም፣ እንደሚያስተላልፍ የታወቀ ቢሆንም ንጉሡ ለዚህ መልዕክት የተለየ ግንዛቤ የሰጡት አይመስልም። አሁን ስናየው ግን ትንቢቱ እንደ ደረሰ እንገነዘባለን።

ንጉሠ ነገሥቱ ከመንግሥቱ ንዋይ ያልተሳካ የመንግሥት ግልበጣ በኋላ ንግግራቸው ላይ "...እኛን የመረጠ እግዚአብሔር ብድር መላሽነቱንና ውለተኛነቱን ስለምናምን ሕይወታችን እስከፈቀደ ድረስ ሕዝባችንን እናገለግለዋለን" እንዳሉት ሥልጣናቸውን ለማስተላለፍ ፈቃደኛ አልሆኑም። የሚቀርቧቸው ራስ እምሩና ሌሎችም ያስፈጁናል፣ ሥልጣንዎን በጊዜ ይልቀቁ ሲሉዋቸው እየተቆጡ እምቢ ይሉ ነበር። ሌተና ጄኔራል ዓቢይ አበበ ይህንኑ ፍርሃታቸውን ቀደም ብለው 'አውቀን እንታረም' በሚል መጽሐፍ ቢናገሩም ሰሚ አልተገኘም። ቢትወደድ

[21] አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ አዲስ መጽሐፍ ለማስተዋወቅ በበተኑት ወረቀት ላይ የተጻፈ.

ሚኒስትር?" ብለው ሲጠይቁ ለመመለስ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ። ለአስቸኳይ የመንግሥት ሥራ ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጃንሆይን ለማነጋገር በዚሁ በ1966 ዓ.ም. መግባደጃ ላይ እቢሯቸው ሲገቡ ከፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር የግል ጭውውት ያደርጉ ነበረና መለስ ብለው "አንተን ብቻ ነው እንዴ ሁል ጊዜ የምናነጋግረው!" ብለው አሳፍረው መለሷቸው። በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የጃንሆይ እርጅና የመንግሥቱን ሥራ ለማቀላጠፍ ከማስቸገሩ በላይ የተተኪ ጉዳይ ግልጽ ያልሆነበት ወቅት ተፈጥሮ እያለ በሥልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች እርምጃ አለመውሰዳቸው ራሳቸውንም አገሪቱንም ጎዳ።

በ1966 ዓ.ም በሕዝባዊ አመጽ የተቀሰቀሰው አብዮት እየገነፈለ ሲመጣ ለልጆቻቸው፣ ለተከታዮቻቸው ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ደህንነት እንኳን ሳይቀር ፈጽሞ ባለማሰብ ሁኔታውን በዘዴ ለማሳለፍና በጥንቱ አገዛዛቸው ለመቀጠል ስላቀዱ አልፈው ተርፈው ሚኒስትሮቻቸው በደርግ ሲታሰሩ ተባባሪ ሆኑ። አንዳንድ የጦር መኮንኖችም የመጣውን ችግር በኃይል እናጨናግፈው ይፍቀዱልን ቢሏቸውም እየተቆጡ ተከላከሉ። በተለይ የክብር ዘበኛ አዛዥ የነበሩት ጄኔራል አበበ ገመዳ ደጋግመው ቢጠይቁ ፈቃድ አጡ። ከተከላከሉት ሰዎች መካከል ደጃች ከበደ ተሰማም እንደነበሩበት ታምተዋል።

ሆኖም መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ወርደው ታሰሩ። ጥቂት ወራት ከቆዩ በኋላ የደርግ ጽሕፈት ቤትም ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ተዛውሮ ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱም ወደእዚያው ተወስደው በእስር ተቀመጡ። በመሃሉ የፕሮስቴት ህመም ስለ አስቸገራቸው የታወቁት ሃኪም ፕሮፌሰር አሥራት ወልደ የስ የቀዶ ጥገና ህክምና አድርገውላቸው ተሻላቸው።

የመንግሥቱ ለውጥ ባስገኘው ዕድል ሥልጣን የጨበጡት የደርግ አባሎች ከተደበቁበት ብቅ እያሉ መታወቅ ቢጀምሩም ውስጥ ውስጡን ልባቸው ይፈራ ስለነበረና ተቃውሞም እየበረታባቸው ስለሄደ ተጠራጥረው ከንጉሡ ባለሥልጣኖችና መኳንንቶች የሚፈሯቸውን ራሳቸው በድምጽ ብልጫ ወስነው ያለፍርድ ፈጇቸው።

ምንም እንኳን የተማረው ክፍል የለውጥ ደጋፊ መሆኑ ቢታወቅም ከዚሁ ክፍል ጥቂቶች ብቻ የእነሱ ደጋፊ ሲሆኑ አብዛኛው ተቀዋሚያቸው



መሆናቸውን ተረዱ። በዚህም የተነሳ ሶሽያሊዝም መርሃቸው መሆኑን አስታውቀው "ዕድገት በኅብረት" የሚል ዘመቻ አውጀው በዚህ ሽፋን ተማሪውን ከከተማ አስወጥተው በየአውራጃውና በየወረዳው በተኗቸው። እዚህ ላይ "ዕድገት በኅብረት" የሚለው ስም ታዋቂው የስፖርት ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማና ጓደኞቹ አቋቁመውት ለነበረው የመረዳጃ ማኅበር የሰጡት ስም እንጂ ደርግ ያወጀውን የዘመቻ ተግባር አይገልጽም።

ከመቶ አሥር በላይ የሆኑት (በስህተት መቶ ሃያ ነን ብለው የተናገሩት) የደርግ አባሎች መካከልም የማይመስሏቸውን ወደ መጡበት ክፍለ ጦር መልሰው በሌላ በሚታዘዛቸው ሲተኩ አንዳንዶችም እየከዱ መጥፋት ጀመሩ። በተፈጠረው የሥልጣን ሽሚያ ቤተ መንግሥት ውስጥም የተገደሉ ነበሩ።

የንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት መኖር የእነ ኮሎኔል መንግሥቱን ሕሊና አላሳርፍ ስላለና በወቅቱ ሽፍተው ጫካ የገቡትን ተስፋ ለማስቆረጥ ጃንሆይን በትራስ አፍነው ከገደሉ በኋላ ለማሳሳት ባዶ ሳጥን ባዕታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በር ላይ አስቀምጠው ጉድጓድ ሲያስቆፍሩና መሞታቸውንና መቀበራቸውን ሲያስወሩ ዋሉ።


ጃንሆይ በማረፊያ ቤት

በሌላው መልኩ ሻለቃ ጌታቸው የሮም 'የለውጡ ረመጥ የታሪክ ማስታወሻ' በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ደርጎች የጃንሆይ አስከሬን ላይ መርዝ (Synide) አፍስሰው ወህኒ ቤት ወስደው በማይለይ ቦታ እንደቀበሩዋቸው ጠቅሰዋል።

ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ መቃብሮችን እያስቆፈረ የብዙ ሰዎችን አስከሬን ለቤተሰቦቻቸው እየሰጠ እንደገና በክብር እንዲቀብሩ አድርጓል። የጃንሆይ አስከሬን ከመንግሥቱ ኃይለ ማርያም

ቢሮ ሥር 16 ዓመት ተቀብሮ ከቆየ በኋላ በውስጥ አዋቂ ጥቆማ ተቆፍሮ ወጣ ተባለ። የተገኘው አስከሬን በቁመ እርቃኑን የተቀበረ ሲሆን በቀብሩ ሰዓት ዘፍ እንዳይል አንገቱ በሽቦ እንደታሰረ ተገኘ ተብሎም ተወርቷል። አስከሬን መርማሪዎች ከውጭ አገር መጥተው የጃንሆይ መሆኑን ባያረጋግጡም አስከሬኑ ታች ግቢ ውስጥ በምትገኘው ባዕታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው እንዲያርፍ ተደረገ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ስለቀብሩ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ጉዳይ ኮሚቴ ተቋቁሞ ለረጅም ጊዜ ብዙ ውዝግብ ካስነሳ በኋላ በመጨረሻ በ1992 ዓ.ም በነቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወትና በሌሎች የኮሚቴ አባላት ብርታት ልዑላን ቤተሰቦቻቸውና ብዙ ሕዝብ በተገኘበት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በሕይወት ዘመናቸው ባሠሩት መቃብር ውስጥ አስከሬናቸው እንዲያርፍ ተደርጓል። ይሁንና አሁንም ቀብሩ ይፋ በዓል ባለመሆኑና በተጨማሪም ብዙ ወዳጆቻቸው ከውጭም አገር ሳይቀር መጥተው ባልተገኙበት የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው መከናወኑ በሰዎች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል። ይህም የሆነበት ምክንያት መንግሥት ለውጪ እንግዶች ደህንነት ዋስትና ባለመስጠቱና ይፋ መሆኑንም ስላላስታወቀ ነው።

ንጉሥ ዳዊት የሰው ልጅ ዕድሜ ሰባ ዓመት ቢበረታም ሰማንያ ዓመት ነው ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው እንዳለው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለራሳቸውና ለኢትዮጵያ ክብር ብለው ሰማንያ ዓመታቸውን አክብረው ከሥልጣን ዘወር ብለው ቢቆዩና ሞትም ሲመጣ በይፋ የኢትዮጵያ ሕዝብ እያለቀሰ በቀበራቸው ኖሮ ምንኛ ታሪክ ያምር ነበር። እንደ ተወለደ ከእናቱ ዘንድ በድብቅ ተወሰዶ ያደገው ጨቅላ በ83 ዓመታቸውም ከሚወዷቸውና ከሚያከብሯቸው ቤተሰቦቻቸውና ባለሟሎቻቸው መካከል ተወስደው ታስረውና በመጨረሻም ተገድለው አስከሬናቸው በድብቅ ተቀበረ።

ተፈሪ መኮንን በ13 ዓመታቸው ደጃዝማች ሆነው በመንግሥት ሥልጣን ወጥተው በ83 ዓመታቸው ከንጉሠ ነገሥትነት እስከ ተሻሩ ድረስ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ለ70 ዓመት በኢትዮጵያ የመንግሥት ሥልጣን ላይ የቆዩ ነበሩ። በዚህ ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያ ከፊውዳል ሥርዓት ወጥታ፣ በዘመናዊ አስተዳደር ለመተዳደር የሞከረችበት ዘመን ሲሆን፣ በመሃሉ ያልለመደችው በውጭ ኃይል መሸነፍ፣ የሃይማኖት ነፃነትና የምዕራባውያን ጥበብ የታየበት ዘመን ነበረ። እንደዚሁ ሁሉ



በምዕራባውያን ተንኮልና ሤራ የኢትዮጵያ ባለሥልጣን የተሻረበትና የተሾመበት፣ የተገደለበትና የእነሱን ክፋት የኢትዮጵያ ሕዝብም መንግሥትም መማር የጀመረበት ዘመን ነበር። ምንም እንኳን ጃንሆይ ከቀደሙት ነገሥታት በተለየ ዕድለኛ ቢሆኑም በጥቅሉ ሲታይ ዘመነ መንግሥታቸው ለረጅም ጊዜ የሠላም ዘመን ሆኖ እያለ አገሪቷ የኤኮኖሚ እመርታ ልታገኝ ስትችል አልተሳካላትም። ከጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አስከትሎ አገሪቱ ለአደጋ እንድትጋለጥና በኮሙኒስት ሥርዓት እንድትዘፈቅ መንገድ የተጠረገበት ዘመንም ነበር።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደስ የሚሉ ንጉሥ ስለነበሩና የሚወዳቸው ሰው ብዙ እንደመሆኑ መጠን ውስጥ ውስጡን የማይወዱዋቸውም ሰዎች ስለነበሩ 'የጁን ነው ያገኘው' እያሉ ይናገሩ ነበር። ስለቀብራቸው ሲነሳም እሳቸው እንዳደረጉት ከኾነ ይሄም ይበዛባቸዋል የሚሉም አሉ። እንደ ጌታቸው ኃረደው ዓይነት የንጉሠ ነገሥቱ ተቃዋሚ በስጡት አስተያየት "የንጉሠ ነገሥቱ አፅም በክብር ከመቀበሩ በፊት ንጉሡ ያስገደሏቸው ሰዎች አፅም ከየተጣለበት ተሰብስቦ በክብር መቀበር ቅድሚያ ማግኘት ይገባዋል። ስማቸው የማይታወቀውን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን በዝርዝር ለመጥቀስ ባይቻልም የታህሣሥ 5 ቀን 1953 ዓ.ም ንቅናቄ መሪ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይን ሞት አስፈርደውበት ከሰቀሉት በኋላ አስከሬኑን ጥለውታል። የእሱ ጓደኞች ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ሻምበል ባዬ ጥላሁን፣ አቶ ገርማሜ ንዋይ ራሳቸውን ከገደሉ በኋላ አስከሬናቸው አደባባይ ተሰቅሎ ውሎ እንደውሻ ሬሳ የትም ወድቆ ቀርቷል። ጄኔራል ጽጌ ዲቡን ያህል የፖሊስ ጄኔራል ተገሎ አስከሬኑን ወታደሮች ሲጫወቱበት ከዋሉ በኋላ በፅዳት መኪና ተጭኖ አልታወቀ ስፍራ ተጥሏል" ሲሉ አትተዋል። በበኩሌ መርምሬ ለመድረስ እንደቻልኩት የጄኔራል ጽጌ ዲቡ መቃብር እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ኮለኔል ወርቅነህና ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ እንደ በላይ ዘለቀ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በሌሊት የተቀብሩ መሆናቸውን ነው።

ኢትዮጵያን የመሰለ አንድ ባለታሪክ አገር 58 ዓመት ያስተዳደረውን መሪ ሲሆን እስከ ዕለተ ሞቱ ታሪክ ይፍረደው ብሎ በክብር ማስቀመጥ፣ አለበለዚያም ፍርድ ላይ አቅርቦ ተገቢውን ፍትሕ መስጠት በተገባ ነበር። ሲሞትም በክብር መቅበር እንጂ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ የተደረገው ድርጊት ግን በሙሉ ውርደቱ ለቀሪው ባለታሪክ ሕዝብ ነው። ስለሆነም የተሳሳቱትና ሕዝቡንም ያሳሳቱት አመራሩን የያዙት የሥልጣን

